# የህሊና ደወል

ልብ ወለድ

ከበአሉ ግርማ

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

በ፲፱፻፷፪ ዓ. ም

©መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

የመጀመሪያ ዕትም 1966 ዓ.ም

ሁለተኛ ዕትም 2001 ዓ.ም

ሦስተኛ ዕትም 2005 ዓ.ም

ማንኩሳ አሳታሚ

የኢትዮጵያን ጥቅም ከራሱ ጥቅም በላይ አድርጎ ለሚ መለከት ፣ ለሚሠራ ፤ ጊዜ ፣ ቦታና ሁኔታ ሳይመርጥ ጥሪዋን ለመቀበል ለተዘ ጋጀ ሁሉ ይህች ድርሰት መታሰቢያ ትሁንልኝ ።

በአሉ ግርማ ።

# የበአሉ ግርማ ቀደምት ሥራዎች

- ደራሲው
- የቀይ ኮከብ ጥሪ
- ሀዲስ
- ኦሮማይ
- የሀሲና ደወል

እጅህን በተሰሩ ስጠባበቅ ኖርኩ ልጄ አሁንስ ታከተኝ...... በማለት እናቱ በመጨረሻ ትንፋሻቸው ያሰሙትን ከውስጡ ተዳፍኖ የቆየ አርር የቅድስት ማርያም ትምህርት ቤት አሳዛኝ ሁኔታ ነካክቶ እየቀሰቀሰበት ወደ ሱጴ ቦሮ ከመጣበት አጭር አላማ በላይ ነግሶ በሀሊናው ውስጥ ደጋግሞ በማስተጋባት እረፍት ይነሳዋል — ሀዲስ ሳሀሌን ። በትምህርት ቤቱ ችግር እየተጠመደ ፤ ለችግሩ ጀርባውን ሳይሆን ልቡን እየሰጠ ሲሄድ ባንድ ፊት ደግሞ ወደ አዲስ አበባ የመመለስ ፍላጎቱ እየበረታ ይታገለዋል ። ትምህርት ቤቷ በእናቱ ምትክ በምታቀርብለት የሀሲና ጥሪና በራሱ ፍላጎት መካከል ተይዞ አሳቡ እንደ ገባ ኛኙቱ እየተነሳ ይወድቃል ።

ሀዲስ ሳሀሌ የገባን ወንዝ ተሻግሮ ሱጴ ቦሮ በገባ በሶስተኛው ወር አንድ ቀን ጧት ፤ ጠይም ፤ ሰፋ ያለ ፊቱ ላይ የተሣፈውን ብስጭት ለመሸሸግ ሳይሞክር ወደ ትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ወደ አቶ ይርጋ አለሙ ቢሮ ዘው ብሎ ገባና ፤ የወትሮው ርጋታ በተለየው ድምፅ ፤ «አሁንስ ለማስተማር አልቻልኩም ። ስድሳ አምስት ልጆች

ባንድ ክፍል ውስጥ አጉሮ ለማስተማር መሞከር በነሱም ሆነ በራስ ላይ መቀለድ ነው ። ቀልዱ እየመረረኝ ሄዷል ። በዚህ ላይ የማስተማሪያ መሳሪያ የለም ። ከጠመኔ አቅም ይቸግረናል ። የሌሎችን እንጃ እንጂ እኔ በበኩሌ በዚህ ሁኔታ የምዘልቀው አይመስለኝም ። ከሁሉም ነገር በይበልጥ የሀሊና እረፍት የሚነሳኝ ፣ በማስተምርባቸው ክፍሎች ውስጥ ፊታቸውንና ስማቸውን ለይቼ የማላውቃቸው ልጆች መኖራቸው ነው» እያለ ፣ በውስጡ ታምቆ የከረመውን ስሜት ያገነፍለው ጀመር—

አቶ ደርጋ አለሙ ያዳምጡት ፣ ወይም ሌላ ነገር ያስቡ እንደሆነ ለመገመት አልቻለም ። አቀርቅረው ላብ ችፍችፍ ማድረግ የጀመረውን በራቸውን እያሳዩት ዝም ብለው በመቅረታቸው እርሱም የራሱን ድምፅ ብቻ ከመስማት ተቆጥቦ ዝም አለ ።

«ጨረስክ ወንድም?» ከወፍራም ፣ ረገርም ሰው እንደዚያ ያለች ቀጭን ሰላላ ድምፅ ስትወጣ ለሰሚ ግራ ይገባል ። ሀዲስ ግን ተላምዶታል ።

«ጨረስክ ብሎ ጥያቄ — መቼ ጀመርኩና!» አላቸው በቁጣ ።

«ወንድም — ሳይህ ጭምት ትመስለኝ ነበር — እንደዘመኑ ወጣቶች የመቸኮል ጠባይ የሌለብህ ። ትእግስት ። ከትእግስት ብዙ ነገር ይገኛል ...»

«እስከ መቼ ድረስ? የትእግስት ልጓም! ዘላለም ትእግስት ። ለሁሉም ነገር ትእግስት ። ክርስቶስም ትእግስቱን ጨረሶ በመስቀል ላይ ኤሎሄ ኤሎሄ ብሏል ።»

«በሶስት ወር እንዲህ የሆንክ ብዙ ብትቆይማ ምን ልትሆን ኖሯል»



«ብዙ ብቆይማ እፈነዳለሁ ። እዚህ ያለው ህዝብ አለመፈንዳቱ ነው እኔን የጨነቀኝ ።»

ነገሩ ያልጣማቸው መሆናቸውን ለማሳወቅ ጀርባቸውን አዞሩበት ። ሰፊው ትከሻቸው ከሀዲስ ፊት ላይ ተደነቀረ ። ከዚያ ሰፊ ትከሻ ላይ ጉች ያለችው ትንሿ መላጣ ጭንቅላታቸው ለግዙፉ ሰውነታቸው ባእድ መስላ ነበር የምትታየው ።

«እየህ ወንድም — ከሰባት አመት በፊት ዲሬክተር ሁኜ ስመጣ ባንድ ትንሽ ክፍል ውስጥ ከሰማንያ የሚበልጡ ልጆች ይማሩ ነበር ። የሌላውን ነገር አታንሳ ። ምንም አልነበረም ለማለት ይቻላል ። አንተ የመጣኸው ከተሻሻለ ወዲህ ነው ። ያኔ ብትኖር ባሁኑ ይዘታህ አንድ ቀን አታድርም ነበር ። ዛሬ እንደምታየው እዚህ ደርሰናል ። ነገደግሞ ወደፊት መራመዳችን አይቀርም ። ለማንኛውም ነገር ትእግስት ያስፈልጋል» አሉትና ፣ ለጠቅላይ ግዛቱ ትምህርት ቤቶች ፅህፈት ቤት በየጊዜው የፃፉትን አንድ ዶርዘን ደብዳቤዎች አውጥተው እንዲመለከታቸው ሰጡት ። ከቅርቡ ያለውን ወንበር ሳበና ተቀምጦ እያንዳንዱን ደብዳቤ እያገላበጠ ያነብ ጀመር ......

አሁን ያሉት ስድስት ክፍሎች በተማሪዎች ብዛት ስለተጣበቡ ተጨማሪ ክፍሎች እንዲሰሩልን......ለሁለት መቶ ሰባ አምስት ተማሪዎች አራት አስተማሪዎች ብቻ በቂ ስላልሆኑ ተጨማሪ አስተማሪዎች እንዲላኩልን...... አሁን ያሉት ክፍሎች ከግርጊዳታቸው የተነሳ መፈራረስ ስለጀመሩ ፣ ተጨማሪ አዲስ ክፍሎች ለማሰራት ባይቻል እንኳ ፣ ያሉት እንዲታደሱልን.....የማስተማሪያ መሳሪያ ስላለቀብን እንዲላኩልን......ደመወዝ በወቅቱ የሚደርስበት መንገድ ባስቸኳይ እንዲታሰብበት......

ሀዲስ ደብዳቤዎቹን አንድ ባንድ ተመለከተ ። ያልተጠቀሰ ችግር የለም ። አንብቦ መጨረሱን አዩና ፣ «በየጊዜው የሚሰጠውን መልስ ለማወቅ ከፈለግህ ደግሞ ያውልሀ» ብለው ፣ ሌሎች ደርዘን የሚሞሉ ደብዳቤዎች ሰጡት ። እንደመጀመሪያው አንድ ባንድ አነበባቸው ። መልሶቹ አጫጭር ስለነበሩ ጊዜ አልፈጀም ። ሁሉም ባንድ ቃል የሚሉት ፣ በጀት የለም ነበር ። ትእግስት !

ሀዲስ በመደነቅ ፣ «በየትኛውም አለም ደልቷቸው የሚኖሩ አስተማሪዎች የሉም ። ያስተማሪዎች ታሪክ ከሀዋርያት ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው መሰለኝ። የኛ ግን ይብሳል ፣ ዝቅዝቅ መሰቀልና መወገር ነው የቀረን» አለ ።

«ያለብንን ከባድ አላፊነትና ችግር ተገንዝበውልን ምቾቱ ቢቀርብን እንኳ ግድ የለም ። የሚያስተምሯቸውን ልጃገረዶች የሚያባልጉት - የአባ ወራ ሚስት በሄዱበት የሚያስከበልሉት - ወጣቶችን መጠጥና ዳንስ የሚያስተምሩት-የሚያባልጉት - ለክፉ ነገር ሁሉ አርአያ የሚሆኑት እነርሱ ናቸው እያሉ ያሙናል ። ለደሞዝና ለምቾት እንጂ ለሙያው ደንታ የላቸውም ይሉናል ። እንዳልከውም ወንጌልን የሰበኩት ሀዋርያትም አልተመሰገኑም» አሉት ። መልስ አልሰጣቸውም ።

የተስፋ መቁረጥ ስሜት ሀዲስ ፊት ላይ ጉልቶ ስለታያቸው ፣ አቶ ደርጋ ጉሮሮአቸውን አሳሉና ፣ «ወንድም አሁን ችግሩ የገባህ ይመስለኛል» አሉት ። ትምህርት ቤቱን ለማሻሻል በበኩላቸው ያልሞከሩት ነገር የሌለ መሆኑን ያሳወቁት ስለመሰላቸው በራሳቸው ላይ ያላቸው እምነት እንደገና ታደሰ ። ከጥቁር ፊታቸው ጋር ሲነፃፀር ንጣቱ የሚጉላውን ጥርሳቸውን አሳዩት ።



«ችግሩ ገብቶኛል ። መፍትሄውስ?» አላቸው ።

«ትእግስት ። መፍትሄው ትእግስት ብቻ ብልሀቱ ደግሞ ያለውን ማብቃቃትና ባለው ተስፋ ሳይቆርጡ መፍጨርጨር ። ክርስቶስ በገሊላ የፈጸመውን ተአምር ለማድረግ አይቻልም ። ሰው ወሀውን ወደወይን ጠጅ ሲለውጠው አይችልም ማለቱ ነው.....»

ሀዲስ ፣ ለጥቂት ጊዜ አሰበና «ጋራው ወደ እኛ ካልመጣ እኛ ወደ ጋራው መሄድ አለብን እንደሚባለው ሁሉ ፣ እነሱ ካልሰሩልን እኛው ተጣጥረን መስራት አለብን እንጂ ፣ ችግሩ እስኪውጠን ድረስ እያየን ዝም ማለት አይገባም» አላቸው ፣ ሳይታሰበው ተስፋው እያንሰራራ ። ትናንሽ አይኖቹን ሳይሰብር በዚያው ትንፋሽ ቀጠለና «መቼም አሁን ባለው ሁኔታ አስተማርን ማለት ቀልድ ነው ። ቦታ የለም እያልን በየቀኑ ከውጭ የምንመልሳቸው ለትምህርት የደረሱ ልጆች ቁጥር ፣ ትምህርት ቤቱ ውስጥ ካሉት ምናልባት በአስር እጅ ሳይበልጡ አይቀሩም ። እነርሱም ኢትዮጵያውያን ናቸው ። መማር መብታቸው ነው ። እንዳሉት ባለው መፍጨርጨር ደግ ነው ። ለችግሩ መፍትሄ መፈለግም አይከፋም ። ሙከራው ባይሳካ እንኳ ሀሊናን ያረካል ። ሰበብ ሀሊናን መግደል የለበትም ። መፍትሄውን እኛው ካልፈጠርነው እንደመና ከሰማይ አይወርድም ። መንግስት በጀት የለም ስላለ እንደጲላጦስ እጃችንን ታጥበን ቁጭ ማለት አንችልም ። ህዝቡን አነሳስተን ፣ ጉልበቱንና ገንዘቡን በማስተባበር ተጨማሪ ክፍሎች ለምን አንሰራም?» ሲል የገዛ ድምፁ ተመልሶ ከጆሮዎቹ ውስጥ እያስተጋባ አሳቡ አእምሮው ውስጥ ነፍስ ሲዘራ ተሰማው። ተጨማሪ ክፍሎች ለማሰራት ወዲያውኑ ቆረጠ።

ሳይታሰበው እጆቹ ይንቀጠቀጡ ጀመር ። ሊቆጣጠራቸው አልቻለም ።

አቶ ይርጋ ሲያዳምጡት ቆዩና በቀዘቀዘ መንፈስ ፤ «ወንድም — ሙከራ ዕድቅ ከሆነ መሞከር ነው!» በማለት ከፊታቸው ላይ እንደሙጫ የሚጣበቅ ፈገግታ እሳዩትና እየተኩሳተሩ ፤ «ለመንገድ ገንዘብ አዋጡ — ለድልድይ — ለክሊኒክ — ለትምህርት ቤት — ገንዘብ አዋጡ ። ባለስልጣኑ ፤ ባላባቱ ፤ ጭቃ ሹሙ ሁሉ የሚሉት ገንዘብ አዋጡ ነው ። እዚህ እንደምታየው የሁሉንም ፍላጐት ሊያረካ የሚችል ገንዘብና ጉልበት የለም ። ህዝቡ ገንዘብም ጉልበትም የለውም ። እምነትም የለውም ። ለመንገድ ስራ ገንዘብ አዋጡ ሲባሉ አንዳንዶቹ ምን መልስ እንደሚሰጡ ሰምተሀል? መንገድ ከወጣ ወዲህ ነው ኑሮአችንና የቤተሰባችን አቋም መላላት የጀመረው — የደረሱ ልጆቻችንና ሚስቶቻችን ወደ ከተማ መኮብለል ያመጡት — ኑሮ ውድ የሆነው — ጉልበታችን የረከሰው — እያሉ ነው የሚናገሩት ። ውነትም ደሞ የዚህ ጥርጊያ መንገድ መከፈት አራጣ አበዳሪውን ፤ አትራፊ ነጋዴውን ፤ ቀላድ ገዢውን — ቀላድ ለማኙን በብዛት አመጣ እንጂ ከባላገሩ ኪስ ውስጥ የጨመረው ቤሳ ብስቲን የለም ። ሞፈርና ቀንበራቸውን ጥለው መሬቱን ጦም በማሳደር ወደ ከተማ የኮበለሉ ነባር ገበሬዎች ጥቂቶች አይደሉም ። ሱጴ በመለወጥ ላይ ነች ። ለውጥ ሁለት አይነት ነው — አንዱ ወደፊት ሌላው ወደ ሁዋላ ። ሱጴን ችግር እየለወጣት በመሄድ ላይ ነው — ወደ ሁዋላ ። ነባር ቤተሰቦች በመፈራረስ ላይ ናቸው ። የአስፋልት መንገድ ሲገባማ ምኑ ቅጡ ። በዚህ ላይ ደሞ ህዝቡ አንተ እንዳልከው ጉልበቱንና ገንዘቡን አስተባብሮ ትምህርት ቤት ቢሰራም ፤ ህንፃ ብቻውን ትምህርት



ቤት ስለማይሆን አስተማሪዎች ያስፈልጋሉ ። አስተማሪዎች ደሞ በተፈለጉ ጊዜ እንደማንኛውም እቃ በፋብሪካ ተሰርተው ለገበያ የሚቀርቡ እቃዎች አይደሉም ። ማንኛውም ነገር ጊዜን ይጠይቃል ። ፕላን ይጠይቃል ። ክፍል በተሰራ ደግሞ ትምህርት አይስፋፋም ። የትምህርት ሚኒስቴር ህንፃ ከመስራታችሁ በፊት አማክሩን የሚለው ለዚሁ ነው ። ከተማራችሁት ወጣቶች የሚጠበቀው'ኮ ያገሪቷን ችግር በጥሞና አስተውላችሁ ዘላቂ መፍትሄ መሻት ነው ። ለግልቢያውማ ማይምንስ ብልጭ ካለበት ይጋልብ የለም እንዴ! ታዲያ የግልቢያው ውጤት ሁዋላ ጥሩ አይሆንም ። ከኮርቻ ተፈንጥሮ መሰባበር ይመጣል ። ገንዘባችንና አለኝታችን ትእግስት ነው ። አዲሱ የትምህርት አጠቃላይ ጥናት የተጀመረው ትምህርትን በተቻለ ፍጥነት ለማዳረስ ታስቦ ነው ። በቅርቡ ስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል ይባላል ። ሰማንያ በመቶ የሚሆኑ ለትምህርት እድሜ የደረሱት ወጣቶች ከትምህርት ቤት ውጭ ናቸው ። ሁሉም ነገር እንደሰምሀ አዲስ ሆኖብህ መሰለኝ» አሉት ፤ አፍንጫቸውን እንደ ወናፍ እየነፉ ።

አቶ ይርጋ የሚሉት ሁሉ እንግዳ ባይሆንበትም በአእምሮው የሚያባዝተውን አሳቡን በግል ሊያስታውቃቸው ፈልጐ ፤ «ርግጥ ነው ። የሚሉት ነገር ሁሉ ይገባኛል ። ግን ጊዜ የለም ቁጭ ብለን ለማሰብ ። መዳህ ሳንችል እንድንሮጥ ጊዜው ይጠይቀናል ። የኔ አሳብ — እምን — ህዝቡ ጉልበቱንና ገንዘቡን አስተባብሮ ትምህርት ቤት ከሰራ ፤ አስተማሪዎችም መቅጠር መቻል አለበት ። ትምህርት የህብረተሰቡ ጉዳይ ነው ። በህብረተሰቡ የሚካሄዱ ትምህርት ቤቶች ናቸው በሁኑ ጊዜ የሚያስፈልጉን ። እጃቸውን አጣምረው የመንግስት እጅ የሚጠብቁ

ትምህርት ቤቶች አይደሉም በእዝነ ልቡናዬ የሚታዩኝ ። እኔን የሚታዩኝ በህብረተሰቡ ስጦታ ፤ ድጋፍና አሳብ የሚመሩ ትምህርት ቤቶች ናቸው ። መዋጮውም ቢሆን — የሚዋጣው ገንዘብ በቀጥታ በፕላን መሰረት ስራ ላይ ሲውል ቢታይ'ኮ ህዝቡ አይሰለችም ። እምነት አያጣም ። ብዙ ጊዜ የተታለለ ሰው ርግጥ እምነት ሊያጣ ይችላል ። እምነት ካልታደሰ — የእምነት ተንሳኤ ካላገኘ አደገኛ ነው ። አንዱ ገንዘብ አዋጡ ብሎ አጭበርብሮ ሲሄድ ሌላው መጥቶ ገንዘብ አዋጡ ሲል ሕዝቡ ይሰለቻል ። ይጠራጠራል ። የተዋጣው ገንዘብ በፕላኑ መሰረት ስራ ላይ ሳይውል ሲቀር የህብረት ስራን መንፈስ ያደክማል ። ስልጣኔና መሻሻል የሚመጡትም የተሰሩትን መንገዶች ተከትለው ስለሆነ ከጊዜ በሁዋላ ከጉዳቱ ጥቅሙ እንደሚበልጥ ማስተማር አለብን ። አለዚያማ ግርግር ለሌባ ያመቻል እንደሚባለው ገንዘብ አዋጡ ማለት ብቻ አይበቃም» አላቸው ።

ከእርሳቸው በቀር ትምህርት ቤቱን ለማሻሻል በሌሎች የሚደረገውን ማንኛውንም ጥረት አቶ ደርጋ በጥሩ አይን አይመለከቱም ነበርና የእርሳቸውን ጥቅም ለመፈታተን የሚደረግ ሙከራ መሰላቸው ። በሀምሳ አራት አመት እድሜ ከሀያ ሰባት አመት ወጣት ጋር የአሳብ ፈለማ ለመጀመር አልፈለጉም ። «እኔን'ኮ የሚገርመኝ ላንድ ዓመት ብለህ መጥተህ ይህን ያህል መጨነቅህ ነው ። ማማና ልብስህን አሻልተህ ወደ ዩኒቨርሲቲህ ብትመለስ አሁን ምንቸገረህ ወዳጄ! ተቸግረህ የምታስቸግረኝ! አፍ በተናገረ ተራራውን ሜዳ ለማድረግ ከዚያው ቤት መለስ ይቀል የለም ። ስራ አታስፈታኝ ወንድሜ!» አሉት እየተነጫነጩ ።



ንጭንጫቸውና ከፊታቸው ላይ የሚታየው ብስጭት አዲስ አሳብ በሀሊናው አስቀረፁበት — እጆቹ እየተንቀጠቀጡ ወጣ ......

የጥር ወር የሱጴን ከተማ ከረጂም እንቅልፍ ለመቀስቀስ ተጉዞ መጥቷል ። ህይወት እግሯን በጋድ የታሰረች ይመስል ባንድ ቦታ ረግታ ማዘጋጃቷን ከጥር ወር ዋዜማ ጋር አቁማለች ።

የአብዛኛው የሱጴ ቦሮ ህዝብ ኑሮ ከቡና ንግድ ኡደት ጋር የተያያዘ እንደመሆኑ ደን መመንጠር ፤ የቡና ችግኝ ማፍላት ፤ መትከል ፤ መኰትኰት ፤ ቡና ሲደርስ ደግሞ መልቀም ፤ ማድረቅ ፤ መፈልፈል ፤ ማጠብና መጫን ሲሆን ፤ ቡና ተለቅሞ ከገባ በሁዋላ ግን ስልቱ ይለወጣል— በጥር ወር እግር ሳቢያ ።

የጠጅ ነጋዴዎች ገበያ ይደራል ። አዝማሪ የመሲንቆውን ጭራ በባህር እጣን ማሻሸት ይጀምራል ። በአዲስ አበባና በሌሎች ርእስ ከተሞች ተቀማጭ የሆኑ ቀፈታቸው ወደፊት የገፋ ባለርስቶች ፤ አትራፊ ነጋዴዎችና አራጣ አበዳሪዎች እንደመስቀል ወፍ ቀጠሮ ጠብቀው ሱጴ ላይ ከወይዘሮ ዝናሽ ቤት ይገናኛሉ ። ከወሎ ፤ ከሰባት ቤት ጉራጌ ፤ ከጎጃም ፤ ከትግሬና ከሌላም ስፍራ ለቡና ለቀማ የሚመጡት የቀን ሠራተኞች በቡድን በቡድን ሆነው ሱጴን ማጣበብ ይጀምራሉ ። ሴትኛ አዳሪዎችም የአዲስ መጤዎችን ዱካ ተከትለው መጥተው እንደየደረ

ጃቸው ሰፈር ያበጃሉ — የሻማ — የኩራዝ — የፋኖስ —
የማሾ ቤቶች እንደአሸን በየቦታው ይፈላሉ ። አዝማሪዎች
በየሰፈሩ ያቅራራሉ ። ጠላው — ካቲካላው — ጠጁ —
አረቂው በያይነቱ — ኮኛክና ውስኪው ይንቆረቆራል —
ያለማቋረጥ እንደገባ ወንዝ ፍፍቱ ። የወንጀሉም ብዛት
በዚያው መጠን ይጨምራል ። በየቀኑ ከቡና ዛፍ ስር ፤
በጭቤ ፤ ወይም በማጭድ ፤ ወይም በቆንጨራ ተዘን
ጥሎ የወደቀ ሬሳ አይጠፋም ። የፖሊስ ጣቢያው በእስ
ረኞች ተሞልቶ ፤ ቤቱ ቀርቶ ደጁም ይጨናነቃል — ለቤ
ትኛ አዳሪ ገንዘብ ያልከፈለው — ከቀን ሰራተኛ ገንዘብ
የሰረቀችው — በስካር ጓደኛውን የገደለው — ልጃገ
ረዷን የደፈረው — ከእባ ወራ ሚስት ላይ የተያዘው —
በስርቆት — በነፍስ መግደል ሙከራ — በማጭበርበር
የተወነጀለው ሁሉ ባንድነት ይታጐራሉ ።

ተፈጥሮም — የደረሰው የቡና ፍሬ እንጆሪ መስሎ
ወደጥቁር አረንጓዴነት ቀለም ከሚያደሉት ወዛም ቅጠላ
ቅጠሎች ጋር እያነፃፀረች ፤ ምንጮችና ጅረቶችን በጥራታ
ቸው ኩል መስሎ ከሚንጣለለው ሰማይ ጋር እያወዳደ
ረች ፤ የንብ መንጋዎችን ካንዱ ቀፎ ወደ ሌላው እያዘመ
ተች — በየሜዳው አበባዎችን እያፈነዳች — ትሳለቃ
ለች — ትስቃለች - ታሾፋለች - ሳንዳፍታ ቋም የሚያደን
ቃት የለም ።

በክረምቱ ወራት የእርሱንና የቤተሰቦቹን ችግር
ለመወጣት ገና ያላፈራውን ቡና ዛፉ ላይ እንዳለ በርካሽ
ዋጋ የሸጠው ገበሬ ፤ ቡናው ደርሶ በአበዳሪው በገፍ
ሲሸመጠጥ ይመለከትና ባዶ እጁን ወደ ቤቱ ተመልሶ
ከእሳት ዳር ተቀምጦ ይተክዛል ። ከአራጣ አበዳሪዎች
በክረምቱ ወራት የተበደረውን ገንዘብ ከነወለዱ መክፈል



ያቃተው ፤ እፍኝ ጥሬ እየቆረጠመ ከንፈሩን ይነክሳል ።
ባሏ የኮበለለባት ሚስት ከልጆቿ ጋር ከእሳት ዳር ተቀ
ምጣ እንባዋን ታፈስሳለች ። በሴትኛ አዳሪዎች ምክር ፤
የደረሰች ልጃቸው የኮበለለችባቸው ወላጆች ፤ ሚስቱ
ቡሀቃውን ሳትከድን ሀፃን ልጅ ጥላበት የኮበለለችበት
ባል ፤ ከቡና ሺያጭ በተገኘው ትንሽ ትርፍ ባሏ በየመ
ጠጥ ቤቱ እየሰከረ የሚያስቸግራት ሚስት — ሁሉም
በየቤቱ ከንፈሩን ይመጣል ። የቤተሰብ ግንኙነት ይላላል ።
የቤተሰብ ኑሮ ይፈርሳል ። ቤተሰቦች ይበተታናሉ ።

እንግዲህ ሀዝቡ ቡናን የሚያከትምበት አዲስ ወግ
ይሻል ። እንደመሸቱም ፤ ወግ የሚያጣበት ጊዜ እምብዛም
ነው ። እንደሀዲስ አይነት ጥቁር እንግዳና እንደአይና
ለምና ዳኛቸው ሰርግ አይነቱን ይጥልለታል ።

ሀዲስ ቀን በስራ የደከመውን ሰውነቱን ለማዝናናት
በአስር ብር ከተከራያት ደሳሳ ጉጆው ታዛ ስር እግሮቹን
አጣምሮ ተቀምጧል ። ግን ለመዝናናት አልቻለም ። በአ
ሳቡ ፤ መዝናናት የሚችሉ የተባረኩ ናቸው ይላል ደጋግሞ ።
መማርኮ በአንድ በኩል ጭንቀትን ማብዛት ሳይሆን
አይቀርም እያለ ያስባል ። አሳቡ ግን አንድ አግጣጫ
ይዞ አይጓዝም ።

ከቤት ውስጥ ከሚነደው ፋኖስ እየተነነ የሚወጣው ጋዝ
ከቀዝቃዛው የምሽት አየር ጋር እየተዋሀደ አንዳንዴ መጥቶ

እፍንጫውን ይወጋዋል ። ስለተላመደው አያስጨንቀውም ። እንደፈርጥ በሚንቦገቦጉ ከዋክብት የታጀበች ብርማ ግማሽ ጨረቃ በቀዝቃዛ ብርሀኗ ሜዳውን ፣ ቤቱን ፣ ዛፉንና ቁጥቋጠውን ጥቁር ግራጫ ቀለም እየቀባች ታሽኮረጉራቸዋለች — ቁጥቋጠውን ያደፈጠ ነብር ፣ ጉቶውን ያደፈጠ ወንበዴ ፣ አንዱን ዛፍ አሳብ የተማነው ጐልያድ ፣ ሌላውን አንገቷን እንደባህር ማሽላ የዘለሰች ልጃገረድ እያስመሰለች ። ደገዛ ፈንጣዎች ጭርር ጭርር እያሉ ከእልቁ ወንዝ እንቁራሪቶች ቁርርታና እልልታ ጋር በመቀባበል የተወሳሰበ ህብረ ሙዚቃ ይፈጥራሉ ።

ለምን ጀመርኩት? ምን ሲያቀብጠኝ? እያለ ራሱን በራሱ እየደጋገመ በመጠየቅ ከአሳብ ወደ አሳብ ይራመዳል — ሀዲስ ። ስለትምህርት ቤቱ ሲያስብ አይናለም ከፊቱ መጥታ ትደቀንበታለች ። እንዴት ባጭር ጊዜ ውስጥ በአእምሮዬ ትፀነሳለች ... ግና ትምህርት ቤቱስ አዲስ ፅንስ አይደለ ... በማለት በአሳቡ ይንከራተታል ። ስለአይናለም ላስብ ሲል ደግሞ ትምህርት ቤቱ በግድ መጥቶ ጣልቃ ይገባል ። ትምህርት ቤቱና አይናለም ፣ አይናለምና ትምህርት ቤቱ ይጋጩበታል ። ይዤአት ብኮበልልስ? ብሎ ልቡን ለማነሳሳት ሲሞክር ትምህርት ቤቱ ከፊቱ ይደቀንና እኔስ የሚል ድምፅ ያሰማዋል ። ያኔ ከገባበት ማጥ የሚወጣበት መንገድ ይጠፋዋል ። ይጨነቃል ። የሚይዘው የሚጨብጠው ነገር ይጠፋዋል ። ህይወት ውሉ የጠፋ ልቃቂት ትሆንበታለች ።

ለምን ጀመርኩት? ለተባለው ጥያቄው መልስ እያጣ በሄደ ቁጥር ታዲያ ለምን አትገፋበትም የሚል አሳብ መጥቶ ጥርጣሬውን በመደምሰስ ሲፋለመውና እይሎ



ሲማነው እጆቹ መንቀጥቀጥ ይጀምራሉ ። የእናቱ ድምፅ ከሩቅ እየመጣ ከጆሮዎቹ ውስጥ ማስተጋባት ይጀምራል — ቃለ አዋዲ ይሆንበታል — እጅ እጅህን ስጠብቅ ኖርኩ ። ደከመኝ ልጄ ። በእጅህ ለራስህ ብቻ አትቁረሰበት ። እጆችህን በተስፋ ስጠባበቅ ታርጄና ተርቤ ሞትኩ ...

ሁለት እጆቹን ወደላይ ያነሳና በጨረቃዋ ብርሀን ይመለከታል — በአሳቡ እየጐሉ ሲሄዱ — እምን — የእጆቹ ፍሬ እንዲሁ በከንቱ መቅረት የለበትም ። የትምህርት ቤቱን ስራ ከፍፃሜ ማድረስ አለብኝ ። ዘለቄታ ያለው የትምህርት ቤቱ ስራ ነው ። እጆቹ የመጀመሪያውን ፈተና መውደቅ የለባቸውም — እጆቹ ይልና ለአሳቡ እልባት ሊያደርግ ሲል ልጓሙ እንደገና ያፈተልክበታል ። አይናለም ከፊቱ መጥታ ትደቀንበታለች ። አይኔ እያየ እንዴት ለሌላ ሰው ተድራ ትሄዳለች? ፍፁም በድን ነኝ ማለት ነው — ስሜት የሌለኝ ። ስሜቴን ከቀጨሁ ሰው ነኝ ለማለት አልችልም ። ይዤአት መኮብለል — ምርጫው ይሄው ነው ። አባቷ ፈታውራሪ ተካ ገደል ሊገቡ ይችላሉ ። ትምህርት ቤቱም በጅምር ይቅር — የፍቅራችን ሀውልት ሆኖ ...

ለምን ጀመርኩት? በማለት እንደገና ወደሁዋላ ተመልሶ ፣ በፊት ተራምዶ ያለፋቸው የአሳብ ደንጋዮች እያደናቀፉት ራሱን ይጠይቃል ።

ብቸኛ ስለሆንኩ ብቸኝነቴን ለመርሳት ወይም እንደቀንድ እውጣ የሚያዘግመውን እንደተከፈተ መቃብር የሚያዛጋውን የሱጴን ህይወት ለመቋቋም ፣ ለይምሰል የጀመርኩት ይሆን? ግን ሁልጊዜም ቢሆን ብቸኛ ነኝ ። ብቸኝነት አይሰለችም ። አብሮኝ አድጓልና ። ሙዚቃዬ

ነው መስተዋቱ ። ከብዙ ጠባያት ጋር የምውልበት ። በገሀነም አድርጌ ፤ መንግስተ ሰማያት ወጥቼ ፤ በነገሰታት እልፍኞች አልፌ ፤ ከልእልቶች ጋር ተሳስቄ ፤ ለምድር ከከበዱ ባለስልጣኖች ጋር ትከሻ ለትከሻ ተጋፍቼ — አዎን — ዳገት — ቁልቁለት — ገደል — የብረት መዝጊያ — አድማስ የማያግደው አለሜ ነው — ብቸኝነቱ ። ብቸኝነቴን እወደዋለሁ — አብሮ አደጌን ። አልፈራውም......አልፈራውም......እወደዋለሁ!

ታዲያ ለምን አመነታለሁ? የሚሰራ እጅ የኢትዮጵያ ቤዛ ነው ስል አልነበረም? ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ ሰማይ ዘርግታ የምትማለደው ከእጅ ሰባራ ትውልድ አድነኝ እያለች አይደለም? ምናልባት የጀመርኩት ስራ የልጆች ጨዋታ ሆኖ — ልጅ ያቦካው ለራት አይበቃም እንዲሉ — የእምቧይ ካብ የሆነ እንደሆነ በማለት ፈርቼ ይሆናል ። ሳይሆን አይቀርም? ነው ። ከሆነ ተመልሼ የድሮው......ያሁኑ ሀዲስ ለመሆን አልችልም ። አዎን — በኔ ላይ የሚያስከትለውን ለውጥ ፈርቼ ነው መሰለኝ ። ለውጥ አይቀርም......ግን ያስፈራል ። ፈረሱም ይሄው ፤ ሜዳውም ይሄው እንደሚባለው ፤ እጆቼና ስራ ሲገጣጠሙ እያየሁ ወደሁዋላ ለማለት አልችልም ። ወደሁዋላ ብል የምፈራው እኔነቴን ነው ። ወደፊት ብገፋበት እኔነቴን ለማወቅ......የህይወት ፈለግ......

«ብቻህን በአሳብ ምን ትዋዥቃለህ?» — የሽታዬ ድምፅ ነበር ። ስትመጣ ባለመስማቱ ድምፅዋ አስደነገጠው ። ከሚዋኝበት የአሳብ ባህር ወጥቶ «እኔ'ኮ የሚገርመኝ ስትመጪም ስትሄጂም ኮቴሽ አይሰማም ። እየተንሳፈፍሽ ነው እንዴ የምትሄጂው ወይስ ጥላ ነሽ!» አላት ፤ እንደመበሳጨት ብሎ ።



«የኔ መምጣት ነው እንዴ በሽታህ! እግሬ'ኮ ነው የሚያዋርደኝ ። ተመልሼ እሄዳለሁ ። ጥላነሽ ብሎ ጥያቄ! ቀትረ ቀላል ነሽ ማለትህ ነው? ለመሰደብ አይደለም የመጣሁት — የሞቀ ገበያ ትቼ ፤ ስንቱ ሲማለደኝ—ጠጪልኝ የኔ እመቤት ሲለኝ ። እኔ'ኮ የሚገርመኝ በጨለማ እየተደናበርኩ ለስድብ ሮጬ መምጣቴ ነው» አለች ፤ ባጭር ባጭሩ እየተነፈሰች ።

ሀዲስ እግሮቹን አጣምሮ ከተቀመጠበት ተነስቶ እየተጠጋት «ሽቱ — አንቺን ለማስቀየም አስቤ አይደለም ። አንቺ ደግሞ ቶሎ ብለሽ ሁሉን ነገር ወደመጥፎ ለመተርጎም ትጣደፊያለሽ ። አንቺ አይታወቅሽ እንደሆን እንጂ ስትሄጂ እንደጥላ ውልብ ነው የምትይው ። ያላሰቡትና ያልጠበቁት ነገር በድንገት ሲደርስ ያስደነግጣል—ሰይጣንና መልአክ ፤ መርዶና ደስታን አይለይም......» እያለ በተንገዳገደ አሳብ ስሜቱን ሊያስረዳት ሲሞክር አቋረጠችውና «አላሰብከኝም ፤ አልጠበቅከኝም ማለት ነዋ! እኔ ብቻ ነኝ ጧትና ማታ ወዳንተ'ምሮጠው! ወይ እድሌ! ወይዘሮ ዝናሽ ይሆን ጊዜ የት ሄደች ብለው ጓዳውን ይበዘብዙታል ። ላንተ ስል ስራዬን ትቼ እዚህ ስመጣ ደሞ አንተ ጥላ ቢስ ትለኛለህ ። ምን ታደርግ! የማያርፈው እግሬ ነው ለዚህ ያበቃኝ» አለችው ፤ የወትሮ ስልቱን ባጣ ድምፅ ።

እየተበሳጨ ፤ ቢሆንም ብስጭቱን በትእግስት ልጓም እንደምንም እየገታ «ይህንን'ኮ ነው የምለው ። ሁሉንም ነገር ወደመጥፎ ትተረጉሚዋለሽ ። በምን ቋንቋ ላናግርሽ እንደምችል አንዳንዴ ይቸግረኛል ። ከመምጣትሽ በፊት የአሳብ ማካ ውስጥ ገብቼ መንገድ ጠፍቶኝ ስማ

ስን ነበርኩ ። ከዚያ አሳብ ስለገላገልሺኝ ደስ ይለኛል ።
እንኳን መጣሺልኝ» አላት በረጂሙ ተንፍሶ ።

ተያይዘው ወደቤት ገቡ ። የፋኖስ ብርሀን ተቀበ
ላቸው ። የሀዲስ ጠይም ስፊ ፊት ወደጥቁረት አድልቷል ።
ትናንሽ አይኖቹ ጥልቀት ካለው ጉድጓድ ውስጥ ጭል
ጭል እያለ የሚታይ ወሀ ሊመስሉ ምንም አልቀራቸ
ውም ። እንደደንጊያ ያጉጡት የጉንጮቹ አጥንቶች ውጠ
ዋቸዋል ። ከርዳዳ ጠጉሩ ማበጠሪያ የዞረበት አይመስ
ልም ። ድሮም ቢሆን እምብዛም ፀድተው የማይታዩት
ጉንጮቹ ከምላጭ ጋር ከተለያዩ ውለው አድረዋል ።
እንደልማዱ እጆቹን ከሱሪው ኪሶች ውስጥ ከትቶ አቀ
ርቅሮ ቆመ ። አቀርቅሮ ሲቆም ከትከሻው የባሰውኑ ይጉ
ብጣል ። ሽታዬ ከእግር እስከራሱ እንደቤተክርስቲያን
ጫፍ በሚያበሩት ትናንሽ ውብ አይኖቿ ተመለከተችው ።
በተመለከተችው እልተደሰተችም ። ሀዲስም ቀና ብሎ
በሚሰቁት ትናንሽ አይኖቹ አማተራት ። ዳሌዋ ኮርቶ
ታየው ። የለበሰችው ያገር ልብስ ይሆናል ዳሌዋን እንደ
ዚያ ያኮራው ብሎ ገመተ ። ቁመቷም ከወትሮው ዘለግ
ብሎ ታየው ። በቁመት ትንሽ ነበር የሚበልጣት ። ሀዲስ
ረጂምም አጭርም የሚባል ሰው አይደለም ። በድንገት
የተመለከቱት ሰዎች ምናልባት በቅጥነቱ የተነሳ ከረጂ
ሞች ይቆጥሩት ይሆናል ።

ሽታዬ የተከናነበችውን ነጠላ አውርዳ ከክብ ትከ
ሻዎቿ ላይ ጣል ስታደርገው በሻሽ ወይም በጠጉር መያዣ
ያልተዳኘው ረጂም ሉጫ ጠጉሯ ተዘናፍሎ አጭር ክብ
ፊቷን የባሰውኑ አሳጠረው ። ቀዳዳዎቹ ወደላይ እንደ
መገልበጥ የሚሉት አጭር አፍንጫዋ የሚያሸፍበት ስለ



መሰለው ሀዲስ ፈገግ አለ ። ቀሚሷን ወደላይ ወጥረው
የያዙት ጡቶቿ አፈጠጡበት ።

«እኮ ለምን ነበር ብቻህን በአሳብ የምትዋኘቀው?»
አለችው ።

«የት ሰዋኝርቅ አየሺኝ ?»

«አይመስለኝም ። ሰሞኑን ነው ብቻህን እንደአብድ
መለፍለፍ የጀመርከው —አዲሱን ትምህርት ብቻ እስ
ራሰሁ ብለህ ከተነሳህ ወዲህ »አለችው ፤ የጀመረውን
ስራ በእዝነ ልቡናዋ እንደጣውንት እያየችው ። ቀጠለ
ችና «ምናለ ብትተወው ፤ ምናስጨነቀህ ፣ ላንድ አመት
ብቻ ነው እዚህ የምቆየው ብለህኝ አልነበረም፣ ትረሳህ
እንዴ! ደሞ እዚህ ትምህርት ቤት ሰራህ አልሰራህ ምን
ልዩነት ሊያመጣ ነው! ጉሽ የሚልህ እንኳ የለም ። ትርፉ
ጠላት ማፍራት ብቻ በገዛ እጅህ ። አቶ ይርጋ አለሙ
በጣም አዝነውብሀል ። የመቶ አለቃ አሸኔ ደሞ ያቶ አለሙ
የቅርብ ጓደኛ ነው ። አብረው ነው የሚውሉት ፤ የሚጠ
ጡት ። ወይዘሮ ዝናሽም በደምበኞቻቸው በአቶ ይርጋና
በመቶ አለቃ አሸኔ አሳብ በመመራት በነገሩ አልተደሰ
ቱበትም ። ካንተ ጋር እንዳልገናኝ አጥብቀው ነው የሚ
መከሩኝ ። ባንተ ሰበብ ከቤታቸው አንድ ቀን ሳያስወ
ጡኝ አይቀሩም ። አባ ጨፌም ማንገራገር ጀምረዋል
ይባላል ። ሌላው ቀርቶ መምሬ መሀሪ እንኳ አልደገፉ
ሀም ። ከስንቱ ጋር ተጣልተህ ትዘልቀዋለህ ። እኔ የም
ፈራው ለህይወትህ ነው ። በተለይ አባ ጨፌ ይወጉህና
ሳታስበው ትቀጠፋለህ!» አለችው ።

ሀዲስ የውይይታቸውን አርእስተ ጉዳይ ለመለወጥ
እድል የገጠመው መስሎት ስለታየው ስለሉዱ በሮው

ቃልቻ ፤ ስለአባ ጨፌ ማውራት ጀመረ ። «በቀዳማዊ
ሀይለ ስላሴ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ አመት ትምህርቴን
እንደጨረስኩ የነበሩኝ ጥቂት ልብሶቼ ሳስተው በመቀዳ
ደድ ፤ ማማዎቼ በመንጋደድ በክፍልም ሆነ በውጭ ከጓ
ደኞቼ በታች ሁኜ እንድታይ ስላደረጉኝ ላንድ አመት ባስ
ተማሪነት ለመቀጠር ማመልከቻ አገባሁ ። ሱዴ ቦሮ ግን
በአሳቤ ውስጥ አልነበረችም ። በየትኛው ጠቅላይ ግዛት
እንደምትገኝ ቀርቶ ስሟንም ሰምቼ አላውቅም ። ሱዴ
ቦሮ በኢሉባቦር ጠቅላይ ግዛት ፤ ከመቱ በስተምእራብ
ከገባ ወንዝ ባሻገር የምትገኝ ፤ የሱዴና የቦዶ ወረዳ መሆ
ኗን ያወቅሁት የአይሮፕላን ቲኬት በተሰጠኝ እለት ነበር ።
ከመቱ በተከራየሁዋት መጋዣ በቅሎ የበቅሎዋን ጌታ አስ
ከትዬ መጀመሪያ የሶርን ፤ ቀጥሎ የገባን ወንዝ በተሻ
ገርኩበት የዝናብ ዶፍ በሚወርድበት እለት ፤ ተጉዤ
ከአለም መጨረሻ የደረስኩ ስለመሰለኝ ስልጣኔ ደህና
ሁኚ ማለቱ አልቀረም ። ያን ቀን የገባን ወንዝ ተሻግረ
አቀበቱን ወጥቼ ከአፋፍ ላይ ስደርስ ተከትሎኝ የነበ
ረው የበቅሎዋ ጌታ ወደፊት በመቅደም የበቅሎዋን ልጓም
ይዞ ይውረዱ ጌታዬ አለኝ ። ይገርምሻል እጢዬ ዱብ
አለ ። የደነገጥሁት ድንጋጤ አይረሳኝም ። ብርክ ይዞኝ ፤
ጥርሶቼ እየተጋጩና ሰውነቴ እየተንቀጠቀጠ ... ለ...ምን?
ብዬ ጠየቅሁት ። ይህን ...በቅሎ ላይ ተቀምጠው ዝም
ብለው ቢያልፉ የአባ ጨፌ ውቃቢ ይቀየምዎታል ።
የሱዴ አድባርም አትቀበልዎትም አለኝ ከመንገድ ዳር
ከትንሽ ኮረብታ ላይ የተቆለለ ድንጋይ በሌባ ጣቱ ጠቁሞ
እያሳየኝ።ንፍስ ከዘራሁ በሁዋላ ምንድን ነው እሱ? ብዬ
ጠየቅሁት ። አባ ጨፌ ቤት ከአፋፍ ላይ እንዳለ የሚያ
ሳይ ምልክት ነው አለኝና የተቆለለውን ድንጋይ እየ

ተሳለመና ርጥብ ሳር እየነጨ ይጥልበት ጀመር ። ማን
ነው? አባ ጨፌ ብዬ ጠየቅሁት ። የታወቁ የሱዴ ባለውቃቢ
ናቸው አለኝ ። ገረመኝና ክርስቲያን ነህ? ስለው ምን ብሎ
እንደመለሰልኝ ታውቂያለሽ? እንዴታ!... ከአያት ከቅመ
አያቴ ጀምሬ ብሎ አንገቱ ላይ ያሰረውን ክር አሳየኝ ፤
ቀጥሎም ከቅርብ ጊዜ በፊት ከዚህ ላይ ሳር ብቻ ጥሎ
የሚያልፍ ሰው አልነበረም ። የዛሬን አያድርገውና — ነጋ
ዴው ከሸቀጡ አይነት ፤ ሌላው ገንዘብ ፤ ሴቱ ጌጣጌጥ
ጥለው ያልፉ ነበር ። ያንን ደፍሮ የሚነካ ሰው አልነበረም ።
ይህ ቀውጢ ጊዜ መጣና ይሄውና እንደሚያዩት ገንዘብ
ቀርቶ ክር እንኳ ጥሎ የሚያልፍ የለም ። ሰዉም ጊዜውም
ተበላሽቷል ። ገልቻ የሚደፈርበት ጊዜ መጣ እያለ
በሀዘን አንገቱን ደፍቶ ይከተለኝ ጀመር ። ክርስቲያን
ሆነህ እንዴት በቃልቻ ታመልካለህ? አልኩት ። አባ
ጨፌን ምን የሚሳናቸው ነገር አለ — ይሄው ብቻ ነበር
መልሱ ። እንቺም ከእርሱ አልተሻልሽም ። አባ ጨፌ
ብሎ ወጊ!» አላት ።

ሽታዬ በሙሉ ልቧ አላዳመጠችውም ። ከመጀመ
ሪያው ቀን አንስታ የትምህርት ቤቱን ስራ ያለመውደ
ዷን ነበር የምታሰላስለው ። ለስራው ያላት ጥላቻ በየቀኑ
ልቧ ውስጥ ነፍስ እየዘራና እያደገ መሄዱን ነበር እያወ
ጣች የምታወርደው ። ሁለቱን ለማራራቅና በረጂሙ
የተወጠነውን አሳቧን ለማጨናገፍ በመካከላቸው የተ
ፈጠረ ጠንቅ ነበር የሚመስላት ። እና እንደ ጣውንት
ነበር የምትመለከተው የትምህርት ቤቱን ስራ ። ግን ሀዲስ
በመጀመሪያ አሳቡ ፀንቶ አንድ አመት በአስተማሪነት
ከቆየ በሁዋላ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለስ ለማድረግ የም

ትጠቀምበት ሀይል እየጠፋት ግራ በገባት ቁጥር ፣ ከእርሱ እየራቀች ፣ የውጥኗን ቀስት ወደሌላ ኢላማ እየደገነች በመሄድ ፋንታ ፣ ጠረኗ ሱስ ሆኖበት አሳቡን ያስለወጠው ይመስል እየቀረበችው ፣ አዳሯን ከእርሱ ጋር እያዘወተረች መሄዷ ነበር ከፊቷ ተደቅኖ የሚታያት ። ከወይዘሮ ዝናሽ መጠጥ ቤት በአሻሻጭነት ተቀጥራ በሴትኛ አዳሪነት የምትኖር ብዙ ፈላጊ ያላት ብትሆንም የእለት ገቢያዋን መስዋእት አድርጋ ከሀዲስ ጋር መቆራኘቷ በኑሮዋ ላይ ኪሳራ እያስከተለ መሄዱ ነበር የሚያብከነክናት ። ቢሆንም……

«ከፊታውራሪ ተካ ጋር ደሞ ምናገናኛችሁ ?» ብላ ያላስበውን ጥያቄ በድንገት ወረወረችበት ።

ለመልሱ የአእምሮውን ጓዳ ሲበዘብዝ ጥቂት ቆየና በረጅሙ ተንፍሶ «ያገናኘን እኔ ለርሳቸው ፣ ምናልባት ደሞ እርሳቸው ለኔ ያለን ግምት ይመስለኛል ። ዘመናዊ እውቀት ባይገበዩም ፣ ተፈጥሮ ብሩህ አእምሮ ሰጥቶአቸዋል ። ተመራማሪ ናቸው ። ለምን? ብሎ መጠየቅን ይወዳሉ ። ለምን? ብሎ መጠየቅ የመጀመሪያ ጥበብ ነው ። አእምሮአቸው ዝግ ስላልሆነ አሳብ ይቀበላሉ ። አሳብ የሚቀበል ሰው ተራማጅ ነው ። አሳብ የሚቀበል ሰው ለውጥ ያመጣል ። ለውጥ አይፈነቅለውም ። እደንቃቸዋለሁ ። እርሳቸው ግን ምን እንዳዩብኝ አላውቅም ። ምኔ ሰው ይማርካል ። ተራ ሰው ነኝ ። አንቺ እወድሀለሁ ስትይኝ ይገርመኛል ። መልኬ ተራ ፣ ቁመቴ ተራ ፣ አሳቤ ተራ……» ሲል —

ሳታስጨርሰው ፣ «ልጃቸው አይናለምን ታውቃታለህ» ብላ ሌላ ዱብ እዳ ጣለችበት ።



«አዎን — አውቃታለሁ……»

«ውብ ናት?»

«እንከን አይወጣላትም»

«አይንህ እርፎባታል ማለት ነዋ! የፊታውራሪ አይን ወዳንተ ፣ ያንተ አይን ወደሷ ። እናንተ የገጠር አስተማሪዎች በየሄዳችሁበት የባላባት ፣ የባለስልጣን ፣ የሀብታም ልጅ ነው እሱ የምትፈልጉት — ቶሎ ለመክበር ። እይደለም» አለችው እጆቿን አወናጭፋ ።

በአይኖቿ ውስጥ የሚነበበውን ጥርጣሬ አልወደደም ። ሊከተል የሚችለውን ነገር በመፍራትና ተጨማሪ ጥያቄ እንዳታቀርብለት በማሰብ በሩን ዘግቶ ወደመኝታው ሲጉትታት —

«ጥያቄዬን አልመለስክልኝም» ብላ ስታንገራግር —

«ምን ያደርጋል» እያለ ከመኝታው ላይ ወስዶ ጣላት ።

የጣማምዎቹን ክሮች ሳይፈታ አወለቃቸው ። ልብሶቹን ለማውለቅ የፈጀው ጊዜ በመርዘሙ ተራገመ ። ከንፈሮቻቸው ሲገናኙ ፣ ሰውነታቸው ሲግል ፥ ጠረናቸው ሲወሳሰብ ፥ ላባቸው ሲወህድ ፥ በተፈጥሮ ሙዚቃ ታጅበው በስልት ሲደንሱ — ያማልክት ውብ ዳንስ — የልባቸው ትርታ ሲሰምር — ትንፋሽ እያጠረ — እያጠረ……

በሶስት ኩብ ዙሪያውን የታጠረው የፊታውራሪ ተካ ባለአንድ ፎቅ ቤት ፤ ከቡጂ ቦሮ መንደር እናት ላይ በሰፈው ተንጣሏል ። ከግርጌው በስተቀኝ ጥንታዊቷ ቡጂ ቦሮ ፤ ከግራው ግርጌ ደግሞ ፤ አውራ መንገድ ዳር በመሆኑ ከጊዜ ወደጊዜ እየተስፋፋ የሚሄደው ሰንበተ ጉዳ የተባለው አዲሱ መንደር ፤ ከፊት ለፊቱ የእልቁ ወንዝ ፤ ከወንዙ ማዶ ባለው ጉብታ ላይ ደግሞ የእልቁ ማርያም ቤተክርስቲያን ይገኛሉ ። ከቤቱ በስተጀርባ የፊታውራሪ ቡና ተክል ለአይን እስኪታክት ድረስ እየተዘረጋ ይሄዳል ። የቤቱ አረንጓዴ ቀለም ደብዝዟል ። ባለፈው ዘመን በሳምንት ሶስት ቀን እንደጭራ ብቅ ብለው የህዝቡን አቤቱታ የሚቀበሉበትና ቁጭ ብለው የሚዳኙበት የቤቱ ሰገነት ፤ በአበባ ምንጣፍ እንዳልተሸቀጠቆጠ ሁሉ ፤ ጭር ብሏል ። ባለፈው ዘመን የተሰራ ቤት ይመስል እንጂ ግርማ ሞገሱን አላጣም ።

ፊታውራሪ ተካ ቦሮ ከመከዳቸው ላይ ጋደም ብለዋል ። የግራዋ አበባ የመሰለው ሽበታቸው ፤ ጥቁር ጥለት ጣል ያለባትን የነጠላቸውን ቀለም ይጋራል ። ከፊት ለፊታቸው በብርሌ ተቀድቶ የተቀመጠው ንፁህ የማር ጠጅ የፊታቸውን ቀለም ሲመስል ምንም አይቀረውም ። በልጅነታቸው እጅግ መልከ መልካምና ግልፍተኛ ስለነበሩ «አባ ሰይጣን» የሚል የቅፅል ስም ተሰጥቷቸው ነበር ይባላል ። አሁንም ቢሆን እድሜ መልካቸውን እምብዛም አልለወጠውም ። የስድሳ አንድ አመት አዛውንት ሆነዋል ። ጠጉራቸው ሽበት እንጂ አልተመለጠም ። የፊታቸው ቆዳ መሸብሸብ ለሁኔታቸው ግርማ ሞገስ ከመለገስ ሌላ የነፈጋቸው ነገር የለም ። ፈዘዝ ባሉት ትላልቅ አይኖቻቸው ውስጥ የግልፍተኝነቱ ጠባይ በእድሜ ተበርዞ የቀዘቀዘ ይመስላል ።

የእልፍኝ አስከልካያቸው ፤ ፊታውራሪ ከመከዳ ላይ ጋደም ካሉበት ክፍል ገብቶ እጅ ነሳና ፤ «መምሬ መሀሪና ቶሎሳ መጥተዋል» ይላቸዋል ።

መምሬ መሀሪና ቶሎሳ ከደጅ ቆመው ለስርጉ በርበሬው ሲቀነጠስ ፤ ጌሾው ሲወቀጥ ፤ እህሉ ሲፈጭ ፤ የደረቀው ሲገባ ፤ ሌላው ሲሰጣ ፤ አንዱ ገባር ጭኖ ያመጣችውን እህሎች አራግፎ ሲወጣ ፤ ሌላው ጭኖ ሲገባ ፤ የጠጁና የጠላው ጋን በግራዋ ሲታጠብ ይመለከታሉ ። ስራ ፈቶ የቆመ ሰው በምድረ ግቢው አይታይም ። ፊታውራሪ ስለጊዜ ያላቸውን አስተሳሰብ ያውቃሉና ፤ ለስርጉ ቀደም ብሎ ዝግጅቱ እንዲጀመር መደረጉ መምሬ መሀሪን አላስገረማቸውም ።

«አስገባቸው» አሉት ።

መምሬ መሀሪ ክብሳታቸውን ባለሙያ ፊታይ ያወጣችው ትልቅ ልቃቂት አስመስለው ከፊታውራሪ ተካ መከዳ በስተቀኝ ካለው በርጩማ ላይ ተቀመጡ ። ግዙፍ ሰውነታቸው በርጩማውን ዋጠዉ ።

መምሬ መሀሪ ቄስ ይሁኑ አይሁኑ በርግጥ የሚያውቅ የለም ። እርሳቸው ከጐጃም ነው ይላሉ እንጂ ከየት እንደመጡ አይታወቅም ። ለማንኛውም ነገር ፣ ከብዙ ዘመን በፊት ፣ ሉዴ ቦሮ ሲደርሱ ፣ ከብሳታቸውን እሳምረውና መስቀላቸውን ደቅነው ስለነበረ የመጡት መምሬ ተብለው ቀሩ ። ፊታውራሪ ከእልቂ ወንዝ ባሻገር ካለው ጉብታ ላይ በግቢያቸው ትይዩ አድርገው ፣ የእልቂ ማርያምን ቤተክርስቲያን ካሳነፁ በሁዋላ ነበር በቅርቡ ቄስ ገበዝ የተባሉት ። ከዚያ በፊት የሚኖሩት የየመንደሩን የገባር ልጆች ሀ ሁ እያስቆጠሩ ነበር ።

መምሬ መሀሪ ረጂሙን ጢማቸውን በረጃጅም ጣቶቻቸው እየደባበሱ «አንድ ወሬ ከጆሮዬ ገብቶ አስደንግጦኛል» አሉ ።

ፊታውራሪ ተካ ስለልጃቸው ስርግ ማሰብ ከጀመሩ ቆይተዋልና ስለዚያው መስሏቸው «ምን፣ ምን አዲስ ነገር መጣ?» ብለው በችኮላ ጠየቁ ።

«ፈረንጆች ከየሀ መጥተው ሚሲን ሀይማኖት ሊሰብኩ ነው ይባላል ። እንሱ'ኮ መርፌ እየወጉ ፣ ትምህርት ቤት እያቋቋሙ ፣ ልብስና ገንዘብ እየሰጡ ነው አሉ የሚሰብኩት......»

«ታዲያ ምን ያስደነግጣል? እንደነሱ መርፌ እየወጉ ፣ ትምህርት ቤት እያቋቋሙ ፣ ልብስ እየሰጡ መስበክ ነዋ......»

«ከየት መጥቶ?»

«ካልሆነም መገዘት......»

«ይቀልዳሉ መሰለኝ!»



«መፅሀፉ ሂዱና አስተምሩ ብሎ የለም? ማስተማር ነው ። ለመሆኑ መምሩ ፣ ወላጆች በገዛ ፈቃዳቸው ወደ ቤተክርስቲያን ወስደው ከሚያስጠምቋቸው ህፃናት ሌላ ፣ እርስዎ በገዛ ጥረትዎ አስተምረው ፣ ሰብከው በማሳመን እንዲጠመቁ ያደረጓቸው አረመኔዎች ቁጥር ስንት ናቸው?» ብለው ፊታውራሪ በቁም ነገር ጠየቁ ።

«እነዚህ ሚሲዮኖች የሚባሉት'ኮ የሚያጠምቁት አረመኔውን መቸ ሆነ? የኛኑ ሰዎች ነው......»

«ችግሩ ከዚህ ላይ ነው ። የእምነቱን መሰረት የማያውቅ ምእመን ከረመኔ ምንም ያህል አይሻልም ይል ነበር መከብብ ነፍሱን ይማረውና ። የእምነቱ መሰረት የሆነውን ትምህርት ምስጢር ነው ስትሉት ምን ያድርግ? በናንተ ቤት ሁሉም ምስጢር ነው ።ከማስተማር መማር ሁልጊዜ መቅደም አለበት ፣ እለዚያ ጉጂነቱ እያመዘነ ነው የሚሄደው......»

«በየእድሩ ፣ በየሰርጉ ፣ በየክርስትናው ቤት ፣ በየተዝካሩ ፣ በየሰንበቴው ፣ በየበአላቱ ፣ በየአድባራቱ......»

«አየ መምሩ — ዳቦ መቁረስ ፣ ጠበል መቅመስ ፣ ቡራኬ መስጠት ፣ ፍታት ፣ ኑዛዜ — እነዚህ ሁሉ መልካም አገልግሎት ቢሆኑም ፣ ትምህርት ናቸው ለማለት አይቻልም ። አንድ ጊዜ አንዱን ሚሲዮናዊ ፈረንጅ ለምን የኛን ሰዎች እየሰበካችሁ እንደገና ታጠምቃላችሁ? ብዬ ብጠይቀው ምን ብሎ መለሰልኝ ይመስልዎታል? የሰውን አእምሮ መሻማት በተጀመረበት ባሁኑ ዘመን ፣ «ሂዱና አስተምሩ» የተባለውን ቃል ቤተክርስቲያናችሁ አጥብቃ

መከተል ይኖርባታል አለኝ ። እውነቱን ነው ። ለሀይማኖ ታችን ቀናተኞች ነን ። ግን ቀናተኞች መሆን ብቻ አይ በቃም ። በዱር በገደሉ ተሰዶ ሀይማኖታችንን በበለጠ ማስፋፋት ያስፈልጋል ። የተጠመቀውም ምስጢሩ እን ዲገለጥለት......»

«እስካሁን እምነታችንን ያስፋፋው ማን ሆንና ነው? እኛው አይደለንም?»

«አዩ መምሩ — ቤተክርስቲያናችን አሁን ካለችበት ደረጃ የደረሰችው በናንተ ጥረት ብቻ አይደለም......»

«እረ በስመ አብ ይበሉ......»

«ይቆዩ እንጂ ፣ ያድምጡኝ......»

«እረ የሰይጣን ጆሮ አይስማው ባክዎን......»

«ወቸ ጉድ ያዳምጡኝ እንጂ ! የክርስቲያን ሀይማኖት ኢትዮጵያ ከገባ ፣ ከአብርሀ ወአፅብሀ ዘመን ጀምሮ ፣ ቤተ ክርስቲያናችንና እምነታችንን ያስፋፉት ያገር መሪዎች ፣ ባለስልጣኖች ፤ ራስ ፤ ደጃዝማች—ክርስትና በማንሳት ፣ ጡት በማጥባት ፣ በመሾም በመሸለም ፣ አብያተ ክርስቲያናትን በየሄዱበት በመትከል ነው ። በኛም ቤት እንኳ ሚካኤ ልን የተከሉት አያቴ ፣ ስላሴንና ገብርኤልን ደሞ የተከ ሉት አባቴ ፤ እኔም የእልቂ ማርያምን ይሄውና ተክያለሁ ። እናንተ የመሪዎችን ዱካ ከመከተል ሌላ ምኑ ቀድማችሁ ታውቃላችሁና ? ሂዱና አስተምሩ 'የሚለውን ቃል በመ ከተል የሰሩት ፤ እኔ የማውቃቸው ጥቂት ናቸው......»

«እረ በስመ አብ ይበሉ ጌታዬ! ዛሬ በማለዳ ተነስ ተው ዳዊትዎን አልደገሙም መሰለኝ......»



«አዎን — ድግምት ፣ ጥንቆላ ፣ መተት — ሰይጣን ፣ ጂኒ — ኀብስማ ፣ ወሰራ — ቡሀ ፣ ዳለቻ — ክታብ እያሉ ምእመናኑን ወደሌላ የሚጎትቱም የናንተው ደባትር ናቸው ። ከአባ ጨፌ አይሻሉም ። ታዲያ ምን ያስደነግጣል? ምነስ ያስገርማል ። ሾላ በድፍን ብሎ መተው »አሉና ፣ ፊታው ራሪ በረጂሙ ተነፈሱ ።

«ችግራችንንኮ አልተረዱልንም......»

«መቼ አጣሁት ። አለማወቅ ክፉ መሆኑን ። የራሶች ፣ የደጃዝማቾች ፤ የጦር አበጋዞች ስልጣን ከደከመ ወዲህ የክ ርስትና ሀይማኖት እምብዛም አልተስፋፋም ። እኔ የምፈ ራው ጨርሶ ወደሁዋላ እንዳይቀር ነው» አሉ ፣ ፊታው ራሪ በለሆሳስ ፣ ተክዘው ።

መምሬ መሀሪ እርእስተ ጉዳዩን ለመለወጥ ያሀል «ለሰርጉ የሚደረገው ዝግጅት ካሁኑ የተፋፋመ መስሎ ይታያል» አሉ ፣ ሲገቡ ደጅ ያዩትን በማስታወስ ።

«ከጊዜው ቀድሞ መገኘት ያስፈልጋል ። ለጦርነት ያል ተዘጋጀ የጦር አበጋዝ ሰራዊቱን ያስፈታል ። ህዝብን ከጊዜ ጋር ያላራመደ መሪ ግዛቱን ያጣል ። ሙሽራ ከመጣ በሁ ዋላ መንቃት ፣ መርበትበትን ፣ መርበድበድን ፣ ሚዛን ማጣ ትን—አዎን—እነዚህ ደሞ ተደምረው ስህተትንና ውርደ ትን ያስከትላሉ ። ሁዋላ ከንፍ ጥለው ቢሮጡ አይሆንም ። ክርስቶስም በዚች አለም ባስተማረበት ወቅት ዘገይታችሁ በር ብታንኳኩ አይሆንም ብሏል ። አዩ መምሩ—በመፅሀፍ ቅዱስ ከተገለጠው ከብልሆችና ከሰነፎቹ ቆነጃጂቶች ታሪክ ልንማር የሚያስፈልገው ጊዜና ቀጠሮ ሲከበሩ የሚገባቸው ነገሮች መሆናቸውን ነው ። ሰው ማንነቱ የሚገመተውና የሚለካው በዚሁ መሆን ያለበት ይመስለኛል ። ምሳሌውም

ይሄው ነው» አሉ ፣ ፊታውራሪ በተለመደው የለዘበ እንደበታቸው ። ቀጥለውም «ብርሀንና ጨለማ ፣ ወራትና ዘመናት ቀጠሮአቸውን ጠብቀው ነው የሚፈራረቁት ። ክረምትና በጋ በቀጠሮ ይመጣሉ ፣ ይሄዳሉ ። የመስቀል አበባ ቀጠሮውን ጠብቆ ነው የሚያብበው ። እህል አለጊዜው አይዘራም ፣ አለጊዜው አይታጨድም ። ማህፀን ከቀጠሮ ውጭ ዘር አይቀበልም ። ሰውም ከተወለደበት ቀን ጀምሮ እስከ እለተ ሞቱ የሚኖረው በቀጠሮ ነው — ይወለዳል — ያድጋል — ያረጃል — ይሞታል — ከቀነ ቀጠሮው አያልፍም ። ጊዜ የሁሉም መለኪያ ፣ መነሻና መድረሻ ነው ። ማንኛውም ነገር እንደጊዜው ይወደዳል — ይጠላል — ይነሳል — ይወድቃል — ከጊዜ ውጭ የሚሆን ነገር የለም ። በዘመኔ በባላባትነቴ ስልጣን ሰርቼበታለሁ ፣ ገርፌአለሁ ፣ አስሬአለሁ ። የስቀልኩበትም ጊዜ ነበር ። ዛሬ ጊዜው ተለወጠና ጭቃ ሹሙ ፣ የወረዳው ፀሀፊና ተራ ፖሊስ ከኔ የበለጠ ስልጣን አላቸው ። ተፈጥሮ አንዱ ከሌላው ጊዜ ውስጥ እንዲታሰር አድርጋለች ። ርግጥ ሰው ከተፈጠረ ጀምሮ ጊዜን ድል ለማድረግ ከመሞከር ቦዝኖ አያውቅም ። ግን ጊዜን ድል ማድረግ የሚቻለው ጊዜን በማክበር ብቻ ነው ። ህልውና ማለት ራሱ ጊዜ ነው — ከጊዜ ውጭ የሆነ ነገር ከዚህ አለም አይደለምና ፣ ጊዜን ማምለክ እግዜርን በቅርብ ማወቅ ነው — መምሩ በዚህ አለም ቀጠሮን ከማክበር የበለጠ ቁም ነገር የለም» አሉ በረጅሙ ተንፍሰው ።

መምሩ ፣ ፊታውራሪ ስለጊዜና ቀጠሮ ያላቸውን ፍልስፍና ብዙ ጊዜ የሰሙ እንደመሆናቸው መጠን «ነው ። እውነትዎን ነው» በማለት የፊታውራሪን አሳብ ከማስተጋባት ሌላ የሚሰጡት አስተያየት አልነበራቸውም — እን



ደወትሮአቸው ። ፊታውራሪ ከማቴዎስ ወንጌል ምእራፍ ፳፭ ቁጥር ፩ እስከ ፲፫ ያለውን ጥቅስ ሳያነብቡ ሳምንት አልፎ አያውቅም ። ከዚሁ ንባባቸው የተነሳ «ቀጠሮ የማያከብር ሰው ውስጠ — አውሬ ነው» ማለትን ያዘወትራሉ እንጂ ሰው እንደሚለው እርጅና የጊዜ ንፉግ አድርገቸው አይደለም ። ፊታውራሪ ቀጠሉና ፣ «ለመሆኑ የሱዱ ቦሮ ህዝብ ስለጋብቻው ምን ያወራል?» ብለው ጠየቁ ።

የጡት ልጃቸው ቶሎሳ ከተቀመጠበት ተነስቶ ፣ «አረኞች በየሜዳው ፣

ገባ አላሻግር ቢል ክረምት ከበጋ

የጋብቻ ድልድይ ላዩ ተዘረጋ ።

ቦሮና ዋቅጅራ ተፋጥጠው አለፉ ደም እየተቃቡ ፣

ተካና እያና ፣ በጋብቻ ቂሙን ፣ ለመፋቅ አሰቡ እያሉ ይዘፍናሉ ። ሰው ግን በየቤቱ ለሰርጉ ባደረሰን እያለ ነው የሚመኘው» አላቸው ።

ፊታውራሪ ወደመሬት አቀርቅረው ትንሽ ከተከዙ በሁዋላ ፣ ቀና ብለው ፣ «የሚረሳ ነገር የለም ። ሆኖም አያልፍ የለምና ሁሉም ነገር አልፏል ። ማሰብ ያለብን ያለፈውን ሳይሆን የወደፊቱን ነው» አሉ ።

የፊታውራሪ ተካና የፊታውራሪ እያና አባቶች ፣ እንዲሁም አያቶች ፣ የታላቁ የገባ ወንዝ የወዲህና የወዲያ ማዶ ባላባቶች ነበሩና በግዛት ፣ በስልጣንና በክብር ስለሚቀናቀኑ አንደኛው ቤተሰብ ለሌላው አይተኛም ነበር ። ሱዱ ነፍስ የገደለው ገጦን ተሻግሮ ወደናጂ ሲያመልጥ ፣ እንዲሁም ኖጆ ውስጥ ወንጀል የፈጸመው ሱዱ ሲገባ ፣

ባላባቶቹ መጠለያ ስለሚሰጡት የሚቀጣው ስልጣን አልነበረም ። እንዲሁም ፣ ሁለቱም ባላባቶች ከገባ ወንዝ ላይ ማዶ ለማዶ ኬላ ተክለው አንዱ ሌላውን ሲቀርጥ ለረጂም ዘመን ኖረዋል ። የፊታውራሪ ተካና የፊታውራሪ አያና አባቶች ኬላው ላይ በተፈጠረው ውዝግብና መቃቃር ምክንያት የተነሳ ሰራዊቶቻቸውን አሰልፈው ጦርነት የገጠሙበትና ከሁለቱም ወገን ከአራት መቶ ሰው በላይ ያለቀበት ጊዜ ነበር ። ሁለቱም ግራዝማቾች የየጦራቸው ግንባር ቀደም በመሆን ሲዋጉ በጠና መቁሰላቸውና ፣ የፊታውራሪ አያና አባት በዚሁ ጠንቅ የተነሳ ለብዙ ዘመን የአልጋ ቁራኛ በመሆን ኖረው መሞታቸው ይነገራል ። ያኔ ነበር—

«ዝናብ ባገር ጠፍቶ ገባ እንደሰው ቢጠማው

በባላባቶች ደም ጥማቱን ተወጣው» ተብሎ የተዘፈነው ። ሆኖም እያንዳንዱ ባላባት በቀበሌው ከእግዜር በታች ያለውን ስልጣን ጨብጦ ፣ ትንሽ ዘውድ ደፍቶ ፣ ስሜቱን ህግ አድርጎ የሚኖርበት ዘመን ካለፈ ቆይቷል ። የማእከላዊው መንግስት ስልጣን ተስፋፍቶ ፣ የወረዳ ገዢው የአስተዳደሩንና ግብር የመሰብሰቡን ፣ የወረዳው ፍርድ ቤት የዳኝነቱን ፣ የወረዳው ፖሊስ ፀጥታ የማስከበሩን ስራ ከተረከቡ ወዲህ ባላባቶች በቀድሞው ዘመን የነበራቸው ፍፁም ስልጣን ጨርሶ በመዳከሙ ፣ ፊታውራሪ ተካና ፊታውራሪ አያና ከአባቶቻቸውና ከአያቶቻቸው የወረሱት ቂም ቢኖርም ፣ ሁለቱን የሚያሳስብ የጋራ ችግር እንጂ ፣ የሚያጋጫቸው ጥቅም ከቶ አልነበረም ። ከማእከላዊው መንግስት በመጠጋት አንዱ ሌላውን ለማሳጣት የተደረገው ሙከራና መሽቀዳደም ምንም ውጤት



አልሰጠም ። የደረሰባቸው ውድቀት ፣ ቂጥኛም ከውርዴ እንዲሉ ፣ እያደር ስላቀራረባቸው ያለፈውን ቂም በጋብቻ ለመሻር መረጡ ። የልጆቻቸው ለአቅመ አዳም መድረስ ጥሩ አጋጣሚ ሆነላቸው ። አይናለም የአስራ ሰምንት አመት ኮረዳ ፣ ዳኛቸው ደግሞ የሀያ ሁለት አመት ጉረምሳ ናቸው ። ፊታውራሪዎቹ በጉዳዩ ቀደም ብለው ያሰቡበት ቢሆንም ፣ አንዱ ሌላውን ለመነ እንዳይባል ፣ መምሬ መሀሪ አሳቡን ራሳቸው ያመነጩት አስመስለው ፣ ሁለቱን ቤተሰቦች በጋብቻ ለማቀራረብ ያደረጉት ሙከራና የተገኘው ውጤት በሱጴ ቦሮ ህዝብ ዘንድ ብልህና አርቆ አሳቢ አሰኝቷቸው ነበር ። አሳቡ ግን የኖጺው ባላባት የፊታውራሪ አያና ነበር ።

«በየቤቱ ሰሞኑን የሚወራ ሌላም ነገር አለ» አሉ ፣ መምሬ መሀሪ ፣ የቶሎሳን ፈለግ በመከተል ።

«ስለጋብቻው?» ብለው በመጣደፍ ፊታውራሪ ጠየቁ ።

«አይደለም ። አንድ አሁን በቅርቡ ተቀጥሮ የመጣ አስተማሪ ተጨማሪ ክፍሎች ካልሰራሁ ብሎ ባዶ እጁን ተነስቶ ፣ በሰላም የቆየውን ትምህርት ቤት ጨርሶ በጥብጦታል ። ብቻውን ሌሊት እየተነሳ ሲጐደፍር ሳየው ሰው እብድ ነው እንጂ ደህና ሰው አይመስልም……»

ፊታውራሪ መምሩን አቋረጧቸውና «ልስራ ካለ ምኑ ላይ ነው እብደቱ?» ብለው በትካዜ መልክ ጠየቁ ።

መምሩ አላመኑቱም — «ልጅ ያቦካው ለራት አይበቃም ይባላል ። የትምህርት ቤቱ አላፊ እስካሁን ሞክረው ያቃታቸውን እሱ ባዶ እጁን ተነስቶ ልስራ ቢል ይሆናል? የትምህርት ቤቱ አላፊ አቶ ይርጋ ተቃውመውታል ።

የአባ ጨፌም ሰዎች ተነስተውብታል ። እብድ ቢሆን ነው እንጂ» አሉ ።

«ባዶ እጁን ተነስቶ አንድ ነገር ልፍጠር የሚል ሰው የፈጣሪ ባህሪይ ያለው መሆን አለበት እንጂ እብድ አይባልም ። አንዱ ያቃተውን ሌላው ልሞክረው ብሎ ቢነሳ ደግሞ ምን ሀጢአት አለበት? ቶሎ አንፍረድ ። አንድ ቀን ይፈረድብናል ። በሀቅ ልስራ ብሎ በቅን መንፈስ የሚነሳሳውን ሰው መወንጀል — ጭንቅላቱን እንደ እባብ መቀጥቀጥ—ማጥፋት — ከፊቱ ላይ የተንኮልና የሸር መንጠባእት መዘርጋት — የቆየ ልማዳችን ነው ። በሀቅ የሰራው በተንኮል ማጭድ ተገዝግዞ ፤ ያልሰራው የክብር ካባ ሲጎናፀፍ በየጊዜው እናያለን ። ይህ አጉል የልማድ ነቀርሳ ካልተነቀለ — ከመወንጀል ማበረታታት ካልቀደመ — ዘመን ከመቁጠር እናልፍም — እንደግመል ሽንት ወደ ሁዋላ እያልን ። ታዲያ አባ ጨፌ ትምህርት ቤቱ እንዳይስፋፋ ቢቃወም ምን ያስደንቃል! ቃልቻዎችን መቋቋም ሲሆን የናንተ የቀሳውስት ፈንታ አልነበረምን? ቤተክርስቲያን ያስተከልኩት አንዱ ዋናው ምክንያት ቃልቻዎችን ለመቋቋም ነበር ። እርስዎ በዚህ ረገድ ሕዝቡን ምንም ሊረዱት አልቻሉም ። ይልቅ የልጁ ትምህርት ቤት ላስፋፋ ብሎ መነሣት የተሰፋ ጭላንጭል የሚሰጥ ሙከራ ነው ። በየገደሉ እየዞሩ መቀደስ ፤ የተኛውን ሰይጣን መቀስቀስ ነው የምትሉት እናንተው አይደላችሁም?» ብለው ለጥቂት ጊዜ በትካዜ ተዋጡና ፤ የራሳቸው ባልሆነና በጐረና ድምፅ «ብሩህ አእምሮና ጠንካራ መንፈስ ያለው ልጅ ነው ። ከዚህ ቀደም አነጋግሬዋለሁ ።



ቶሎሳም ከሱ ጋር ሲሰራ እንደሚውል አውቃለሁ ። አዎን — ርዳታ ያስፈልገዋል ከዚህም ሌላ» — ፊታውራሪ ወደእሩቅ ሲመለከቱ ቆዩና «አዎን — ልጁ አስተማሪዩን ያስታውሰኛል — አዎን — ስሙም መክብብ ነበር — ነፍሱን ይማረውና ። ጠይምነቱ ፤ የጠጉሩ ከርዳዳነት — የሚስቁ የሚመስሉት ትናንሽ የዋህ አይኖቹ — አካሄዱ ሳይቀር — ልዝብ አንደበቱ — መክብብን ያስታውሱኛል»— በዚያው አሳባቸውን አልገቱም—በተመሰጠ መንፈስ — «እንደመክብብ ሀይወቴን የለወጠው ሰው የለም» ብለው ጀመሩ — «መክብብ ከቤተክርስቲያን አቋም አስተያየቱ ያፈነገጠ ፤ ለምን? ብሎ መጠየቅን የሚያዘወትር ፤ በዚህ ላይ ደግሞ የሚጥል በሽታ በየእለቱ የሚያጠቃው ፤ ተፈጥሮ ብሩህ አእምሮ የለገሰው ደብተራ ነበር ። አንዳንዴ ወደቤተመቅደስ ገብቼ ወደፅላቱ ስቃረብና ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ስሜት ሲያድርብኝ በሽታዬ በድንገት ይጥለኝ ስለነበር ፤ ሰይጣን የተጠናወተው ርኩስ ሰው ነው ተብዬ ወደቤተ መቅደስ እንዳልገባ ተከለከልኩ እያለ ያጫውተኝ ነበር ። ይሁን እንጂ ወደቤተ መቅደስ እንዳይገባ የተከለከለው በሌላ ምክንያት ነበር ። ክርስቶስን በጣም ስለሚወድ የስቅለት ምስል በተመለከተ ቁጥር እንባው አይቆምም ። ሰው መጥቶ ካልወሰደው ምስሉን እያየ ፈዝዞ ይቀር ነበር ። ከተራ ፍቅር በላይ የሆነው ስሜት ሰቅዞ ሲይዘው እንደእብደት ያደርገው ነበር ። ትንሽ ቆይቶ በሽታው መጥቶ ማጅራቱን ይጨመድደውና ይጥለዋል ። እንደታረደች ዶሮ ተንደፋድፎ ፤ በአፉ አረፋ ደፍቆ ካበቃ በሁዋላ ነፍስ ገዝቶ በተነሳ ቁጥር ምንም ስህ የሌለበት አምላክ — ክርስቶስ ይል ነበር ። ከፍቅሩ የተነሳ የክርስቶስን አርአያና ትምህርት ብቻ

መከተል አለብን የሚል ብርቱ እምነት ስላደረበት ፤ ከመፅሀፍ ቅዱስ ሌላ የእምነት ምንጭ ሊኖር አይችልም ፤ እንጨት ማለሰለስ ፤ በአመት ውስጥ ያሉትን ቀኖች ሁሉ በበአላት ማስጌጥ ፤ ፆመ ልጓምን ፤ ስራ መፍታትን ማብዛት እምነት አይደለም ......

ለሌሎች አማልክት መስገድ የክርስቶስን ክብር መቀነስ ይሆናል ፤ ለብዙ አማልክት መስገድ በግሪኮችና በሮማውያን ዘመን ቀረ ፤ በአንድ ቀናተኛ አምላክ ብቻ ነው ማመን ያለብን እያለ ይከራከር ነበር ። ከጊዜ በሁዋላ ደግሞ የክርስቶስን አርአያ የምንከተል ከሆነ መፆም ያለብን አርባ ቀኖች ብቻ መሆን አለበት ማለት ጀምሮ ነበር ። ዝንባሌውን የጠሉ የሥራ ጓደኞቹ ርኩስ ስለሆነ ነው ወደቤተ መቅደስ ሲገባ የሚጥለው ፤ ሰይጣን በልቡ አድሮአል እያሉ ወሬ ስለነዙበት በሽታው እየባሰበት ሄደ ። ያኔ ነበር ወደቤተ መቅደስ እንዳይገባ የተከለከለው ። እና......ጀርባውን ለቤተክርስቲያን ሳይሆን ለቀሳውስት ሰጥቶ እግሩ ወደመራው ኮበለለ ። ሱዱ ቦሮ ደረሰ ። ያኔ ነበር አባቴ እኔን እንዲያስተምረኝ የቀጠሩት ። ለምን፣ ብለህ አትመራመር የሚልን ቄስና ፤ ፍርሀትን በደንቆሮዎች ልብ እየነዛ የሚገዛን ቃልቻ አታሳዩኝ ፤ የእውቀት መሰናክሎች ናቸውና ። እግዜር በቸርነቱ ተመራማሪ አእምሮ የሰጠን ፤ ለምን? ብለን ጠይቀን ከእውነቱ ላይ ስንደርስ ጥበቡን አድንቀን እንድንወደው ነው እንጂ ፤ በድንቁርናና በፍርሀት እንድንሰግድለት አይደለም ይለኝ ነበር አዘወትሮ ። የእውቀቱ ምንጭ መፅሀፍ ቅዱስ ነበር ። መፅሀፍ ቅዱስን አዘውትረህ አንብብ ። ለምን? የሚለውን ጥያቄ ግን አትርሳ ይለኝ ነበር ። ሌሎች ቄሶች አባቴ



ዘንድ በየጊዜው እየቀረቡ መክብብ እኔን እንዳያስተምረኝ ብዙ ጊዜ ደጋግመው ሳያሳስቡ አልቀሩም ። ታዲያ አባቴ መክብብን ለማባረር ቁርጥ አሳብ አድርገው በተነሱ ቁጥር እንባዬ መልሶ እንደልጓም ይገታቸው ነበር ። አባቴ አንዳንዴ መክብብን ለማባረር የሚነሱት ፤ በኔ አእምሮ የሚቀርፀውን አስተያየት ከከፍተኛ ጉዳይ በመጣፍ ሳይሆን ፤ በሽታው ወደልጄ ይተላለፍበት ይሆናል በሚል ፍራቻ ነበር ። መክብብ እንደቤተሰብ ሆኖ ለአስር አመቶች ያህል እኔን እያስተማረኝ ከኖረ በሁዋላ ፤ በሽታው እየጠናበት ፤ በቀን ከሁለት ሶስት ጊዜ በላይ በየቦታው እየጣለው ፤ ከእለታት አንድ ቀን ከአለት ላይ ተፈጥፍጦ ሞቶ ተገኘ ። ትዝታው ግን አይረሳኝም ። ይህ ልጅ ደሞ እሱን በጣም አድርጎ ነው የሚያስታውሰኝ — ሳየው — ሳነጋግረው» አሉና ትንሽ ተክዘዉ ሲያበቁ ቀጠሉና «የሰርጉ ጣጣ ይዞኝ ነው እንጂ በሚቻለኝ እረዳው ነበር» ሲሉ ፤ ቶሎሳ ያደረበትን የደስታ ስሜት ለማግታት ተስኖት ፤ ጮቤ እንደመርገጥም ፤ መሬት እንደመሳምም እየቃጣው ያቁነጠንጠው ጀመር ። ፊታውራሪ ሁኔታውን ሳያጤኑት አላለፉም ። «ሂድና በቅሎዩን ማንልኝ» ብለው አዘዙት ። እየፈነደቀ ወጣ ። መምሬ መሀሪ ባይናገሩም ፊታውራሪ ሀዲስን ለመርዳት ባደረባቸው ስሜት ያልተደሰቱ መሆናቸው በረጂም ጢም በተወረሰው ረጂም ፊታቸው ላይ ሊነበብ ይችል ነበር ።

«በዚህ እድሜ ካንድ ቦታ እጅና እግር አጣምሮ መቀመጥ የባሰውኑ ያስረጃል ። በስተርጅና ስራ መፍታት ደግ አይደለም ። ሆኖም ሁሉንም ካልሰራሁ ማለትም አያዋጣም ። ህይወት አስካለች አቅምን እየገመቱ መፍጨር

ጨር አይከፋም ፡፡ በተለይ በብርቱ ስራ ተጠምዶ የኖረ
ሰው ባንዴ ሲገለል ቶሎ ሰውነቱ ይወድቃል ፤ ያረጃል ፡፡
መንቀሳቀስ ደግ ነው ፡፡ ስለሰርጉ ሳወጣና ሳወርድ እርሻቸ
ንም ረሳሁት ፡፡ የዘንድሮ ሰራተኞች በአይን ቁራኛ ካልያዟ
ቸው አስበው አይሰሩም» አሉና ፊታውራሪ ተነሱ ……

ቀኑ ፀሀያማ በመሆኑ ይወብቃል ፡፡ ነፋሱ ፀጥ ስላለ
ዛፎቹ አይንቀሳቀሱም ፡፡ ፀጥ ብለው ቆመው ፀሀይ የሚ
ሞቁ ይመስላሉ ፡፡ ሰማዩ የጠራ ኩል መስሎ ተንጣሏል ፡፡
ግን ትምህርት ቤቱ የቀድሞ ፀጥታውን አጥቷል ፡፡ በፊት
ከክፍል ሲወጡ ወደየቤታቸው የሚሮጡት ተማሪዎች
ያለወትሮአቸው በመቆየት ከትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ
ይኯኯጣሉ ፡፡ ጠና ጠና ያሉት የአዲሱን ትምህርት ቤት
መሰረት ይቆፍራሉ ፡፡ ሀዲስም ከተማሪዎች መካከል
ወዲህና ወዲያ እያለ ይቆፍራል ፡፡ ሰውነቱ በላብ ርሷል ፡፡

አቶ ይርጋ አለሙና የመቶ አለቃ አሸኔ ይምታቱ
ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር ቢሮ ተቀምጠው የሀዲስ
ንና የተማሪዎቹን ስራ በአድናቆት ሳይሆን በጥላቻ አይ
ኖች ይመለከታሉ ፡፡

ሀዲስ እያነሳ የሚጥለው ገሶ ልባቸውን በድሶ የሚ
ጥለው ያህል ነበር የሚሰማቸው — ለአቶ ይርጋ ፡፡ ሀዲስ
እጆቹን አንስቶ በጣለ ቁጥር ልባቸው በንዴት አብሮ



ተነስቶ ይወድቃል ፡፡ ሰባት አመት ሙሉ …… ሲሉ
አሰቡ—የተጋፋኝ ሰው አላጋጠመኝም ነበር ፡፡ እና አሁን
ይህ ግትር! አሉና በአይናቸው እንደጦር ወጉት ፡፡

አቶ ይርጋ አለሙ ከሰባት አመቶች በፊት የቅድ
ስት ማርያምን ትምህርት ቤት እንዲያስተዳድሩ ወደሱጴ
ተልከው ሲመጡ ፤ አንዲት ከቦንዳ እንጨት የተሰራች
ሳጥን ይዘው ነበር የመጡት ፡፡ ግን ዛሬ የሶስት ጋሻ የቡና
መሬት ባለቤት ለመሆን በቅተዋል ፡፡ ግማሹ መሬት በባ
ለቤታቸው በኩል የመጣ ሲሆን ፤ የተቀሩትም ደግሞ
ከጡት አባታቸው ከዳሪሙ ባላባትና ፤ ልጆቻቸውን ተቀ
ብለው በማቀማጠል ከሚያስተምሩላቸው አንዳንድ የሱጴ
ከበርቴ ነጋዴዎች ነበሩ ፡፡ አቶ ይርጋ በግምቢ ከሚሲዮ
ናውያን ካገኙት ጥቂት የእንግሊዝኛ ትምህርት ሌላ ራስን
በራስ ሊያስተማምን የሚችል እውቀት አልገበዩም ፡፡
በህይወታቸው ይህንን ያህል ሀብት አገኛለሁ የሚል
አሳብም አልነበራቸውም ፡፡ ኑሮአቸው በሰባት አመቶች
ውስጥ ተቃንቶ በማግኘታቸው የቅድስት ማርያምን ትም
ህርት ቤት እንደ ገፀ በረከት መመልከትና በየአመቱም
በማርያም ስም ሰንጋ ጥለው የትምህርት ቤቱን ልጆች
ወላጆችና የሱጴን ታላላቅ ሰዎች ጠርተው ማብላት ከጀ
መሩ ቆይተዋል ፡፡ አንዳንዴ ትምህርት ቤቱን እንደልብ
ሩቅረኛ የሚመለከቱበትም ጊዜ አለ ፡፡ «በአይኔና በገዴ
የለም ዋዛ» ይላሉ የትምህርት ቤቱ ነገር በተነሳ ቁጥር ፡፡
ከዚህ ሌላ ስለትምህርት ቤቱ ያላቸውን ልዩ ስሜት ለማ
ስረዳት አይችሉም ፡፡ በአቶ ይርጋና በትምህርት ቤቱ
መካከል ያለውን መስተፋቅር በመረዳት ሳይሆን አይቀ
ርም አቶ ይርጋ ወደአባ ጨፌ በሄዱ ቁጥር ፤ «ከትምህርት

ቤቱ ከተለየህ ጤንነትህንና ሀብትህን ያሰጋቸዋል» ሳይላቸው አያልፍም ። ከሚሲዮናውያን ያገኙት ትንሽ እውቀት ፤ እምነታቸው ለአባ ጨፌ አባባል ጨርሶ እንዳይንበረከክ እየታገለ በማመንና ባለማመን መካከል እንደወሀ ላይ ኩበት ይንሳፈፋሉ ። ስለዚህ ወደሌላ ቦታ አዛውሩኝ ብለው የጠየቁበት ጊዜ የለም ። ወደተሻለ ቦታና ትምህርት ቤት በተሻለ ደመወዝ እንዲዛወሩ ከአንድም ሁለት ጊዜ ጥያቄ ቀርቦላቸው አልተቀበሉትም ። ይህን ትምህርት ቤት ወደከፍተኛ ደረጃ ሳላደርሰው ፤ ለድሎትም ሆነ ለተጨማሪ ደመወዝ ወደሌላ ቦታ ለመዛወር ምኞት የለኝም በማለት የግል ጥቅማቸውን ለከፍተኛ አላማ መስዋእት ያደረጉ በማስመሰል ሁለቱንም ጊዜ መልሰዋል ። ሆኖም ፤ ይህን ያደረጉበት ምክንያት ለሀዲስም ሆነ ለሌሎቹ አስተማሪዎች የተሰወረ አይደለም ። አብዛኛውን ጊዜአቸውን የሚያሳልፉት በትምህርት ቤቱ ሳይሆን ፤ የቡና ችግኝ በማፍላት ፤ በማስተከል ፤ በማስኮትኮት ፤ ደን በማስመንጠር ፤ ቡና በማስለቀም ፤ በማስፈልፈልና በማሳጠብ ፤ በመሸጥና በመጫን ነው ። የሰው ልቡ ያለው ጥቅሙ ካለበት ቦታ ነው እንደሚባለው አቶ ይርጋ ከሱጲ ቦሮ እግራቸውን ለመንቀል ፍላጎት የላቸውም ። ለትምህርት ቤቱ እንደሆነ ፤ የበጀት አለመገኘት ፤ ጉዳዩን ውርድ ከራስ አድርጐታልና ፤ ሀሊናቸውን የሚያስጨንቅ ነገር ከቶ የለም ። የሚያስጨንቃቸው ነገር ቢኖር በየአመቱ እየጨመረ የሚሄደው ውፍረታቸው ብቻ ነው ። አሁን ግን ……

«የዳቆን ሰይጣን ሳይቀስ አይለቅም ይባላል ። ይህን ሰው ምን ባደርገው ይሻል ይሆን?» አሉ ፤ አቶ ይርጋ ። አይኖቻቸው ደም ለብሰዋል ። መንፈሳቸው ተረብሿል ።



«ወደመቱ ፅፈህ ለበላይ አመልክት……»

«ምን ብዬ? ትቀልዳለህ መሰለኝ ። አዲስ ትምህርት ቤት ለመስራት ተነሳስቷልና ከዚህ አዛውሩልኝ ብዬ ላመለክት አልችልም ። ይህማ ራሴን ማጋለጥ ይሆናል ። ሌላ መላ መምታት አለብኝ ……»

«ያንተ ወንድምነት ባይዘኝኮ ለዚህ ልጅ ልቤ ይራራል ። ለምን እንደሆነ አላውቅም ። እኔ ሸካራ መልኩ ወይም ጩጉጉት ፊቱ አይደለም የሚታየኝ ። በውስጡ ያለችው የማትስገበገበው ጠንካራ ነፍሱ ናት የምትታየኝ ። የጉርምስናዬን ዘመን ስለሚያስታውሰኝ ነው መሰለኝ ……»

አቶ ይርጋ ከበራቸውና ካንገታቸው ላይ የተንጠፈጠፈውን ላብ በመሀረብ ጠረጉና ፤ «ተማሪዎቹ በትምህርት ሰአትም ሆነ ከክፍል ውጭ እንዳይሰሩ ደንብ አውጥቻለሁ ። ረዳትና አማፋሪ ሲያጣ ተስፋ ቆርጦ ይተወው የለ!» አሉና ከንፈራቸውን ነከሱ ።

የመቶ አለቃ በረጂሙ የጀመረውን አሳብ አቋረጠና በግማሽ ልብ «አዎን — ከክፍል ሲወጡ እዚህ እንዳይቆዩ ደንብ ማውጣት ነው ። አባ ጨፌም በበኩሉ ሊረዳን ይችላል ። ሁሉም ባይሆኑ አብዛኞቹ ወላጆች ከእርሱ ቃል አይወጡም ። ችግሩ ተማሪዎቹ እምቢ ያሉ እንደሆን ነው ። እንዲያውም ባዲሱ ደንብ ምክንያት ተማሮች ሊያድሙ ነው የሚል ወሬ ሰምቼ ነው የመጣሁት ። የዘንድሮ ተማሪና ጤጣ አንድ ናቸው!»

«እሱማ በጀ ። እሺይ ላሜ ወለደች ማለት ነው ። ጉዳዩ ወደወንጀል ያመራና ባጠመዱት ወጥመድ መግ

ባት ይመጣል ። ምን ከፍቶኝ ። ተማሪዎቼ አድመው በእ
ምቢተኛነት እንሰራ ባሉና ደስ ባለኝ» አሉና ቀጥለውም
«ነገሩ መቼ የተማሪዎች ብቻ ሆነ ። ወላጆችና የከተማው
ታላላቅ ነጋዴዎችም እየመጡ ፤ ይህን ሰው ያዙልን ማለት
ጀምረዋል ። ለቤት ቀርቀሮ ፤ ለምስማርና ለአሸዋ ገንዘብ
ለማግኘት ሲል ፤ ተማሪዎቹን እየሰበሰበ እንደኩሊዎች
በቡድን በቡድን ሆነው በቡና ለቀማ ስራ እየተሰማሩ
ገንዘብ እንዲያገኙለት አድርጓቸዋል ። ልጆቹ ባነስተኛ
ዋጋ ስለሚሰሩ ከየቦታው ለቡና ለቀማ ስራ የመጡትም
ኩሊዎች ተናደው በማደም ላይ ናቸው አሉ ። የቡና ገበ
ሬዎችም በነገሩ ተደናግጠዋል ። ትናንት እንኳ ሶስት
የቡና ነጋዴዎች ስለዚሁ ጉዳይ ሊያነጋግሩኝ እዚህ መጥ
ተው ነበር ። ኩሊዎቹ ለንጀራቸው ብለው አንድ ቀን
ተነስተው ልጆቹን በቆንጨራ እንዳይጨፈጭፉና ጉድ
እንዳይፈላ ብቻ ነው የምፈራው ። ልጆቻችን ትምህርታ
ቸውን ትተው ለምን ቡና ይለቅማሉ እያሉ የሚያማር
ሩም ወላጆች እየበዙ ሄደዋል ። ይህ ሁሉ ተደምሮ በቅ
ርቡ ከፍተኛ ብጥብጥ ማስከተሉ አይቀርም ። ፀጥታን
ማስከበር የናንተ ፖሊሶች ፈንታ ነው» አሉት ።

«እኔም ሆንኩ አንተ ቀድመን ባናስተጓጉለው ፤ የመ
ጣው ድርቅ ሳያጨናግፈው አይቀርም ። በዚህ መከራ
ጊዜ የእለት ጉርሱን ከማባረር አልፎ እሱን የሚረዳው
አይገኝም ። እህል የለም ። ወሀም ችግር ሆኖአል ። እሱም
ችግሩ ሲጠናበት ይተወዋል» ———

የዘንድሮም የበልግ ዝናብ እንደአምናው ቀጠሮውን
ጠብቆ በሰአቱ ባለመድረሱ የሱኬ ሜዳዎች ፤ ተራሮ
ችና ሸንተረሮች እንበጣ እንደመታው ማሳ መራቆት



ጀምረዋልና ህይወት አይታይባቸውም ። ተፈጥሮ በጥ
ማት ታዛጋለች ። ነፋስ የሚያስነሳው አቧራ ሀልውናን
ለማፈን እየቃጣ ይነሳል ፤ ይወድቃል ። የመሬቱ ግስት
እንደረመጥ እየተፋጀ ይሄዳል ። ርጥብ አረንጓዴ ሳር ቀስ
በቀስ ወደአቧራ እየተለወጠ ስለሄደ ከብቶች ለግጦሽ አን
ገታቸውን ወደመሬት መቅልበስ ካቆሙ ሰንብተዋል ።
ከዛፍ ተጠግተው ያለርህራሄ እንደጦር ከምትዋጋው ፀሀይ
እንዳይጠለሉ ፤ የግራር ዛፎች ሁሉ ቅጠሎቻቸው ረግፈው
ምስጥ በልቷቸው ካበቃ በሁዋላ ከመቃብር የወጡ አጥን
ቶች መስለው ቆመዋል ። በየሜዳው የተሰማሩት ከብቶች
የሚያመነዥጉት ነገር የላቸውም ። እነርሱም እንደግራር
ዛፎች ከመቃብር የወጡ አጥንቶች እየመሰሉ በመሄድ ላይ
ይገኛሉ ። አብዛኞቹ ተዳክመው በየቆሙበት ያንቀላፋሉ ፤
ጥቂቶቹ የጣሉትን እበት ያሸታሉ ። ያንዱ ሰርግ የሌላው
ሀዘን እንዲሉ ፤ ጆፌ አሞራዎች ከየግራሩ ላይ አሰፍስፈው
ይጠባበቋቸዋል ። በየሸንተረሩና በየወንዙ ወደጥቁር አረ
ንጓዴ ቀለም ተለውጦ የረጋው ወሀ ከርፍቶ ፤ አፍንጫ
ይወጋል ። እረኞች እንደወትሮአቸው ከመንጋ ያፈነገጠ
ከብት ሲያባርሩ አይታዩም ። የበሬ ትከሻ ከቀንበር አር
ፎአል ። የተሳለ ማረሻ ከቤት ቀርቶአል ። ገበሬ ሰማይ
ሰማዩን በአይኖቹ እያማተረ እጆቹ ስራ ፈትተዋል ።
የእርሻው መሬት ተሰነጣጥቆ እንደተከፈተ መቃብር ያዛ
ጋል ። ህይወት አሸልባለች ።

አቶ ይርጋ ሲያስቡ ቆዩና «ድርቁስ ቢሆን መቼ
እጁን አሰረው ብለህ ነው! ተማሪዎቹንና ጓደኞቹን ፤
እያግባባ እንዲሁም በራሱ ገንዘቡ ኩሊ እየቀጠረ የወሀ
ጉድጓዶች ማስቆፈር ጀምሮአል ። በገንዘቡ አምስት አህዮች
ገዝቶ ከገባ ድረስ ወሀ ያመላልሳል ። ትንሽ ጊዜ ሲያገኝ በየ

ቤቱ እየዞረ ርዳታ ይለምናል ። በቀደም ለት ብቻ ተመላልሰ በልመና ሰላስቸገረው አንዱ ነጋዴ ባሽከሮቹ አስገፍትሮ ከግቢው አስወጣው አሉ ። የሚገርመው ነገር ከዚያ አል ሄደም ። ሰውዬው ከቤቱ ሲወጣ ደጅ ቆሞ ስላየው ተገ ርሞ መቶ ብር ሰጠው አሉ……» ሲሉት የመቶ አለቃ አቋረጣቸውና —

«ውነትም የሚያስገርም ሰው ነው ። ምን አይነት ጠንካራ መንፈስ ቢኖረው ነው ባካችሁ? እኔ የፖሊስ ጣቢያ አሰራለሁ ብዬ ከተነሳሁ ቆይቻለሁ ። ማን ነው ወንድሜ? — አንዱ ደግሞ ክሊኒክ አሰራለሁ ብሎ ሲፎክር ቆይቶ ሳይሆንለት ሄደ ። ብቻ ነገሩ አንተ እንዳልከው ወደከፋት ሳያመራ መቆጣጠሩ አይከፋም ። ተማሪዎቹ ትምህርታቸውን ካቆሙ — ኩሊዎቹ በተማሪዎች ምክንያት ካደሙ — እሱን የምናጠምድበት መንገድ ይገኛል» አለና የልብ ልብ ሰጣቸው።

ፊታውራሪ ተካ ወደቤታቸው የሚያመራውን ዳገት በበቅሎ ተያይዘውታል ። ቀደም ሲል አንድ ሰድስት ጊዜ ጥይት መተኮሱን ሳይሰሙ አልቀሩም ። ሰው ሲሯሯጥ በማየታቸው ነገሩ እየከነከናቸው ሄደ ። ቶሎሳ እየ



ሮጠ ወያኢርሳቸው ሲመጣ በማየታቸው በቅሎአቸውን አቁመው ጠበቁት……

«ምንድን ነው ነገሩ?» አሉት ።

«እረ ከተማው ተረብሿል» አላቸው ።

«በምን የተነሳ?»

ገበሬው እጁን ሳይታጠብ ወደከተማው ይሮጣል ። ሴቷ ሊጥ ያቦካችበትን እጇዋን ሳታለቀልቅ ነጠላዋን ጥላ ወደ ከተማው ትከንፋለች ። ተማሪዎች ከከተማው ወደ መንደር ይሮጣሉ ። ፊታውራሪን ማጀብ ቀርቶ ቆም ብሎ እጅ የሚነሳቸው ሰው እንኳ አልነበረም ።

ቶሎሳ እየተጣደፈ «ተማሪዎች ከክፍል እንደወጡ ወደየቤታቸው እንዲሄዱ የሚል አዲስ ደንብ ስለወጣ እድማ በማድረጋቸው በትምህርት ቤቱ ብጥብጥ ተነስቷል ። ተማሮቹን ለመበታተን ጥይትም ተተኩሶ ነበር ። ወላጆች ሁሉ ተሰብስበው በመላቀስ ላይ ናቸው ። ያ አዲሱን ትምህርት ቤት አሰራለሁ ብሎ የተነሳውም ልጅ ፣ ተማሮቹን አሳድመሀል ተብሎ ወደፖሊስ ጣቢያ ተወሰዷል ። ታስሮ ሲሄድ በየመንገዱ ልጆቻችንን ወደ ከፋት ለመምራት የመጣ ይሁዳ እያለ የማይረገመውና የማይተፋበት ወላጅ አልነበረም» አላቸው በሀዘን ተውጦ ፣ የእንባ ጭጋግ አይኖቹን ሸፍኖት…… በዚያው ትንፋሽ ቀጠለና «ግማሹ እየረገመው ፣ ሌሎቹ እየተፋበት ፣ ተማሪዎቹ ደግሞ አይዞህ ጋሼ! አይዞህ! ሲሉት ክርስቶስ በመስቀል ጉዳና እየተሰቃዩ ሲጓዝ በአሳቤ መጥቶ ታየኝ ። የሚሰሩትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አላለም ። ብቻ የትምህርት ቤቱን ስራ የጀመረበትን ፣ እግሩ የሱጴ ቦሮን

ምድር የረገጠበትን ቀን ይረግም ነበር ። ህዝቡን ጠላ ። ሱቁ ቦርን ጠላ ። ራሱንም ጠላ ። የህዝቡ ስሜትና አስተሳሰብ ሲገባው አልቻለም ። ምስጋና ለሌለው ስራ ምን አታከተኝ ምን አለፋኝ እያለ ራሱን ይጠይቅ ነበር . . . »

ፊታውራሪ ፤ ቶሎሳን ካዳመጡ በሁዋላ ደማቸው ወደ ራሳቸው ወጥቶ አይኖቻቸው መቅላት ጀመሩ ። ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ እሳት የሚተፉ መሰሉ ። በቅርብ የሚያውቋቸው ሰዎች ፊታውራሪ ተቆጥተው እንደሆኑ ለማወቅ ሲፈልጉ አስቀድመው አይኖቻቸውን ነበር የሚመለከቱት ። አይኖቻቸው ቀልተው እሳት የሚተፉ ከመሰሉ ደፍሮ የሚያነጋግራቸው ሰው የለም — ካንዷ ልጃቸው ከአይናለም ሌላ ።

ቶሎሳ ፤ ፊታውራሪ መቆጣታቸውን በማወቁ እንደሌላው ጊዜ አልደነገጠም ። ፊታውራሪ እንደዚያ ተቆጥተው የበቅሎአቸውን ፊት ወደከተማ በማዞራቸው በደስታ ብዛት የልቡ ትርታ ጨመረ......

ፊታውራሪ አዘውትረው ፤ «ከመወደድ መከበር ፤ ከመከበር ደግሞ መፈራት ይሻላል» ይላሉ ሰለሰው ማግኘት አንስተው በተናገሩ ቁጥር ። ከነአጃቢዎቻቸው ወደፖሊስ ጣቢያው በቀጥታ አመሩ ።



ፊታውራሪ ዳገቱን ወርደው ፤ የእልቁን ወንዝ ወደ ግራ በመተው ሜዳ ሜዳውን ይዘው ወደሰንበተ ጉዳ ማምራት ሲጀምሩ የአጃቢዎቻቸው ቁጥር ወደአስር ደርሶ ነበር ። ግርግርና ሩጫ ባይበዛ ኖሮ የሚሄዱበት አግጣጫ ወደሌላ ቢሆንም ዝም ብሎ የሚያልፋቸው ሰው ከቶ አይገኝም ።

ከጣቢያውም ሲደርሱ ተማሪዎች ከፖሊስ ጣቢያው ቅፅረ ግቢ ተሰብስበው እንባ ሲራጩ አገኟቸው ። ይሁን እንጂ የፊታውራሪ ከዚያ መገኘት በመጠኑም ቢሆን እርጋታ ለመፍጠር ቻለ ። ሁሉም በየፊናው መንጫጫቱንና እንባ መራጨቱን አቁሞ ፤ ፊታውራሪ ምን ሊያደርጉ ይሆን የመጡት? በማለት በልቡ ማሰብ ጀምሮ ነበር ። ወዲያውኑ ፤ የጣቢያው አዛዥ ፤ የመቶ አለቃ አሸኔ ከየት መጣ ሳይባል ከተፍ አለ ። ፊታውራሪ ከመጠን በላይ አጎንብሰው እጅ ነሱት ።

«ምንነው? ደህና መጡ እንዴ?» አላቸው ፤ የመቶ አለቃ አሸኔ ። እርሱ መጠጥ ቤት ገብቶ ይጠጡልኝ ብሎ የማይለምነው ሰው ስለሌለ ፤ የአይኑ የተፈጥሮ ቀለም ምን እንደሚመስል የሚያውቅ የለም ። ኮከቡን ጭኖ ፤ መለዮውን ደፍቶ ብቅ ሲል ፤ የማሰርና የመፍታት ስልጣኑ እስከ ምን ድረስ እንደሆነ የሚያውቁት ሁሉ ስለሚሰግዱለት ፤ መለዮው ትንሽ ዘውድ መስላ ነበር የምትታየው ። ፊታውራሪ ከሚጠበቅባቸው በላይ ትህትና ሲያሳዩ ፤ የመጡበት ጉዳይ እንዲፈፀም ምን ያህል ፍላጎት እንዳላቸው የሚያስገነዝብ መሆኑን ሳይረዳው አልቀረም ። ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ አለ በልቡ ።

«ወዳጄ ነህና በማእረግህ ያልጠራሁህ እንደሆን አት
ቀየመኝ ። ሽማግሌ ነኝና የዘመኑ ማእረግ አይያዝልኝም ።
እኛ የምናውቀው ራስ ደጃዝማች ፊታውራሪ ፣ ቀኛዝማ
ችና ግራዝማች ነው ። የመጣሁበትም ጉዳይ ቀላል ነው ።
አንድ ዘመዴ እንዲያውም ሳታውቀው አትቀርም የቅድ
ስት ማርያም አስተማሪ ነው — እዚህ ለጊዜው ታስሯ
ልና ዋስ ሁኜ ላስፈታው ነው የመጣሁት» አሉት በጥ
ሞና ።

«እንዴ — ፊታውራሪ እሱ'ኮ የተያዘው በከባድ
ወንጀል ነው ። ተማሮችን እያሳደመ አስቸግሮአል ። ፀጥታ
መጠበቅ አለበት ። ፀጥታው በሱ ምክንያት ሲደፈርስ ዝም
ብሎ ማየት አይቻልም ። አሳፊነት አለብኝ ። እንዴት አድ
ርጌ?» አላቸው ።

«የለም'ኮ» አሉ ፊታውራሪ — «ነፍስ አልገደለም ።
ልስራ የሚል ሰው ደግሞ ሊሳሳት ይችላል ይል ነበር
መክብብ ነፍሱን ይማረውና ። የምጠይቀው ምህረት
እንዲደረግለት አይደለም ። ጥፋቱ እስኪጣራ ድረስ ዋስ
ልሁነውና ይለቀቅ ነው የምለው» አሉት በርጋታ ።

«እርስዎ ዋስ ከሆኑ እኔ ምንቸገረኝ» አለና ፣
ጉዳዩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ ለማስገንዘብና ለማስ
ፈራራት ያህል ፣ «ወንጀሉ ቀላል አይደለም ። የፀጥታን
ጉዳይ የሚመለከት ነው ። ለጥያቄ በተፈለገ ጊዜ ያቀርቡ
ታል ። አሳፊነቱ ሁዋላ ከርስዎ ላይ አይወርድም» አላቸው ።

«ሳላፊነቱስ ግድ የለም» አሉት ።

ሀዲስ ከነበረበት እስር ቤት አንገቱን ደፍቶ ሲወጣ
ውጭ ምን እንደሚጠብቀው አያውቅም ነበር ። ግራ እን



ደገባው ሰፋ ያለው ጠይም ፊቱ ይናገራል ። ወደፊት ያፈ
ጠጠው አገጩ ግን ቅስሙ ገና እንዳልተሰበረ ያረጋግጥ
ነበር ። ሆኖም ትናንሽ አይኖቹ በንዴት ቀልተዋል ።
ከርዳዳ ጠጉሩ አልተበጠረም ። ድርውኑ ፀድተው የማ
ይታዩት ከሲታ ጉንጮቹ የሳምንት እድሜ ባለው ጢም
ተወርሰው ጠቁረዋል ።

እጆቹን እንደልማዱ ከሱሪው ኪሶች ውስጥ ከትቶ
እንደተዋጊ በሬ አቀርቅሮ ብቅ ሲል ፣ ፊታውራሪ በአ
ይኖቻቸው እየቃኙት ፣ «ወዳጄ ፣ የረገሙህንና የተፋ
ብህን ሁሉ ይቅር በላቸው ባያውቁ ነው ። አለማወቅ
ክፉ ። ክርስቶስም የተወገረው አስተምራለሁ ብሎ ስለ
ተነሳ ነው» አሉትና ወደ መቶ አለቃ አሸኔ ዞር ብለው
«እንዳከበርከኝ እግዜር ያክብርህ» ብለውት በቅሎአቸው
ላይ በቶሎሳ ርዳታ ወጥተው ከነአጀባቸው ወደትምህርት
ቤቱ አመሩ ።

ትምህርት ቤቱ የተሰራው የእልቁ ወንዝ የሱዳ
ንና የሰንበተ ጉዳን መንደሮች እንደመቀነት ሊዞር ትንሽ
ሲቀረው ወደገባ ወንዝ ቁልቁል ለመውረድ ከሚጀም
ርበት ከፍታ ቦታ ላይ ነው ። ከዚያ ሲደርሱ ከበቅሎአ
ቸው ላይ ወርደው ያዲሱ ትምህርት ቤት መሰረት ወደ
ተጣለበት ቦታ በማምራት እግረ መንገዳቸውን አንድ
ከባድ ድንጋይ አንስተው ከተጀመረው ካብ ላይ አስቀ
መጡ ። የእርሳቸውን ፈለግ በመከተል የተከተላቸው
ሰው ሁሉ ድንጋይ እየወሰደ ይክብ ጀመር ። በሀዘን ጠቁሮ
የነበረው የሀዲስ ፊት በፈገግታ ቀለወጠ……

አቶ ይርጋ ተኝተው ያደሩ አይመስሉም ። ጥቁሩ ፊታቸው ዱቄት የተነፋበት መስሏል ። አይኖቻቸው ቀልተዋል ። የርጋታ መንፈስ አይታይባቸውም ። አንድ ቦታ ረግተው መቀመጥ እንኳ አልቻሉም ። እንደተራበ ነብር ከቤታቸው በረንዳ ላይ ወዲህና ወዲያ እያሉ ይንጎራደዳሉ ። የመቶ አለቃ አሸኔ ቀልተው በሚታዩት አይኖቹ ይከተላቸዋል — ረጃጅም ቅልጥሞቹን ዘርግቶ ።

«ጉድ ሰራህኝ'ኮ» አሉት ። ሰላላዋ ድምፃቸው የባሰውኑ ቀጥናለች ።

«ምን ላድርግ ጋዲያ! ፊታውራሪ ተካ በነገሩ ይገባሉ ብዬ አላሰብኩም ነበር ። ነገሩ ሳይከር በቀላሉ ማብረዱ ደግ ነው ። ፊታውራሪ የዋዛ ሰው አይደሉም ። ከእርሳቸው ጋር ከተጋጨሁ አንድ ቀን በህይወቴ ማደሬን እጠራጠራለሁ ። ደመከልብ ሆነህ ቅር ነው እንዴ የምትለኝ — ጉዳዩን ስታውቀው? ትምህርት ቤት እንዳይሰራ ነው ይህን ያደረጉት ብንባልስ በሁዋላ ምን ይውጠናል? »አለ የመቶ አለቃ ፤ በርጋታ ፤ ረጃጅም ቅልጥሞቹን ሲሣምር ።

አቶ ይርጋ በንዴት በረጂሙ ተንፍሰው ፤ «አንተን ያመነ ጉም የዘገነ አንድ ነው ። ባላብህ አትፀናም ። ታወ



ላውላለህ ። ጓደኝነትህ ለዚህ ጊዜ ካልሆነኝ ለመቼ ሊሆነኝ! ለኔ ብለህ ርምጃ ወሰድክ ፤ ፊታውራሪን ፈርተህ ለቀቅከው ። እንደተልባ መንሸራተት ደግ አይደለም ። ያስተዛዝባል ። ትምህርት ቤቱ ተሰራም አልተሰራም ፤ እኔን ማሳጣቱ አልቀረም ። ለበላዮቼ እንዳልፅፍ የጠየቁት እንደሆነ ፤ አንተ እንዳልከው ፤ እሱም ምክንያቱን ይሰጣል ። አንድ ለፍዳዳ ግትር እንዲህ ሲጫወትብኝ ወይኔ ይርጋ! መቼም ፊታውራሪን ተገን ባያደርግ ይህን ያህል የልብ ልብ አያገኝም ነበር ። ምናባቴ አድርግ ትለኛለህ?» አሉት ጭንቀት ተጭኖአቸው ።

«እንደምታውቀው የፊታውራሪ ተካ እጅ አይጠመድም ። ብቻ ነገሩ ቀላል ነው ። እስከዚህ የሚያስጨንቅ አይደለም» አላቸው ፈገግ ብሎ ። ቀጠለና «አንተም የምትፈልገውን እንዴት ለማግኘት እንደምትችል አታውቅም ። ማንኛውም ነገር በእድልና ባጋጣሚ ተሳክቶ ካልተገኘልህ ግራ ይገባሀል ። ለምን እንደምትጨነቅ አይገባኝም ። ትምህርት ቤቱን እንደሚሰትህ ትቀናበታለህ ። ፅላት አይደለ መሻሻል አለበት ። አንተ ደሞ አታሻሽለውም ። ይልቅ ምክር ልስጥህ ። እሱ ይስራ ። አንተ ምናስጨነቀህ ። ሲሆን ከዛሬ ጀምሮ በትምህርት ቤቱ ስራ ተባባሪ መሆንክን ማሳየት ነው ። እባጨፌም ፊታውራሪ ተካን ፈርቶ በነገሩ አልገባም ። የዋዛ ቃልቻ አይደለም ። እንዲህ አይነት ትምህርት ቤት ማሰራት ጀምሬአለሁ ብለህ ለበላዮችህ ግለፅ ። ትምህርት ቤቱ በሚመረቅበት ጊዜ ቀደም ብለህ ንግግር ማድረግና ምስጋናውን መቀበል ነው ። ሁሉም የሚጠቀምበት ዘዴ ነው ። አንዱ በለፋው ሌላው ለመመስገን ። ሀዲስ እንደሆን ለምስጋና ደንታ ያለው ሰው አይመስለኝም ። ትምህርት ቤቱ ከፍፃሜ

ደርሶ ከማየት ሌላ ደስታ ያለው አይመስለኝም ። ባንድ ሞኝ መጠቀም እንዴት ችግር ይሆናል — ያውም ጋልቡኝ የሚል ፈረስ ሲገኝ» አላቸው ።

አሳቡ ለትክክኛቸው የከበደ ይመስል መንጐራደዳቸውን አቁመው «እስካሁን አካፋና ዶማ ይዞ የተነሳብኝ ጠላት አጋጥሞኝ አያውቅም ነበር ። ቀን አያመጣው የለ — ይህን ጉድ ከምን ጣሰብኝ ባካችሁ?» አሉ ፣ ተከዘው ።

«እኔም ሳየው ይገርመኛል» አሉ ፣ የመቶ አለቃ— «ተማርን ተመራመርን ፣ አወቅን እንደሚሉት ሌሎች በርሱ ደረጃ እንዳሉት ወጣቶች አይለፈልፍም ፣ ዝግ ነው ። ተናግሮ እንኳ አያጠግብም ። ከመናገር መስራትን ይመርጣል ። የኢትዮጵያ መድህን ፣ ስረየት የሚሰራ እጅ ነው የሚል ፈሊጥ አለው ። በእጁ ያመልካል ። እብድ ነው እንዳልል አይደለም ፣ እንዲህ ያለው ሰው አደገኛ ነው…»

አቶ ይርጋ የመቶ አለቃ አሸኔ የሚናገረውን በሙሉ ልባቸው አልነበረም የሚያዳምጡት ። ግማሽ ልባቸው የሚያሰላስለው ወደጠቅላይ ግዛቱ ትምህርት ቤቶች መምሪያ ሲፅፉ ያሰቡትን ደብዳቤ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የመቶ አለቃ ማወላወሉን አቁሞ ከእርሳቸው ጋር በሙሉ ልብ የሚሰለፍበትን መንገድ ነበር — ከየቦታው ለእንጀራ — ለእለት ጉርስ ብለው ተሰድደው ለቡና ለቀማ የመጡት ኩሊዎች — እምን — ለግል ጥቅማቸው ሲሉ — ተማሪዎች ስራቸውን በቀላል ዋጋ ሲማረቷቸው — ወላጆችም ነጋዴዎችም በነገሩ ሲገቡ — የመቶ አለቃ ጢስ አይደለም — በምን ቀዳዳ ይወጣል — የአቶ ይርጋ ተስፋ እያንሰራራ ሲሄድ ፊታቸው ላይ ይነበብ ነበር ። የመቶ



አለቃ የአዲሱ ተስፋቸውን ምንጭ ለማወቅ «ታዲያስ?» አላቸው ።

«ጊዜ የለኝም ። ወደቡና እርሻዬ መሄድ አለብኝ ። ማታ ዝናሽ ቤት እንገናኛለን» ብለው ተለዩት……

ፊታውራሪ ተካ ከአዲሱ ትምህርት ቤት መሰረት ላይ ድንጋይ ጥለው ወደ ቤታቸው እንደተመለሱ ፤ መምሬ መሀሪ ነገሩ ከንክኖአቸው ነበረና «በዚህ ጉዳይ እጅዎን ማስገባት ጥሩ መስሎ አልታየኝም ። ሰውዬው ተማሪዎችን አሳድሞ ፀጥታ አደፍርሷል ተብሎ መወንጀሉን እያውቁ……» ብለው ነገራቸውን ሳይገቱ ፊታውራሪ አቋረጧቸውና «ልጁ ምንም ጥፋት የለበትም ። ልስራ ነው የሚለው ። ስራ ወንጀል አይደለም ። በተንኮል የተወነጀለ መሆኑ ገብቶኛል ። አብዛኛው ሰራሉ ሲል ተንኮል ከመጠንሰስ በቀር ለወገናቸው በቅና መንፈስ የሚያስቡት ጥቂቶች ናቸው ። አቶ ይርጋ የቡና እርሻውን ከማስፋፋት ሌላ ስራ የለውም ። ትምህርት ቤቱ ባለፉት አስር አመቶች ምንም መሻሻል አድርጎ አያውቅም ። የሚያሻሽለው ሲመጣ መደገፍ ይገባል ። ትምህርት ቤቱ የተሰራበትን መሬት የሰጠሁት እኔ ነኝ ። እንዲሻሻል እፈልጋለሁ ። በሱጴ ሌላ ትምህርት ቤት የለም» አሏ

ቸው ። ወዲያውኑ የአልፍኝ አሽከራቸው ገብቶ ውጭ
ብዙ ሰዎች እንደሚጠብቋቸው ነገራቸው ።

ፊታውራሪ ተካ በሀዲስ ያደረባቸውን ስሜት መምሬ
መሀሪ አልወደዱም ። የቅናት መንፈስ መጥቶ በልባቸው
ተሰረፀ ።

«እዚህ በየቀኑ ተሰብስበው የሚመጡብኝ ምን አድ
ርግ ሊሉኝ ነው? ስልጣን የለኝም ውሳኔ ለመስጠት የሚ
ያበቃ ። ዳኛ አይደለሁ ፍርድ አልሰጥ ። ጠበቃ አይደለሁ —
አልሟገትላቸው ። የባላባትነቱ ወግ እንደሆን ድሮ በሰ
ብሰቱ ጊዜ ቀርቷል! እኔም እንደነርሱ አፈር ገፍቼ ነው
የምኖረው ። ሰው መርዳት ቀርቶ የራሴንም ኑሮ ማሸነፍ
እያቃተኝ ሄዷል ። ምን እንዳደርግላቸው ኖሯል! በል
አንድ ባንድ አስገባቸው ወንድሜ! መምሩ ይቅርታ ያድ
ርጉልኝ» አሉ ። መምሬ መሀሪ የቀረበላቸውን ጠጅ ባንድ
ትንፋሽ ጨልጠው ወጡ ።

እድሜ በጣም የተማናቸው ሽማግሌ ገብተው እጅ
ነሱ ።

«ምንድን ነው ጉዳይህ ወዳጄ! አባዋሪ አይደለህም
እንዴ! ምንነው በደህና? ደህና ብትሆንማ አትጠይቀኝም
ነበር ። ሳላይህ ብዙ ጊዜ ሆኗል ። እሺ በል ተናገር »አሉት ።

«አባ ብያ — እግዜርንም ቢሆን ሲጨንቀን ነው
የምናስታውሰው ። ሳይጨንቀው ማን ቀና ብሎ ሰማዩን
ይመለከታል? ተቸግሬ ነው የመጣሁት ። ከአልቄ ወንዝ
ዳር ያለችኝን የቡና መሬት አንዳንድ ሰዎች ካልሸጥክ
ልን እያሉ ያስፈራሩኛል ። ጪትና ማታ ። ዘንድሮ የቡና
ምርት የለኝም ። ባገር የመጣው ትል በልቶታል ። እድሜ



ያላደለኝ ሰው ነኝ ። ልጄ ከብልሎ ከሄደ ዘመን የለውም ።
የፈረንጅ ፊደል ቆጠረና ስራ አላጣም ብሎ ወደአዲስ
አበባ ወጣ ። በህይወት ይኑር አይኑር አላውቅም ። የደ
ረሰች ልጄ ፤ በእርሷ እንኳ አማች እንዳላፈራ ፤ ዘመድ
እንዳላበጅ ፤ በቅርቡ ኮበለለች የወንድሟን ዱካ ተከትላ ።
የት እንደደረሰች አላውቅም ። በስተርጅና ያለጧሪ ቀረሁ ።
እንደኢዮብ በትእግስት ኖርኩ ። የትም ሄጄ ሰርቼ እና
ራሴሁ የሚሉት ፈሊጥ ከመጣ ወዲህ እንደኔ ያለጧሪና
ያለቀባሪ የቀሩትን የወላድ መካኖች ቤቱ ይቁጠራቸው ።
አሁን ደግሞ ያለችኝን የቡና መሬት በወስኑልኝ ዋጋ ልቀማ
ነው ። አሁን የመጣሁት መሬቱን ለእርስዎ አውርሼ እኔ
እድሜዬ እስከፈቀደ ድረስ ከኖርኩበት በሁዋላ......»

ፊታውራሪ አቋረጡትና «የምትለው ነገር ገብቶ
ኛል ። አሳብህ ጥሩ ነው ። ውርሱ በውል መፅናት የለበ
ትም ። መሬቱ ለልጆችህ አንድ ቀን ሊያገለግል ይችላል ።
የኮበለሉት አንድ ቀን መመለሳቸው አይቀርም ። እስከ
ዚያ ድረስ ግን መሬቱን ሽጥልን ለሚሉት አውርሻለሁ
ብለህ መልስላቸው ። ችግር ከገጠመህ ደጃፌ ክፍት ነው ።
ብቻ እግዜርንና ወዳጅን ማስታወስ ችግር በገጠመ ጊዜ
ብቻ አይደለም» ብለው ሸኙት ። ሽማግሌው እጅ ነስ
ተው ፤ መሬት ስመው ፤ እድሜ ለምነው እየመረቁ ሲወጡ ፤
ሌላ ሰው ተተካ ። በመካከለኛ እድሜ ያለ የተጐሳቆለ
ሰው ነው ።

«አንተስ ወዳጄ ምን እግር ጣለህ? በጣም ያዘንክ
ትመስላለህ ። ጉዳይህ ምንድን ነው?» አሉና ጠየቁት ።
የመጣበትን ጉዳይ እንደማስረዳት እንባውን አስቀድሞ
ይዘራው ጀመር ።

«ኢዲያ — እኔ የሚያለቅስ ወንድ አልወድም ። ወኔ የሌለው ነው የሚመስለኝ ። ልቅሶውን ለሚስትህ ተወውና የመጣህበትን ጉዳይ ንገረኝ »አሉት ተቆጥተው ።

«አባ ብያ» አለ ሲቃውን ውጦ — «እንዴት ያይኔ ማረፊያ ልጅ አለችኝ ። የወረዳው ፀሀፊ በግድ ይዞ ካበላሻት በሁዋላ እምጥቶ ደጄ ጣለልኝ ። እንዳልከሰው የፋይል መክፈቻ ገንዘብ የለኝም ። እንዳልቋቋመው አቅም የለኝም ። ያልነደደ እንጨት ይጨሳል ። መውጫ ያጣ ወንድም እንዲሁ ማልቀሱ ስለማይቀር ነው የማለቅሰው......»

እንደገና አቋረጡትና «ታዲያ እኔ ዳኛ አይደለሁ — ፍርድ አልሰጥህ — ምን አድርግ ነው የምትለኝ» አሉት ።

«አባ ብያ — እርስዎም ሴት ልጅ አለዎት......»

«በል ሂድልኝ ወዳጄ! ሂድልኝ ነው የምልህ!» አሉት ተናድደው ። አይናቻቸው ቀልተው እሳት የሚተፉ መሰሉ ። እጅ ነስቶ እንባውን እየዘራ ወጣ ። ሌላው ባለጉዳይ በእግሩ ተተካ ። ፊታውራሪ ተካ በጣም ተክዘው ስለነበረ ገብቶ እጅ ሲነሳ ቀና ብለው አላዩትም ። አደግድጎ ዝም ብሎ ቆመ ። ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ነበር ሌላ ባለጉዳይ መኖሩን የተከገነዘቡት ።

በጉረና ድምፅ «ምን ነበር!» አሉት ።

የሚያርሰውን አፈር የመሰለ ጨርቅ ያገለደመ በእድሜው ጠና ያለው ገበሬ የፊታውራሪን ሁኔታ በማየቱ ተደናግጦ ፤ የሚናገረው ነገር ጠፍቶት በዝምታ ተውጦ ቀረ ። ፊታውራሪ ውጦአቸው ከነበረው አሳብ ዋኝተው ወጥተው «ተናገር እንጂ !» አሉት ።



«የመጣሁበት ጉዳይ — አባ ብያ — እምን ። ነገሩ — እኔና ቤተሰቦቼ በክረምቱ ወራት የምንበላው እጥተን በአራጣ ገንዘብ ተበድሬ ነበር ። እንደሚያውቁት እምና ድርቅ ነበር ። ያንን ገንዘብ ለመክፈል ቡናዬ ሳያፈራ እን ዳለ ሸጥኩት ። እኔም ባዶ እጄን ቀረሁ ። ከብቶቼን ሽጩ እንዳልከፍል ድንገተኛ በሽታ ጨረሳቸው ። አሁን ደሞ ግብር ተጠየቅሁ ። መሬቴን ከመሸጥ ሌላ ምርጫ የለኝም ። የሰባት ልጆች አባት ነኝ ። መሬቱን ከሸጥን የምንደርስበት የለንም ። አሁን ደግሞ እንደገና ድርቅ ሆነ ። የበልግ ዝናብ ይሄውና ጊዜው ሲያልፍ ነው ። ለዘር ያቆየነውን ወደ መብላቱ ላይ ነን ። የዘራነውንም አፈር በልቶት ቀረ ። የምደርስበት ባጣ ነው ወደ እርስዎ የመጣሁት......»

«አንተስ መሬት አለህ ። ለሌላቸው ይብላኝ እንጂ ። ለግብር ስንት ነው የተጠየከው?»

«ስማንያ ሶስት ብር የትምህርትም የጤናም ታክስ ታስቦ......»

«ትምህርትም ጤናም የለም ። ሁለቱም የሚገኙት በታላላቅ ከተሞች ነው ። ግብሩ ግን የሚከፈለው ከዚህ ነው ። እሙቱን ሙሉ ለፍተህ ግብር መክፈል አልቻልክም ማለት ነውን?»

«ድርቅ ሆኖ ነው ። ዝናብ አልነበረም ። ቡናውም ፍሬ አልሰጠም ። ትል በላው ። እግዜሩንም ብንማለደው አልሰማንም ። እግዜር ልመናችንን መስማት ካቆመ ቆይ ቷል ። የድሮ እግዜር አይደለም ። የሰራነውን ሀጢአት

አላውቅም ። የመጣውን መአት እንዲያሳልፍልን ለእግዜሩ እግዚኦ አልን— እግዜሩ ሳይሰማን ቀረ ። አባ ጨፌም ቤት ተሰብስበን ለብዙ ቀናት እየተለማመንን ወዳጄ አደርን ። ብዙ ጥቁር በጐችና ገብስማ ዶሮዎችም ታረዱ ። ግን ደመናው እየሸሸን ሄደ ። የቡና ትሉም — ውርጩም ከፋ ። ከብቶቻችንም በበሽታ አለቁ ። አባ መርጋ ዱሮ ዝናብ ማምጣት ይችል ነበር ። ዘንድሮና አምና አልሆንለትም ። እግዜሩ አልሰማንም ። መከራ ብዙ ያሳስባልና ደመናው እየሸሸ መሄዱን የተመለከቱ ሰዎች ፤ እግዜሩ ጆሮውን የነፈገን ድሮ ነጭ ኮርማ አርደን በምንለምነው ቦታ ላይ አዲሱ ትምህርት ቤት በመሰራቱ ተቆጥቶ ይሆናል የሚል አሳብ እየተሰራጨ ሄዷል ። እናፍርሰው የሚሉም አሉ ። እርስዎ ከመሰረቱ ላይ ድንጋይ ባይጥሉ ኖሮ እስካሁን ሳያፈርሱት አይቀሩም ነበር......»

«እግዜርን መለመን ጭንቅ በመጣ ቁጥር ብቻ አይደለም ። እግዜር ለሰጠን ሀይወት የዘወትር ምስጋና ያስፈልገዋል ይል ነበር መክብብ ነፍሱን ይማረውና ። ሀይወት የእርሱ ናት እንጂ የእኛ አይደለችም ። ያንተ ችግር ባንተ ብቻ የተወሰነ አይደለም ። ብዙ ገበሬዎች በየቀኑ የሚያሰሙኝ እሮሮ ነው ። ለዚህ ችግር መፍትሄው — ምንድነው የሚሉት ወዳጄ — አምን — የገበሬዎች ማህበር አባል መሆን ነው ። እኔ የሰንቱን ግብር ከፍዬ እችላለሁ? ትምህርት ቤቱን ግን ባትነኩት ይሻላል...»

«አባ ብያ — የቡና አምራች ገበሬዎች ማህበር አባል ሆኜ ነበር ። ገንዘብ አዋጡ ብለው ተለቅቼም ቢሆን ስከፍል ቆየሁ ። የማህበሩ አላፊ የምናደርገው ሰው ገንዘቡን ይዞ ይጠፋል ። ለገባ ወንዝ ድልድይ ከዚህ ቀደም ሶስት ጊዜ ገንዘብ አዋጡ ተብለን አዋጥተናል ። ከእግዜሩ የምንታረቅበት መንገድ አጣን እንጂ ፤ እግዜሩ ነው የተጣላን......»

«ደግ ነው ። የተጠየከውን ግብር እከፍልልሀለሁ ። ግን በምን ትከፍለኛለህ?»

«በገንዘብም በጉልበትም እንዳሉት ። ብቻ የዘንድሮን ያውጡኝ ። ልጆቼን የማገባበት የለኝም»

«ምን ስራ ትችላለህ?»

«ሱቂ ስራ የለም እንጂ የአናጢነት ስራ እሞክራለሁ ። የተፈጥሮ ስጦታዬ ነው»

«በል — ከነገ ጀምረህ አዲስ ከሚሰራው ትምህርት ቤት ሄደህ በአናጢነት እንድትረዳ — በትርፍ ጊዜህ ። የምከፍልልህ ገንዘብ በዚያው ይታሰባል ። አዲሱ ትምህርት ቤት ተሰርቶ ሲያልቅ ልጆችህም የእድል በር ይከፈትላቸው ይሆናል ።»

«ከሰባቱ ልጆቼ አምስቱ ለትምህርት የደረሱ ናቸው ። በቂ ክፍል የለም ስለተባልኩ የሰው ከብቶች ሲጠብቁ ነው የሚውሉት ። ትምህርት ቢያገኙ በማን እድሌ ። ከተማሩልኝ እኔንም ከዚህ የኑሮ ሰቃይ አንድ ቀን ያወጡኝ ይሆናል የሚልም ተስፋ አለኝ ። ይህን እንደእዳ አልቆጥረውም ። እድሜን ከጤና ጋር ይስጥልኝ» ብሎ መሬት ስሞ ወጣ ። እፎር የመሰሉ ብዙ ሰዎች በእርሱ እግር ተተኩ ።

ሁሉም ተንጥፈው መሬት ሳሙ ። ከመካከላቸው አንዱ ሽማግሌ ከተነጠፉበት እንደምንም ቀና ብለው እየተንገዳገዱ ወደ ፊታውራሪ ቀረቡ —

«ጉዳያችሁ ምንድን ነው !» አሉ ፊታውራሪ እንደ መበሳጨት ብለው——

«አባ ብያ — በማናውቀው ምክንያት በጭሰኝነት እድሜ ልካችንን ከኖርንበት መሬት ተባረርን - - - - »

«ጊዜ ያመጣው ችግር ነው ። በናንተ አልተጀመረም ። ጊዜ ያድነዋል . . . . »

«እስከዚያ የት ልንደርስ ? ስምና አድራሻ የለን ። ያባቴ ስም ገባር ነበር ። የኛ ስም ተሻሽሎ ጭሰኛ ከተባለ ቆይተናል ። የአያት የቅድመ አያቶቻችን እትብት በተቀበረበት መሬት ገባር — ጭሰኛ ተብለን ከሰብአዊ ፍጡር በታች ሆነን ኖርን ። ሰው የመሆን ጉዳይ ቀርቶ ስሞኑን ደሞ እድሜ ልክ ከኖርንበት መሬት ተባረርን ። የት ልንደርስ ነው — የኢትዮጵያ ከርሰ — ምድር ከነህ ይወታችን ካልዋጠን በቀር . . . .»

«ፍትህ እንጂ ምሬት አያዋጣም ። ትእግስት መሳሪያቸሁ ይሁን ። ንተራዬ ባዶ እስከሆነ ድረስ አትራቡም ። ትስፋችሁን አታጣልሙት ። ደህና ቀን ይመጣ ይሆናል» ሲሏቸው ሁሉም እንደገና መሬት ስመው ሊወጡ ሲሉ ሽማግሌው ከደረት ኪሳቸው ውስጥ ቱባ ቱባ ብር አውጥተው ለፊታውራሪ ሰጡ ።

«ምንድን ነው እሱ !» አሉ ፊታውራሪ እንደመደንገጥም እንደመናደድም እያደረጋቸው ።



«መሳሪያ እንዲገዙልን ነው ። በመዋጮ ነው የሰበሰብነው . . . .»

ፊታውራሪ ተቆጥተው አይናቸው ደም ለበሰ — «ለችግር ቀን ብታስቀምጡት ይሻላል ። ከመሳሪያ ይልቅ ያንድነት ሀይል ይበልጣል ። ዉጡልኝ ! » አሉ ።

ለመግባት የሚጠብቁ ሌሎች ብዙ ባለጉዳዮች ቢኖሩም ፊታውራሪ ምርር ብለው «በቃኝ ፣ በቃኝ ። አቅምም ገንዘብም ፣ ብልሀትም የለኝም — ለሁሉም የሚሆን ። ለዛሬ በቃኝ!» አሉ እየተንገፈገፉ ።

በጎዴት ፣ በጥላቻና በስካር አይኖቻቸው እሳት የሚተፉ የሚመስሉ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ጠብደል ጠብደል የቀን ሰራተኞች ደን የሚመነጥሩበትን ቆንጨራ ፣ ማጭድ ፣ የብረት መንሽና ገሶ ይዘው በአንድ ፊት ተደርድረዋል ። የእልቄ ማርያም ትምህርት ቤት ተማሪዎች በፍርሀት ተውጠው ፣ ከድንጋጤ ብዛት አሸቦ መስለው እንደበግ መንጋ በአንድነት እጅብ ብለው አይኖቻቸውን ያቁለጨልጫሉ ። ወጨፎ ጠብመንጃ ፣ ጦር ፣ አንካሴ ፣ ጭቤና ዱላ የያዙ ወላጆች ከልጆቻቸው በስተሁዋላ እፍጥጠው የቀን ሰራተኞቹ የሚወስዱትን ርምጃ ይጠባበቃሉ ።

በፈረስ የሽምጥ እየጋለቡ ፤ በእግር እየሮጡ ገና የሚመጡ የተማሪዎቹ ወላጆች ፤ ዘመዶችና ወንድሞችም ነበሩ ። ከየማካው ቆንጨራቸውን ይዘው እየተሽሎከሎኩ ብቅ ብቅ የሚሉም ኩሊዎች — አንድ አይኑ የጠፋ — አንድ እጅ የሌለው — ማጭድ እጁን ያረደው — ቆንጨራ እግሩን የቦደሰው — የሾለ እንጨት ደረቱን የወጋው — ቆንጥር ጉኑን የቧጠጠው — በብዛት ነበሩ ።

እያንዳንዷ ደቂቃ ባለፈች ቁጥር ከሁሉም ወገን ያለው ስሜት እየጠነከረ ፤ አየሩ እየከበደ ፤ ጥቂት ኮሽታ የያንዳንዱን ልብ እያስበረገገ ፤ ትንሽ ንቅናቄ ወኔን ከቋፍ እያደረሰ ይሄዳል ። ጅማት እንደደጋን ተወጥራለች ። የልብ ትርታ ጨምራለች ። ስጋ ይርበደበዳል ። ጥርስ ይንቃጨጫል ። ሆድ እየተሸበረ — እግር እንደመከዳት እያለ — እጅ እየተንቀጠቀጠ — ብብት — እጅ — ጀርባ — ግንባር — የጆሮ ግንድ በላብ እየተጠመቀ — ከሁን አሁን ምድር ቀውጢ ሆነች — በደም ታጠበች — አንጀት ተዘርግፎ — አንገት ተበጥሶ ወደቀ ሲባል የመቶ አለቃ አሽኔ ጠብመንጃ ከያዙ ከአራት ፖሊሶች ጋር ከቦታው ገስግሶ ሲደርስ ፤ ከሌላ አግጣጫ ደግሞ ሀዲስና ቶሎሳ ከሌሎች ሶስት ጉረምሶች ጋር ቁና ቁና እየተነፈሱ ከተፍ አሉ ።

ሀዲስ ጊዜ አላጠፋም ። ልጆቹ በቀጥታ ወደትምህርት ቤታቸው እንዲሄዱ አዘዘ ። የያዙትን ጉልቻ ጉልቻ የሚያካክል ድንጋይ እየጣሉ በሶስት በሶስት ረድፍ ገብተው ከመካከል ሲወጡ ሀዲስ ብቻ ከኩሊዎቹ ጋር ተፋጦ ቀረ ። ፖሊሶቹ ጠብመንጃዎቻቸውን ደግነው ቦታ ቦታ ይዘው ቆመዋል ። የመቶ አለቃ ኮልት ሽጉጡን ከማህደሩ አላወ



ጣም ። በወላጆችና በኩሊዎች መካከል እንደአንበሳ ወዲህና ወዲያ ይንጎራደዳል ፤ አንዳንድ ጊዜ ሀዲስን በአይኑ ቂጥ እየተመለከተ — አፍንጫውን እንደወናፍ እየነፋ — ጥርሱን እየነከሰ—ከየጠቅላይ ግዛቱ የመጡት ኩሊዎች ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድነት ለአንድ አላማ ተሰልፈው በማየቱ እየተገረመ ። የሰለቸው የእነርሱ እርስ በእርስ ጥልና ፍጅት ነበር — በየአመቱ ።

ሀዲስ ድምፁን እንደዮሀንስ መጥምቁ ከፍ አድርጎ «ጥፋተኛው እኔ ነኝ ። ተማሮቹን ይቅር በሏቸው ። አላማቸው የናንተን የወገኖቻቸውን እንጀራ ለመጣረት አይደለም ። ቆንጥር እየቧጠጣቸው ፤ እሾህ እየወጋቸው ፤ እባብ እየነደፋቸው በትንሽ ዋጋ የሚሰሩት ለትርፍ አይደለም......»

ጅል! አለ የመቶ አለቃ በልቡ ። ከየትም ተጠራቅመው በጎሳ በጎሳቸው በቡድን በቡድን ሆነው በአመት አንድ ጊዜ እንደመስቀል ወፍ ለቡና ለቀማ ብቅ ለሚሉት ኩሊዎች ፤ ተማሪዎች ለትርፍ አይደለም የሚሰሩት እያሉ መለፈፍ ጅልነት ነው ብሎ አሰበ ። ግን እነርሱም ከጅል ምን ይሻላሉ — አገር አቋርጠው መጥተው ፤ ቀን ከሌት እየሰሩ ከርመው አንዲት ቅርስ ሳይቋጥሩ — ውስኪ — ጠጅ በየቡናው ዛፍ ስር ተኝተው ሲጠጡ — በየቡናው ዛፍ ስር ግብረ ስጋ ሲፈፅሙ — ገንቦ ጠጅ — ጠርሙስ ውስኪ — በየቡናው ዛፍ ስር ሲጋደሉ — ሀይለኛው የጎሳ ቡድን የደካማውን ስራ ሲሻማ—ሲማረት—የደም ጉማ — ባዶ እጃቸውን አጨብጭበው ወደየመጡበት ይመለሳሉ ። ድራሻቸውን ጠላ ። ሀዲስንም ጠላ ።

ሁለት ወፍራም የቡና ነጋዴዎች መጥተው አሳቡን እንዲያቋርጥ አደረጉት ። እነርሱንም ጠላ ።

ሀዲስ ይቀጥላል — «ልጆቼ እንደናንተው ላባቸውን አንጠፍጥፈው በቡና ለቀማ ስራ በሚያገኙት ትንሽ ገንዘብ ተማሪ ቤታቸውን ለማስፋፋትና ለወንድሞቻቸው የመማር እድል ለመስጠት ነው ። የናንተን እንጀራ ለመማረት ፤ እናንተ የምታገኙት ገቢ ዝቅ እንዲል ለማድረግ አይደለም ። ምናልባት አንዳንድ ሰዎች — አንዳንድ ተንኮለኞች ፤ ተማሮቼ ታጥቀው የተነሱት በርካሽ ዋጋ እየተቀጠሩ ስራ ሊያሳጡችሁ ነው ብለው ነግረዋችሁ ይሆናል —»

የመቶ አለቃ አሸኔ አቶ ይርጋ ስለኩሊዎቹ ዝንባሌና በተማሪዎቹ ላይ ስላደረባቸው ብርቱ ጥላቻ አንስተው ያማወቱት ነገር ትዝ አለው ። ወይዘሮ ዝናሽ ቤት አብረው ሲጠጡ አቶ ይርጋ ፊት ላይ ይነበብ የነበረውን የተንጠለጠለ አሳብ አስታወሰ ። ቡና ቤቱ ሳይገቡ በፊት እጅበዋቸው የመጡት የቀን ሰራተኞች ቁጥር ከፊቱ መጥቶ ተደቀነ ።

ሀዲስ ይቀጥላል — «የተማሮቼ ስራ ተንኮል የለበትም ። ላባቸውን አንጠፍጥፈው በሚያገኙት ገንዘብ ትምህርት ቤት ለመስራት ነው ። አባቶቼ — ወንድሞቼ — ይህ ጥፋት መስሎ ከታያችሁ እኔን በያዛችሁት ቆንጨራ ቆራርጣችሁ ከፊታችሁ ጣሉኝ» አላቸው ። የገዛ ድምፁ ተመልሶ ከጆሮዎቹ ውስጥ አስተጋባ ። እንደዮሀንስ መጥምቁ በምድረ በዳ ብቻውን ያለሰሚ የሚጮህ መሰለው ። ለህይወቱ ግን እንዳችም ፍርሀት አላደረበትም ። ለሞቱ ቆርጦ ነበር ።



ደም ጉርሰው ፤ ደም ለብሰው ደም ለመፋሰስ አሰፍስፈው ቆመው የነበሩት ኩሊዎች እርስ በእርሳቸው ተያይተው ሲያበቁ አስቀድመው የተነጋገሩበት ይመስል በአንድነት በእፍረት አንገታቸውን ወደመሬት ደፍተው አቀረቀሩ ። ተወጥሮ የነበረው የሰውነት ጡንቻ እየላላ ፤ ግሎ የነበረው የጆሮ ግንድ እየበረደ ፤ በላብ ርሶ የነበረው ጀርባ እየቀዘቀዘ አየሩን ተጭኖት የነበረው የስጋት ጉም እየተገፈፈ ሄደ ።

«ይህን ዳተኛ ሰው አንድ ብትልልን ምናለበት!» አሉ ፤ ከሁለቱ ወፍራም የቡና ነጋዴዎች አንዱ ወደመቶ አለቃ ጠጋ ብለው ፤ የታጠቁት ቀበቶ በቦርጫቸው ተሸፍኖ አይታይም ። ከደረታቸው ቀጠን ብለው ሆዳቸው ጠብደል ደብተራ ሊያነሳው የማይችል ከበሮ ያክላል ። ወደሀዲስ እየተመለከቱ ፤ ቀጠሉና — «በመጣው ትል ምክንያት እንደምታየው ዘንድሮ ቡና የለም ። የቀረችውን አንዳንድ ፍሬ በጊዜ ካላስለቀምን እሷም ትረግፍና ባዶ እጃችንን መቅረታችን ነው ። በቡና ለቀማ ሰአት ኩሊዎች ጌቶቻችን ናቸው ። ተማልደን ፤ ተማጥነን አባብለን ካልያዝናቸው አፍንጫችሁን ላሱ ብለው ነው ዞር የሚሉት ። ይህን እብድ ሰው ካልያዝክልን ሁዋላ አይሆንም» አሉት ። በሱጼ የታወቁ ሀብታም ናቸው ። በንፉግንትም የሚስተካከላቸው የለም ።

የአቶ ይርጋ ተንኮል ከፊቱ መጥቶ እንደገና ተደቀነበት ። ፊታውራሪ ተካ በትምህርት ቤቱ ስራ ያላቸው አግባብ ታወሰው ። ፀጥታ በማስከበር ረገድ ያለበትንም አላፊነት አመዛዘነ ። እንደጲላጦስ እጆቹን በአደባባይ ታጥቦ ምንም ሀጢአት አላየሁበትም ለማለት ግን አልቻለም ።

ሽበታቸው እንደብር የሚያብለጨልጭ አዛውንት ነጠላቸውን አደግድገው ከፊቱ ቀርበው በታላቅ ምገስ እጅ ነሱትና «እግዜር ያሳይዎ ። ልጆቻችንን ወደተማሪ ቤት የምንልከው እንዲማሩልን ነው ። ቡና እንዲለቅሙ አይደለም ። እርስዎ ባይደርሱ ይህች የቆምንባት መሬት እስካሁን በደም ታጥባ ነበር ። ከዚች ከመከራ ጀምበር ለሰወረን አምላክ ምስጋና ይገባዋል ። ዘንድሮ መአት መጥቶብናል ። ይህን ጥፋት ሁሉ ሊያደርስ የነበረው ሰው በነፃ ሊሄድ አይገባውም» አሉና ወደሀዲስ ተመለከቱ ። የመቶ አለቃ አሸኔ ሀዲስን ለመያዝ ወስኖ ፖሊሶቹን ለማዘዝ ሲቃጣው ፤ አንዱ ኩሊ እንዳቀረቀረ መጥቶ ከሀዲስ እግር ስር አምስት ብር ጥሎ ተመለሰ ። የመቶ አለቃ አሸኔ አይኖቹን ለማመን አቃተው ። የኩሊውን አርአያ የተከተሉ ሌሎች ኩሊዎች አንድ በአንድ እየመጡ የተቻላቸውን ያህል ብር ይጥሉ ጀመር……ከደስታው ብዛት የሀዲስ አይኖች ወፍራም እንባ አቀረሩ ። በተራው ህዝብ ላይ ያለው እምነት ታድሶ በልቡ ውስጥ እንደጧፍ ሲነድ ይሰማው ነበር ።

የመቶ አለቃ ፤ የኩሊዎቹ ልግስና አስገርሞት ይሁን ፤ ወይም ከማን አንሼ የሚል መንፈስ ገፋፍቶት ይሁን ሳይታወቀው እጁ ከኪሱ የመዘዘውን አዲስ የአስር ብር ኖት አውጥቶ ከሀዲስ እግር ስር ጣለ ። ወፍራሙ ነጋዴ አይናቸውን ለማመን አልቻሉም ። የሁሉም አይን ስላረፈባቸው ብቻ እየተርበተበቱ እጃቸውን ወደኪሳቸው ሰድደው የመዘዙት ገንዘብ የመቶ ብር ኖት በመሆኑ ከሙቅዕበት መለሱት ። ለሁለተኛ ጊዜ የመዘዙት ገንዘብ የአስር ብር ኖት ነበር ። የአስር ብሩንም ኖት ደንግጠው መለሱት ። በሶስተኛው ጊዜ እንደበፊቱ አልቻኮሉም ። ከግንባራቸው ላይ ላብ ተንቻርፍፎ ይታያል ። ከኪሳቸው ውስጥ ያለው እጃቸው በዳበሳ የብሩን አይነት ለመለየት እንደሚሞክር ያስታውቅ ነበር ። አንድ ብር ስትወጣ ፈገግ ብለው ሀዲስን በጥላቻ አይን እየተመለከቱ ከእግሩ ስር ጣሏት ።



የመቶ አለቃ አሳብና ልብ እንደተንጠለጠለ ቀረ ።

ፊታውራሪ አያና ዋቅጅራ ከፊታውራሪ ተካ ቦሮ በአራት አመት ያህል በእድሜ የሚበልጡ ቢሆኑም ፤ ከልጅነት ጀምረው አንድ ቦታ ተቀምጠው ከቤት መዋል አይወዱም ። ያሁኑን እየደርገውና ፤ በቀድሞም ዘመን ቢሆን ፤ በባላባትነት ስልጣን የሚያስተዳድሩትን የኖዳን ህዝብ አቤቱታ የሚቀበሉትና ፍርድ የሚሰጡት ካንዱ ቦታ ወደሌላ ስፍራ እየተጓዙ ስለነበረ ቋሚ ችሎትም አልነበራቸውም ።

ከቤት እንደገቡ «ዳኛቸው የት አለ?» ብለው አንዱን ነባር አሽከራቸውን ጠየቁ ። አሽከሩ አቀርቅሮ መልስ ሳይሰጥ ዝም ስላለ ፤ ቀጥለውም «የለም እንዴ?» አሉት ።

«መኖሩንስ አሉ ፤ ብቻ በጊዜ ገብተው ተኝተዋል» አላቸው ።

«እንደልማዱ ሰክሮ! እኔ መቼ አጣሁትና! ይህ ጋን ገልባጭ ውላጅ! ምናባቱ ባደርገው ሰው እንደሚሆን እንጃ» ብለው ጥቂት እንደተንጐራደዱ ፤ ያው ፤ እድሜው የገፋ ጥቁር አጭር አሽከራቸው መጥቶ ፤ ወኪሎቻቸው እንደሚፈልጓቸው ነገራቸው ።

«አስገባቸው!» አሉ በችኮላ ። ሰዎቹ ገብተው ገና ሳይቀመጡ ፤ «እንኳን መጣችሁ ። ልጄ ወሮበልነቱንና መጠጡን እንዲተው ምከሩልኝ ብዬ ብለምናችሁ ዝም በማለታችሁ አዝኛለሁ» አሏቸው ።

ከሁለቱ አንደኛው ፤ አጭር ፤ ጥቁር ፤ ራሰ መላጣው ወኪል እያዘኑ «መክረናል'ኮ ፊታውራሪ ። ምክሩ አባሰበት እንጂ አልጠቀመው ። እግዜር ይመልሰው እንጅ ሰው ሰዉን በምክር አይመልሰውም» አሉ ፤ የተሰፋ መቁረጥ ስሜት በተሞላነው ድምፅ ። ሰውዬው ከፊታውራሪ ጋር ባንድ ማእድ በልተው ያደጉ ከመሆናቸውም በላይ የፊታውራሪ ርስት ጠባቂና ወኪል ናቸው ። አንዳንድ ሰዎች የፊታውራሪ አባት የቤት ውልድ ናቸው እያሉ ይንሾካሾኩባቸዋል ።

«ተቀመጡ በእግዜር ። ራሴ ቁጭ ማለትን ስለማል ወድ ተቀመጡ ማለት ይረሳኛል» አሏቸውና ፤ እርሳቸውም ቀይ ምንጣፍ ጣል ካለበት የድንክ አልጋቸው ላይ ሄደው ተቀመጡ ። ረጋ ብለው አይቀመጡም ። ይቁነጠነጣሉ ።

«ታዲያ ይህን ሰው ምን አድርገው ትሉኛላችሁ ? ምን ጉድ እንደመጣብኝ አላውቅም እንጂ በዘሬ እንኳ ሰካራም የለም» አሉ ፤ በሀዘን አንገታቸውን ወደ መሬት ደፍተው ።



ዳኛቸው ከአባቱ ይልቅ ፤ ከወኪሎቹ ጋር የቅርብ ግንኙነት ያደርጋል ። በየእለቱ ከሁለቱ አንዳቸውን ገንዘብ ሳይጠይቅ አይውልም ። እንዳይከለክሉት ይፈሩታል ። ዝም ብለው የጠየቀውን እንዳይሰጡት ፊታውራሪ በበኩላቸው ይቆጣሉ ። ልጄን የምታበላሹት'ኮ እናንተው ናችሁ እያሉ ይወቅሷቸዋል — በየጊዜው ። ይሁን እንጂ ፤ ዳኛቸው በጠየቃቸው ቁጥር ሁለቱም ገንዘብ ሲከለክሉት የማይችሉበት ልዩ ምክንያት አላቸው ። ፊታውራሪ አላባቸው ባይሞትም በርጅና ምክንያት ተዳክመዋል ። ዳኛቸውን ካሁኑ ካስቀየሙት ፤ ፊታውራሪ የሞቱ እለት ምናልባት አሁን የሚተዳደሩበትን ውክልና በውድም ሆነ በግድ ይነፍገናል የሚል ፍራቻ አድሮባቸዋል ። ስለዚህ ነው ዳኛቸው ገንዘብ በጠየቃቸው ቁጥር የማይከለክሉት ።

«እርስዎ ቀድመው አነሱት እንጂ እኛም የመጣነው ለዚሁ ነበር ። በየእለቱ ገንዘብ አምጡ እያለ አስቸግሮናል ። የተወሰነ ገንዘብ ካልፈቀዱለት እኛ ብንከለክለው ካንዱ ሄዶ መበደሩ አይቀርም ። ይህ ደሞ ለርሶም ቢሆን ውርደት ነው ። ውርደትን እንደማይወዱ እናውቃለን ። ሆኖም አይዘኑ ፊታውራሪ» አሉ ነጭ የእስላም ኮፊያ ያደረጉት ወፍራም ሰው — «ትዳር ይመልሰው ይሆናል ። ከትዳር የበለጠ መካሪ የለም። »

«ያድርገዋ!» ካሉ በሁዋላ ቀጥለውም «ፊታውራሪ ተካ የድግሱን ነገር በሰፊው ይዞታል አሉ ። አላማው መቼም እኔን ለማስናቅ ነው ። እኔ እያና ግን እንኳን ደግሼ ፤ በሌላውም ቀን ቢሆን በቤቴ ሰርግና መልስ ነው ። እንደሱ

ካሁኑ ባንጀምረውም እንደርሳለን ። ምን ጠፍቶ ። ያኔ የማ ድግስ እንደሚበልጥ ይታያል» አሉ በትምክህት ።

ፊታውራሪ ኢያና ፤ አስቀድመው መዘጋጀት አይሁንላቸው እንጂ ፤ እንኳን ሰርግን የሚያህል ነገር ቀርቶ ሊተራውም ግብዣ ቢሆን በትንሹ መደገስ አይወዱም ። ድግስ ይዋጣላቸዋል ። ብቻቸውንም ሲሆኑ እህል አይዋጥላቸውም ። ባለቤታቸው ፤ መኪና ካስደነበራት በቅሎ አፍጥጠ ከቆመ ጉቶ ላይ ወድቀው ከሞቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፤ ዘመድ ወይም ጉረቤት ፤ ይህም ባይሆን ሰው ከመንገድ እየተለመነ መጥቶ ነበር እህል የሚቀምሱት ። ቤታቸው ተጠርቶ የሄደ ሰው ሆዱን ሰፋ ማድረግ አለበት ። እርሳቸው ደስ እስኪላቸው ድረስ ያልበላውን ሰው ዳግመኛ ቤታቸው አያደርሱትም ። ቶሎ ስለሚቀየሙ ከእግዜር ሰላምታም ጭምር ይነፍጉታል ። ማእዴን የናቀ ሰው እኔን እንዴት ሊያከብረኝ ይችላል? የሚሉት ፈሊጥ አላቸው ። እርሳቸው ግን የድስት ጥራጊ ተፈልጐ ካልቀረበላቸው ሌላ ምግብ ከጉሮሮ አይወርድላቸውም ። ከሰው ቤትም ተጋብዘው የድስት ጥራጊ ተፈልጐ ካላቀረቡላቸው አይመገቡም ። ከሁሉም ደግሞ አብሮ አደግ ገረዳቸው ከድስት ጠራርጋ የምትሰጣቸው ምግብ ነው የሚጣፍጣቸው ። አንዳንድ ጠላቶቻቸው ቅም አያታቸው ያወረሷቸው የአሽከርነት ጠባይ ነው ብለው በሹክሹክታ የሚናገሩት ሀሜት ከጆሮአቸው ሲገባ እጅግ ይናደዳሉ ። ከእመሳቸው መላቀቅ ግን አይችሉም ።

ያብሉ ያጠጡ እንጂ ፤ እጃቸው ግን ለገንዘብ አይፈታም ። ባለፈው ዘመን ይጠቀሙበት የነበረውን የባላባትነት ስልጣን ካጡ ወዲህ ፤ በምትኩ ገንዘብ መሰብሰብ ጀመሩ ።

የዛሬን አያድርገውና የፈለጉትን አስረው ፤ ያበኛቸውን ፈትተው ፤ ያስደሰታቸውን ሸልመው ፤ ያስቆጣቸውን ገርፈው ፤ ምኞታቸውን ሀግ አድርገው በኖሩበት በዚያ ደጉ ጊዜ በሚሉት ዘመን የገንዘብን ጥቅም ስለማያውቁ ከመጤፍ አይቆጥሩትም ነበር ። የሚያረካቸውና ህልውናቸውን የሚያረጋግጥላቸው «አቤት! አቤት!» እያለ በመጮህ ወደእርሳቸው የሚመጣው የህዝብ ብዛት ብቻ ነበር ። «ከህዝቡ አትገልሉኝ ። አንድ ቀን ቤት የዋልኩ እንደሆነ የሞትኩ ይመስለኛል ። የህዝቡን አቤቱታና ጩኸት ሳልሰማ መዋል አልችልም ። ክብሬ የህዝቡ ትንፋሽ ነው» ይሉ ነበር ። በዚህ የተነሳ ነበር ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ የህዝቡን አቤቱታ ለመስማት የሚመርጡት ። የባላባትነት ስልጣናቸውን ጊዜ ሽሮት ካረከሰው ወዲህ ግን በህዝቡ ትንፋሽ ፈንታ የገንዘብ ክምችት የክብራቸው መሰረትና ምሰሶ እየሆነ ይታያቸው ጀመር ። የገንዘብ ሀይል የበለጠ ስልጣንና ክብር ያስገኛል ብለው ማመን ስለጀመሩ ፤ ገንዘብ አውጥተው የሰጡ እንደሆነ ስልጣናቸውን ያካፈሉ ይመስላቸዋል ። ከእግዜር በታች ሌላው ትልቅ ሀይል ገንዘብ ነው ። ገንዘብ አፍ አለው — ይናገራል ። ገንዘብ ጆሮ አለው — ይሰማል ። ስልጣኑ አይበገርም ። ቃሉ ከመሬት አይወድቅም ማለትን ያዘወትራሉ ። ይህም በመሆኑ ካንዱ ልጃቸው ይልቅ ፤ ገንዘብን በሚመለከት ነገር ባእዳንን መወከል ይመርጣሉ ። ልጃቸውን ይጠላሉ ማለት አይደለም ። እንደአይን ብሌናቸው ይወዱታል ። ስራ ለሌለው ፤ በቅ

ምጥል ላደገው ላንዱ ልጃቸው ለምን ስራ እንደማይሰጡት በተጠየቁ ቁጥር ፤ «ባእድ ይከሰላል ። የራስ ስጋ ምን ይደረጋል? ለየትኛው እድሜ ብላችሁ ነው? ከእንግዲህ እኔ የቀረኝ ቀጠሮ ከሞት ጋር ብቻ ነው ። ለሀብቱ እንደሆነ ከሞትኩ በሁዋላ ይደርስበታል» በማለት ምርር ብለው ይመልሳሉ ። የባለኮፊያውን ሰው አሳብ ወደጉን ለማድረግ ነበር ፤ መልስ ሳይሰጡ ወደድግስ ጉዳይ ያመሩት ። ግን ፤ እንደዱባ የተድበለበሉት ሰው በዙሪያ መንገድ ላቀረቡት አሳብ መልስ ባለማግኘታቸው ፤ «የተወሰነ ገንዘብ በወር ቢቆረጥለት ምናለ ታዲያ?» ብለው እንደገና ጠየቁ ።

ራስ መላጣውም ቀጠሉና ፤ «እንግዲህ ጉጃ ሊወጣ ሁለት ወር ቀርቶታል ። ካሁኑ በገቢው ራሱን ማስተዳደር መቻል አለበት ። የተወሰነ ገንዘብ ቢቆረጥለት እኛንም በየቀኑ እየመጣ አያስቸግረንም» አሉ ። ወዲያውኑ ዳኛቸው ጉምለል እያለ ገባ ። ለጊዜው እልፍኙን ዝምታ ዋጠው ።

ዳኛቸው ከአባቱ በቁመት ትንሽ ከፍ ይበል እንጂ ረጂም አይባልም ። ፊቱ እንዳባቱ የረቀቀ ባይሆንም ፤ አፍንጫውና አይኖቹ ጉልተው ስለሚታዩ የወንዳወንድ መልክ ይሰጡታል ። የእናቱን ጠይምነት ሳይሆን ያባቱን ቅላት ነበር የወረሰው ። ፊታውራሪ አጭር ቀጣጣ ናቸው ።

«ስላንተው ነበር የምንነጋገረው» አሉት ፤ ፊታውራሪ ፊታቸውን ወደዳኛቸው መልሰው ። ቀጠሉና «መቼም ብመክርህ ፤ ባስመክርህ አስቸግረሀኛል ። የኔ ሀዘን ደስታ የሚሰጥህ ከሆነ……» ከማለታቸው ፤ ዳኛቸው አቋረጣቸውና ፤ «ምክር ሰልችቶኛል! አንተ ያንተን ክብር እንጂ



የኔን ጉዳት አላየሀልኝም ። ሌላ ቦታ ሰርቼ እንዳልበላ አላስተማርከኝም ። አንተን እንዳላገለግል አታምነኝም ። እኔ ልጅህ እያለሁ ንብረትህንና ሀብትህን የሚያስተዳድሩት ሌሎች ናቸው ። ምን ሆነህ ነው ኑሮ የምትለኝ? አትጠጣ — አትሰከር — ሰሜን — ክብሬን ጠብቅ እያልክ ጧት ማታ የምታሰማው እሮሮ ሰለቸኝ» አላቸው ፤ በቁጣ ፤ ድምፁን ከመጠን በላይ ከፍ አድርጎ ።

ፊታውራሪ አልተናደዱም ። እየተገረሙ «ያለኝ ሀብት ሁሉ ያንተ ነው ። በሀብቴ ለማዘዙ እንደሆነ ትደርስበታለህ ። ለየትኛው እድሜ!» አሉት ።

«ባገራችን አባት ካለ አጊጥ ፀሀይ ካለች ሩጥ ይባላል ። ቆሞ ብለህ የሞቴን ቀን ጠብቅ ነው የምትለኝ? አባት ልጁ እንዴት ሞቴን ተመኘልኝ ይላል? እስካሁን አልተመኘሁም ነበር ። አሳብህ ይህ ከሆነ — ለምን ድብን አትልም ታዲያ!……» ከማለቱ ፊታውራሪ እያና ከተቀመጡበት ድንክ አልጋ ላይ እንደወጣት ተወርውረው ጉሮሮውን ያዙት ። አልተከላከላቸውም ። እድሜ ከንዳቸውን አድክሞታል ። ወኔ ብቻ ነበር የቀራቸው ። ወኪሎቹ በቀላሉ ገላግለው አላቀቋቸው ። ዳኛቸው በንዴት ተንደርድሮ ወጣ ።

ፊታውራሪ እያና የሚጥል በሽታ እንደያዘው ሰው ያረጁት አጥንቶቻቸው እስኪንቋቁ ድረስ በንዴትና በእልክ ተንቀጥቅጠው ሲያበቁ ወደድንክ አልጋቸው ተመልሰው እንገታቸውን ደፍተው በዝምታ ተዋጡ ። ከንዴቱ ይልቅ ለጋብቻው የነበራቸው ጉጉት በአሳባቸው እየጉላና እየበረታ ሄዱ ። አለምክንያት አይደለም ። ፊታውራሪ ተካ ከአይናለም ሌላ ወራሽ እንደሌላቸው

ያውቃሉ ። የጋብቻው መሳካት አባቴና አያቴ ለብዙ ዘመን በህልም ይመኙት የነበረውን የሉጬን ባላባቶች ሀብትና ክብር የመጠቅለል እላማ ያለደም መፋሰስ ከግቡ ያደር ሰዋል ብለው አሰቡ ። ለብዙ ዘመን ሲታለም የቆየ ድል መጥቶ በር በሚያንኳኳበት ሰአት ልጃቸው ያልታሰበ እንቅፋት በመሆን አዘኑ ። ወደውነት ሊለወጥ የተቃረበ ህልም — የብዙ ዘመን — የብዙ ትውልድ ህልም — አይ የዘመኑ ልጅ አሉ በብስጭት ።

ይህን ህልም በመጀመሪያ ያለመው የፊታውራሪ አያና ቅመአያት ነበር ይባላል ። ከፊታውራሪ ተካ በሮ ቅመ አያት ቤት በባለሟልነት በሚያገለግልበት ወቅት ፤ ለርሱ የታጨችው ልጅ ለሌላ ባላባት ልጅ በድንገት በመዳሯ ፤ በንዴት ሸፍቶ የገባን ወንዝ ተሻገረ ። የዚያን ጊዜው የሉጬ ባላባት ህዝቡን እየጨቆነ ንብረቱንና ገንዘቡን ይበ ዘብዘው ነበርና ፤ የገባ ወንዝ ማዶው የኖጳ ህዝብ በጀግ ንነቱና ቆራጥነቱ እየተማረከ በብዛት ይከተለው ጀመር ። የሚመከተው ስለጠፋ ከጊዜ በሁዋላ የኖጳን የባላባትነት ስልጣን ለመያዝ በቃ ። ሆኖም በዚህም ብቻ አልረካም ። ሉጬንም ለመጠቅለል ይመኝ ነበር ። እርሱ ለጊዜው ስላ ልሆነለት ፤ በየቀኑ ልጆቹን እያስጠራ በቁም ነገር «እና ንተ እያላችሁ ምኞቴ አይሞትም ፤ የሉጬን ነገር እንዳ ትረሱ» ይላቸው ነበር ይባላል ። ይህ ማሳሰቢያ ከልጅ ልጅ ሲወርድ ሲዋረድ መጥቶ የተቋረጠው በነፊታውራሪ አያና ዘመን የማእከላዊው መንግስት ስልጣን መስፋፋት ከጀመረ ወዲህ ነበር ። የአባቶቼ ህልም እንደሲጋቸው በመቃብር ውስጥ በስብሶ መቅረት የለበትም ብለው ወሰኑና ወደ ወኪሎቻቸው መለስ ብለው «አባቱ ነፍሳ



ቸውን ይማርና ሲተርቱ ከወዳጅ ጠላት ፤ ከስጋ ብስናት ይሰውረን ይሉ ነበር ። እምን — ሲጋዬ ነውና መቼስ ምናደርገዋለሁ ። በሉ ፤ እያንዳንዳችሁ በወር ሰባ አም ስት ብር እንድትሰጡት ይሁን ። እህሉ ከቤት ይሰፈር ለታል ። ሰርጉ ባይደርስ ኖሮ ይህን እንደማላደርገው ያባ ቶቼ አጥንት ይመሰክራሉ» አሉ ፤ በጐረና ድምፅ ።

ሁለቱም ሰዎች ተያይተው የደስታ ፈገግታ ተሰዋወጡ ።

«በሉ — ከልጂ ጋር አስታርቁኝ ። የራስ ስጋ መቼም ተቆርጦ አይጣልም ። በድዬው እንደሆነ ግን እግዜር ይፍ ረደኝ» አሉ ። ፊታውራሪ አያና ቶሎ ይቆጣሉ ። ደሟ መራራ ነውና አትንኩኝ ባይ ናቸው ። ግን ቁጡው መንፈ ሳቸው በትንሽ ምክንያት ቶሎ ተመልሶ ይበርዳል ። የሚ ጨክን ሆድ ምንነው በሰጠሆኝ ኖሮ እያሉ ብዙ ጊዜ ፈጣ ሪያቸውን ያማርራሉ ።

ወኪሎቹ ወጥተው ጥቂት ቆዩና ዳኛቸውን ይዘው ተመለሱ ። ፊታውራሪ ከተቀመጡበት ተነስተው «ቢል — ልጂ አጥፍቼ እንደሆነ ይቅር ለግዜር በለኝ» አሉት ። ዳኛቸው ፤ እግር ሳመና እንገታቸው ላይ ተጠምጥሞ አለቀሰ ። ፊታውራሪ ጊዜ አላጠፉም ። ወደ ሁለቱ ሰዎች መለስ ብለው ፤ «እንግዲህ የሰርጉን ነገር አደራ» አሏቸው ። ወደዳኛቸው ተመልሰው ፤ «ከዛሬ ጀምሮ በወር መቶ ሀምሳ ብር ተቆርጦልሀል ። ይህ ለጊ ዜው ነው ። ትዳር ከያዝክ በሁዋላ ደግሞ ሌላው ሁሉ ይሆ ናል ። አንተም ባትል እኔም አስቤበታለሁ» አሉት.....
ግን ፊታውራሪ አጥብቀው የሚያስቡት የቅም አያታቸው ህልም ወደውነት የሚለወጥበትን መንገድ ነበር ።

ፊታውራሪ ተካ ከተከታዮቻቸው ጋር መጥተው አንድ ድንጋይ ከቤቱ መሰረት ላይ ከጣሉ ወዲህ ፤ በቤቱ ስራ በኩል ከወሀ በቀር ሀዲስን የገጠመው ሌላ ችግር አልነበረም ። ቶሎሳና ጓደኞቹ ከስራው አይለዩም ። ሀዲስ ክፍል በሚያስተምርበት ጊዜ ሁሉ ሌሎቹን በገፈቃደኞች በማስተባበር ስራውን የሚያካሂዱት እነርሱ ነበሩ ። በተለይ ፤ ከገባ ወንዝ ዳር የሚኖሩት ፤ ሰው የማይቀርባቸው እዶ የሚባሉት ሸክላ ሰሪዎች ፤ ሀዲስ ቤታቸው እየገባ የሚያቀርቡለትን ሲበላና ሲጠጣ በማየታቸው ፤ እምነት ስላሳደሩበት ፤ ከድንጋይ የጠነከረ ከገባ ወንዝ ወርቅማ አሸዋ የተሰራ ልዩ ሸክላ በብዛት ለማቅረብ ስለፈቀዱ የትምህርት ቤቱ ስራ በጭቃ መሆኑ ቀርቶ በሸክላ ተሰርቶ እንዲያልቅ ተወሰነ ።

ተማሪዎቹ ከቤታቸው ምግብ ፤ ጠላ ፤ ጠጅና ገንዘብ እንደተቻላቸው ፤ እንደቤተሰቦቻቸው የኑሮ ሁኔታ በየእለቱ ፤ በየጊዜው ከድርሻቸው በመቆጠብም ሆነ በመስረቅ ስለሚያመጡ ፤ ለቤቱ ስራ የሚያስፈልገው መዋጮ ከሚያስፈልገው በላይ ሆኖ ስለተገኘ ፤ የቤቱ ስራ ፍጥነት ቢጨምርም ፤ ሀዲስ አይናለምን እያሰላሰለ ከመጨነቅ አላረፈም ። ለቤቱ የሚያስፈልገውን ቆርቆሮና መስተዋት



በከፊል ተማሪዎቹ በትርፍ ጊዜአቸው ተቀጥረው ቡና በመልቀም ባመጡት ገንዘብ ቢገዛም ፤ በሱጴ ቦሮ የታወቀው ግሪካዊው የቡና ነጋዴ ፤ ሀዲስ እየተመላለሰ በልመና ስላደከመው ብቻ ፤ ለቤቱ ስራ የጐደለውን ቆርቆሮ ለማሟላት ፈቀደ ። «ኢኔ ጋንዛብ ብዙ አላኝ ይመስላችአል ። ኢኔ ጋንዛብ የላም ። ደሀ ኖ ። አንታ ብቻ አስቸጋሪ ሳው ኖ ። የላም ሲሉ አታውቁም ። እንዲሀ አይናት ሰው ኢኔ አላጋጠመም ። ዛንዲሮ ቡና የላም ። ጋባያ የላም ። ቡና ቲል ጨረሳ ። ቲምርት ዳሞ ሚን ያዳርጋል ። ኢኔ አልታማረም ። ቲንሽ ቲምርት ጊዜ በሁዋላ ማብት ማብት ማላት ብቻ ። ኢኒ ዱሮ ቡና ባአሲር ሳንቲም ቢቻ አስላቂም ነበረ ። ዛሬ ቢር — ናገ ዳሞ ሁለት ቢር ። አይን ታካፈቶ ። ቲንሽ ቲምርት በሁዋላ ቡዙ ማብት — ማብት ማለት ቢቻ» እያለ ነበር ሲያንገራግር ቆርቆሮዎቹን የሰጠው ። ፈረንጅ ታማኝ ነው የሚል ግምት በህዝቡ ዘንድ ስላለና ሁሉም እርሱ ዘንድ ገንዘብ ወስዶ በአደራ ያኖር ስለነበረ ፤ ግሪኩ የተቀበለውን ያደራ ገንዘብ ንግድ ላይ በማዋል ከበረ......ከዳቦና ከዱቄት ንግድ ወደ ግብርና ዞረ ። እንዲሁም በርጩማ በመስራት በሱጴ ቦሮ የታወቀው ጉሳ በበኩሉ ሊጣውላ ፤ ለመዝጊያና ለመስኮት የሚሆነውን የዝግባ እንጨት ጠርቦና ሰንጥቆ የድርሻውን በማበርከቱ ፤ የትምህርት ቤቱ ስራ አልቆ አገልግሎት መስጠት የሚጀመርበትን ቀን በናፍቆት ከመጠበቅ ሌላ የሚያሳስብ ጉዳይ አልነበረም ። ከአይናለም ሌላ......

የአዲሱ ትምህርት ቤት መሰረት ወጥቶ ፤ ወርቅማ በሆነው ሸክላ የተሰሩት ግድግዳዎቹ በየእለቱ እያደጉ ሲሄዱ ፤ የሀዲስ ልብ አብሮአቸው እያደገ ይሄድ ነበር ። ሀዲስ ከቤቱ ስራ ጋር ቀን የሚያሳስብ እህል እንደልብ የማያስበላ — ሌሊት እንቅልፍ የማያስወስድ — የሚያቃዠ — የሚያባንን — ፍቅር ይዞት ነበር ። ጧት ሁል ጊዜ በአስራ አንድ ሰአት ሄዶ ቤቱን እየተዘዋወረ በሚጉበኝበት ሰአት የሚሰማው ደስታ ለብዙ ጊዜ የተለየችውን ፍቅረኛውን እንዳገኘ ሰው ያህል ይሆንበታል ። ከጉብኝቱ በሁዋላ ፤ ከቤቱ ፊት ለፊት ካለው ትልቅ ድንጋይ ላይ ተቀምጦ ቤቱን በፍቅር አይን — አይኖቹ እስኪፈዙ ድረስ መመልከት ይጀምራል ። ወደ አስራ ሁለት ሰአት ላይ የፀሀይ ጮራ ወርቅማዎቹ ሸክላዎች ላይ አርፋ ነጥራ ስትመለስ ፤ ከየቤቱ ማእዘን ላይ የሚታዩት የውርጭ ጠፈጠፎች በጮራዋ አማካይነት ከእንቁ የተሰራ መርገፍ መስለው ሲታዩ ፤ የቤቱ ቅርፅ እየደበዘዘ — እየመነመነ — እየጠፋ ሄዶ በምትኩ ውብ የሆነች ሴት ብቅ ትላለች — ፊገግታዋ የጮራዋን ብርሀን እየተሻማ......እጆቿን ዘርግታ ትጠጋዋለች ። ትንፋሿ እንደጧቱ አየር ህይወቱን ያድሰዋል ። እቅፉዋ እንደጧቱ ጮራ ይዳስሱታል ። ከንፈሮቿ ይሞቁታል ። ሰውነቷ ከሰውነቱ ሲጠጉ — ገላቸው



አንድ ሲሆን......የቶሎሳና የጓደኞቹ መምጣት ብቻ ነበር ከህልሙ የሚቀሰቅሰው......እና የእለቱ ስራ ይጀመራል ።

አንድ ጧት እንደልማዱ በሌሊት ተነስቶ ከትምህርት ቤቱ እንደደረሰ ቶሎሳና አንድ ሌላ ሰው መሳሪያ ይዘው ዘብ ያደሩ መሆናቸውን በማወቁ ፤ «ምን ነው፣ በደህናም ፥ አዲስ ነገር መጣ?» ብሎ ተደናግጦ ጠየቃቸው ።

«ፊታውራሪ አዘውን ነው — ቤቱን እንድንጠብቅ» አለው ቶሎሳ ።

«ከመቸ ወዲህ?»

«ከትናንት ጀምሮ»

«እኮ ለምን?»

«የትምህርት ቤቱ መሰረት የተጣለው የሱዴ ሰዎች ድሮ ድርቅ ወይም በሽታ ባገር በመጣ ቁጥር ነጭ ኮርማ ጥለው እግዜሩን ይለማመኑበት በነበረው ቦታ ላይ ነው ። አሁን እንደምታየው የበልግ ዝናም ጊዜው ሲያልፍ ነው ። እምናም የበልግ ዝናብ አልነበረም ። ህዝቡም እግዜሩን ቢለማመን አልሆነም ። ቡናም በትል ምክንያት ጠፍቷል ። ታዲያ ትምህርት ቤቱ በዚህ ቦታ ላይ በመሰራቱ እግዜር ተቆጥቶ ይሆናል ብለው የሚያምኑ ሰዎች እየበዙ ሄደዋል ። መሰረቱን ለመናድ አድብተው የሚጠብቁ ሰዎች አሉ በለተባለ ፊታውራሪ እዚህ እያደርን እንድንጠብቀው አዘዙን» አለው ፤ እንቅልፍ አጥተው ያደሩትን አይኖቹን እያሸ ።

«እኔ መቸ አወቅሁና ። አስቀድሞ የነገረኝ ሰው የለም ። አሮጌው ትምህርት ቤት ከዚህ ቦታ ላይ ባለመሰራቱ እኔ

ንም ይገርመኝ ነበር ። ከፍታ ያለው ጥሩ ቦታ ነው ። ደስ ይላል ። ታላቅ ቁም — ነገር እንዲሰራበት በገዛ እጁ ተደ ልድሎ የተቀመጠ ቦታ ይመስላል ። እምና ነቄ ኮርማ ታርዶ ነበር ከዚህ ቦታ ላይ?»

«አዎን — የበልግ ዝናብ በመቅረቱ ......»

«ታዲያ ዝናብ መጣ?»

«አልመጣም ። አሁን ነገሩን የሚገፋፉት አንዳንድ ምቀኞች ናቸው — ጠላቶች» አለ ቶሎሳ በቁጭት ።

ቡናው ተለቅሞ ፣ ተፈልፍሎ ፣ ተሸጦ ፣ ተጭኖ ከለቀ በሁዋላ ሱጴ ቦሮ ድርቅ ባይመታትም ለወትሮ እንበጣ እን ደዋለበት ግላ ጭር ትላለች ። የተሸመጠጠው የቡና ዛፍ የተጋጠ እጥንት መስሎ ቆሞ ሲቀር — አቧራው ሲነሳ — ኑሮ ትስክንና ሱጴ ቦሮ ማዛጋት ፣ ማንቀላፋት ትጀምር ነበር ። ድርቁ ደግሞ የባሰ መልክ ሰጥቶአት የሚ ያዛጋ ባዶ መቃብር አስመስሎአታል ።

ከስር መሬቱ እንዶረመጥ ያቃጥላል ። ከላይ የአየሩ ወበቅ እንደእሳት ላንቃ ይጋረፋል ። ሳር ቅጠሉ ደርቋል ። ዛፎቹ ከስል መስለዋል ። ወፎቹ ተሰደዋል ። ጉድናቸው እንድ ሁለት ተብሎ የሚቆጠር በሞትና በሀይወት መካ ከል የሚንገዳገዱ ፣ ጣእረ ሞት የሚመስሉ የቤት እንስ ሳት ፣ መጠለያና መኖ አጥተው በየሚዳው በቁም ያን



ቀላፋሉ ። እረኞቻቸውም እንደነርሱ አጥንታቸው ወጥቶ ፣ ፊታቸው ገርጥቶ ፣ ሆዳቸው እንደከበሮ ተነፍቶ ፣ አይና ቸው ጉድጉዶ ፣ እግሮቻቸው ቀጥኖ — የያዙትን ዘንግ መስለው — እንደሌላው ጊዜ ዋሽንት አይጫወቱም — ከወንዝ ወዲህና ወዲያ ማዶ ሆነው የእረኛ ዘፈን አይቀ ባበሉም ። እንደ ወንዞቹ ደርቀው ፣ እንደከብቶቹ ከስ ተው በዝምታ የተፈጥሮን ልግስና ይጠባበቃሉ — በት እግስት ። በተስፋ የእግዜሩን ምህረትና ቸርነት ይጠባበ ቃሉ - ሌላ የሚደርስላቸው ሀይል አያውቁምና! ጉልበት ያለው ጐረምሳ እንደወፎቹ በጊዜ አገር ለቅቆ ወጥቷል — የእለት ጉርስ ፍለጋ ። አዝማሪዎች መሲንቆዎቻቸውን በባህር እጣን ማሟሸትና መቃኘት ከተው ቆይተዋል ። ዘፈን የለም ። ብር የለም ። ጠጅ የለም ። ከጠላ ቤቱ ደጅ የቆርቆሮ ጣሳ አይታይም ። ከጠጅ ቤቱ ደጅ እምቡላ አይሸትም ። ንቦች አይታዩም ። እነርሱም ከአገር ወጥተ ዋል ። በየዛፉ ላይ የተሰቀሉት የማር ቀፎዎች ጭር ብለ ዋል ። በእድሜ የገፉ ገበሬዎች በየደጃቸው እግርና እጃ ቸውን አጣምረው ከተፈጥሮ ጋር ያሸልባሉ — ያንቀላ ፋሉ — ያዛጋሉ ። የሞት ፍርዱን የሚጠባበቅ እስረኛ ይመስላሉ ። ተፈጥሮ ፊቷን አዙራባቸዋለች ። የእግዜር ቸርነት ብቻ ነበር ተስፋቸው ። ሁሉም ወደሰማይ እን ጋጠው የእግዜሩን ቸርነት ይጠባበቃሉ ። ሀዲስ ብቻ ነበር ፊቱን ወደምድሯ አዙሮ የሚያስበው — ተፈጥሮ የሰው ልጅ ተገዥ እንጂ የበላይ አይደለችም — ሰው ተፈ ጥሮን ድል ማድረግ አለበት — ተፈጥሮ ድል የምትሆን በት መሳሪያ እውቀት ነው — የእውቀት ምንጩ ትም ሀርት ቤት ነው — እጅ — የሰው እጅ — ድል የማይነሳው ምን ነገር አለ? ተፈጥሮ ራሷ ለጠንካራ እጅ

ምስጢሯን ትገልጣለች ። ተፈጥሮ የሰውን ልጅ እንድ ታገለግል እንጂ እንድትገዛው አልነበረም የተፈጠረችው — ግን ምስጢሩዋን ለማወቅ የሰው ልጅ ጥበብ ያስፈልገዋል ። ምስጢሩዋን እንደነፈገችው ነው ። ተፈጥሮ የእግዜርን ቦታ በመውሰድ በሰው ዘንድ ልትመለክ ትፈልጋለች ። ተመልካለችም — ግዙፍነትዋ — ምስጢሩዋ — በሰው ልጅ ላይ ያላት ሀይል ። ተፈጥሮ የምትመከው በሰው ልጅ ድንቁርና ነው — ከድንቁርና ሌላ መሳሪያ የላትም ። ሀዲስ የተፈጥሮን ንፉግነትና ዋላዋይነት ድል ለማድረግ አስቀድሞ በወሰደው ርምጃ መሰረት ባስቆፈራቸው ሶስት የወሀ ጉድጓዶች ብዙ ሰዎች ሲጠቀሙ በማየቱ ቢደሰትም ፣ ብዙ የወሀ ጉድጓዶች በየቦታው ቢቆፈሩ ፣ የእልቁ ወንዝ ቢገደብ — የገባ ወንዝ ለኤሌክትሪክ ሀይል መስጫ እንዲውል ቢደረግ ፣ ተፈጥሮን በመግራት የሰው ልጅ ባርያ ለማድረግ የሚቻል መሆኑን ቢያጤንም ፣ ተፈጥሮን ድል ለመንሳት የመጀመሪያ ርምጃ ትምህርት ቤቶችን ማስፋፋት አስፈላጊ እንደሆነ በበለጠ ተገንዘበ ። አዲሱ ትምህርት ቤት ሊሰጥ የሚችለው ጥቅም በይበልጥ በአእምሮው ውስጥ ጉልህ ሆኖ ታየው ። እጆቹ ከመጠን በላይ ይንቀጠቀጡ ጀመር ። የትምህርት ቤቱ ስራ ተፈጽሞ ከስራ ላይ የሚውልበት ቀን ናፈቀው — አጓጓው ። አይኖቹ እንባ አቀረሩ ። ተፈጥሮ እንደ እንቅፋት ከፊቱ ላይ መጥታ በመደንቀሯ ረገማት ። እንደ ሸርሙጣ ለሀይለኛው ብቻ የምታደላ በመሆኗ ጠላት ። ተፈጥሮን ድል ለማድረግ የእጅ ሀይል — የሰለጠነ እጅ የሚሰራው ተአምር — ብቻ እንደሆነ በይበልጥ አመነ ። ኢትዮጵያ በምህላ ወደሰማይ የዘረጋቻቸውን እጆቿን ወደምድሪቱ እንድትመልስ ተመኘ ። የጀመረው የእጅ ጉዞ በትምህርት ቤቱ ስራ ብቻ ከአፎቱ ተመልሶ እንደማይዝግ አመነ ። አሳቡ እንሰራራ……



በየአድባራቱ ካህናቱ ፀሎተ ምህላ ፣ ህዝቡ እግዚኦታ እያሰሙ ፈጣሪያቸው በምህረቱ የመጣውን ቁጣ እንዲያባልፍላቸው መለማመን ከጀመሩ ቆይተዋል ። መምሬ መሀሪ እንደዚያን ሰሞን ስራ በዝቶባቸው አያውቅም ። እግዜር መአቱን ያመጣብን ሀጢአታችን በዝቶ ነው ይላሉ ።

እግዚኦ ብሎ በግንባሩ ከተደፋበት ቀና ሲል ዱ ብሎ የተንጣለለውን አመድማ ሰማይ የተመለከተ አንድ ገበሬ ተስፉ ቆርጦ አጠገቡ ለነበረው ጓደኛው ፣ «ነጭ ኮርማ ወስደን ከተለመደው ቦታ ላይ መሰዋት አለብን ። አለዚያ አድባሯ አትታረቀንም ። እኔ ነጭ ኮርማ አለኝ» አለ ፣ ትላልቅ አይኖቹን ከተንጣለለው ባዶ ሰማይ ላይ እያንገዋለለ ።

«ትምህርት ቤቱስ?» አለ ጓደኛው በአሳብ ተመስጦ ።

«ማፍረስ ነዋ ። ስናልቅ እንዴት ዝም ብለን እናያለን!» ሲል —

«ካድባሯ ጋር መጣላት ሌላ ። ከፊታውራሪ ተካ ጋር ተጣልተን የት ልንገባ?……» ብሎ ሳይጨርስ — አቋረጠውና «ፊታውራሪ በችጋር እለቁ ይሉናል እንዴ አይናቸው እያየ? እርሳቸው ከጉተራቸው እህል አውጥተው ይበ

ላሉ ። ችግሩ መቼ ለጌቶች ሆነ ለድሆው እንጂ ። ቢራብ ድሀ ቢጠማ ድሀ ። ያለው ይጨመርለታል ተብሎ የለ ። እግዜሩም ያደላል ። በምድር ያልሆነለት ድሀ መንግስተ ሰማያትም አይገባም ። ዘንድሮ የከበሩት እህል በጐተራ ያከማቹት ናቸው ። ድሀ እንደሆነ ለዘር ያኖረውን በልቷል ። የዘራውን አፈር በልቶታል ። በዚህ ላይ መንግስት ግብር ክፈሉ ይለናል ። ባለርስት ሲሶ ይጠይቃል ። እኛ ምን እን ሁን? እንለቅ ባንድ ትምህርት ቤት ምክንያት!» አለ በብ ስጭት እየተንገፈገፈ — ቀጠለና «ልጆቹ የሚበሉት አጥ ተው ሰውነታቸው አልቆ ሆዳቸው ብቻ አፍጦ ቀርቶ አል ። በጠኔ ሊያልቁ ነው ። እህል እህል እያሉ — እህል ያልዞረበት ትንፋሻቸው ጠረኑ ተለውጦ ። ከብቶቹ በየሜ ዳው ይወድቃሉ ። እኔንም እንደነሱ አንድ ቀን ጥምብ አንሳ ይቃረጠኛል ። በዚህ ሁኔታ ቀባሪስ የት ሊገኝ? የፊ ታውራሪ ቁጣ ከዚህ ይብሳል?» ብሎ ጠየቀው ።

ሁለተኛው ባላገር መልስ ሲፈልግ ፣ እግዚአታቸ ውን አቁመው በጥሞና ሁለቱን ያዳምጡ የነበሩት አዛ ውንት ጣልቃ ገቡና «የትምህርት ቤቱ መሰረት ድሮ ላድባሯ መሰዋእት ከምናቀርብላት ቦታ ላይ መጣሉ ለድ ርቁ ምክንያት ሊሆንም ላይሆንም ይችላል ። ምክንያቱን የሚያውቀው እግዜር ብቻ ነው ። ይልቅ እኔን የሚከነክ ነኝ ሌላ ጉዳይ ነው ። እንደምታዩኝ በእድሜ ብዛት ቀኑ እየመሸብኝ ሄዷል ። የማዝነው በዚህ ሰአት ጧሪና ረዳት በማጣቴ ነው ። ትልቁ ልጄ የፈረንጅ ፊደል ቆጥሬአለ ሁና እዚህ አልኖርም ብሎ ኮበለለ ። ሴቷ ልጄም አዲስ አበባ ከርመው በጌጣጌጥ አሸብርቀው ዘመድ ጥየቃ የሚ መጡትን አንዳንድ ጓደኞቿን አይታ እኔም ለምን እንደ ነርሱ አልሆንም በማለት ከቤት ኮበለለች ። ይህ ጥርጊያ መንገድ ሱዳ ከገባ ወዲህ ሁሉም እግር አወጣ ። አሮጊ ትና ሽማግሌዎች ብቻ ከቤት ቀሩ — ያለጧሪ ያለረዳት ። የርሻ መሬት ሁሉ እዳሪ ሆነ ። ይህ አሁን የምትከራከሩ በት ትምህርት ቤት ሲስፋፋ ደሞ ከብት የሚያግዱልንና የሚላላኩልን ልጆች ጠርሶ ሊጠፉ ነው ። ዘመኑ በሽማ ግሌዎችና በአሮጊቶች ላይ ፊቱን አዙሮአል ። ከቤት ኮብ ልለው የሚጠፉት ሁሉ በሄዱበት ኑሮ ቢሳካላቸው እንኳ ደግ ነበር — አብዛኞዎቹ ከወሮበልነትና ከሴትኛ አዳሪነት አያልፉም ይባላል ። ይህ ሁሉ ውድቀት ፣ የቤተሰብ መፍረስ ፣ ያሮጊትና የሽማግሌዎች ያለጧሪ ፣ ያለረዳትና ያለቀባሪ መቅረት የመጣው በስልጣኔ ሳቢያ ነው ። ነገሩ ግራ ሆነ ብኝ ። ዳገት አይሉት ቁልቁለት ። ስልጣኔ ነው ይሉናል ። የስልጣኔ ትርፉ ይህ ከሆነ ባፍንጫ ቢወጣ ምናለበት! እኔ ይህን ስልጣኔ አልለውም ። የግዜር ቁጣ ነው ። እግ ዚኦ እንበል — እግዚኦ እንበል — ያመጣብንን ቁጣ እንዲ መልስልን እግዚኦ እንበል ከስልጣኔ መቅሰፍት እንዲሰ ውረን» ብለው በግንባራቸው ከመሬት ተደፉ ።

ሁለተኛው ባላገር አዛውንቱ የሚናገሩትን አላጤነም ። ጓደኛው ላቀረበለት ጥያቄ መልስ ሲፈልግ ከቆየ በሁዋላ «ያምናውን ግብር ማን ከፈለልህ! ይህን እንኳ አታስታው ስም ። ከችጋርም ብናመልጥ እጃቸው ይጥለናል። ፊታው ራሪ ባለውለታዬ ናቸው ። በትምህርት ቤቱ ላይ እጄን አላነሳም» አለ ።

«በትሞት እያየህ?» አለው ጓደኛው በቁጣ ።

«የማትብ ጉዳይ ነው» አለ፣ ኩምጪጭ ብሎ......

እንዳለፈው ሰሞን ንፋሱ በሀይል አይነፍስም ። ደመናዎች ኳ ብለው በከረመው ሰማይ ላይ ብርማ ቀለማ

ቻውን እየለወጡ መሰብሰብ ጀምረዋል ። መንፃና የነበ
ረው የሀዲስ ተስፋ እንደገና አንሰራራ ። ወደሰማይ አን
ገቱን ቀና አድርጎ በልቡ አግዜሩን ተለማመነ ። የደመና
ምቹን መሰብሰብ የተለመከቱት ገበሬዎች ከርከራቸውን
አቁመው ወደ ሰማይ አንጋጠው በመገረምና በድንጋጤ
መንፈስ ይመለከቱ ጀመር ። ፍርሀትና ደስታ የተቀላቀለ
በት ስሜት አድሮባቸው ብርክ ይዞአቸው በደስታና በፍ
ርሀት መካከል ይዋልሉ ነበር ። ሰማዩ እየጠቆረና እያጉረ
መረመ ሲሄድ የቤተክርስቲያን ደወሎችና የአባ ጨፌ
ድቤ እንደመፎካከር እያሉ ያለማቋረጥ ይሰሙ ጀመር ።
አባ መርጋም ምና ምን እየተጉመጠመጠ ወደ ሰማይ
ይተፉል ። ወደምሽት ላይ ዝናብ ጣለ ። ጥቁሩ አፈር ረጥቦ
አደረ ።

የተአምር ዘመን እላለፈም አለ ሀዲስ በልቡ ።

የቤቱ ግድግዳዎች ስራ ለመጠናቀቅ ትንሽ ቀርቶ
ታል ። ለቤቱ ከዳን የሚያስፈልገው ቆርቆሮ ሁሉ መጥቶ
ተከምሯል ። ሀዲስ እንደልማዱ በማለዳ ተነስቶ ከትልቁ
ድንጋይ ላይ ተቀምጦ ቤቱን ከጮራዋና ከአይናለም ፣
አይናለምን ከቤቱና ከጮራዋ ጋር ባሳቡ እያማታ ሲያልም
ቆየ ። ቶሎሳና ጓደኞቹ አልመጡም ። ተማሪዎቹ በሚያ



ዋጡት ገንዘብ ተቀጥረው የሚሰሩት እናጢዎችም ስራ
ቸው ላይ አልተገኙም ። ሀዲስን ከቀን ህልሙ የቀሰቀ
ሰው የትምህርት ቤቱ ደወል ነበር ። ለጊዜው ነገሩ ብያስ
ደነግጠውም ግራ ሳይገባው አልቀረም ። ክፍል ገብቶ
ማስተማር ስለነበረበት ለማሰብም ጊዜ አላገኘም ። ከአ
ርባ አምስት ደቂቃዎች በሁዋላ ከክፍል ሲወጣ ቶሎሳና
ጓደኞቹንም ሆነ በገንዘብ የተቀጠሩትን እናጢዎች ባለ
ማየቱ ልቡ መሸበር ጀመረ ። በድንጋጤ ወደ ዲሬክተሩ
ወደ አቶ ይርጋ አለሙ ቢሮ ሮጦ ገባ ።

የፊቱን መለወጥና የትንፋሹን ማጠር በመገረም
ተመለከቱና ፣ «ምን ነካህ? የቤቱ መሰረት ተናደ እንዴ?»
አሉት እየተመፃደቁ ።

የአቶ ይርጋ አነጋገር ቢያስቆጣውም ንዴቱን ዋጥ
አድርጎ ፣ «የሚረዱኝ ሰዎችም ሆኑ ሌሎች ሰራተኞች
እስካሁን ያለወትሮአቸው አልመጡም ። የቀሩበትን ምክ
ንያት ማወቅ አለብኝ......» ከማለቱ አቋርጠውት ፣ «አሁን
ማስተማር የለብህም እንዴ? »ብለው ጠየቁት ።

«አዎን — ያራተኛ ክፍል ተማሪዎች ይጠብቁኛል ።»

«ስራህን ስትጨርስ ትደርስበታለህ ። ሰራተኞቹ የዘ
ገዩ እንደሆነ ያለም ፍፃሜ አይሆንም ። ምናስቸኮለህ?»
አሉት ፣ እንደመርፌ ጆሮ በምትወጋው ቀጭን ድምፃቸው ።
ሀዲስ ንዴቱን በመቆጣጠር ስሜቱን ገታ ። አልተናገራ
ቸውም ። ዝም ብሎ ወጣ ።

ጠይምነቱ ወደጥቁረት ሊለወጥ ደርሷል ። ድሮ
የሚስቁት ትናንሽ አይኖቹ ፈገግታቸውን አጥተዋል ።
የገባን ጫካ የመሰለው ከርዳዳ ጠጉሩ ማበጠሪያ ካየ ሰን

ብቷል ። ድሮውኑ እጆቹን ከሱሪው ኪስ ውስጥ ከትቶ ሲሄድ ከወገቡ ይጎብጥ ነበር ። አሁን የባሰውኑ ጉብጧል።

ከአቶ ይርጋ ቢሮ ወጥቶ ወደአራተኛ ክፍል ሲያመራ ከሩቅ የመቶ አለቃ አሸኔን አየው ። የማናቸው ኮከቦች ከሩቅ ያብለጨልጫሉ ። ሀዲስ ሊያነጋግረው አልፈለገም ። ግን የመቶ አለቃው በእጁ በለጠቀመው ቆሞ ጠበቀው ። የማወቅ ፍላጎትም አደረበት ።

«አዲሱን ትምህርት ቤት እግረ መንገዱን አይቼው ነው የመጣሁት ። ለማለቅ ምንም አልቀረውም ። እንኳን ደስ ያለህ» አለው ።

«እንኳን አብሮ ደስ ያለን»

«ሰሞኑን ብቻ ስራው ሳይቆም አይቀርም»

«ለምን!»

«ሀዝቡ ለአፈርሳታ እንዲቀመጥ ታዟል»

«የምን አፈርሳታ!»

«የወረዳው ፀሀፊ መገደሉን አልሰማህም እንዴ ? ያ ያንድ ባላገር ልጃገረድ ያበላሸው ። ማን እንደገደለው እስኪታወቅ ድረስ ከአፈርሳታ ዝር የሚል የለም...»

«እስከ መቼ ይቆያል!»

«ማን ያውቃል! ሳምንት ሁለት ሳምንት» አለው ፤ የመቶ አለቃ ፤ የበለዙ አይናቹንና ጥርሶቹን እያሳየው ።

«እስከዚያ ድረስ ነጋዴው ንግዱን ፤ ገበሬው እርሻውን ትቶ ቁጭ ማለቱ ነዋ!»

«ከቦታው ዝር የሚል የለም ስልህ......»



«በቀድሞው ዘመን ቢሆን የአፈርሳታ ጥቅሙ ይገባኛል ። ባሁኑ ዘመን ግን ጥቅሙ አይታየኝም ። ስራ ማስፈታት ነው ። የመሬት ፣ የግቢ ፣ የትምህርት ፣ የጤና ታክስ - የልማት መዋጮ ሁዋላ ላይቀርለት! ይልቅ ወንጀለኛውን በቶሎ ለማግኘት የናንተ ፖሊሶች ምርመራ አይሻልም? ዶሮ የማረችው አያመልጠንም የምትሉት ሰዎች......»

«እዚህ የቀድሞው ዘመን የምትለው አሁንም እንዳለ ነው ። የጋርዮሽ አላፊነት ያስፈልጋል ። ጥቂት ፖሊሶች ብቻቸውን ወንጀልን ለመከላከል አይችሉም» አለው ።

የሀዲስን ፊት የሀዘን ጥላ መጥቶ ጋረደው ።

የመቶ አለቃ አሸኔ እዚህ ላይ ነገሩን አላቆመም ። «በመታሰርህ በኔ አትዘንብኝ ። እሳቡ የኔ አይደለም» አለው ፤ መለዮውን እያስተካከለ ። ሀዲስ መልስ ሳይሰጥ ዝም በማለቱ ቀጠለና ፤ «ካለቃ ጠላት ይሰውረኝ ማለት ብቻ ነው» አለው ።

ሀዲስ ፤ አንዳችም ስሜት የማይነበብበት ፊት እያሳየው «እኔ ያለቃ ጠላት የለኝም ። ባንግባባ ይሆናል» አለው ።

የመቶ አለቃ አሸኔ በሀዲስ መልስ እንደመበሳጨት ብሎ ጥሎት ለመሄድ ከቃጣው በሁዋላ መለስ አለና «ሳይሀ የጉርምስናዬን ወራት ታስታውሰኛለህ ፤ እኔም እንዳንተ ዳተኛ ነበርኩ ። አለምን ለመለወጥ የምችል ይመስለኝ ነበር ። ታዲያ ነገሩ የተጣባቢጦሽ ሆነና አለም እኔን ለወጠችኝ ። ብቻ በልጅነት ዳተኛ መሆን በኔና ባንተ አልተጀመረም ። ሁሉም የሚጓዝበት መንገድ ነው ። እኔ ያኔ

በራሴ ላይ የፈጠርኩት ጠንቅ እንደጥላዬ ሲከተለኝ ይናራል ። ብዙ ጓደኞቼ ዛሬ ሻለቃዎች ሆነዋል ። እኔ ግን ይሄውና እንደምታየኝ በመቶ አለቅና ቀረሁ» አለውና በረጅሙ ተነፈሰ ።

«እኔ'ኮ ዳተኛ አይደለሁም ። ልሰራ ማለት ዳተኛ ያሰኛል እንዴ......»

የመቶ አለቃ አቋረጠውና «አየህ እኔ ከአባ ዲና ተመርቄ ስወጣ — ጊዜ ሲያመልጥና ጠጉር ሲመለጥ አይታወቅም — የበላዮቼን እየተጋፋሁ ለፍትህ ሽንጤን ገትሬ እሟገት ነበር ። አንዳንድ እስረኞች በገዛ ስልጣኔ ፈትቼ የለቀቅሁበትም ጊዜ ነበር ። አንዳንድ የአሰራር ዘዴዎች እንዲለወጡ የማላቀርበው አሳብ አልነበረም ። አንዳንዶቹን አሳቦች በገዛ ፈቃዴ ስራ ላይ እንዲውሉ ሞክሬ ነበር ። መቸም አለቃ ያልወደደው ነገር አይባረክም ። ሚዳውን ገደል የሚያደርጉበት ዘዴ አላቸው ። ብቻ ምን ያደርጋል ፤ ያለፈውን ቢያወሩት ተረት ይሆናል ። ያኔ የነበረኝን አሳብ አንዳንዱን ሳስታውሰው ያስቀኛል ። ድፍረቴና ግትርነቴ ያስገርመኛል ። እድሜ መስተዋት ነው ይሉ የለም ። ነገሩ እንደዚያ ሆነና ነው ። ከህብረተሰቡ ውስጥ መብቀል ያስፈልጋል ። ላይ ላዩን እናብብ ብንል ስር እንሰድም» አለውና ከሀዲስ መልስ ሳይጠብቅ ጭንቱን ያራገፈ ይመስል በረጅሙ ተንፍሶ እየተውዘገዘገ ወደእቶ ይርጋ ቢሮ አመራ ።

ሀዲስ በመቶ አለቃ አሸኔ አስተያየት እየተገረመ ለማስተማር ወደ ክፍል ገባ ። ሳምንት እንደዋዛ አለፈ ። ወደስራ የተመለሰ ሰው አልነበረም ። ሀዲስ አስተምሮ ከክፍል በወጣ ቁጥር ብቻውን ከመፍጨርጨር አላቋረጠም ።



ያናጢነቱንም ሆነ የግምበኛነቱን ስራ እንደነገሩ የተለማመደው ቢሆንም ፤ አልፎ አልፎ በራሱ ላይ አንዳንድ አደጋ ማድረሱ አልቀረም ። አንድ ቀን ምስማር እመታለሁ ብሎ ግራ እጁን ክፉኛ ቀጠቀጠው ። ስቃዩ ከስራ አላገደውም ፤ ጠንካራው ምኞቱ ይገፋፋው ነበር ። ተማሪዎቹ አንዳንድ ነገር ከማቀበልና ከመሳላክ በቀር በዚህ ደረጃ የሚሰጡት ርዳታ እምብዛም ነበር ። ሰውነቱ እየደከመ ፤ እየከሳና እየጠቆረ ሄደ ።

አንድ ቀን ከሰአት በሁዋላ ከንች እመታለሁ ብሎ ሲታገል ተንሸራትቶ ከጣሪያው ላይ ወደቀ ። በመደነቅ ቆመው ይመለከቱት የነበሩት ብዙ ተማሪዎች እየሮጡ ከወደቀበት ደረሱ ። ግማሽ ጐኑ ጭቃ ውስጥ ተቀብሮ በጀርባው እንደተንጋለለ ትናንሽ አይኖቹን አፍጦ ጣሪያ ጣሪያውን ይመለከት ነበር — ሊያነሳው የመጣ ያለ ይመስል ቀኝ እጁን ወደጣሪያው እየዘረጋ — ሳንዳፍታ ከጣሪያው ላይ ሆና አይናለም እጆቿን ወደታች ስትዘረጋለት በእዝነ ልቦናው ተመለከተ ። የተማሪዎቹ ጩኸት ወደእውነት መለሰው ። ለመነሳት ሞከረ ። ግን ግራ እግሩ ከዳውና ተመልሶ ወደቀ ። ያኔ ነበር የእግሩ መሰበር የታወቀው — እና በደረቱ ዞሮ ፊቱን ከጥቁሩ ጭቃ ውስጥ ቀበረው — ኀድሉን እየረገመ ።

ተማሪዎቹ ወዲያውኑ ወሳንሳ ይዘውት ከጐጆው ወስደው እንዳስገቡት ተደናግጠው ፤ ነጠላ እንኳ ትከሻቸው ላይ ሳይጥሉ በመጀመሪያ የደረሱለት ጐረቤቶቹ ወይዘሮ ዝናሽና ሽታዬ ነበሩ ። ከእግር መሰበር የባሰ አደጋ በብዙ ወንዶች ላይ ሲደርስ የገፋው እድሜዋ ያሳያት በመሆኗ ፤

ወይዘሮ ዝናሽ ይህን ያህል አልተጨነቀችም ። ሽታዬ ግን እንባዋን ትዘራ ነበር ።

ፍቅር የሸርሙጣ መቃብር ነው ማለትን የምታዘወትረዋ ዝናሽ ፣ የሽታዬ ዝንባሌና ስሜት ባያስደስታትም ፣ ሀዲስ እንደሷ ያዲስ አበባ ልጅ በመሆኑ ስለማትጠላው «በገዛ እጅህ ጠላት ባታበዛ — በእጅህ መቃብርህን ባትቆፍር ምን ነበረበት?» ሳትለው አታልፍም ባገኘችው ቁጥር ።

ሽታዬ አንድ ቀን ወደአዲስ አበባ ወጥታ ፣ ያንን በዝና የሰማችውን የብር ማእድን የሆነ ከተማ ማየት ነበር ምኞቷ ። እድሏ አልሆን ብሎ ወደአዲስ አበባ በመሄድ ፈንታ ወደ ሱጴ ቦሮ ወረደች ። ከሀዲስ ጋር ከተዋወቀች ወዲህ ግን ወደአዲስ አበባ ለመውጣት የነበራት ብርቱ ምኞት እንደገና ማንሰራራት ጀምሮ ነበር ።

ብቻዋን በምትሆንበት ጊዜ ፣ ገረዶቻቸውን ከነቡቱቻቸው አግብተው የሚሄዱ አስተማሪዎች አሉ አይደለም እንዴ? እኔ እንኳ ስንት አውቃለሁ — ከገረዶቻቸው የወለዱ አስተማሪዎች ። ስንት ገልቱ የባላገር ገረዶች ቀን አልፎላቸዋል! እኔ ታዲያ ከነሱ በምን አንሳለሁ? መልኬ ውብ — ፀጉሬ ዞማ — ቁመቴ ሎጋ — እድሜዬ ለጋ — ምን እንከን ይገኝብኛል? የለም — ደሞ ለገጠር አስተማሪ ይህን ያህል መጨነቅ እያለች ስታስብ ትቆይና ፣ ሀዲስ ፣ አይኑ አፋር ፣ መንፈሰ ግትር ፣ ብዙ የሚያስብና የሚሰራ ፣ ግን ከትንሽ ፈገግታ ሌላ ብዙ የማይናገር መሆኑን ስትገነዘብ ፣ ያገባኝ ይሆን? በማለት ፣ በጥርጣሬ ትጨነቃለች ። ሽታዬ መንፈሷ ታውኮ ስትጨነቅ ወይዘሮ ዝናሽ ባየቻት ቁጥር ፣—



«ፍቅር ያዘኝ ብለሽ አትበይ ደንበር ገተር
እኛም አንድ ሰሞን እንዲህ አርጎን ነበር» ካለች በሁዋላ ትቀጥልና የከበደ ሚካኤልን ግጥም በመቀየር ፣—

«ሸርሜ ሞቷን ስትሻ ስታበዛ ሩጫ
ሄዳ ታሸታለች የፍቅር አፍንጫ» ሳትላት አታልፍም ። አባባሉ ለሽታዬ እንደ ማስጠንቀቂያ የተሰነዘረ ይሁን እንጂ ወይዘሮ ዝናሽንም ቢሆን ኮከብ ተዋናይት ከነበረችበት ከደጃች ውቤ ሰፈር መድረክ ላይ ወድቃ ሱጴ ቦሮ የደረሰች በትን ምክንያት ያስታውሳታል ።

"እንደሰራ አይገድል......መጠጥ ቤቱን ክፍት ትተን ነው'ኮ የመጣነው" አለችና ፣ ዝናሽ ወደፊት የገፋውን ሆዷንና ወደሁዋላ ያፈጠጠውን ቂጧን ተሸክማ ተነሳች ።

"ውይ እትዬ......ብቻውን ባዶ ቤት ውስጥ ጥለነው እንሂድ እንዴ?" አለች ሽታዬ ፣ እያመነታች ።

«ካንቺ የተሻለ ምን ወጌሻ አለው ብለሽ? አንቺ ባይሆን እዚሁ ሁኚለት» አለችና ፣ ወደሀዲስ ፊቷን መለስ አድርጋ ፣ «ብቸኛ መሆን ክፋቱ እዚህ ላይ ነው» አለችው ፈገግ ብላ ። ፈገግ ስትል ከጉንጮቿ ላይ ስርጉድ እያሉ አይን የሚስቡት ምልክቶች የቀድሞ ምትሀታቸውን አጥተዋል ። ስትስቅ አይን የሚስቡት ያስተከለቻቸው ሁለት የወርቅ ጥርሶች ብቻ ናቸው ። ሀዲስ ስቃዩን ላንዳፍታ በመርሳት በወይዘሮ ዝናሽ አነጋገር ተደንቆ ፈገግ አለ ። ፈገግ ሲል ከግራ ጉን ያለችው ወሊቃው ትታያለች ።

ወይዘሮ ዝናሽ እንደወጣች ፣ ሽታዬ ፣ ሀዲስ ከተኛበት አልጋ ጠርዝ ላይ ቁጭ ብላ ፣ አይን አይኑን እያየች

«ወይዘሮ ዝናሽ ያሉትን ሰምተሀል? ብቸኛ መሆን — ያውም በማያውቁት አገር — ጥሩ አይደለም» አለችውና እጁን ያዘችው ። እርሱም ጠበቅ አድርጐ ያዛት ።

ቀጠለችና «አርግዤልሀለሁ'ኮ» አለችው ። አልደነገጠም ። ሽታዬ አርግዤልሀለሁኮ ስትለው ይህ የመጀመሪያዋ ጊዜ አይደለም ። እየቀለደች ደጋግማ ያረገዘችለት መሆኗን ትነግረው ነበር ። ካረገዘችለት ይዟት ወደ አዲስ አበባ መሄድ የግድ እንደሚሆንበት ስለምትገምት ፤ በዚህ ልታጠምደው ካሰበች ወዲህ ከሴላ ወንድ ሄዳ አታውቅም ። ከሀዲስ እንድታረግዝ ያልሰገደችለት ታቦት ፤ ያላየችው ጠንቋይ ፤ መፅሀፍ ያላስገለጠችው ደብተራ በሱዱ ቦሮ አይገኝም ። ከደረቱ ላይ ጋደም አለች ። ሉጫ ፀጉሯ ግማሽ ፊቱን አለበሰው ። በግራ እጁ ጡቷን መደባበስ ጀመረ ። የወንድነት ስሜቱ መቀስቀስ ለጊዜው ሲቃዩን አስረሳው ። እጁ ፤ ከጡቷ ወደዳሌዋ ፤ ከዚያም ወደጭኗ እያለ ወደታች መንሸራተት ሲጀምር ፤ ሽታዬ በመገረም ፤ «እንዴ?» አለች ።

«ምንነው?» አላት ፤ ትናንሽ አይኖቹን እያንከባለለና ትናንሽ ንፁህ ጥርሶቹን እያሳያት ።

«እግርህ ተሰብሮ!»

«መድሀኒት ነው እሱ!»

«ይልቅ ነገ አባ ጨፌ ዘንድ ሄጄ ልንገርልህ!»

«ምን ትነግሪልኛለሽ?»

«ሁለተኛ አደጋ እንዳይደርስብህ......ጠላቶችህ እንዲወድቁልህ ...... የነካሽውና ያሰብከው ነገር እንዲሆንልህ......»



«ቃልቻ ይህን ሁሉ ለሰው ለማድረግ ቢችል ኖሮ ለራሱ አያንሰም ነበር......»

«እረ እንዲህ አትበል! ውቃቢያቸው ይወግሀል ። ከአባ ጨፌ የሚሰወር ነገር የለም ። የተናገሩት አይወድቅም ። ወይዘሮ ዝናሽ ከአዲስ አበባ ባዶ እጃቸውን መጥተው የከበሩት በምን ምክንያት መሰለህ? ከአባ ጨፌ ቤት አይጠፉም......»

«እንዲህ ስትይ ከሀያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ውስጥ ያለሽ አይመስለኝም ። የአባ ጨፌ ትልቅነትና ክብር የተገነባው በህዝቡ ድንቁርና ላይ ነው ። ሌላ መሰረት የለውም ። ትምህርት በበር ሲገባ ቃልቻ በመስኮት እንደሚወጣ የታወቀ ነው ። በድንቁርና ላይ የተመሰረተ ማንኛውም እምነት ከተመሳሳይ እድል አያመልጥም ። ይልቅ ይህን ተይና......»

«ምን ልትሆን?»

ሽታዬ ከደረቱ ላይ ቀና ብላ ከአልጋው ላይ ለመጋደም ስታስብ በር ተንኳኳ ። ፈንጠር ብላ ከአልጋው ፊትለፊት ካለው ወንበር ላይ ቁጭ አለች ። የመጣው ቶሎሳ ነበር ።

«ጋሼ የመጣሁት አደጋ የደረሰብህ መሆኑን ሰምቼ ነው ። ባይመሽ ኖሮ ፊታውራሪም ለመምጣት አስበው ነበር ። ግን ይዘኸው ና ብለውኛል» አለው ።

«እግሬ ተሰብሮ ምኑን ይዘኸኝ ሄድክ......»

«ወንድሜን! እግርህ ነው እንዴ የተሰበረው? እኔን ይሰበረኝ ። እኔ መቼ አውቄ ። ቀላል አደጋ መሰሎኝ ነበር ። በል አሁን ሰዎች ይገዙ መጥቼ እወስድሀለሁ» ብሎት

እንባውን እንዳቀረረ ሊወጣ ሲል ፤ ሀዲስ አንገቱን ቀና አደረገና «እዚሁ ተኝቼ አገግማለሁ ። ይልቅ ጥሩ ወጌሻ ፈልግልኝ» አለው ።

«የለም'ኮ ጋሼ……»

«ምንነው ወጌሻ ብትፈልግልኝ!»

ከአይናለም ጋር አንድ ጣሪያ ስር ማደሩን አልጠላም ። እንዲያውም ከቶሎሳ ጋር ለመሄድ አስቦ ነበር ። ግን ስለ አይናለም ያደረበትን ስሜት ፈራው ። ፊታውራሪ ተካ ስሜቱን ገምተው የነቁበት እንደሆን ከአይናለምም ሆነ ከትምህርት ቤቱ ሳይሆን ከሁለት ዛፍ ያጣ ጉሬዛ መሆኑ ይመጣል ብሎ አሰበ ። የመሄድ ፍላጎቱን ገታና ነገሩን ለመለወጥ ያህል «ለመሆኑ የአፈርሳታው ጉዳይ ከምን ደረሰ?» ብሎ ጠየቀው ።

«የምስራች»

«ምስር ብላ»

«ዛሬ አለቀ»

«ገዳዩ ተገኘ ማለት ነው?»

«እሱ ምን ይገኛል ። አምናም አንድ ፖሊስ ተገድሎ አፈርሳታ እንድንወጣ ታዘን ነበር ። ካቻምናም እንዲሁ ነበር ። ባሁኑ ጊዜ ወፍ ነገረችን የሚል እንኳ አልተገኘም ። ምንም ፍንጭ ስላልተገኘ አፈርሳታው ተበትኗል ። እንግዲህ የአይናለም ሰርግ ካለፈ የትምህርት ቤቱን ስራ ከፍፃሜ ከማድረስ በስተቀር ሌላ ስራ የለንም» አለው ።

«መቼ ነው ሰርጉ?»

«ከሁለት ሳምንት በሁዋላ — እሁድ……»



«ለምን አጣደፋችሁት?»

«እኛ መቼ ሆንና የተጣደፍነው — የኖጻዎቹ ናቸው…»

«መጣደፍ አለባቸው እንጂ አይናለምን የምትመስል ልጅ ሲያገኙ……» ከማለቱ ሽታዬ በድንገት ብድግ ብላ ወጣች ። ሀዲስ ስለአይናለም ያለውን ስሜት በመግለጡ ደነገጠ ። ሽታዬ በድንገት ተፈንጥራ ለምን እንደ ወጣች ገባው ።

«እንዴ የአይናለም ስም በመጠራቱ ምን አስቆጣትና ሄደች !» አለ ቶሎሳ እየተገረመ ።

ሀዲስ የሚመልሰው ነገር ጠፍቶት «እ……የለም…ተ……ተቆጥታ አይደለም ። ቅድምም እቸኩላለሁ ስትለኝ ነበር» አለ ።

«ታዲያ ስትሄድ ደህና እደሩ እንኳ አትልም ። አውቃታለሁ'ኮ ። ከወይዘሮ ዝናሽ ቤት አሻሻጭ ነች ። እነርሱ አስተማሪዎችን ሲያገኙ የሙጢኝ ብለው ይቀራሉ ። መድሀኒት እንዳታቀምስህ ተጠንቀቅ ጋሼ» አለው ።

ቶሎሳ የሽታዬን ማንነት በማወቁ ሀዲስ እንደማፈር ብሎ አቀረቀረ ። ስለአይናለም ያለኝ ስሜት ተከስቶለት ይሆን ? ብሎ ጠረጠረ ። ብነግረውና ይገዴአት እንድኮበልል ቢረዳኝስ ብሎ አሰበ ። ሰውነቱን ዘገነነው ። የእግሩ ህመም ሁሉ ተረሳው ። ምስጢሩን ሊያካፍለው ከቀረቀረበት ቀና አለና መልሶ አሳቡን ለወጠ ። ሊሆን አይችልም ፤ ቶሎሳ ለፊታውራሪ ተካ ያለው ታማኝነትና ፍቅር በምንም ነገር የሚፈታ አይደለም አለና አሳቡን ገታ ። የተሰበረውን እግሩን ረገመ ። የትምህርት ቤቱን ስራ የጀመረበትን ቀን ረገመ ። አይናለምን ያየበትን ቀን

ረገመ ። ሱጲ ቦሮ የመጣበትን ቀን ረገመ ። የሰርጉን ቀን መድረስ ረገመ ። ራሱን ወጥመድ ውስጥ እንደተዘፈቸ አይጥ አድርጐ ተመለከተ ። እና ራሱን ጠላ ። የአፈርሳ ቃው መነሳትና የትምህርት ቤቱ ስራ እንደገና መቀጠል ስሜት አልሰጠውም ። የሀዲስ ጠይም ፊት በሀዘን ተዋጠ ።

ኙሎሳ የሀዲስን ምስጢር ዘልቆ ለማወቅ ትክ ብሎ ይመለከተው ነበር……

ከዶጋው ፤ ከቆላው ፤ ከአልጌ ፤ ከዳሪሙ ፤ ከሜኮ ፤ ከጐብ ፤ ከጉቤ — ከምእራብ ፤ ከምስራቅ ፤ ከሰሜን ፤ ከደቡብ — ከሩቅ ፤ ከቅርብ — ከሚካኤል ፤ ከማርያም ፤ ከሰላሴ — ህዝቡ የክት ልብሱን ለብሶ — ጃኖ ፤ ድርብ ፤ ጥንግ ድርብ — በእግር ፤ በበቅሎ ፤ በፈረስ — መሳሪያ ውን እንደያዘ — ሽጉጥ ፤ ጠብመንጃ ጦርና ጋሻ ፤ ዘንግ — ወደፊታውራሪ ተካ ቦሮ ቤት ይጓዛል ። በጃኖ ፤ በዘንባባ አጊጦ የተንጣለለው ዳስ አይሞላም — የመጣውን ሁሉ ይውጣል ።

ፊታውራሪ ተካ ከዳሱ መግቢያ ላይ ቆመው የመ ጣውን እንግዳ ሁሉ በፈገግታ ይቀበላሉ ። ከላይ ጣል ያደ ረጓት ኩታ ፤ የለበሱት ነጭ ልብስና የግራዋ አበባ የመሰ



ለው የጠጉር ሽበታቸው ተዋሀደው ቀይ ፊታቸውን በበ ለጠ ብሩሀ አድርገውታል ።

ከዳሱ ወደቀኝ ሲል ተከናንበው — ዘንግ — ሽመል — አንካሴ — ጦር የያዙ ሎጋ ሎጋ ጐረምሶች ባንድ ረድፍ ፤ ባዱላቸው በአደስ ተለውሶ እንደጨረቃ የሚያበራ — ጐር ባቸው ከትከሻቸው ላይ ወርዶ ዘፍ ያለ —እግሮቻቸውንና እጆቻቸውን እንሶስላ የሞቁ ፤ አይኖቻቸው በስርኩል ደም ቀው እንደፈርጥ የሚንቦገቦጉ — በግራ እጆቻቸው ከት ከሻዎቻቸው አንገር ከቆዳ የተሰሩ ድቤዎች የያዙ ሾጤ ልጃገረዶች ከያንዳንዱ ጐረምሳ አንፃር በሌላ ረድፍ ሆነው በሀብረት እየተቀባበሉ በመዝፈንና የአንገት እስክስታ በማሳየት ግቢው በበለጠ እንዲደምቅ አድርገውታል ።

ጆሬ አሞራዎች በየዛፉ ላይ ሰፍረዋል ። ጭልፊቶች በብዛት ያንዣብባሉ ። ለማኞች በብዛት ካጥሩ ስር ተኮ ልኩለዋል ። የመንደሩ ውሾችም አልቀሩም ። አልፎ አልፎ አጥንት ወይም የስጋ ልፋጭ በመናጠቅ ሁከት ሲፈጥሩ ይታያሉ ። ባልና ሚስት አዝማሪዎች ፤ በተን ጣለለው ዳስ ውስጥ እየተንጐራደዱ በመቀባበል ይዘፍ ናሉ ። የፊታውራሪ ተካን ስም እንስተው በዘፈኑ ቁጥር ብር እየመዘዘ ግንባራቸው ላይ የሚለጥፈው ሰው ቁጥር መጠን የለውም ። ደጋግሞ አምስት ብር ከአዝማሪው ግንባር ላይ በመለጠፍ የመቶ አለቃ አሸኔ የአንደኛነቱን ደረጃ በመያዝ ፤ በተጋባዥ ዘንድ «ያባ መስጠት ልጅ» አሰኝቶታል ። ከዚያ በሁዋላማ ምኑ ቅጡ ! ይመነዝረው ገባ ። አቶ ይርጋ ግን በይሉኝታ አንድ ጊዜ ብቻ አምስት ብር ከሰጡ በሁዋላ እጃቸውን እንደተለመደው አጥፈው ቁጭ አሉ ። ገንዘብ ማውጣት ፊዕም አይወዱም ።

ሀዲስ ፣ በቀርቀሀ ከቁርጭምጭሚቱ እስከ ጉልበቱ ድረስ የታሰረውን የግራ እግሩን እንጠልጥሎ ፣ በምርኩዝ ሰንከል እያለ ከበር ሲደርስ ቶሎሳ እየሮጠ ሄዶ ተቀበለው ። ፊታውራሪ ከዳሱ መግቢያ ላይ ቆመው አልጠበቁትም ። ቶሎሳን ተከትለው ወደ እርሱ ሄዱ ።

«ተሻለህ ወዳጄ? በጣም ያዘንክ ትመስላለህ ። በዛሬው ቀን መደሰት ነው እንጂ» አሉት ፣ በአባትነት ፍቅር አይን አይኑን እየተመለከቱ ። ቀደምብዬ አውቄው ብሆን ምን ኖሯል የሚል አሳብ መጣባቸው ።

«ተሽሎኛል ። ህመሙ ትንሽ ትንሽ እየተሰማኝ ነው ። የላኩልኝ ጠቦት ረድታኛለች» አላቸው ።

«ብታርፍበት'ኮ ቶሎ ይሻልህ ነበር ። ይህንኑ እግርህን እየጐተትክ ያንን መከረኛ ትምህርት ቤት ስትሰራ ትውላለህ አሉ ። እንደምሰማው ሰሞኑን ጨርሶ አታርፍም ይሉኛል ። አይዞህ ። ይህ የሰርግ ጣጣ ካለፈ ሁላችንም እንረዳሀለን ። የጀመርከው ስራ ትልቅ ፣ በጣም ትልቅ ነው ። በርታ» አሉትና ወደዳሱ እንዲገባ መንገድ ለቀቁለት ።

ፊታውራሪ ለግብዣም ሆነ ለማንኛውም ጉዳይ የቀጠሮ ሰአት የማያከብር ሰው በጣም የሚጠሉ መሆናቸውን ቶሎሳ ካንድም ሁለት ጊዜ አጫውቶት ነበርና ፣ ከእርሱ በሁዋላ የሚመጣ ሰው ባለማየቱ ሀዲስ ደንግጦ ፣ «ዘገየሁ መሰለኝ ። ይህ እግሬ እንደልብ አላስኬድ ብሎኝ ነው» አላቸው ።

«ደህና ደርሰሀል ። አሁን ልክ ሰባት ሰአት ነው» ካሉ በሁዋላ ፣ ስለቀጠሮ ሰአት ማክበር ያላቸውን ፍልስ



ፍና ለመወርወር ያሀል «የሰው ማንነቱና ትልቅነቱ ፣ እንዲሁም ስለሌላው ሰው ያለው በጐ ፈቃድ ፣ ርህራሄና አሳቢም ጭምር የሚገመተው በቀጠሮ ሰአት አክባሪነቱ ነው» አሉት ። በዚህ አሳብ ላይ ያላቸው ጠንካራ እምነት ካነጋገራቸው ገባው ። በምርኩዙ ተደግፎ እያነከሰ ከፊታውራሪ ጋር ወደዳሱ ሲገባ ተጋባዡ ህዝብ አድናቆቱን በይፋ ገለጠለት ። የሚያመሰግኑትም ፣ የሚመርቁትም ብዙዎች ነበሩ ። በዚህ መካከል አዝማሪ በግጥም ሲያሞግሰው ህዝቡ አድናቆቱን በጭብጨባ ሲገልጥለት ከመደንገጡ ብዛት ምርኩዙ ከእጁ ሊወድቅ ምንም አልቀረውም ። አቶ ይርጋና የመቶ አለቃ አሸኔ ሳይወዱ በግድ ከሌሎቹ ጋር አጨበጨቡለት ። ከሰው እንለይም በሚል ስሜት ።

ሀዲስ ፣ ባንዳፍታ ሰውነቱ በላብ ተጠመቀ ። የሰውነቱ ግለት እንደእሳት ሲያቃጥለው ተሰማው ። ያልጠበቀውና ያላሰበው ክብር ስለተሰጠው ባንድ በኩል የስሜት ሲቃ ያዘው ። አይኖቹ በእንባ ጭጋግ ተሸፈኑ ። ካስቀመጡት በሁዋላ ነበር የት እንዳለ ያወቀው ። ከፊት ለፊቱ አቶ ይርጋና የመቶ አለቃ አሸኔ ፣ ከጐኑ ደግሞ «ሀኪም» የሸጥላ ተቀምጠው አገኛቸው ። እንደምመሬ መሀሪ «ሀኪም» የሺጥላ ከየት እንደመጣ አይታወቅም ። ሱጴ ቦሮ ሲደርስ ሁለት የመርፌ መውጊያ መሳሪያዎች ይዞ እንደመጣ የሚያስታውሱ ሰዎች ይገኛሉ ። ታመምኩ ብሎ የሚመጣውን ሁሉ መርፌ ስለሚወጋ ፣ ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ «ሀኪም» ለመባል በቃ ። ዶቶር የሚሉትም አሉ ። የአይናለም እናት በድንገት ፣ አልጋ ላይ በዋሉ በሶስተኛው ቀን ሰውነታቸው አብጦ የደም ስሮቻቸው ተኮማትረው ከእስራ

እምስት አመት በፊት የሞቱበትን ምክንያት ምናልባት የሚያውቅ ሰው ቢኖር «ሀኪም» የሺጥላ ብቻ ሳይሆን አይቀርም ። ለአይናለም እናት ሞት ያኔ የተሰጠው ምክንያት ልክፍት የሚሉት በሽታ ነበር ። ፊታውራሪም ቢሆኑ ከዚህ የተለየ እምነት አልነበራቸውም ። የአይናለም እናት እንዲያው ቀብጠው መርፌ ከተወጉ በሁዋላ ፤ ሶስት ቀን ሙሉ «ተቃጠልኩ ፤ ነደድኩ» በማለት እንደወተወቱ አረፉ ።

አቶ ይርጋ ደም በለበሱ አይኖቻቸው ሀዲስን ትክ ብለው እየተመለከቱ «ዝነኛ ሆነሀል ለካ!» እሉት እያሸሟጠጡት ።

በተገታ አንደበት «ዝና ሲበዛ ነጃሳ ነው — ራስ ላይ ይወጣል» አሳቸውና ሳቡን ከፊቱ ላይ ጠረገ ።

«አንተ የምታስበው በራስህ ሳይሆን በእጅህ ነው — ለራስህ ምን አስጨነቀህ» አለው የመቶ አለቃ ፤ በምፀት ።

«ከብዙ አሳብ ትንሽ ስራ ይበልጣል ብዬ ነው ። እግዜር ለሰው ከሰጠው ትልቅ መሳሪያ አንዱ እጅ ነው ። ግን ባገራችን በእጅ የሚሰራ ሰው እስካሁን በወራዳነት ሲታይ ቆይቷል ። ኢትዮጵያን ወደሁዋላ ያስቀራት እንዲህ አይነቱ ዝንባሌ ነው ። ኢትዮጵያ ባሁኑ ጊዜ የምትፈልገው የሚሰራ እጅ ነው» ብሎ መለሰለትና ፤ ቀጥሎ በቁም ነገር «የኔ ጥሪ ስራ ነው ። መናገር አላውቅም ። ያ የጥሪ ሰአት ሲደርስ በቆራጥነት መነሳቱ ሀጢአት አይደለም ። ከማፍረስ መገንባት ፤ ከብዙ ምላስ ትንሽ ስራን ፤ ከበቀል ይቅርታን ፤ ከጥላቻ ፍቅርን ፤ ከማይምነት እውቀትን እመርጣለሁ ። ቂል ነኝ ፤ ግን አንድ ነገር አውቃለሁ ። በሁሉም ነገር ላይ እምነት ከማጣት የበለጠ አገርን የሚያጠፋ በሽብ የለም» አለው ።

«ሀኪም» የሺጥላ የደረቀውን ጉሮሮውን በማር ጠጅ አረጠበና «አሉስ ሀጢአት አይደለም ፤ ከስራ በፊት ማሰብና መመካከር ግን ያስፈልጋል ። መቸም የዘመኑ ወጣቶች ስትናገሩ ስትሰሩም ትቸኩላላችሁ መንፈሳችሁ ቁጡ ነው ። የሀይል መንገድን ትመርጣላችሁ ። ገደሉ ሁሉ ሜዳ መስሎ ነው የሚታያችሁ ።» አለና ፤ ነገሩን ለማራዘም ወደሀዲስ ዞሮ ከወንበሩ ላይ ተመቻቸ ። ወይዘሮ ዝናሽ ከመቶ አለቃ አሸኔ ጐን በስተግራ ፤ ከሷ ቀጥላ ደግሞ ሽታዬ በፒያሳ ልብስ አሸብርቀው ቁጭ ብለው የባላገር ሴቶች አይመስሉም። የባላገሩ አይን ማረፊያ ሆነዋል ። ዳሱ ውስጥ የሚታየው ግርግርና ድምቀት የጥንቱን የደጃች ውቤ ሰፈር ትዝታ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ አለባበሷ የባላገሩ አይን ማረፊያ ስላደረጋት የጥንቱን ኮከብነቷን ስላስታወሷት ወይዘሮ ዝናሽ የደመቀ ፈገግታ ፊቷ ላይ ጉልቶ ይታያል ። ሽታዬ ግን አይኗን ሳትሰብር ሀዲስን ነበር ትኩር ብላ የምትመለከተው — ከህዝቡ የተሰጠው ክብርና ያገኘው ዝና ስለሀዲስ ያላትን አሳብ በበለጠ ያጠነከረው ይመስል ። የመቶ አለቃ አሸኔ አይን ደግሞ ዞሮ ዞሮ ከዝናሽ ላይ ያርፋል ። በአይኖቻቸው አንድ አይነት ስሜት ይለዋወጣሉ ።

የደጃች ውቤው ትዝታ በአሳቧ ይመጣል ። ዝናሽ — ያሁኑን እያደርገውና ፤ በዘመኗ የደጃች ውቤ ሰፈር ኮከብ የሆነችበት ጊዜ ነበር ። በዚያ በደጉ ዘመን ፤ እንኳን ጠጥታላቸው እንዲሁ ጠርሙስ ውሺኪ አስከፍታ ብትተወው ፤ ዝናሽ'ኮ ግብዣዬን ተቀበለች በማለት ዝናውን በሰፈሩ የሚነዙ ወንዶች ቁጥር ጥቂት አልነበረም ። ከልቧ

ሲቃ ፣ እንደእንቁ የሚያበሩትን ትላልቅ ውብ አይኖቿን የወረወረችበት ወንድ በሰፈሩ የምሽቱ ንጉስ እንደሆነ ይቆጠር ነበር ። ያ ሁሉ ካለፈ ዘመኑ ቀይቷል ። አይ ዘመን — አያልፍ የለም አለች ።

የአዝማሪዎቹ ድምፅ ሊዘጋ ደርሷል ። ግንባራቸው ላይ ብር የመለጠፉ ነገር አላቋረጠም ። ሁለት ሽምገል ያሉ ጥቋቁር ሰዎች እምቢልታ እየነፉ የአዝማሪዎቹን ገቢ መሻማት ከጀመሩ ቆይተዋል ። የመሲንቆውና የእምቢልታው መናር ፤ የአዝማሪዎቹ ድምፅ ፤ የተጋባዡ ህዝብ ቱማታ ፤ የብርሌው ቻቻታ ፤ የአጋፋሪዎቹ ጋጋታ ከዳሱ ውስጥ ባንድነት ሲሰሙ ፤ ከውጭ ደግሞ የልጃገረዶቹ ዲቤ ፤ የጉረምሶቹ ጭፈራና የቅብብሎሽ ዘፈን ፤ የውሾቹ እርስ በርስ መፋጀት — ለገላጋይ እስኪ ሰለቹ ድረስ — በባዶ ሆድ የደረቀ ጠጅ በአንኮላ የለጉ ለማኞች እርስ በርስ ዱላ የመማዘዝ—ለገላጋይ እስኪሰለቹ ድረስ — ግርግሩ ፤ ሩጫው ፤ ከበሮው ፤ ዘፈኑ ፤ እልልታው — ሁሉም ባንድነት ውሉ እንደጠፋ ልቃቂት ተወሳስበው የድግሱን ድምቀትና ታላቅነት ያበስራሉ ። ፊታውራሪ በዚያ መሀል በፈገግታ ተውጠው ይዘዋወራሉ — ሳያርፉ ።

ዝናሽ በአሳቧ ተመሰጣለች ። የደጃች ውቤ ሰፈር ትዝታ — ቀይ ፤ ብጫ ፤ ሰማያዊ ፤ አረንጓዴ ቀለሞች አይን የሚስቡ — ከርቤ ፤ እጣን ፤ ብርጉድ ፤ ሀሬቲ ፤ ሰንደል ፤ ሽቶ ፤ ሎሚ — እቦል ቡና እፍንጫ የሚያደነዝዙ — ቡሉ ታንጐ ፤ ላቪዮሌታ ታንጐ ፤ ቡሉ ዳንዩብ ዎልትዝ ፤ ላኮኩራቻ ሩምባ ፤ ማምቦ ነምበር ፋይቭ — ዲን ማርቲን — ዛቪየር ኩጋት — ቢል ሄሊ — ሊትል ሪቻርድስ — ፋትስዶሚኖ — ኤልቪስ ፕሬስሊ — ናት ኪንግ ኮል — ዶሪስ ዴይ — የሳችሞ ጡሩምባ — ከየቤቱ የሚሰማው ሙዚቃ እንደተጐለጐለ ልቃቂት ውሉ ጠፍቶ ከገነት ፅጌ መናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ደወል በላይ ነግሶ የሰፈሩን ህይወት እውነት ሲያበስር —

«ሀኪም» የቪጥላ ንግግሩን በመቀጠል ድምፁን ከፍ አድርጐ «አመጣጥህ እንደብጤዎችህ ላሞር አላማ መስሎኝ ነበር ። ተማርን የምትሉት ሰዎች የባላገር ኑሮአን ደለምፅ ያስፈራችሁዋል ። ከሩቅ ትሸሹታላችሁ ። አዲስ አበባ የምትንደላቀቁበት ሀብት እንደለምፅ ከምትሸሹት ህዝብ አፍ ተነጥቆ የመጣ መሆኑን አታውቁም ። ከዚህ ጣጣ ውስጥ ገብተህ ራስህን ከመጠን በላይ የምታሰቃይበትና የምታስጨንቅበት ምክንያት አልገባኝም ። ዛሬ ትምህርት ቤት የምትሰራላቸው ልጆች ነገ የፈረንጅ ፊደል መቁጠር ሲችሉ ከቤታቸው ኮብልለው የሚሮጡት ወደ አዲስ አበባ ነው ። ሁለተኛ አይመለሱም ። ቢመለሱም ወላጆቻቸውን እንደቆማጣ የሚፀየፉ ከተማ ነኮች ብዙ አይቻለሁ ። ሱዲ እንደሆነች — እንደሌሎቹ ባላገሮች ሁሉ — ዛሬም ነገም ያው ነች ። ታዲያ ......» ብሎ ሰነገሩ ማሰሪያ ሳያገኝለት ፤ ከዳሱ ወደ ግራ ሲል የሽጉጥ ጥይት ጧ አለ ። በድንጋጤና በትንታ የታፈኑ ሰዎች እልጠፉም ። ግማሹ ከተቀመጠበት ሳይነሳ ሀውልት መስሎ ሲቀር ፤ ተነስተው ለመሮጥ የቃጡም ነበሩ ። አንዱ ሞቅ ያለው ነበር የተኰሰው ። ሽጉጡን እንደያዘ ተነስቶ እየተንጐራደደ «እድሜ ለፊታውራሪ — ለጠጃችን ጌታ፤ ጠጡ — ጮማው ገና — ለዛሬ ያልሆነ ጥይት — ጥይት'ኮ ለጠላት ብቻ አይደለም — ለደስታም ይተኰሳል» አለና እንደገና

ሁለተኛውን ጥይት ጧ አደረገ ። ወጺያውኑ ጓደኞቹና አስተናባሪዎቹ ይዘውት ወደውጭ አወጡት ። ፊታውራሪ ከዚህ ሁኔታ የተረዱት ነገር ቢኖር ተጋባዡ በባዶ ሆድ በደረቅ ጠጅ መጐዳቱን ነበር ። ለምንት ለእት ሆኗል ። ሙሽራው ግን አልመጣም ።

ዝናሽ የአሳብ ጉዞዋን ቀጥላለች — በጠፍ ጨረቃ የጩቤ ስለት ብልጭ ሲል — የሽጉጥ ተኩስ እንደቡሄ ጅራፍ ሲንጣጣ — ግብ ግብ ፤ ትርምስምስ ፤ ኡኡታ ፤ እሪታ — የውቤ በረሀው ጀግና ወድቆ ወሀ ፤ ወሀ ሲል — የፖሊሶች ፊሽካ — ሩጫ ወደግራ ፤ ወደቀኝ — ሙዚቃው ተመልሶ ነፍስ ሲዘራ — ወገብ ቅንጥል ብሎ እግር እስኪዝል ድረስ ዳንኪራው ሲቀጥል — የደርሶ መልስ ፍቅር በየጓዳው ሲደራ — ውስኪ እንደወሀ ሲፈስ — ብር እንደዋዛ ሲመዘዝ — ህይወት ፍጥነቷን ስትጨምር — ጉርምስና ልቡን ያሳበጠው ጐልማሳ ደረቱን ነፍቶ ፤ የኮቱን ኮሌታ እስከ ጆሮው ድረስ ወደላይ ቀልሶ ፤ ተረከዙ መሬት ሳይዝ በጣቱ እየተራመደ የሚገባውንና የሚወጣውን ሲገላምጥ ፤ ሴቶቹን ሲጐንትል ፤ የተናገረችውን በቃሪያ ጥፊ ሲያጋይ — ሌላ ግርግር ፤ ግብ ግብ ፤ ትርምስምስ — ኡኡታ ፤ እሪታ — ጥርስ እንደቀሎ ከመሬት ሆጭ ሲል — ፊሽካ — ሩጫ — ትንሽ ፀጥታ — እንደገና ሙዚቃ ሲደራ ሌሊቱ አልፎ ሰፈሩ እስኪያዛጋ ድረስ —

«ህኪም» የቪጥላ ድንጋጤው ካለፈለት በሁዋላ በረጀሙ ተንፈሰና ነገሩን ለማጠቃለል ያህል «ለስራ ከመሮጥ ማሰብ ማለቱ ነው ። ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል ሲሉ አልሰማህም» አለው ።



ሀዲስ መልስ ለመስጠት አላመነታም ። ንግግሩን በመጀመር «ብዙ ጊዜ በርጋታ ስናስብ ቆይተናል» ካለ በሁዋላ ፤ ቀጥሎ «አሁን ደግሞ የሩጫ ዘመን ነው ። መዳህ ሳንጀምር መሮጥ አለብን......»

«ጠጡ ተጋበዙ ጮማው ይቀጥላል
የፊታውራሪ ግብዣ እንኳን ሱዳንና አገር ይመልሳል»
«አበጀሽ አበጀሽ»

ከጭብጨባውና ከእልልታው በሁዋላ ሀዲስ ይቀጥላል —«አዎን የሩጫ ዘመን ነው ። ከሩጫ ስህተት አይጠፋም ። ሆኖም ስህተት ተፈርቶ ሳይሰራ ቁጭ ማለት አይቻልም ። ለውጥ ለውጥን ያስከትላል ። በዚህ አለም የማይለወጥ ቢኖር የለውጥ ህግ ነው ......»

«ገባ አላሻግር ቢል ክረምት ከበጋ
የጋብቻ ድልድይ ላዩ ተዘረጋ
ገባ ገራም ሆኖ ሲያሻግር ሁሉን
መገን ተካ ቦሮ በአይናለም አየን»
«አበጀሽ አበጀሽ»

ሌላ ጭብጨባ — ሌላ እልልታ ። ጠጁ እንደወሀ ይንቆረቆራል ። ብሩ እንደ ዋዛ ይመዘዛል......ሀዲስ ይቀጥላል — «በሌላ አነጋገር ፤ ለውጥን መቀበል እንጂ መከላከል አይበጅም ። ትንሽ ንፋስ ሆኖ የመጣው ለውጥ ከታፈነ ትንሽ ቆይቶ አውሎ ነፋስ ይሆናል ።...»

«መገን ተካ ቦሮ የሱዴው ባላባት
የጀግኖቹ ጌታ የድኩማን አባት»
«አበጀሽ — አበጀሽ»

ወይዘሮ ዝናሽና የመቶ አለቃ አይን ለአይን ይጋጣሉ ። የምኞት ድባብ ከሆነችበት ከደጃች ውቤ ሰፈር እንዳልነበረች ሆና የወጣችበት ምክንያት መጥቶ ከፊቷ ይደቀናል — የክብር ዘበኛ ሻምበል — የመጀመሪያ ፍቅር— እርሷ ስለወደደችው በሰፈሩ እርሱን የማትመኝ ሴት አልነበረችም — በርሱ የማይቀና ወንድ አልነበረም — እንደቅናትም ፤ እንደእልከም እያደረጋት ሳትወድ በግድ ከሌሎች ወንዶች ተገለለች — ሳታውቀው ገበያዋ እየቀዘቀዘ ሄደ — አሻሻሙጧ እየከዱ ሌላ ሌላ ቤት ገቡ — በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ፤ ከሻምበል አረገዘች — በስባት ወሩዋ አስወረዳት — ቀደም ሲል ሻምበሉም ቤቷን ማዘወተር አቁሞ ነበር — አይ ወንድ አለች — አመቱን ሙሉ ያሸለባት እንቅልፍ አልፎ አይኗን በገለጠችበት ጊዜ ፤ በሰፈሩ የቀድሞ ዝናዋ ደብዝዞ ፤ ስሟ ተረስቶ ፤ የእርሷን ቦታና ዝና የወሰዱ ፤ ፊገግታቸው ብቻ ጠርሙስ ውስኪ ከመደርደሪያ የሚያስወርድ ፤ እሽታቸው ያባትርስት የሚያሸጡ ሴቶች ተፈጥረው ቆዩዋት — አይ እድል— አንዳንዶቹ የቀድሞ አሻሻሙጧ ነበሩ — ፅጌ — ብርሀኔ — አልማዝ — ፋናዬ — ፋንታዬ — ሻምበሉም ተለወጠ ። የወደዳት የሰፈሩ ኮከብ እስከሆነች ብቻ ነበር — ወንድ ሁሉ አሰፍስፎ ለማይመኛት ሴት ደንታ አልነበረውም — ዝነኛዋን ሴት ይዞ ወንዶቹን በማስቀናት የበላይነት ስሜት ካላደረበት ህልውና ባዶ መስላ ነበር የምትታየው — በመጨረሻ ከናካቴው እርግፍ አድርጎ ተዋት — እርሷም ሰፈሩን ጥላ በረረች……ወደታች ……አንዱም ቀና ሳትል ……ከወደቀችበት ሳትነሳ……ቁልቁል……ቁልቁል………
በዚያ ላይ እድሜ ወዘናዋን ሟጥጦ ልጅነቷን ሳታውቀው እየሰረቀ……ከግንባሯ ላይ ድርብ መስመር እየሰራ……



ቁልቁል ስትንዝ……ባለሺላ……ባለግሮሰሪ — ባለመኪና የሆኑትን የዱሮ አሻሻሙጧን አይን እያፈረች ስትሸሽ…… እዩኝ ፤ እዩኝ እንዳባለች ሁሉ ስትደበቅ……እንደኮከብ ከታየችበት ፤ እንደጣኦት ከተመለከችበት ከተማ ስትርቅ ……ስትርቅ የማታ እድሏ ወደመራት ከሱዳ ቦሮ ደረሰች ።

ሀዲስ ይቀጥላል — «ታዲያ ወደፊት ልንራመድ የምንችለው በወሬ — በፍልስፍና — በስራ በማይገለፕ የመፅሀፍ እውቀት አይደለም ። ስረየታችን ስራ ነው ፤ ማህሌት ቆሞ በማደር ፤ ቤተ መቅደስ በማጠን — በፆም በፀሎት ብቻ አይደለም ። ስልጣን ይዞ በመኩፈስ — ስልጣንን እንደእውቀት በመቁጠር — ስልጣንን እንደአላፊነት ሳይሆን እንደመብት በማየት አይደለም ። በስልጣን ሰገነት ላይ ወጥቶ ከህዝብ ትንፋሽ በመራቅ እንደ ኮከብ እያንፀባረቁ በመቀመጥ — የህዝብ እንባ ከማይደርስበት ቦታ — በስራ እንደገና መወለድ ያስፈልጋል ። የዘመኑ ጀግና ሰራተኛው ነው ። ስራ ስሩ ብሎ መለፈፍ ብቻም አይበቃም ። ሰርቶ ማሳየት ያስፈልጋል ። ትችት ብቻውን የአእምሮ መካንነት — የወኔ ማጣትም ምልክት ነው ።»

«ሀኪም» መልስ ለመስጠት አፉን እሞጥሙጦ ነበር ። ምሳ በመቅረቡ አሳቡን ለወጠና «ፊታውራሪ ዛሬስ ብለው ብለው ምን ፈሊጥ አመጡ ፤ ሙሽራው ሳይመጣ ምሳ ያቀርባሉ እንዴ!» አለ ።

ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት ሆኗል ። ፊታውራሪ ተካ ከዳሱ ውስጥ አይታዩም ። ምግቡ ግን በያይነቱ እንደጠጁና አረቄው በገፍ መቅረብ ጀምሯል ። የተጋበዘው ህዝብ በጠጅና ባረቄ ተዳክሞ ተርቧልና ምግቡ በመቅረቡ የተ

ደሰተ ቢሆንም ፤ እየተንሾካሾከ ፤ «ሙሽራው የት ቀረ?» በማለት ይጠያየቅ ነበር ። መምሬ መሀሪ ከተጋባገሩ ህዝብ መሀል ተነስተው ወደጓዳ ገቡ ። የሰአቱን መርፌድ ፤ የሙሽራውን የወሀ ሽታ መሆን ፤ የፊታውራሪን እምነትና ስለክብር ያላቸውን አስተያየት ሀሳብ እያሰበ ያሰላስል ጀመር ......

«መገን ሱጴ ቦሮ — ነጭ ጤፍ እንጀራ አጥቶ በላተኛ
ደንታ ማን ቢኖረው ለኖጳ ሰርገኛ»
«አበጀሽ አበጀሽ አበጀሽ»
«ጓያ የሰበረው የኖጳ ሙሽራ ያው እንዳመሉ
ከገባ ዳገት ላይ ወገቤን እያለ ቆሞ ቀርቷል አሉ»
«አበጀሽ አበጀሽ አበጀሽ»
«የኖጳ ውላጆች እፍታ እርማቸው
የድስት ጥራጊ እስቲ ቢቆያቸው
ያው እንደጥንቱ እንደልማዳቸው»

«አበጀሽ አበጀሽ አበጀሽ...» እልልታው ከመጠን በላይ ይቀልጣል ። አዝማሪዋ ግጥሙን እንድትደግም ትጠየቃለች ። ቶሎሳ ሮጦ ከግንባሯ ላይ ብር ይለጥፋል ።

በገፍ የቀረበው ምግብና መጠጥ ሲበላና ሲጠጣ ቆይቶ ፤ ማእዱ ከፍ ማለት ሲጀምር ፤ የጠብመንጃ ተኩስ እሩምታ ተሰማ ። «ሀይ ሀይ ሀይ — ሎጋው ሽቦ...» የሚል ድምፅ መጀመሪያ እንግደባ ወንዝ ፏፏቴ ከሩቅ ፤ ቀጥሎ ደግሞ ፤ እየቀረበ — እየጐላ ፤ የድምፁ ሀይል እያስደነገጠ— ልብ እያሸበረ — በዚያ ላይ የተኩስ እሩምታ እየጨመረ — እየቀጠለ ይሰማ ጀመር ።



የኖጳውን ሙሽራ ፤ ልጅ ዳኛቸው አያናን የተከተለው ህዝብ ብዛት ጠብመንጃው የመስቀል ችቦ መስሎ ሲታይ ለአድዋ ጦርነት የተሰለፈ እንጂ እድምተኛ መሆኑ ያጠራጥራል ። የፈረሶቹ ኮቴ አቧራውን እያስነሳ ቡናማ ጉም ይፈጥራል ። የሚያስፈራና የሚያሸበርቅ ግርማ ሞገስ የተጐናፀፈው ስፍር ቁጥር የሌለው እድምተኛ መጥቶ ከፊታውራሪ ተካ የውጭ በር ሲደርስ የጠብመንጃው ተኩስ እሩምታ እንደጐልጐታ ነጐድጓድ ወርዶ አባራ ። ዘፈኑና ሆታው ቆመ ። አቧራው ረጋ ። ፀጥ አለ ። የውጭውን በር የሚከፍት ግን አልተገኘም ። ፊታራሪ የውጭውን በር ቀደም ብለው አዘግተውት ነበር ። በሩ የተዘጋው ለወግ የመሰላቸው ሽማግሌዎች ለአይናለም የመጣውን ጥሎሽ በወርቅ የተንቆጠቆጠ ሳንቃ ካባ — ሀር ጨርቅ በያይነቱ — የወርቅ እምባር ፤ ጉትቻ ፤ መስቀልና አልቦ — በመልክ በመልኩ ይዘው አደግድገው እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት ተቀብለው የሚያነጋግራቸው ሰው ይጠባበቁ ጀመር ። ሌሎቹም እድምተኞች ከፈረሶቻቸው ወርደው አደግድገውና ጠብመንጃዎቻቸውን እንደሰልፈኛ ከትከሻቸው ላይ ይዘው ይጠባበቃሉ ። አስር ደቂቃ ። ሀያ ደቂቃ ። ሰላሳ ደቂቃ ። ከውስጥ ዘፈኑና እልልታው ይቀልጣል ። የአዝማሪዋ ድምፅ ከመሲንቆው ምት ጋር በመወዳደር እየወደቀ እየተነሳ አፍአዊውን አካል እያደነዘዘ ውሳጣዊውን ህይወት ይኮረኩራል ። እልፎ እልፎ የእምቢልታው ድምፅ ከዘፈኑ ፤ ከመሲንቆውና ከእልልታው በላይ እየገነነ ስሌቱን ይሰብራል ። በሩን ግን የሚከፍት ሰው አልተገኘም ።

«እኔ ባውራ ፣ ባረመኔ ሺረ ምን ሲቆርጠኝ» አሉ ፊታውራሪ ፣ በቁጣ ፣ እየተንጐራደዱ ። አይኖቻቸው እሳት የሚተፉ መሰለዋል ።

«ሺረ ባማላጇቷ ፣ ድፍን ኢሉባቦር ጉድ ይለናል» አሉ ፣ መምሬ መሀሪ ፣ እየተርበተበቱ ። ከብሳታቸው ወደጐን አዘንብሏል ። ጭራቸውን ይነሰንቧታል ።

«ድፍን ኢሉባቦር ያለውን ይበል ። መላእክት ቢሰለፉ ፣ ከሰማይ መቅሰፍት ቢወርድ ፣ የምደግመው ዳዊት ቢታጠፍብኝ ፣ ያሳነፅኳት ቤተክርስቲያን እዚሀ በእግሯ ብትመጣ እኔ ልጄን — ያውም አንዷን ልጄን — ቀጠሮ ለማያከብር ሰው አልሰጥም — ፍፁም! ቀጠሮ የማያከብር ሰው ከሌላው ሰው ህይወት ጊዜን የሚሰርቅ ሌባ ነው......»

«የጥንቱን ቂም በዚሀ የተቀደሰ ጋብቻ ለመሻርና ፍቅርን ለመመስረት የነበረዎት አላማስ፤ ላንድና ለሁለት ሰአት ተብሎ ገደል ይግባ ነው የሚሉት?»

«ለትንሽ ደቂቃዎች የዘገዩት ቀንጃጂቶችም በሩ ተዘግቶባቸዋል ። የማቴዎስ ወንጌል ምእራፍ ፳፭ ፣ ቁጥር ፩ እስከ ፲፫ ፍርዱን ጨርሶታል ። ደቂቃ እንኳ የዘገዩ በር አይከፈትላቸውም ። እኔም የተፈጠርኩት የመፅሀፉን ቃል እምኜ በስራ ላይ ለማዋል እንጂ ለመሻር አይደለም! ሀይማኖትኽ እንጨት ማለስለስና መሸከም — አዎን — መስቀል መደገን — መገዘት — ቀናት እየቆጠሩ በበአላት ማስጌጥ አይደለም ።»

«በስመ አብ ይበሉ! ጆሮ እያደር የማያሰማው ፣ እድሜ እየሰነበተ የማያሳየው ጉድ የለ ። ባማላጇቷ!» አሉ መምሬ



መሀሪ በድንገት ሰሜታቸው ገንፍሎ ምእመናኑን የሚያሳልሙበትን መስቀል ከጉያቸው እየመዘዙ ።

«መምሩ ፣ ሰይጣን አይሁኑብኝ ፣ ከፊቴ ዞር ይበሉ ። ለየትኛው ቂም—ነገር ተሰልፎ እዩትና ነው የሚከራከሩለት! በኖጲ የታወቀ ጋን ገልባጭና ቤት አውላ ነው ። መቼ አጣሁትና ። ቂም በቀሉን በጋብቻ ለመሻር አስቤ ነበር ። እሱ ግን የባሰ ቂም በቀል ከመፍጠር አይመለስም ። የዛሬውን ቀጠሮ አለማክበሩ ለዚሀ ጥሩ ምልክት ነው ። አላማ የለውም ። አውሬ ነው ። እኔ ባውሬ አንዷን ልጄን አልሰጥም» አሉ ፊታውራሪ ፣ ሰልቱን በሳተና በጐረና ድምፅ ። መምሩ የፊታውራሪን አይኖች ተመለከቱ ። መንፈሳቸው በፍርሀት ተሸበረ ።

ያገር ሽማግሌዎች ተሰብሰበው ባባቶቻቸው አጥንትና በሱጴ አድባር ስም ቢለምኑ ፣ እግር ላይ ቢወድቁ ፣ ቀሳውስት — የስላሴ— የሚካኤል — የእልቄ ማርያም — መስቀል ደግነው ቢማለዱ — ፊታውራሪ ቆመው ያሳነፁዋት የእልቄ ማርያም ታቦት ብትወጣ — በማለዳ ተነስተው ዘወትር የሚደግሙት ዳዊት ከማህደሩ ወጥቶ ፊታቸው ቢዘረጋ ፣ ፊታውራሪ ተካ እኔ ልጄን ላውሬ አልሰጥም — ቃል ቃል ነው ብለው አሻፈረኝ አሉ ።

ከእድምተኞቹ አንዱ ዘለግ ያለው ወጣት ፣ «እኛስ ወግ መሰሎን ነበር ። ለካስ አብዶት ኖሯል! የናንተን አላውቅም — እኔ ግን ውርደት አልቀበልም ። ታዲያስ ጐበዝ!» አለና ጠብመንጃውን አቀባበለ ። ሌሎችም ፣ ሁሉም ባይሆኑ አብዛኞቹ ፣ ጠብመንጃቸውን እያቀባበሉ ወደፊት መጡ ። የፊታውራሪ ተካ አሽከሮች የእድምተኞቹን ዝንባሌ በተመለከቱ ጊዜ ፣ ጠብመንጃቸውን ደግነው በተጠ

ንቀቅ ጥግጥግ ይዘው ቆሙ ። አለም ፀጥ እረጭ አለች ።
ከዳሱ ውስጥ ካሉት ተጋባዦች መካከል አንዳንዶቹ የዋ
ጡት ሙዳ ስጋ ይተናነቃቸው ጀመር ። ዘፈኑና ጭፈራው
ቆምአል ። መሲንቆው ፀጥ ብሏል ። ዳኛቸው በጣም አል
ቤት ፤ እንግባ—እንግባ ፤ እያለ ከስሜቱ ጋር ሲሟገት
ቆየና «እኔ ቆማ ለቀረች ልጅ ግድ የለኝም ። እንሂድ»
አለና በጌጥ ከተሽቆጠቆጠው ቀበጥባጣ በንጋ ፈረሱ
ላይ ወጣ ።

ዘለግ ያለው ወጣት እድምተኛ በንዴት እንደሸሮ
ጡጥ እየገነፈለ «ከባለቤት ያወቀ ቡዳ የለም» አለና ምራ
ቁን ጢቅ አድርጐ ከፈረሱ ላይ ጉብ አለ ። ዳኛቸውና እድም
ተኞቹ አፈሙዛቸውን አዙረው ፊታቸውን ወደገባ መለሱ ።
ከፊታውራሪ ቤት የነበሩት ተጋባዦች ሁሉ ከትከሻቸው
ላይ ከባድ ሸክም የወረደ ይመስል በረጅሙ ተነፈሱ ።
ፊታውራሪ በዳኛቸው ወኔ ማጣት ሌላ ትዝብት አደረ
ባቸው ።

ዳኛቸው ከእድምተኞቹ ጋር በዝምታ እየተከዘ ጎተ
ከገባ ወንዝ አፋፍ ላይ ሲደርስ ከትልቅ ወርካ ስር ሄዶ
ከፈረሱ ወረደ ። እርሱን ተከትለው ሌሎቹም ወረዱ ።
የገባ ወንዝ ኟኟቴ እንደበጋ ዝናም ሸሸሸ...... እያለ ሲወ



ርድ ከሩቅ ይሰማል ። ከገባ በረሀ ወደደጋው የሚነፍሰው
የተበረዘ አየር ሳር ቅጠሉን እየዳሰሰ ያወዛውዛቸዋል ።
ፊት ይዳብሳል — በቀዝቃዛ እጁ ።

ዳኛቸው ለጥቂት ጊዜ ሲያስብ ቆይቶ በቀዘቀዘና
ዝግ ባለ ድምፅ «ወደሱዳ ከኔ ጋር ለመመለስ ፈቃደኞች
የሆናችሁ ከዚሁ ቆዩ ። የማትፈልጉ ብትኖሩ መንገዳች
ሁን ለመቀጠል ትችላላችሁ ። ጓደኝነት ግዴታ አይሁን
ባችሁ» አላቸው ፤ አቀርቅሮ ። የያንዳንዱን እድምተኛ
ስሜት ከፊቱ ላይ ለማንበብ አልፈለገም ።

«ቅድም የት ነበርክ እንግባ ስልህ!» አለው ፤ ዘለግ
ያለው አይነ ፈጣጣ ወጣት ።

ዳኛቸው ከመሬት ላይ የተከለውን ግንባሩን ቀና
አላደረገም ። እቃ እንደጠፋው ሰው መሬት መሬቱን
እያየ «እንሱ ከውስጥ ተዘጋጅተው ሲጠብቁን የኛ ደረት
ገልብጦ መግባት ትርፉ የሳት ራት መሆን ስለመሰለኝ
ነው ። ወኔ አንሶኝ አይደለም! ከብሬን ተገፍፌአለሁ ።
አባቴ ዘወትር እንደሚለው ክብር ከተነካ ህይወት
የለም — ህይወት ያለክብር ባዶ ቀፎ ናት ። ምንም እንኳ
ይህን ጋብቻ የፈለግሁት እኔ ባልሆንም ባዶ እጄን ብመ
ለስ አባቴ ከቤት እንደማያስገባኝ ሁላችሁም ታውቃላ
ችሁ ። ኩሩ ነው ። አዘወትሮ በህይወት በመኖርህ ዶስ ይለ
ኛል ፤ የውርደት ጨርቅ ካመጣህብኝ ግን መቃብርህ ላይ
በመቆም የበለጠ እደሰታለሁ ነው የሚለኝ ። የኔን ፍላ
ጐት ሳይሆን የሱን ክብር ለመጠበቅ እዚሁ የምቀር ከሆ
ነም— ይሁን ። የገባ ዉንዝ ልማዱ ነው — ደም ደም
ሸትቶ ይሆናል» አላቸው ።

ንቀቅ ጥግጥግ ይዘው ቆሙ ። አለም ፀጥ እረጭ አለች ። ከዳሱ ውስጥ ካሉት ተጋባዦች መካከል አንዳንዶቹ የቀ ጡት ሙዳ ስጋ ይተናነቃቸው ጀመር ። ዘፈኑና ጭፈራው ቆምአል ። መሲንቆው ፀጥ ብሏል ። ዳኛቸው በጣም አል ቦት ፤ እንግባ—እንግባ ፤ እያለ ከስሜቱ ጋር ሲሟገት ቆየና «እኔ ቆማ ለቀረች ልጅ ግድ የለኝም ። እንሂድ» አለና በጌጥ ከተሸቆጠቆጠው ቀበጥባጣ ሰንጋ ፈረሱ ላይ ወጣ ።

ዘለግ ያለው ወጣት እድምተኛ በንዴት እንደሽሮ መጥ እየገነፈለ «ከባለቤት ያወቀ ቡዳ የለም» አለና ምራ ቁን ጢቅ አድርጐ ከፈረሱ ላይ ጉብ አለ ። ዳኛቸውና እድም ተኞቹ አፈሙዛቸውን አዙረው ፊታቸውን ወደገባ መለሱ ። ከፊታውራሪ ቤት የነበሩት ተጋባዦች ሁሉ ከትከሻቸው ላይ ከባድ ሸክም የወረደ ይመስል በረጅሙ ተነፈሱ ። ፊታውራሪ በዳኛቸው ወኔ ማጣት ሌላ ትዝብት አደረ ባቸው ።

ዳኛቸው ከእድምተኞቹ ጋር በዝምታ እየተከዘ ተጉዞ ከገባ ወንዝ አፋፍ ላይ ሲደርስ ከትልቅ ወርካ ስር ሄዶ ከፈረሱ ወረደ ። እርሱን ተከትለው ሌሎቹም ወረዱ ። የገባ ወንዝ ፏፏቴ እንደበጋ ዝናም ሽሽሽ...... እያለ ሲወ



ርድ ከሩቅ ይሰማል ። ከገባ በረሀ ወደዱጋው የሚነፍሰው የተበረዘ አየር ሳር ቅጠሉን እየዳሰሰ ያወዛውዛቸዋል ። ፊት ይዳብሳል — በቀዝቃዛ እጁ ።

ዳኛቸው ለጥቂት ጊዜ ሲያስብ ቆይቶ በቀዘቀዘና ዝግ ባለ ድምፅ «ወደሱዱ ከኔ ጋር ለመመለስ ፈቃደኞች የሆናችሁ ከዚሁ ቆዩ ። የማትፈልጉ ብትኖሩ መንገዳች ሁን ለመቀጠል ትችላላችሁ ። ጓደኝነት ግዴታ አይሁን ባችሁ» አላቸው ፤ አቀርቅሮ ። የያንዳንዱን እድምተኛ ስሜት ከፊቱ ላይ ለማንበብ አልፈለገም ።

«ቅድም የት ነበርክ እንግባ ስልህ!» አለው ፤ ዘለግ ያለው አይኑ ፈጣጣ ወጣት ።

ዳኛቸው ከመሬት ላይ የተከለውን ግንባሩን ቀና አላደረገም ። እቃ እንደጠፋው ሰው መሬት መሬቱን እያየ «እኑሱ ከውስጥ ተዘጋጅተው ሲጠብቁን የኛ ደረት ገልብጦ መግባት ትርፉ የሳት ራት መሆን ስለመሰለኝ ነው ። ወኔ አንሶኝ አይደለም! ክብሬን ተገፍፌአለሁ ። አባቴ ዘወትር እንደሚለው ክብር ከተነካ ሀይወት የለም — ሀይወት ያለክብር ባዶ ቀፎ ናት ። ምንም እንኳ ይሆን ጋብቻ የፈለግሁት እኔ ባልሆንም ባዶ እጄን ብመ ለስ አባቴ ከቤት እንደማያስገባኝ ሁላችሁም ታውቃላ ችሁ ። ኩሩ ነው ። አዘወትሮ በሀይወት በመኖርህ ደስ ይለ ኛል ፤ የውርደት ጨርቅ ካመጣህብኝ ግን መቃብርህ ላይ በመቆም የበለጠ እደሰታለሁ ነው የሚለኝ ። የኔን ፍላ ጐት ሳይሆን የሱን ክብር ለመጠበቅ እዚሁ የምቀር ከሆ ነም — ይሁን ። የገባ ወንዝ ልማዱ ነው — ደም ደም ሸትቶ ይሆናል» አላቸው ።

ከዳኛቸው ጋር ወደሱቁ ተመልሰው ሙሽራዋን ለማምጣት ፈቃደኞች የሆኑት ከሌሎች ተለይተው ቆሙ ። ዳኛቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ከመሬት ላይ የተከለውን አይኑን ቀና አደረገ ። ከእርሱ ጋር ለመሄድ የቆረጡት ሰዎች ቁጥር በቂ ሆኖ በማየቱ የልብ ልብ ተሰምቶት የደስ ደስ ያለውን ፈገግታውን አሳየ ። ከሌሎቹ እድምተኞች መካከል የነበሩት እድሜአቸው የገፋ አንድ ሽማግሌ ወደፊት ራመድ ብለው ፤ «ልጆቼ — እኔ ነገሩ አላማረኝም ። የተካ ቤት የተንኰል ቤት ነው ። ርግጥ ሊያዋርደን አስቦ ነው እንጂ ፤ ጊዜ አልፏል ብሎ ሙሽራ ከደጅ የሚመልስ ሰው የለም ። ሆኖም ፤ በጉልበት እንጠቀም ብንል የባሰ ውርደት ላይ እንወድቃለን ። ጥፋት በጥፋት አይታረምም ። ያም ሆኑ ይህ ከቤት ተመልሰን ፊታውራሪ አያናን ብናማክር ይሻላል ። አጥፊን የሚያጠፋ ህግ እያለ ለምን እንቸገራለን? ለምንስ በከንቱ ደም ይፈሰሳል?» አሉ ።

«አባቴን እያወቁት እንዴት እንዲህ ይናገራሉ? ህግ ክብርን አይከስም ብሎ የሚያምን ሰው ነው ። ህግ የሚሉት ፈሊጥ ከመጣ ነው ወኔያችን የሸናው — ክብር የረከሰው — ገባር ባላባቱን ፤ ጭሰኛ ባለመሬቱን ፤ አሽከር ጌታውን መገላመጥ — የጐን ማየት የተጀመረው የሚለውን ሰው ፤ እንዴት አድርጌ ህግ ይካስህ እለዋለሁ? አይንሀን ላፈርነው የሚለኝ ፡ ለምን ከዚያው ፍግም ብለህ አትቀርም ነበር ነው የሚለኝ ። እኔ ያባቴን አሳብ መቼ አጣሁት» አለ ፤ እንደገና ወደመሬት አቀርቅሮ ።

ከእድምተኞቹ አንዱ ስሜቱ ገንፍሎበት «እኛም ብንሆን ከእጃቸው በልተን ጠጥተናል ። አልበላህልኝም ፤ አልጠጣህልኝም ብሎ ለሚያኮርፍ ጌታ እንዴት የውርደት



ጨርቅ ይዘንለት እንገባለን! እሳቸው ዝም ቢሉ ማእዳቸው ይታዘበናል!» አለና ፤ ወደዳኛቸው ዞሮ «ይልቅ ዘዴውን እንመካከርበት» ብሎ አሳሰበ ። ተጨማሪ እድምተኞች ወደሱቁ ለመመለስ ቆርጠው ወደዳኛቸው ገቡ ። ከሽማግሌው ጋር ጥቂቶች ብቻ ቀሩ ። ሆኖም ሽማግሌው ተስፋ አልቆረጡም — «ልጆቼ በኔ ይሁንባችሁ ። ለእድሜዬ ብላችሁ ምክሬን ስሙኝ ። ፍርሀት አይደለም የሚያስለፈልፈኝ ። በዘመኔ ከወፍ የሚቀድም ጀግና እንደነበርኩ ሳታውቁት አትቀሩም ። እኔን ያስፈራኝ የምናደርሰው ጥፋትና በሁዋላ የሚመጣው ፀፀት ነው ። ባማላጅቴ ስሙኝ ። እኛ ከምንፈርድ ህግ ይፍረደን» አሉ ።

«አባቴ በህግ አለኝታ ሄደህ ደካሞችን አፅናና ይለኛል ። የኛ ምኞት ያባቴ ምኞት ነው ። ይልቅ ጊዜ ሳናጠፋ በዘዴው ብንወያይ ይሻላል» አለ ፤ ዳኛቸው በአሳቡ ፀንቶ ።

ፀሀይዋ ፤ ሰማዩን ቀይ ፤ ብጫ ፤ ወርቅ ብጫ ፤ ሀምራዊ ቀለማት እየቀባች የፍም አሎሎ መስላ ከአድማስ ላይ ተንሳፍፋለች ። አእዋፍ ቀዝቃዛውን አየር በክንፎቻቸው እየቀዘፉ መንጋ መንጋ ሆነው ወደየጐጆአቸው — ወደ ገባ በረሀ — ይበርራሉ ። ጨለማው ክንፉን በሰፊው እየዘረጋ ፤ ጥላውን እያጠላ ፤ ሳር ቅጠሉን ፤ ዛፍና ድንጋዩን እያጠቆረ ፤ የሚያስፈራ ቅርፅ እየሰጣቸውና እየዳኸ ሲመጣ የገባ ወንዝ ፏፏቴ እየጐላ ፤ እየቀረበ ይሄድ ጀመር ። «ዘዴው ቀላል ነው» አለ ዳኛቸው — «ሁላችንም መሄድ አያስፈልገንም ። አስራ ሁለት ሰዎች እንበቃለን ። የተቀራችሁት ከዚሁ አድፍጣችሁ ፤ ቀንቶን የተመለስን እንደሆን ፤ የገባን ወንዝ እስክንሻገር ድረስ የሚከታተሉን ሰዎች

ከተገኙ ፣ ተገን በመሆን ትረዱናላችሁ ። ከባዱ ስራ ከዚህ የምትቀሩት ሰዎች ነው ። ወደሱዳ የምንመለሰው ባንድ ነት መሄድ የለብንም ። ከተማ ስንገባ ተነጣጥለን መሆን አለበት ። የእልቂን ወንዝ ተሻግረን አቀበቱ ላይ ካለው ወርካ ስር እንገናኛለን ። አንድ ሰው ከወርካው ስር ፈረሶ ቻችንን እየጠበቀ ይቆየናል ። አንድ ፈረስ ብቻ ይዞን እየተራራቅን ወደቤቱ እንጠጋለን ። የኔን ፈረስ ከያዘው ሰው ሌላ ሶስት ሰዎች ካጥሩ ስር ይቀራሉ ። ሰባታችን በድንገት የተኩስ እሩምታ ከፍተን ወደ ውስጥ እንዘል ቃለን ። ፍፁም አስፈላጊ ካልሆነ ሰው ላይ መተኮስ የለ ብንም ። ደም ለማፍሰሱ የተካ ልጅ ልጃገረድ ከሆነች እንደርስበታለን ። ሁላችንም ድርሻችንን በሚገባ ከፈፀ ምንና ፍጥነት ከተጨመረበት እንደዶራሽ ውሀ በድ ንገት ገብተን ጉድ ልንሰራቸው እንችላለን ። ሄደዋል ብለው ተዝናንተው ስለሚቆዩን ለምንፈፅመው ጥቃት ምቹ ናቸው ። ያልጠረጠረ ተመነጠረ የሚባለው ይኸው ነው ። የጥሪው ሰአት ገና አሁን ደረሰ» አለና ዘሎ ፈረሱ ላይ ወጣ……

መንግሲቱ ለማያት በሩዋን ክፍት አድርጋ የምት ጠብቀው ፣
ጥሪውን አክብሮ የሚደርስ በሰአት ልባም ሙሽራ ነው ።



በሩዋ ከተዘጋ በቃ ተቆለፈ ፣
የሚከፍታት የለም ሰአቱ ካለፈ ።
ያያና ዘመዶች ዛሬ ምን ሊሰሩ ተመልሰው መጡ ፣
ቆይቶ የለም ወይ ፣ ጊዜና ዘመኑ ፣ ከሱዳ ከወጡ ።
ከወጣበቱ ቤት ሬሳ ተመልሶ
ከቶ አይገባም ፣ እርም ነው ጨርሶ ።

ፊታውራሪ ተካ የደብተራ ቅኔ አይጥማቸውም ። ባዶ እውቀት ነው ብለው ስለቅኔ ያላቸውን አስተያየት ይደመድማሉ ። ትርፉ ኮከብ ቆጥሮ ዶሮ ፣ ቅኔ ቆጥሮ ቆሎ ነው ይላሉ አዘውትረው ። ታዲያ ፣ አንድ እበላ ባይ ደብተራ ተነስቶ እያማጠ የተቀኘውን ተራ መወድስ ቅኔ ፊታውራሪ ከቁም ነገር አልቆጠሩለትም ። ይበል ፣ ይበል ያለውም አልነበረም ።

ተጋባዡ ሁሉ ፣ በደረሰው ሁኔታ ተደናግጦ ፣ በግል አሳቡ ተውጦ ፣ የሀዘን ቤት መስሎ ነበር ። እልልታውና ዘፈኑ ፣ ጭፈራውና ከበሮው ፣ እምቢልታውና መሲንቆው ከቆመ ቆይቷል ። ፊታውራሪ ተካ ወዲህና ወዲያ እያሉ የቀዘቀዘውን መንፈስ ነፍስ ዘርተውበት እንደገና ለማደ መቅ ሞክረው ነበር ። አልተሳካላቸውም ።

በቶሎባ ረዳትነት ፊታውራሪ ካንድ ወንበር ላይ ወጥ ተው በቆሙ ጊዜ ተጋባዡ ሁሉ በዝምታ ፊቱን ወደእርሳ ቸው አዞረ ። ደግሞ ምን ሊያደርጉ ይሆን? የሚል ጥያቄ በያንዳንዱ ተጋባዥ ልብ ሳይቀረፅ አልቀረም ።

«በዛሬ ቀን አብረን እንድንጸለት ምኞቴ ነበር ። ያምላክ ፈቃድ ካልተጨመረበት የሰው ምኞት ብቻ አይ በቃም ። ስላሳዘንኳችሁ የበለጠ ሀዘን የተሰማኝ እኔን ነው»

በማለት ፣ ረጋ ብለው ንግግራቸውን ጀመሩ ፦ — «ሁላችሁም በልባችሁ እንደፈረዳችሁብኝ ይሰማኛል ። በክብር የመጣ ሙሽራ ክበር እንዲመለስ ተደርጐ አይታወቅምና ፍረዱብኝ ። የመንግስተ ሰማያት በር ከተዘጋብኝም — ይሁን......

«ሆኖም ፣ ሰው ሲባል ህይወቱን የሚመራበት አንድ እምነት እንዲኖረው ያስፈልጋል ። ለመኖርማ እንስሳትስ ይኖሩ የለም ይል ነበር መክብብ ነፍሱን ይማረውና ። የህልውና ትርጉሙ ግን መኖር ብቻ አይደለም ። አስፈላጊ ከሆነ ፣ የምንሞትለት ፣ ስቃይን በደስታ የምንቀበልለት ፣ የምንጠላበት ፣ ማንኛውንም ፍርድ ፣ መታሰርን ፣ መገረፍን ፣ ስቅላትን ፣ ከማህበራዊ ኑሮ መገለልን ያለማጉረምረም የምንቀበልለት እምነት እንዲኖረን ያስፈልጋል ይል ነበር መክብብ ነፍሱን ይማረውና ። እምነት የሌለው ሰው በድን ነው ። ከእንስሳ አይሻልም ።

«አዎን — እኔም እምነት አለኝ ። ቀጠሮ የማያከብር ሰው ለኔ ሰው አይደለም። የሰው ህይወት በጊዜ የተመጠነ እንደመሆኑ ፣ ጊዜን ማክበር ፣ የሌላውን ሰው ህይወት ማክበር ነው ። የጊዜን ትርጉም አለማወቅ ከእንስሳት ደረጃ መልሶ ዝቅ ያደርገናል ። ሰሎሞን ለሁሉም ጊዜ አለው ብሎ ጽፎታል ። ስለዚህ ስለአድራጐቴ የምጠይቀው ይቅርታ የለኝም ። የእምነት ጉዳይ ነው — ፍረዱኝ!

«የእምነትን ዋጋ ካነሳሁ ዘንድ በመካከላችን የሚገኘውን ፣ ወንድማችንን — ሀዲስ ሳህሌን — ለምሳሌ ሳልጠቅሰው አላልፍም ።



ሀዲስ የፊታውራሪን ንግግር እያዳመጠና እየገመተ ፣ የመንፈስ ፅናታቸውን እያደነቀ ፣ በማሰላሰል ከአሳብ ማካ ውስጥ ገብቶ ነበር ። የስሙ መነሳት ጆሮውን ስለ ጨረፈው ከእንቅልፉ እንደባነነ ሰው ነቅቶ ከአሳቡ ማካ ውስጥ ወጥቶ ወደአካባቢው እውነት ተመለሰ ። አቶ ይርጋና የመቶ አለቃ አሸኔ ተያዩ ።

ሸታዬ የባሰውን ከሀዲስ ላይ አይኖቿን ተከለች ።

«ስለችግር ከማውራት — ብዙ ከመተቸት — ትንሽ ስራ መስራት ጠንካራ እምነትን ይጠይቃል ። በመንፈሳቸው የፀኑ ጠንካራ እምነት ያላቸው አንዳንድ ሰዎች ካልተገኙ መሻሻል ጭራሹን እየራቀ ይሄዳል ። ልጅ ሀዲስ ተጨማሪ የትምህርት ክፍሎች ለመስራት ብቻውን መፍጨርጨር ከጀመረ ቆይቷል ። ደቀመዝሙሮቹ እኛው መሆን አለብን ። ይህ ድግስ የሱ ደቀመዝሙሮች እንድንሆን ካደረገን የበለጠ ቁም ነገር አተረፈ ማለት ነው ። ስራው ለኛ ብቻ ሳይሆን ለልጅ ልጆቻችን የብርሀን ሀውልት ሆኖ ይኖራል ። ያዲሱ ትምህርት ቤት ስራ ከፍጻሜ እንዲደርስ እግዚአብሄርን እንለምነው ። ቸሩ እግዚአብሄር ይርዳን» ብለው ንግግራቸውን እንደፈፀሙ ፣ ተጋባዡ ሁሉ ደስታውን በጭብጨባ ገልጦ ሳያባራ ፣ የተከበሩ እሩምታ ከጭብጨባው በላይ ነግሶ እንደጉልጐታ መብረቅ ያስተጋባ ጀመር ። ከድንጋጤ የተነሳ ከቦታው የተነቃነቀ ሰው አልነበረም ። ዳኛቸው ከስድስት ተከታዮቹ ጋር ፣ ግሎ የሚጤሰውን የጠብመንጃውን አፈ ሙዝ እንደደገነ ዘው ብሎ ገብቶ «ደም ለማፍሰስ አንሻም — ካላስገደዳችሁን ። የጥሪው ሰአት አሁን ነው» አለና ፣ ዳሱን አቋርጦ ከሁለት ተከታዮቹ ጋር ወደጓዳ እንደጥላ ውልብ

ብሎ ገባ ። አይናለምን ካለችበት ጐትቶ ከፊቱ እርሷን ተገን በማድረግ አስቀድሞአት ሲወጣ ፤ አብሮአት የነበሩት ደንገጡሮች በፍርሀት ተለጕመው የኡኡታ ድምፅ ለማሰማት እንኳ ጊዜ አላገኙም ።

አይናለም የመጨረሻ ተስፋዋን ለማረጋገጥ በፍርሀት ደርቀው ያፈጠጡትን አይኖቿን ወደአባቷ መለስ አደረገች ። ፊታውራሪ በንዴትና በእልክ መላው ሰውነታቸው እየተንቀጠቀጠ ወደልጃቸው ሲሄዱ ሲቃጡ ፤ ዳኛቸው የጠብመንጃውን አፈሙዝ ከአይናለም ጀርባ ላይ ደግኖ «ለልጅዎ ህይወት አላፊ እርሶ ነዎት — ሰይጣን አይሁኑብኝ» አላቸው ። ቶሎሳ ባይዛቸው ኖሮ በህይወታቸው ቆርጠው ነበር ። ቶሎሳም ጥርሶቹን እያንቃጨጨ ለመዝለል ሲያቁበቁብ ፤ ዳኛቸው የጠብመንጃውን አፈሙዝ ከቶሎሳ ግንባር ትዩዩ አድርጐ «ትበላኛለህ!» አለው ። ቶሎሳ ካለበት ቦታ ከመርጋት ሌላ ምርጫ አልነበረውም ። የዳኛቸው ተከታዮችም የጠብመንጃቸውን አፈሙዝ ካንዳንድ ተጋባዥ ግንባር ላይ ደግነው ፤ ቃታውን ለመሳብ ተዘጋጅተው ይጠባበቁ ነበር ። የመቶ አለቃ አሸኔ አልተከተሉም ። በነገሩ ለመግባትም አልሞከረም ። ለመፈንደቅም ከጅሎት ነበር ።

ዳኛቸው ፤ አይናለምን አስቀድሞ ፤ ቶሎ ቶሎ እንድትራመድ በጠብመንጃው አፈሙዝ ወደፊት እየገፋት ከዳሱ መውጫ ሲደርስ ፤ «ፊታውራሪ — ለመልሱ የጥሪውን ሰአት እናከብራለን ። ሳደን ወጥቶ ባዶ እጅ መመለስ የኛ ቤቶች ልማድ አይደለም!» ብሎ ወጣ ። እርሱ እንዲወጣ ወደሁዋላ የቀሩትም ተከታዮቹ የጠብመንጃዎቻቸውን አፈሙዝ እንደደገኑ በዝግታ ርምጃ ወደሁዋላቸው በማፈግፈግ አብረውት ወጡ ። የጨለማው ክንፍ ጋረዳቸው ።



«ክንዴ» አሉ ፊታውራሪ ፤ የሚይዙትን የሚጨብጡትን አሳጥቷቸው ።

«ኢጃሌ ወረ ሱጴ» አለ ቶሎሳ ፤ ሰልቱን ስቶ በጐረና ድምፅ ። ሌላ ነገር አላከለበትም ። ጥሪውን የተቀበሉት ጓደኞቹና የፊታውራሪ ተካ አሽከሮች መሳሪያዎቻቸውን ለመፈለግ በየስርቻው ገቡ ። ከመበለጥ ንዴት የተነሳ መሳሪያዎቻቸውን የት እንዳኖሩት የጠፋቸውም ነበሩ ።

«የደጃች ውቤው ሰፈር ግርግር በየት ዞሮ መጣ!» አለች ፤ ዝናሽ ፤ የጥንቱ ፤ የጧቱ በሰካር ልቧ ትዝ ብሏት ። የሰማት አልነበረም — ከሽታዬ ሌላ ። የፊታውራሪ ሰራ ቤቶች ኡኡታ ከመጠን በላይ ነግሶ ጆሮ ይሰነጥቅ ጀመር ።

ዝናሽ ፤ «ጀግናው እንደሆነ የልቡን አድርሶ ሄዷል! ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ — ድሮውኑ በክብር ቢሰጡት ምን ነበረበት?» ስትል ፤ የመቶ አለቃ አሸኔ በጨረፍታ ሰምቷት በቦዙት አይኖቹ ስለጠቀሳት ፤ «እኔ እቴ! የወታደር ፍቅር እርም ይሁን ብያለሁ ። የጠሉት ሲወርስ የፈሩት ሲደርስ—ጥቅሻውን ለሌላ» አለች ።

የቶሎሳ ጓደኞችና የፊታውራሪ አሽከሮች ፤ መሳሪያዎቻቸውን ከየቦታው ፈልገው እስኪሰበሰቡ ድረስ ጥቂት ደቂቃዎች አለፉ ። ሁሉም በንድነት ተንጋግተው ወጡ ። ፈረሶች እስኪያገኙ ድረስ ተጨማሪ ደቂቃዎች ክንፍ አውጥተው በረሩ ።

ፊታውራሪ ተካ ከዳሱ መውጫ ላይ ቆመው ፤ ልጆቹ ተከታትለው በፈረሶቻቸው ከጨለማው አብራክ ሲገቡ እያዩ ደጋግመው ፤ ወይ እርጅና! እያሉ ቢተክዙም

የዳኛቸው ልበሙሉነትና ድፍረቱ እያስገረማቸው የበፊቱን ትዝብታቸውን መልሰው ለመዋጥ እስቸግሮአቸው ፈዝዘው ቀሩ ……

የፊታውራሪ እያናም ድግስ በሰፊው ስለነበረ ግብዣው እጅግ ደምቆ ተጋባዡ ሁሉ እስኪያንገሸግሸው ድረስ ይበላና ይጠጣ ነበር ። ሙሽራው መጥቶ ምን ነው በተገላገልን እያሉ የሚማረሩም ተጋባዦች አልጠፉም ። እንኳን በዚያን ቀን በሌላውም ቀን ቢሆን የፊታውራሪን ግብዣ በቃኝ ብሎ ለመሄድ አይቻልምና ሙሽራው እስኪመጣ ድረስ ከመጠበቅ ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም ።

«ሙሽራው ምን ነው ዘገየ? በጣም መሸቷልኮ» አሉ ከወኪሎቻቸው አንዱ ።

«ያ መናጢ ሰርገኞቹን በዋዛ ይለቃል ብለህ ነው ። የድላችን ቀን ነው ። በትእግስት እንጠብቅ ። ደሞ ምን የሚያስቸኩል ነገር አለ? ይልቅ ህዝቡን ጋብዝልኝ» አሉ ፤ ፊታውራሪ እያና ፤ እንደልማዳቸው እየተንጎራደዱ ።

ህዝብ በብዛት ጠርተው ግብር ሲያገቡ ፤ በባላባትነት ስልጣናቸው ከህግ በላይ ከእግዜር በታች ሆነው ሲኖሩ የነበሩበት ዘመን ከፊታቸው መጥቶ ስለሚደቀንና



ያለፈውን ጊዜ ስለሚያስታውሳቸው የባሰውኑ ይቅበዘበዛሉ ።

«አዎን — እኛም'ኮ ሳናስጠብቀው አልቀረንም ። ሰርገኞቹ አርፍደው ነው ከዚህ የተነሱት» አሉ ፤ ወኪላቸው ።

«ይጠብቅ ። ሴት የወለደ ወንድ ልጅ ሲያገኝ መጠበቅ አለበት ። እኔ የፈራሁት ሌላ ነገር ነው……»

«ምን?»

«ያ ልጄ መጠጥ ካየ ሆዱ አይጨክንም ። እንደልማዱ ጥንቢራው ወጥቶ እንዳያዋርደኝ ፀሎት አድርግልኝ ። ክብር ከተነካ ህይወት የለም!»

ወኪሉ መልስ ከመስጠታቸው በፊት ፤ አንድ ዶብተራ ተነሳና ፤ ድምፁን ከፍ አድርጐ «የተሰማኝን እንድገልጥ ፊታውራሪ ይፍቀዱልኝ» አላቸው ። የፈቀዱለት መሆናቸውን በእጃቸው አመልክተው ፤ ወደፊት እንዲመጣ ጋበዙት ።

ገባን ተሻግሮ ሱጹን ለማስገበር ፤
ህልም ሆኖ የቆየ ጥንትም ምኞት ነበር ።

ምኞት ብቻ ሆኖ አልቀረም ነገሩ ፤
የኖዷ ባላባት ገባን ተሻገሩ ።

ጊዜ መቼ ነበረው ህልሙ ከታለመ ፤
ፍቺ ተገኘለት ራእይ ተፈጸመ ።

ህልምን የሚፈታ በረቂቅ ሀሊና ፤
የሴፍ ዳግማዊ ተወለደ እያና ።

«አይ — የደብተራ ነገር! አታመጡት የለ» አሉና ሀምሳ ብር መዘው ሰጡት ።

«ዳግማዊ ዮሴፍ አለኝ'ኮ» አሉ ደጅ ደጁን እያዩ……

ዳኛቸውና እድምተኞቹ አይናለምን ይዘው ከገባ ወንዝ ወዲህ ካለው ወርካ ስር አድፍጠው ከሚጠብቋቸው ሌሎች እድምተኞች ጋር ከተቀላቀሉ በሁዋላ ነበር ፋታ አግኝተው ትንፋሻቸው ለመመለስ የቻለው ። በዚያ ጨለማ ከዚያ ለመድረስ የአመት ጉዞ መስሎ ታይቷቸው ነበር ። ወደሁዋላ ከመገላመጡና ከፍርሀቱ ይልቅ የጉዞው መርዘም ነበር ልባቸውን ሰቅሎ ትንፋሽ ያሳጣቸው ።

«እንደምን ሆናችሁ!» አሉ ሽማግሌው ተሽቀዳድመው ።

«ሰተት ብለን ገብተን ሰተት ብለን ወጣን» አላቸው ። የዳኛቸው ልብ በእብሪት አብጦ ነበር ።

«ደም ሳትፋሰሱ?»

«ደም ለማፍሰሱ ቤት ስንገባ ያደርሰናል ብዬ አልበረም» አላቸውና ፤ የአይናለምን ወገብ በጠንካራ እጁ ጠበቅ አድርጎ ያዘ ። እንደበረዶ ቀዝቅዛለች ።



አይናለም ፤ ንዴት ይሁን ወይም ፍርሀት የሚያሰቃያት የትኛው እንደሆነ ለይታ ባታውቅም ፤ አዲሱን ትምህርት ቤት አልፈው ሲሄዱ ፤ ከወሰዳችሁኝ ላይቀር ፤ ይህን ትምህርት ቤት አፍርሱልኝ ሳትል በመቅረቷ ውስጥ ውስጡን ይቆጫት ነበር ። የአዲሱ ትምህርት ቤት ጉዳይ ተነስቶ ጭብጨባው ባይበዛና ጥንቃቄ ባይጎድል ኖሮ ፤ መቸ እንደበግ ከቤት ያውም ሰንት ጀግኖች ካሉበት ቤት — ተጎትቼ እወጣ ነበር እያለች ባሰበች ቁጥር አንጀቷ እያረረ ይሄድ ነበር ። ሀዲስ ሳህሌን ጠላችው ።

ዳኛቸው ጆሮዎቹን አንቅቶ ካዳመጠ በሁዋላ ፤ «ገባን እንሻገር!» አለ ። የፈረሶች ኮቴ አይሰማም ። የገባ ወንዝ ፏፏቴ ብቻ ነበር ከጨለማው ፀጥታ በላይ ነግሶ የሚያጉረመርመው ።

የገባን ወንዝ ተሻግረው ወደናዳ የሚወስደውን አቀበት መያያዝ ሲጀምሩ ፤ የአይናለም ተስፋ ልቧ ውስጥ እንደሌሊቱ አየር ቀዘቀዘ ። በንዴት ፤ በፍርሀትና በጥላቻ ስሜት እንደምድረ በዳ ደርቀው የቆዩት አይኖቿ ረጠቡ ። ለመጀመሪያ ጊዜ በዝምታ ሰቅሰቅ ብላ አለቀሰች ። ዳኛቸው የፈረሱን ልጓም አልገታም ።

እድምተኞቹ ዙሪያቸውን የከበባቸውን የጨለማ ግርዶሽ እየጣሱ መንገዳቸውን ሲቀጥሉ ፤ የገባ ወንዝ ፏፏቴ የሚያስተጋባው ድምፅ ወደሁዋላ እየቀረ ፤ እየደከመ ፤ የአይናለምን ተስፋ እያመነመነ ፤ የእድምተኞቹን የድል ማድረግ ስሜት እያጠነከረ ይሄድ ነበር ። አንዳንዱም ቆም ብለው ያዳምጣሉ ። የፈረሶች ኮቴ አይሰማም ።

ከገባ በረሀ ወጥተው ወደናዳ ከሚያመራው ለጥ ያለ ሜዳ ላይ ሲደርሱ ፤ ሙሉ ጨረቃ ከደመና ግርዶሽ

ውስጥ እየተንሳፈፈች ብቅ ብላ ፈገግታዋን ስታሳርፍባቸው ፣ የጠብመንጃዎቻቸው አፈ ሙዞች ፈገግታዋን መልሰው ያንፀባርቁ ነበር። ደመናውና ጨረቃዋ ሲጋጩ፣ ዙሪያቸውን ባህር መስሎ የተዘረጋው ሜዳ በልዩ ልዩ ጥላ እየተዥጎረጎረ ከፊታቸው እየራቀ ፣ ሆኖም ወደ ኖጳ እያቀረባቸው ፣ እያስጠጋቸው ይሄድ ነበር ። ፍጥነት ለመጨመር በመቻላቸው ፍርሀታቸው እየቀነሰ የልብ ልብ እየተሰማቸው ፣ ደስታቸው እየጨመረ የልባቸው ትርታ ከፈረሶቹ ኮቴ ጋር ሲሰምር ፡—

«ሰዎች — ዝምታው ምንድን ነው ? ላሁን ያልሆነ ሎጋው ሽበ ለመቼ ነው!» በማለት ከእድምተኞቹ ውስጥ አንዱ በሁሉም ልብ ውስጥ ያለው ስሜት ንገለጠ ።

«እረ ጉሮሮዬ ደርቋል!» አለ አንዱ ።

«ፍርሀት ይሆናል ያደረቀው» ብሎ መጀመሪያ የተናገረው እድምተኛ መለሰለትና ቀጥሎ፣ «ሆይ ሆይ ሎጋው ሽበ» እያለ ማውረድ ጀመረ ።

ሁሉም ተቀበሉት ። ፈረሶቹ እንኳ ሳይቀሩ ጆሮዎቻቸውን እንቅተው ቀና በማለት ልጓም መዳፈር ጀመሩ ። ዳኛቸው ግን ልቡ አልረጋም ። ምን ቢያስቡ ይሆን የፊታውራሪ ተካ ሰዎች ሳይከተሉን የቀሩት? በማለት ጥርጣሬ ገብቶት ማሰብ ጀመረ። አንዳንዴ ፣ ሁሉም ነገር ሲያስቡት በድንገት ስለሆነ ፣ ፈረሶች አጥተው ይሆናል በማለት ሲፅናና ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ፣ ምን ቢዘገዩ ፣ ጨለማው ከቶ እንደልብ የማያስጋልብ ቢሆን ፣ የመንገዱን ጠባይ ፣ ዳገቱንና ቁልቁለቱን ፣ ጉድባውንና ጠምዛዛውን ፣ ሜዳውንና ገደሉን በሚገባ ስለሚያውቁት ከኛ የበለጠ ፍጥነት ሊኖራቸው ይችላሉ የሚል ጨለማ አሳብ ይመጣበትና እንደገና ጥርጣሬ ይገባዋል ። በተለይ ፣ አይናለምን ከፊት አፈናጥጦ በሚጋልብበት ፍጥነት እንኳን ደህና ፈረስ የያዘ ሰው ይቅርና ፣ መጋጃም የጫነ ቢሆን ሊደርስባቸው የሚችል መሆኑን ባሰበ ቁጥር ጥርጣሬው እየጠነከረ ይሄዳል ። ለጥርጣሬው ፍች የሚሆን ነገር ሲጠፋው የእድምተኞቹ መንፈስና የሎጋው ሽቦ ዘፈን የልብ ልብ ይሰጠዋል ። ሜዳውን አቋርጠው የኖጳ ከለላ ከሆነችው ትንሽ ጫካ ፊት ለፊት ከመንገዱ ግራና ቀኝ ጉልቻ መስለው ከተቀመጡት ኮረብታዎች አጠገብ ሲደርሱ ፣ ዳኛቸው በእድምተኞቹ ዘፈን መፅናናቱን ተወት አድርጎ በሌላ መንገድ ቀድመውን መጥተው አድፍጠው ቢጠብቁንስ? ግን ፣ የገባ ወንዝ ካንድ ድልድይ ሌላ ምን መሻገሪያ አለው!...... እያለ ማሰብ እንደጀመረ በድንገት የተኩስ ዶፍ ወረደ ። እንደቡሄ ጅራፍ ከግራና ከቀኝ የሚንጣጡት ጥይቶች እንደተወርዋሪ ኮከቦች ጨለማውን እየቀደዱ ይጠፉ ነበር ። ፈረሶቹ በርግገው ጨለማውን ለመቧጠጥ የቃጡ ይመስል የፊት እግሮቻቸውን ወደ ሰማይ በሰቀሉ ቁጥር ከኮርቻ ላይ በአፍ ጢማቸው ወደመሬት የሚደፉት እድምተኞች ከመብዛታቸው የተነሳ ኮርቻ ላይ የቀሩት ጥቂቶች ነበሩ ። የፈረሶቻቸውን ልጓም ገተውና ርካብ እንደምንም ቆንጥጠው ከኮርቻ ላይ የቀሩት እድምተኞች ነፍስ ከመግዛታቸው በፊት ቶሎሳና ጓደኞቹ እየጐተቱ ከፈረሶቻቸው ላይ ከመቅፅበት በመጣል መሳሪያዎቻቸውን ይቀሙ ነበር ።

ቶሎሳ ፣ በግራ እጁ አይናለምን አቅፎ ይዞ ፣ በቀኝ እጁ ጠብመንጃውን ፣ መሬት ላይ ከወደቀው ከዳኛቸው

ደረት ላይ ደግኖ ፤ «አሁን ባንድህስ?» አለው በቀዘቀዘ ድምፅ ።

«እሱማ ደግ ነበር ። እኔስ የጠላሁት ባዶ እጄን ያባቴን አይን ማየት ነው» አለው ። አይናለም በፍርሀት የተነሳ ጥርሶቿ እስቲፋጩ ድረስ የምትንቀጠቀጥ ብትሆንም ፤ ተቆጥቶ የነበረው የቶሎሳ ሰውነት ፤ ከዳኛቸው ንግግር በሁዋላ ሲዝናና ተሰማት ። ስሜቱ ስለተነካ አይናለምን ጥሎለት ሊሄድ አሰበ ። አልሆነለትም ። የራሱ ዝና አመዘነበት ።

ቶሎሳና ጓደኞቹ አይናለምን ይዘው ፤ የእድምተኞቹን መሳሪያ ሁሉ አንድ ሳይቀር ዘርፈው ፤ ፈረሶቻቸውን ከፊት እየነዱ ፤ እንደሰርገኛ «ሀይ ሀይ ሀይ ሎጋው ሽቦ» እያሉ ወደገባ ሲያመሩ ፤ ሁሉም ነገር በፍጥነትና በድንገት እንደመሆኑ መጠን ፤ ዳኛቸውና እድምተኞቹ የሆነውን ነገር ለመገመት ጊዜ አላገኙም ። ከመካከላቸው የተጎዳ ሰው አለመኖሩን የተረዱትም ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ነው ።

ዳኛቸው በጀርባው ከተንጋለለበት መሬት አልተነሳም ። በሰፈሩት ቁና መሰፈር ...... የአይናለም ወገብ ...... ያንገቷ መአዛ ...... እንባ ...... ሙርደት ...... የሙርደት ጩርቅ ...... መቃብር ...... አንዳንድ ከዋክብት ለጌጥ ያህል ከተፈናጠቁበት ጥቁር ሰማይ ላይ የተንጣለለችውን ሙሉ ጨረቃ ትኩር ብሎ ለጥቂት ጊዜ በዝምታ ሲመለከት ከቆየ በሁዋላ ብቻውን እንደእብድ ከት ብሎ ሲስቅ ፤ ሳቁን የገደል ማሚቶ እየተቀበለች መልሳ ወደጆሮው ትወረውርለት ነበር — የባለውኑ እያሳቀቸው ......



የጧት ፀሀይ ወርቅማ ጮራዋን ፈንጥቃለች ። ሜዳዎች ፤ እንቁ የተፈጨባቸው አረንጓዴ ወፍጮ መስለው ተንጣልለው ተኝተዋል ። የሱጼ ቦሮ ጉባዎችና ተራሮች ደረቶቻቸውን ለፀሀይ ሰጥተው በታዛቢነት የሱጴን መንደር ወደታች ይመለከታሉ ። በባለሙያ ፈታይ የተነደፉ የሚመስሉ አንዳንድ ጉሞች እንደወንፈል ጥጥ ጉች ጉች ብለው ለጠራው ሰማይ የበለጠ ውበት ይለግሱታል ። ጉሬዛዎች ፤ አንዴ ደረታቸውን ፤ አንዴ ደግሞ ጀርባቸውን ለፀሀይ እየሰጡ ፤ ካንዱ ዛፍ ወደሌላው — በአየር ላይ እየተንሳፈፉ — እየተገለባበጡ — ይዘላሉ ። የሱጼ ቦሮ የማለዳ ተፈጥሮ ውበትን ተጎናፅፋለች ።

ከፀሀይዋ ቀድሞ የተነሳው የሱጴ ቦሮ ህዝብ በየቄዬው ሆኖ ሽቅብ ወደ ፊታውራሪ ተካ ቤት ይመለከታል ። ከየጎጆው እንደወትሮ ጢስ ቡልቅ ቡልቅ አይልም ። እሳት ለማንደድ ጊዜ ያገኘች ሴት የለችም ። የጧት ቡና በየቤቱ ሲወቀጥ አይሰማም ። ከብቶች ሳይሰማሩ በየበረቱ ታጉረው ቀርተዋል ። ሞፈርና ቀንበሩን ይዞ ወደርሻው የወረደ ገበሬ የለም ።

ባንዱ መንደር ፤—

«ገባ ላይ ትልቅ እልቂት ነበር አሉ»

«ስንት ሰው ሞቶ ይሆን?»

«ማን ያውቃል? ብቻ ፣ ነገሩ ክርሮ ወደባስ ጥፋት እንዳያመራ ያስፈራል ። እነዚህ ባላባቶች ያሉበትን ዘመን ረስተዋል መሰለኝ። ምኞታቸው ሁሉ ህግ መሆኑ አሁንም የቀረ አይመስላቸውም ። እነርሱ ለጥቅማቸው ሲሉ በተ ጋጩ ቁጥር ተራው ህዝብ የሚያልቅበት ምክንያት አይ ገባኝም......»

በሌላው መንደር ደግሞ ፡—

«ፊታውራሪ እያና አሽከሮቻቸውን ይዘው ወደሱዲ ማምራት ላይ ናቸው እሉ ። ሰውዬው የዋዛ አይ ደሉም......»

«የኛዎቹስ?»

«የፊታውራሪ ተካ አሽከሮች በሙሉ ተሰብስበዋል ። ከዚህ ቁጭ ብለን እንጠብቃቸው — የለም — እኛም ወደፊት ሄደን እንግጠማቸው — የሚል ክርክር ተነስ ቷል ይባላል ......»

«ሌላ እልቂት ሊሆን ነዋ!»

«በነዚህ ሰዎች የግል ጠብ መአት ሊወርድብን ነው ። ነጭ ኮርማ ጥለን እግዜሩንም መለማመን ከተውን ቆይተናል ። ይባስ ተብሎ ድሮ ነጭ ኮርማ ጥለን እግዚአ በምንልበት ቦታ ላይ ትምህርት ቤት ተሰራ ። እግዜሩም ዝም ብሎናል ። ብንማለደውም አይሰማንም ። በዚህ ላይ ደግሞ ደም መፋሰስ......»

«ምን ያስገርማል! ዱሮም ቢሆን ታላላቅ ሰዎች ሲያስነጥሳቸው በጉንፋን የሚያልቀው ተራው ሰው ነው ። የሱዲ አድባር ትጠብቀን እንጂ»



እንዲሁም በሌሎች መንደሮች ተጋንኖ የሚነገረው ደግሞ ፡—

«ፊታውራሪ ተካ ልጃቸውን ትምህርት ቤት ለማ ያሰራው ሰውዬ ሊሰጡት ነው ይባላል ...»

«እንዴት ተደርጎ? ትናንት ላንዱ ድረው ዛሬ ለሌላ ሰው! እውነትም እንደሚባለው አብደዋል ማለት ነው ። የአባ ጨፌ እርግማን ይሆናል ከዚህ ጉድ ላይ የጣላቸው»

«እሱስ አንድና ሁለት የለውም ። አባ ጨፌ እንዴ ከወጉ ማን ይድናል? ከእርሳቸው ቁጣ ይሰውረን ማለት ነው እንጂ መቸም ስአት አልፎአል ብሎ ሙሽራ ከደጅ የሚመልስ ሰው ጤና ነው ለማለት ያጠራጥራል» ብሎ ርጥብ ሳር ነጭቶ በተነ ።

«ብቻ'ኮ አንዷን ልጃቸውን ከየት እንደመጣ ለማይ ታወቅ አንድ መናጢ ሰው እንዴት አድርገው ይሰጣሉ?»

«አብደታቸው አንድና ሁለት የለውም ስልህ ። የአባ ጨፌ ቁጣ መቸ በዚህ ያበቃል»

አንዳንድ የአገር ሽማግሌዎች ግን ስለፊታውራሪ ተካ በየጊዜው ከአንዳንድ መነኩሴዎች ፣ ባለውቃቢዎች ፣ ቃልቻዎችና ሼሆች የተሰነዘረውን ንግርት አንስተው ነበር የሚወያዩት ።

«ፊታውራሪ ልጃቸውን በዳሩ ማግስት ያርፋሉ ሲባል አልሰማችሁም እንዴ?» አሉ ፣ በከባድ ቡሉኮ የተጀቦኑ ፣ አንድ አዛውንት ።

ሌላው አዛውንት ነገሩ እንዳልጣማቸው ለማሳወቅ ራሳቸውን ነቅንቀው ሲያበቁ ፣ የግራዋ አበባ የመሰለውን ረጅም ጢማቸውን አንድ በአንድ እየጎተቱ ፣ «ስለፊታ

ውራሪ ተካ የሚነገረው ንግርት ስንቱ ተወርቶ! ባለቤታቸው በሞቱ በአርባኛው ቀን እንደ እብድ ያደርጋቸውና የሰው አይን በቁና ይሰፍራሉ ተብሎ ነበር ። ባለቤታቸው ከሞቱ ይሄውና ወደአስራ አምስት አመት ሊሆን ነው ። ከወሎ የመጣ አንድ ሼህ ደግሞ በስድሳ አመታቸው ይሞታሉ ፤ ከዚያ አያልፉም እያለ ርጥብ ሳር እየነጨ ይናገር ነበር ። እርሳቸው ከሞቱ ሱዴ ትጠፋለች የሚሉም ነበሩ ። የሁዋላ ሁዋላ ይህን አለም ትተው ይመንናሉ የሚልም ንግርት አለ ። ይህ ሁሉ ወሬ ነው — እግዜር ያላለው ላይሆን!» አሉ ፤ ወደሰማይ አንጋጠው ......

ሽታዬ ከቤቱ ውስጥ የሚታየውን እቃ እያነሳች አንድ ባንድ ትወረውራለች ። የጢም መላጫው ፤ መስተዋቱ ፤ ሳሁኑ ፤ ሲኒው ፤ ብርጭቆው ፤ ማንቆርቆሪያው ፤ የፊት መታጠቢያው ሳህን — አንድም አይቀራትም ። አልሰበር ያላትን የድንጋይ ብርጭቆ እንደገና አንስታ ትወረውራለች — እንክሽክሹ እስኪወጣ ድረስ ። ፍርክስ ሲል ደስ ይላታል ። የሀዲስን ህይወት የፈረከሰችው እየመሰላት ።

«አብደት ነው ዛሬ?» አላት ፤ ሀዲስ በአድራጐቷ እየተገረመ ።

«እኔ ልጅቷ ነኝ የጊዜ ማሳለፊያ የምሆነው? ...... »

«የምን ጊዜ ማሳለፊያ?»



«ገንዘብ በግራና በቀኝ እንደዋዛ ሲያልፈኝ ...... ወይዘሮ ዝናሽ ተይ አይሆንም ሲሉኝ...... አባ ጨፌም አጣ ክፍልሽ አይደለም ሲሉኝ ......»

«አልገባኝም ። ይልቅ እቃ መሰባበርሽን ትተሽ ብታነጋግሪኝ......»

«ስንት ወር ሙሉ...... ጊዜዬን ላንተ እያጠፋሁ... እኔ ነኝ ርካሽ...... አንተማ ምን ታደርግ ......»

«ምንድነው የምትቀባጥረው? መቀባጠር ሲበዛ ነጃሳ ነው ። ኧረ ተይ እቃዬን አትጨርሽብኝ ባክሽን ?»

«እኔ ሽታዬ ህይወቴ እያለች አንተ እቧን አግብተህ እዚህ አትኖርም ። ሱሚ ነው ። እንዲሁ በከንቱ ለፍቼ የምቀር አይምሰልህ!»

«የምን ጋብቻ ነው እሱ?»

«የእድል በር አልከፈትልኝ ብላኝ ነው እንጂ እኔ ከአይናለም በምን አንሳለሁ!»

«ጥሩ ሀልም አይተሽልኛል ልበል?» ሲላት ጊዜ እቃ መወርወሯን አቁማ ተንደርድራ ሄዳ በረጃጅም ጥፍሮቿ ፊቱን ቧጠጠችው ። እጆቿን ባይዝ ኖሮ አይኖቹን ከማውጣት ወደሁዋላ አትልም ነበር ። ጥፍሮቿ እንደእሳት ቢያንገበግቡትም ሀዲስ አልተናደደም ። ባልገባው ነገር ቀርቶ በግልጽ ግጭትም ቢሆን ሀዲስ ቶሎ አይናደድም ። የዩኒቨርሲቲ ጓደኞቹ «ደመ — በራድ» እያሉ የሚጠሩትም ለዚሁ ነው ። የእርሱ አለመናደድ እርሷን የባሰ ውኑ ስላናደዳት ፤ እጆቿን በመያዛቸው በጥርሶቿ ትነክሰው ጀመር ። የሴቶችን ንዴት ማስታገስ የሚቻለው መምታት ወይም ማፍቀር ነው እያሉ አባቱ ሲናገሩ በል

ጀኖቱ ብዙ ጊዜ ሰምቶ ነበርና ፤ እርሷ ልትነክሰው ስትታገል ፤ አንገቷንና ጉንጮቿን እየሳመ ፤ ጉትቶ ከአልጋው ላይ አጋደማት ። ከላዩዋ ላይ እርሱም ተጋድሞ ከንፈሯን በከንፈሮቹ ይፈልግ ጀመር ። ከንፈሮቻቸው ሲገናኙ በጥርሷ ቀረጠፈችው ። እርሱም መልሶ ቀረጠፋት ። ከንፈሮቻቸው እንደገና ተገናኙ ።

«በሩ አልተዘጋም'ኮ» አለችው ፤ ባጭር ባጭሩ እየተነፈሰች ።

«ምኑ እንዳይመታን ነው?»

«ሰው እንዳይመጣብን»

በሩን አስቀድሞ ባለመዝጋቱ ራሱን እየረገመ ተንስቶ ፤ አንከስ ፤ አንከስ እያለ ሄዶ ከበሩ ሲደርስ ቶሎሳ እየገሰገሰ ሲመጣ በማየቱ ፤ በሩን እንደመዝጋት በጣም ከፈተውና ወደሁዋላ ዞር ብሎ «ምቀኛ መጥቶብናል» አለና እጃቹን ከሱሪው ኪሶች ውስጥ ከትቶ ወደውጭ ወጣ ።

ቶሎሳ እንደሌላው ጊዜ ዱላ ሳይሆን የያዘው ሽጉጥ ታጥቆ ነበር የመጣው ። ጊዜ ሳያጠፋ ፊታውራሪ ተካ በአስቸኳይ እንደሚፈልጉት ነገረው ።

«ምንነው፤ ለደህና?»

«ፊታውራሪ ለክፋት ሰው አይፈልጉም» አለውና ቀጥሎ ፤ «ይህ ትምህርት ቤት ስራው እንዳያልቅ አንዱ አስጠንቀሎበት ነው እንጂ ፤ እንዲሁ በየጊዜው እከል አይገጥመውም ነበር ። እቶ ይርጋን መጠርጠር ከጀርመኩ ቆይቻለሁ......» አለው ።



«ካንጀትህ ነው እንዴ?» አለ ሀዲስ ፤ እየቀለደ ።

«አንተ አታምን ይሆናል — ምክንያቱም እዚህ አላደግህም ። አንዱ ሌላውን በጥንቆላ ፤ በመተት በዶን ቃራ ከማጥፋት አይመለስም ። ቤቱን በምንሰራበት ጊዜ ካንድም ሁለት ጊዜ ምናምንቴ ነገር ከመሰረቱ ላይ ተጥሎ አይቻለሁ ። ሌሎቹ ፈርተው እንዳይቀሩ ብዬ ነው የደበቅሁት» አለው ተኮላትሮ ።

«አንተ አትፈራም ማለት ነው?» አለው ፤ ሀዲስ በነገሩ ተደንቆ እየሳቀ ።

«እንዲህ አይነቱ ነገር እንዳይጠናወተኝ መምሬ መሀሪ ክታብ አስረውልኛል» አለው ።

«አይ የነመምሩ ነገር! የሀይማኖት ነገር አልሆን አላቸው እንጂ ሌላውማ ምን ተስኖአቸው» አለና ፤ አሳቡን ወደሌላ አግጣጫ በማምራት ፤ «ትናንት ማታ የሆነውን ነገር አልነገርከኝም'ኮ» አለው ።

«እነሱ በተጠቀሙበት ዘዴ ተጠቅመን ልጆችን ይዘን ተመለስን ። መንገዱን ስለምናውቀው ገባ ላይ ልንደርስባቸው እንችል ነበር ። ከሁዋላ ብንደርስባቸው ፊት ለፊት መታኮስ ስለማይቀር የሰው ህይወት ይጠፋል ብዬ በማሰብ ፤ መንገዳችንን አሳብረን ፤ የገባ ድልድይ ከመሰራቱ በፊት ጥንት ሲራራ ነጋዴዎች በሚጠቀሙበት በመልካው አድርገን በስንት መከራ ከፈረሶቻችን ጋር እየዋኘን ተሻገርን ። መሻገር አይበለው — በዚያ ጨለማ ። ደግነቱ ወሀው ሀይለኛ አልነበረም ። አፋፍ ላይ ወጥተን ካንድ ምቹ ቦታ ብርድ፦ እያንሰፈሰፈን ጠበቅናቸው ። ቀድመውን ቢሄዱም ኖሮ ቤታቸው ድረስ ለመሄድ ቆር

ጠን ነበር ። እልቂት ይሆናል እንጂ አይናለምን ሳንይዝ ለመመለስ አሳብ አልነበረንም ። ደግነቱ የሱጲ አድባር ከኛ ጋር ነበረች» አለው ።

«በትምህርት ቤቱም ስራ የሱጲ አድባር እንደዚሁ ብትረዳን አሁን ምን ኖሯል!» አለ ሀዲስ በቁም ነገር ። ቀጠለና ፤ «አይናለም አሁን ከቤት ትገኛለች፣ የሚገርም ነው ። ፊታውራሪ ስለቀጠሮ ያላቸው አቋም እስከዚህ ጠንካራ አይመስለኝም ነበር ። መቸም ነገሩን የሰማ ሁሉ አብደዋል ሳይላቸው አልቀረም ። ጋብቻው በዚሁ ፈረሰ ማለት ነው፣ ከዚህ በሁዋላ ምን የሚሆን ይመስልሀል?» አለ ፤ ሀዲስ ። ትናንት በሰርጉ ወቅት ተዳፍኖ የነበረው አሳቡ እንደገና ማንሰራራት ጀመረ ። የአይናለም ሁኔታ ከፊቱ መጥቶ ተደቀነ ።

ቶሎሳ ትክ ብሎ እየተመለከተው «ከእንግዲህ የሚሆነውን እኔ ምን አውቃለሁ ። ይዘዋት ቢሄዱ ኖሮ ለኔ የሞት ሞት ይሆን ነበር ። ባዶ እጄን አልመለስም ነበር ። እነሱም ባይገድሉኝ እኔ ራሴን እገድል ነበር ። የማንን እህት ማን ቀምቶ ይሄዳል!» አለው ።

«ለምን ይሆን የፈለጉኝ?»

«እኔ ምንአውቄ ። ስለትምህርት ቤቱ ይሆናላ ። ሰርጉ ካለፈ በሁዋላ አይዞህ ብለውህ አልነበረም ።»

ተያይዘው ወደፊታውራሪ ቤት መንገዳቸውን ቀጠሉ ። ሳንዳፍታ ፊታውራሪ ለምን በጧት እንደፈለጉት ሀዲስ አስቦ ሊደርስበት ሞከረ ። ነገር ግን የተጨበጠ አሳብ አላገኘም ። ቶሎሳም ሊረዳው አልቻለም ። ምስጢሩ ሰላ ልትገለጠለት መንፈሱ በድንገት ተሸበረ ። የጧት ፀሀይ ፤ ፊቱን በተበረዘ ቀዝቃዛ እጇ የሚዳስሰው እየርና ከዙሪ



ያው የተነጠፈው የተፈጥሮ ውበት የተሸበረውን መንፈሱን ለማረጋጋት አልቻሉም ። ስለሽታዬና ፤ በጥፍሮቿ ፊቱ ላይ ስለተወችው ምልክት ሳንዳፍታ አሰበ ። የሰይጣን ቁራጭ ብሎ በልቡ መራገም ሲጀምር ፤ ቶሎሳ ጉሮሮውን አሳላና «የትምህርት ቤቱ ስራ ሲያልቅ ምን ለማድረግ ታስባለህ?» ብሎ ጠየቀው ።

«ወይ. አዲስ አበባ ተመልሼ አቋርጬ የመጣሁትን ትምህርት እቀጥላለሁ ። ዱሮም የመጣሁት ላንድ አመት ነው ። ሌላ አሳብ የለኝም» አለና መለሰለት ።

«የትምህርት ቤቱ ዳሬክተር ቢያደርጉህስ?»

ሀዲስ የምፀት ፈገግታ አሳየውና ፤ «ዲሬክተር ቢያደርጉኝማ ሌሎች ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎች በመስራት ትምህርት ቤቱ ፤ በደቡብ በምእራብ ኢትዮጵያ ከሚገኙት ትምህርት ቤቶች የበለጠ እንዲሆን አደርገው ነበር ። ብሀንፃ ብዛት ብቻ ማለቴ አይደለም ፤ በትምህርት አሰጣጥም ጭምር — የሚቀጥለውን ትውልድ ኮትኩቶ ማሳደግ የሚቻለው በክፍል በሚሰጠው ትምህርት ብቻ አይደለም ። የወደፊቱ ትውልድ አናጢዎች ገንቢዎች ኮትኳቾች ነን በማለት ራሳቸውን አታልለው ሌሎችንም የሚያሳስቱ አስተማሪዎች ብዙ ናቸው ። አብዛኞቹ አስተማሪዎች ስራ ለማግኘት እንጂ ለሙያው ደንታ የላቸውም ። እንደገረድ ትንሽ የደሞዝ ጭማሪ ሲያገኙ መረማመጃ አድርገውት ይሄዳሉ ። ታዲያ እነዚህ ሰዎች የነገው ትውልድ ገንቢዎች ነን በማለት በሙሉ አንደበት መናገር አይገባቸውም ። በሙያው የጠነከረ እምነት ያላቸውም ቢሆኑ የነገው ትውልድ ገንቢዎች ነን ለማለት አይችሉም ። መሠረት የሌለው አባባል ነው ። የነገው ትውልድ

በአስተማሪዎች ወይም በትምህርት ቤቶች ጥረት ብቻ የሚገነባ አይደለም ።

«አንድ ተማሪ በትምህርት ቤት በቀን የሚያሳልፈው ጊዜ ግፋ ቢል ከስምንት ሰአት አይበልጥም ። የበለጠውን ጊዜ የሚያሳልፈው ከትምህርት ቤት ውጭ ነው — ከወላጆች ከጓደኞች ጋር በፊትም ሆነ አሁን ፤ ወይም ወደፊት ። አስተማሪዎች የነገው ትውልድ ገንቢዎች ነን ቢሉ መመፃደቅ ይሆናል ። ለዚህ ነው ፤ የነገውን ትውልድ መገንባት የሚቻለው በክፍል በሚሰጠው ትምህርት ብቻ አይደለም ያልኩት ። በተለይ ትምህርት ቤቶች ትንንሽ ደሴቶች ሆነው ሲገኙ ከሚሰጡት ጥቅም ጉዳታቸው ሊያመዝንና የአሳብ ዲቃላዎች መፈልፈያ ቦታዎች ሊሆኑ ይችላሉ ። የተማረው ወገንና የተቀረው ህዝብ በኑሮ ባሳብ በእምነትና በሁኔታ የተራራቀው በትምህርት አሰጣጥ አቋም መዛባት ነው ። እኔ የአንድ ትምህርት ቤት ዲሬክተር ብሆን በመጀመሪያ ደረጃ የምወስደው ርምጃ ትምህርት ቤቱን የተማሪዎች ብቻ ሳይሆን የህብረተሰቡ መገናኛና መማሪያ ቦታ ነበር የማደርገው ። በተለይ በኛ ዘመን ትምህርት ቤቶች የልጆች ብቻ ሳይሆኑ በመጠኑ የወላጆችም ጭምር መሆን አለባቸው ። ትምህርት ቤት ህይወትን በሙሉ የሚነካ አዲስ ቤተ እግዚአብሄር እንዲሆን ያስፈልጋል ። ኢትዮጵያዊነት እንጂ ጎሳና ሀይማኖት ባዲሱ ቤተ መቅደስ ቦታ አይኖራቸውም ። የሚሰራ እጅ የሚመለክበት ቤተ መቅደስ ነበር የማደርገው ። ዲሬክተር ብሆን ኖሮ ምኞቴ ይህ ነበር» አለውና በረጅሙ ተነፈሰ ።

«አሳብህ ያጓጓል ። ታዲያ ለምን አትሆንም?» ብሎ ጠየቀው ።



«አላሰብኩበትም ። የመጣሁት ላንድ ዓመት ነው…»

«ላንድ አመት ከሆነ ይህ ሁሉ ድካም ታዲያ ምን ያደርጋል?»

«ሰው ለሚያደርገው ነገር ሁሉ ምክንያት ሊሰጥ አይችልም ። ግን አብዛኛውን ጊዜ ሀሊና ወደመራን መንገድ መሄድ የግድ ይኖርብናል ። ማድረግ ወይም መሞት — የኑሮ አላማዬ ይህ መሆኑ በመጠኑም ቢሆን የተከሰተልኝ እዚህ ከመጣሁ ወዲህ ነው — እና ፤ እዚህ መምጣቴ በጅቶኛል» አለው ፈገግ ብሎ ። ቶሎሳ ሀዲስ የተናገረውን አልሰማም ። በራሱ አሳብ ተውጦ ነበር……

ከፊታውራሪ ተካ ቤት ሲደርስ መሳሪያ የያዙ በርከት ያሉ ሰዎች በተጠንቀቅ ቆመው በማየቱ የትናንቱ ሁኔታ እንደገና መጥቶ ከአእምሮው ውስጥ ተቀረፀ ። በአካባቢው የነበረው ከባድ የስጋት መንፈስ እርሱንም ተጫነው ። በያንዳንዱ ሰው ፊት ላይ የጥርጣሬ ምልክት ጉልቶ ይታይ ነበር ። ስለትምህርት ቤቱ አሰበ — ስለወደፊት እድሉ ። ስለራሱም አሰበ ። በዚያን ሰአት ከፊታውራሪ ተካ ጋር የሚያገናኘውን ጉዳይ ግን ለይቶ ለማወቅ አልቻለም ።

ከቤት ሲገባ ፊታውራሪ ተካ ከሁለት ዘር ዝናር ጋር ፈሻሌ ሽጉጣቸውን ታጥቀው ከድንክ አልጋቸው ላይ ተቀምጠው አገኛቸው ። አይናለም ከትከሻዎቿ ላይ የአንገት ልብስ ጣል አድርጋ ፤ ከአጠገባቸው ቁጭ ብላ ነበር ። አይኖቹ ተወርውረው አረፉባት ። ተነስታ ወደጓዳ ስትገባ በአይኖቹ ሊከተላት ፈራ ። ግን ርምጃዎቿን አንድ ባንድ በአይነ ህሊናው እየቀረፀ ይከተል ነበር ።

ፊታውራሪ ከድንክ አልጋቸው ላይ ተመቻችተው
ተቀመጡና «ለብርቱ ጉዳይ ነበር የፈለግሁህ» «አሉትና
ትኩር ብለው እየተመለከቱ «ለብርቱ ጉዳይ የሚፈለግ
ብርቱ ሰው ነው ። መንፈስ ጠንካራ መሆንክን ራሴ ዶር
ሼበታለሁ ። አባትህ በህፃንነትህ ፤ እናትህ ደግሞ አሁን
ካደግህ በሁዋላ መሞታቸውን ቶሎሳ ነግሮኛል ። ብዙ ምስ
ጢር ታካፍለዋለህ መሰለኝ! ጥሩ ወንድም ነው ። ያሳን
ዳች ድጋፍ በገዛ ራስህ ተጣጥረህ መማርህ አንድ ቁም
ነገር ነው ። ከእውቀት የበለጠ ሀብት የለም ይል ነበር
መክብብ ነፍሱን ይማረውና ። ዋጋ ያለውን ሀብት ለመ
ገብየት ችለሀል ። ትምህርት ቤት ለመመለስም ታስባ
ለህ አሉ ። የትምህርት መጨረሻ የለውም ይል ነበር መክ
ብብ ፤ አሁንም ነፍሱን ይማረውና ። ቁም ነገሩ ብዙ መማር
አይደለም ። ዋናው ቁም ነገር የተማሯትን ስራ ላይ ማዋል
ነው ። ብቻ ቤተክርስቲያን ስትስም እስካሁን ባለማየቴ
ቅር ብሎኛል» አሉት ።

«የኔ ቤተክርስቲያን ልቤ ውስጥ ስለሆነ ነው» አላ
ቸው ።

«እሱ ደሞ ምን የሚሉት ሀይማኖት ነው?» ብለው
ጠየቁት ።

«የግል እምነት ነው» አለና — «በሰዎችና በመላእ
ክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮህ ናስ
ወይም እንደሚንሿሿ ፀናፅል ሆኛለሁ ። ትንቢትም
ቢኖረኝ ፤ ምስጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ ፤
ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፤
ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ ። ድሆችም ልመግብ ያለኝን
ሁሉ ባካፍል ፤ ስጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ



ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም» ብሎ ከቆሮን
ቶስ አንድ ምእራፍ ፲፫ ቁጥር ፩ እስከ ፫ ድረስ ጠቀሰላቸው ።
በዚያው አላበቃም ። ቀጥሎም ፤ «ፍቅር ሀይማ
ኖት ፤ ዘርና ቀለም የማይለይ ፤ ክርስቲያን ፤ እስላም ፤
አማራ ፤ ጋላ ፤ ትግሬ — ነጭ ጥቁር — ሀብታም ድሀ —
ትልቅ ትንሽ — የማይል — ሁሉን በእኩልነት ደረጃ
የሚመለከት ከፍተኛ ሀይማኖት ነው ። ክርስቶስም ቢሆን
በመሰረቱ በመስቀል ላይ ተቸንክረ የሚባለው ስለፍቅር ፤
በፍቅር ለፍቅር ነው ። የመፅሀፍ ቅዱስ መሰረቱ ይሄው
ነው ። እግዜር ይቀጣናል ፤ ይክሰናል በሚል ስሜት ሳን
ወድ በፍርሀት የምንከተለው እምነት ከንቱ ነው ። ተራሮ
ችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፤ ፍቅር
ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ ። ፍቅር እግዜር ፤ እግዜር ፍቅር
ነው ። ከዚህ የእምነት ጫፍ ላይ የሚያደርሰው መሰላል ፤
ክርስቲያን ፤ እስላም ፤ ቡዲዝም ፤ ሺንቶይዝም — አይደ
ለም ። ፍቅር ነው ። የፍቅር መሰላሉ እውቀት — የእውቀት
መሰረቱ ደግሞ ትምህርት ቤት ነው ። ትምህርት ቤት
አዲሱ ቤተእግዜር ነው የምለው ለዚሁ ነው ። ያለፍቅር
ህይወት ትርጉም የላትም ። ህልውና ባዶ ፤ የሚጮህ ናስ
ወይም የሚንሿሿ ፅናፅል ትሆናለች — ያለፍቅር ። ብሄ
ራዊ አንድነት ትርጉም የለውም — ያለፍቅር ። አለም
አቀፍ ግንኙነት ዱር አራዊቶች ከሚተዳደሩበት ህግ አያ
ልፍም — ያለፍቅር ። ፍቅር እግዜር ነው ። ፍቅርን በልባ
ችን በምንጨብጥበት ወቅት እያንዳንዳችን እግዜር እንሆ
ናለን በየቤታችን ። እዩ ፊታውራሪ — ድንቁርናችን ለያ
ይቶ ባይከፋፍለን ኖሮ በአለም ላይ ያሉት ልዩ ልዩ እም
ነቶች ሁሉ የሚያስተምሩት የፍቅርን ታላቅነት ነው ።
የሰው ልጆች አንድነትና እኩልነት በፍቅር ለመመስረ

ትና ለመግንባት ከትምህርት ቤቶች የተሻለ ቦታ የለም ። ባሁኑ ጊዜ ግን በየትምህርት ቤቱ ሙያውን በማይወዱ ሰዎች የሚሰጠው ትምህርት ዱላ እንደማቀበል የሚቆጠር ነው »አላቸው ።

«ከማቴዎስ ወንጌል ምእራፍ ፳፭ ቁጥር ፲ እስከ ፲፫ ያለውን ጥቅስ በዚህ አሳብ ላይ ብታክልበት መልካም ነበር ። ጊዜ ወርቅ መሆኑን ክርስቶስ በምሳሌ አስተምሮናል» አሉት ።

«ፍቅርን በልቡ የጨበጠ ሰው ቀጠሮ አያፈርስም ። አዲሱ መሲህ ፍቅርን በልቡ የጨበጠ ሰው ነው» አለና ፈገግ ብሎ መለሰላቸው ።

«ርግጥ ነው ። ከፍቅር የበለጠ ነገር የለም ። እግዜር ለፍቅር አንዱን ልጁን አሳልፎ ሰጠ ። ልጁም ለፍቅር ቤዛ ሆነ ። በዚያ ፍቅር ደህንነትን አገኘን ። እኔም አንዷን ልጄን ልሰጥህ ነው የጠራሁህ ። ታላቅ ጥሪ ነው» አሉት ።

ነገሩ ግራ ሆኖበት ሰምቶ እንዳልሰማ ሰው ዝም አለ ። በመጀመሪያ ቃላቸውን ለማመን አልቻለም ። አሳቡ እንደመብረቅ ነበር መጥቶ በድንገት የመታው ። ጆሮ ዎቹንም አላመነም ። በሀይል የሚመታውን የልቡን ትርታ እንዳይሰሙበት ከአጠገባቸው ለመራቅ አሰበ ።

«ምንነው ዝም አልክ? ቀጠሮ የሚያከብር ሰው ጨዋ ነው ብዬ ነው ። ስመለከትህ አውሬነት ያለብህ አይመስለኝም ። ያንዷ ልጄ እድል ካንተ ጋር የተያያዘ መስሎ ስለ ታየኝ ነው ። የተማርክ ነህ ። እኔ እንግዲህ እንደምታየኝ አርጅቻለሁ ። ልጄንም ፤ ሀብቴንም ፤ ስሜንም ለተማረ ሰው ማስረከብ መልካም ስራ ስለመሰለኝ ነው ።



ባላባትነት ከእንግዲህ ዋጋ የለውም ። አንተን ያስመረጠኝ ምን እንደሆነ አላውቅም ። የተማሩ ሰዎች ከዚህ በፊት አጋጥመውኛል። ይሁን እንጂ አይኔና ልቤ አላረፈባቸውም ። የግዜር ተአምር ነው» አሉት ፤ አይን አይኑን እየተመለከቱ ።

ቀዝቃዛ ላብ ጀርባውን ለሁለት ከፍሎ ወደታች ሲወርድ ተሰማው ። አይኖቻቸው ወደውስጥ ዘልቀው የሚመለከቱት መሰለው ። እየተንቀጠቀጠ «እንዲህ አይነቱ አጋጣሚ አሁን ምን ይባላል!» አለ ፤ እርሳቸውን ሳይሆን ራሱን በራሱ በትካዜ መልክ እየጠየቀ ።

«የቱ አጋጣሚ?» አሉት ነገሩ እያደናገራቸው ።

«የመጣሁት ባንድ አመት ላጭር አላማ...»

«እንኳን ባንድ አመት ባንድ ቀንም የሰው ህይወት አግጣጫ ለደግም ሆነ ለክፉ ሊለወጥ ይችላል ። የእህልና ወሀ ነገር ነው — የእርባ ቀን እድል......» አሉት ።

ትምህርት ቤቱ እንደምኞቱ ተስፋፍቶ በምእራብ ኢትዮጵያ ከሚገኙት ትምህርት ቤቶች ልቆ የአዳዲስ አሳቦች ምንጭ ፤ የወላጆችና የልጆች መገናኛ ገበታ ፤ የፍቅር ምኩራብ ፤ የአንድነት መሰረት ፤ የእውቀት ሰፈ ገበያ ሆኖ ሳንዳፍታ በአይነ ሀሊናው ታየው ።

«ለኑሮአችሁም ቢሆን እግዜር ምስጋና ይግባውና የሚቸግራችሁ ነገር የለም......»

የፊታውራሪ ድምፅ ከሩቅ ነበር የሚሰማው ።

ከበስተጀርባ ፤ ጉሬዛዎች ከሚፈነጩበት ዛፎች ስር የፊታውራሪ ቡና ተክል ለአይን እስኪታክት አረንጓዴ ብርድልብስ መስሎ ተነጥፎ በአይነ ሀሊናው ታየው ።

ከበስተምስራቅ የእልቂ ወንዝ መሀል ለመሀል ሰንጥቆት የሚሄደው የፊታውራሪ እርሻ መሬት ተጉዞ ፤ ተጉዞ ከአድማሱ ጋር ሲጋጭ ታየው ። ከበስተደቡብ የግራር ዛፎች ግዙፍ ጃንጥላዎች መስለው አልፎ አልፎ ከሚታዩበት አውላላ ሜዳ የፊታውራሪ የጋማና የቀንድ ከብቶች እንደ ጉንዳን ሲተራመሱ ታዩት ። ማሩ በማድጋ ፤ እህሉ በጎተራ ፤ ብሩ በገፍ — ይህ ሁሉ ምድራዊ ኀብት ያንተ ነው የሚል ድምፅ ከጆሮዎቹ ውስጥ አስተጋባ — ክርስቶስን በገዳመ — ቆሮንቶስ የተፈታተነው ሰይጣን ይመስል ። እንዲያ ሞልቶ ከተረፈ ሀብት ሁሉ ጥቂቱ እንኳ ለትምህርት ቤቱ ቢውል ሰንቱን ችግር ባቃለለ ነበር ብሎ አሰበ ። የተስፋ ጮራ ከፊቱ ላይ ነገሰ ።

«አይናለምም እንዳንተ የፈረንጆችን ትምህርት አትቁጠር እንጂ ፤ ያገራችንን ትምህርት በሚገባ ታውቃለች ። በተፈጥሮ ብልህ ናት……»

አይናለም ፅርሀ አርያም መስላ ፤ ከትምህርት ቤቱ ጣሪያ ላይ እርሱ ከወደቀበት ወደታች እጆቿን ስትዘረጋለት ፤ ዘወትር ጧት አይኖቹ እስኪፈዙ ድረስ ትምህርት ቤቱን በሚመለከትበት ወቅት ከቤቱ ውስጥ እንደመና ፍስት ብቅ ብላ ስታቅፈው በአሳቡ መጥቶ እንደገና ከፊቱ ተደቀነ ። ትምህርት ቤቱን ከእርሷ ፤ እርሷን ከትምህርት ቤቱ ለይቶ ማሰብ ከተወ ብዙ ወራት አልፈዋል ። ሁለቱም በአንድነት በአእምሮው ውስጥ በየጊዜው እያደጉ ነበር የሚሄዱት ። አይናለምን ከትምህርት ቤቱ ለይቶ የሚያይበት አይን የለውም ። በቅዠት አለም ውስጥ የሚንሳፈፍ መሰለው ። ጆሮዎቹ የሚሰሙትን ለማመን አልቻለም ። ከተቀመጠበት ተነስቶ ከእግራቸው ላይ ወደቀ ።



«ተባረክ ። ብሩክ ሁን» ብለው መረቁት ።

«ብቻ ጠቡ ሳይበርድ'ኮ……»

«ስለጠቡ አታስብ ። እግዜር የፈቀደውን የሚሽር የለም» አሉና አደፋፈሩት ። ፊታውራሪ አይናለምን በአስቸኳይ ሊስጡት የተነሳሱበት ምክንያት ፤ በታላላቅ ባለስልጣኖች ተፅእኖም ሆነ በአገር ሽማግሌዎች አማላጅነት ላይ አስቀድመው በር ለመዝጋት ነበር ። እንዳጋጣሚ አይናቸው ያረፈበትና ልባቸው የወደደው እንደ ሀዲስ ያለ አማች በማግኘታቸው አላመነቱም ። በተጨማሪ ፤ ልጃቸውን ለሌላ ከሰጡ በሁዋላ የሚደርስባቸው ነገር ቢኖር ካሳ መክፈል ብቻ ሲሆን ፤ ለዚያውም ፊታውራሪ አያና ኩሩ ሰው በመሆናቸው ህይወታቸው እያለች ካሳ የማይቀበሉ መሆናቸውን ጭምር በማመዛዘን ነበር ።

መምሬ መሀሪ በችኮላ ተንደርድረው ገብተው «የምስራች!» ብለው ጮሁ ።

«ምስር ይብሉ» አሉ ፊታውራሪ በፈገግታ ፤ ሀዲስም ምስራቹ ምን እንደሆነ ለመስማት ጉጉት አድሮበት አይኖቹን በሁለቱ ሰዎች መካከል ያንከራትት ጀመር ።

«ጭንቀቱ ሁሉ አለፈ ። ፊታውራሪ አያና ማለዳ በድንገት አርፈዋል……»

«እዬ መምሩ — የምስራች አሉኝ! ምንኛ ክፉ ቢያደርጉኝ ነው? የአያናን ሞት'ኮ ተመኝቼ አላውቅም ። ከመጥፎዎቹ ወዳጆቼ ፍቅር ይልቅ የርሱ ክፉ ጠላትነት ይሻለኝ ነበር ። ያበረታታኝ ነበር ። እንድኖር ይገፋፋኝ ነበር ። ብታሪክ የተሳሰርን ቤተሰቦች ነበርን — ገመዱ ከዚህ ላይ አበቃ!» አሉና ከተቀመጡበት ተነስተው እየ

ተንጐራደዱ «የታሪክ ጓዴ......የጠላት ወዳጇ — የገባ ወንዝ ጓዴ — ሞትክን ማን ተመኘው ጠላትክነትን እንጂ — ጓዴ ጓዴ» እያሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ሲያለቅሱ ፤ ቤት ውስጥ የነበሩትም ሆነ ውጭ የቆሙት ሰዎች ሁሉ ፤ ማን እንደሞተ ባያውቁም ፤ የፊታውራሪን ሙሾ ተቀብለው «ጌታዬ ጌታዬ — ደጉ ጌታዬ — የጠጁ ጌታ — የጮማዬ ጌታ — » እያሉ በመቀባበል ልቅሶአ ቸውን ያቀልጡት ጀመር ። ልቅሶው በሱዴ ቦሮ ባንዳፍታ አስተጋባ ። የፊታውራሪ ተካ ግቢ በለቀስተኞች ተጥለ ቀለቀ ።

«ደጉ የኛ ጌታ መልካም ደግሰህ»

«ዋይ — ዋይ»

«አንተው ተሞሽረህ ምንነው መሄድህ?»

«ውይ — ውይ — ውይ — ውይ»

«ጠጅ ቢያምረኝ ከእንግዲህ ማን አለኝ ?»

«ዋይ — ዋይ»

«ጮማ ቢያምረኝ ከእንግዲህ ማን አለኝ!»

«ዋይ — ዋይ»

«የጌታዬ እጅ ካሁኑ ናፈቀኝ»

«ውይ — ውይ — ውይ»

የሞቱት ፊታውራሪ ተካ እንዳልሆኑ የታወቀው ከጥ ቂት ዋይታ በሁዋላ ነበር ። ሀዲስ ግራ ገብቶት አይኖቹን ከማቁለጭለጭ ሌላ የሚያደርገው ነገር ጠፍቶት ነበር ። የፊታውራሪ ልቅሶ አጉል መመፃደቅ መስሎ ነበር የታ



የው ። ፊታውራሪ አይኖቻቸውን በነጠላቸው ጠራረጉና ወደ መምሬ መሀሪ ዞር ብለው «ለመሆኑ በምን ምክ ንያት ነው የሞተው?» አሉና በጐረና ድምፅ ጠየቁ ።

«በድንገት ነው — እንዲያው በድንገት ። ሰርገኞቹ ባዶ እጃቸውን በእግር ከቤት ደርሰው የደረሰባቸውን እንደነገሯቸው ልቤን ብለው ወደቁ ይባላል ። የውርደት ጨርቅ ይዛችሁልኝ ትመጡ? የገባ ወንዝ ይህን ውርደት አጥቦ ሊያፀዳው አይችልም ። ደም ብቻ ነው ለዚህ መድሀኒቱ — የታለመ ህልም ሳይፈታ አይቀርም እያሉ ሲወተውቱ አድረው ነው አሉ ሲነጋጋ ሲል ደም ተፍ ተው ለመጨረሻ ጊዜ ዝም ያሉት......»

«እግዜር ያለው ላይቀር! ሰው በኔ ይፈርድ ይሆናል ። ልጁስ ምን ያስባል ይባላል? »

«ያባቱን አስከሬን ከቤት አስቀምጦ ፤ ያባቱ ወኪ ሎች የነበሩትን በማባረር ሀብቱን በሙሉ በእጁ በማስ ገባት ላይ ነው አሉ ። ወኪሎቹም በቀላሉ የሚገቱ አይ ደሉም ። ሬሳ አስቀምጠው የገንዘብ ሽሚያ! ጉድ ያላለ የለም ይባላል......»

«ከሁሉም ይበልጥ የሚያሳዝነው የሱዴና የኖዳ ቤቶች የቆየ ታሪክ ከዚህ ላይ ማብቃቱ ነው ። እንደማያልፍ የለም!» አሉ በትካዜ ተውጠው እንባቸውን በዝምታ እያፈሰሱ — ጊዜው ወይም ፊታውራሪ እያና ከሁለቱ የትኛው ከዚህ አለም እንደተለየ ለይቶ ለማወቅ አንዳንዱ እየተሳናቸው ፤ በፊታውራሪ እያና ድንገተኛ ሞት ብቸ ኝነት እየተሰማቸው ፤ በሌላ ወኩል ደግሞ ፊታውራሪ እያና ክፉ ጠላት ይሁኑ ወይም ዘመናትን አብረው ያቋ ረጡ የልብ ወዳጅ መሆናቸውን ለመለየት እያቃታቸው

እንቅልፍ አጥተው አደሩ ። ጧት በማለዳ ተነስተው «በዚች ሰአት ፤ አደግድጌና ጠብመንጃዬን አንግቤ እንደአሸከሩ ሆኜ እሸኝዋለሁ» ብለው ቀብር ላይ ለመገኘት ወደኖዷ ለመሄድ ያላቸውን ቁርጥ አሳብ በገለጡ ጊዜ ፤ አኮ ወይም ሀደ ቢያ የተባለችው ፤ የሱዴ ቦሮ አድባር ተብሎ ከሚጠራው ወርካ ስር የምትኖረው አሮጊት በአንካሴዋ መሬቱን እየወጋጋች ተጎትታ መጥታ ፤ «ከቤትህ ወጥተህ ዛሬ መንገድ አትሂድ ። ዛሬ ቀኑ ያንተ አለመሆኑን አድባሯ አመልክታኛለች» ብላ ወጣች ።

ፊታውራሪ ራቅ ወዳለ ቦታ ሲሄዱ ደም ሳያፈሱ ከቤታቸው አይወጡምና ፤ የታረደውን በግ ሞራ ይዞ የመጣው ሰው ፤ ሞራውን ከፊታቸው ዘርግቶ ባለው ረቂቅ ጥበብ ካነበበ በሁዋላ ፤ «ደግ ነገር አያመለክትም ። ከቤት አይውጡ» አላቸው ። መፅሀፍ የሚገልጡላቸው መነኩሴም በጧት ተነስተው ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያ ሰጥተዋቸው ነበር ። እግራቸውን ከቤት እንዳያወጡ ያልነገራቸው የቅርብ ወዳጅ አልነበረም ። ፊታውራሪ ግን አላመኑቱም ። «ለየትኛው እድሜ ብላችሁ ነው ። ከቀን ቀጠሮው የሚያልፍ የለም ። ለዚያውም......ጠላትን ሲሸሹት እንጂ ከመሀሉ ሰተት ብለው ሲገቡ አይዳፈርም» በማለት አሻፈረኝ ብለው ወጡ......

ፊታውራሪ አጀብ አላበዙም ። ባለቤታቸው ሲሞቱ ቡሎ ያስነከሩትን የሀዘን ልብስ ለብሰው ሙሉ መሳሪያቸውን ታጥቀው ሲነሱ ያልተገረመ አልነበረም ። ቶሎሳ የፊታውራሪ ሀዘን ከቶ ሊከሰትለት አልቻለም ። ጠላት ጠላት ነው ......ወዳጅ ወዳጅ ነው... ለጠላት ማቅ መልበስ ደሞ......ጠላትን ገድሎ መቀባት እንጂ......ሰውን ማመን ቀብሮ ነው ይባል የለም እያለ ሲያስብ የፊታውራሪን በቅሎ ተከትሎ ኖጳ ገባ ። የፊታውራሪ አያና አስከሬን ከቤት ሲወጣና ፊታውራሪ ተካ ሲደርሱ አንድ ሆነ ። ጋሻ ጦሩን አንግቦ ፤ ጎፈሩን አጥልቆ ፤ ሽጉጡን ታጥቆ ፤ ጠብመንጃውን አንግቶ በፈረስና በእግር በረድፍ በረድፍ የቆመው ህዝብ ለጦርነት የተሰለፈ ሰራዊት መስሎ በግርማ ሞገሱ ልብ ያሸብራል ። የፊታውራሪ አያና ሰንጋ ፈረስ ጥቁር ወርቅ ተጥሎበት ፤ መሳሪያዎቻቸውን ይዘው በቀስታ ከሚያዘግሙ ሰዎች በስተሁዋላ ሴጣውን ሲጎትት በተመለከቱ ጊዜ ፤ የፊታውራሪ ተካ አይኖች እንደክረምት ሰማይ የእንባ ዶፍ ያወርዱ ጀመር ። እጅዋን ይወዱላት የነበረችው የፊታውራሪ አያና ገረድ ትንሽ ድስት ይዛ እየተንጎራደደች ተፍተልትሎ ደም እስኪያመነጭ ድረስ ፊቷን ትቧጥጣለች ። ደረት እንደ ከበሮ ይደለቃል ። ጦር ይሰበቃል ። ጥይት ይተኮሳል ። እንዱ የሽምጥ ይጋልባል ። ፊትና መሬት ይቧጠጣል ። በጃኖ የተከፈነው አስከሬን በሰዎች ትከሻ እንደታቦት ግርማ ሞገስ ተጎናፅፎ በዝግታ ያዘግማል ። ፊታውራሪ ተካ አደግድገው ፤ ጠብመንጃቸውን ከትከሻቸው ላይ ይዘው ፤ ያሉበትን እረስተው «ጓዴ ጓዴ የታሪክ ጓዴ» እያሉ ሲያለቅሱ ፤ ቶሎሳ ከመጠራጠሩ የተነሳ በአይኖቹ ግራና ቀኝ እያማተረ ይከተላቸዋል ።

ያው እንዳመሉ የድስት ጥራጊ ቀርቦለት ለራት
ዋይ ዋይ
አፈር አፈር አለኝ ብሎ በማለት
ዋይ ዋይ
ሳይቀምሰው አደረ ድንገት ሆድ ብሶት
ውይ ውይ ውይ ውይ

እንደተቆለፈ ሳይፈታ ወስፋቱ
ዋይ ዋይ
ጢት በማለዳ ቸኩሎ ከቤቱ
ዋይ ዋይ
አፈር አፈር ብሎ አኩርፎ መውጣቱ
ውይ ውይ ውይ ውይ
ሳንዲት ጥሪኝ አፈር
ዋይ ዋይ
እህል ወሀ ሳትል ተንገብግቦ መሄድ አያሻህም ነበር ።
ዋይ ዋይ
ለሰለት ክንድ መሬት መስገብገብህ ምን ነው?
ውይ ውይ ውይ ውይ ውይ
የተደላደለ ሁሉም ለየራሱ በቂ ድርሻ አለው ።
ውይ ውይ ውይ
እንዳፈር ደግሶ ሳይበላ ሳይጠጣ ጠሙን አደረና
ዋይ ዋይ
የድስት ጥራጊ ከቤቱ እንዳጣ ሰው አኩርፎ ወጣና
ዋይ ዋይ
ከመቃብር ወርዶ አፈር ጥረጉልኝ ይል ጀመር አያና ።
ውይ ውይ ውይ
መቃብር ተጠርጎ ሆዱ ላይሞላ ጉርሻ እንኳ ላይሆነው
ዋይ ዋይ
አፈሩን ሰንቅ አድርጎ መጓዙ ለምን ነው?
ውይ ውይ
ውይ ውይ



የፊታውራሪ አያና የቅርብ አሽከሮችም ልቅሶአቸውን ትተው ፤ በምን ቢመኩ ይሆን ትናንት ማታ ጌታችንን ሰሞት ያበቃ በደል ፈፅመው ዛሬ ሰተት ብለው የመጡት፣ በማለት በልባቸው ሲያሰላስሉ ፤ እርሳቸው «ጓዴ — ወዳጄ — የደጉ ቀን ጓዴ —» እያሉ ቆመው አስቀበሩ ። ግብአተ መሬት ሆኖ መቃብሩ እንደተደፈነ ፤ ድስት ይዛ የምታለቅሰው የፊታውራሪ አያና ገረድ እሮጣ መጥታ ድስቱን ከመቃብሩ ላይ ፈረከሰችና ከመቃብሩ ላይ ተደፋች ፤ ጣቶቿ እስኪደሙ ድረስ እየነከሰቻቸው ።

ያልተፈታ ህልም ።
ገል ።
የገል ስባሪ ...... ህይወት ።

የፊታውራሪ አያና ወኪሎች ፤ ፊታውራሪ ተካ ከልብ አዝነው ሲያለቅሱ በማየታቸው ተፀፅተው ይሆናል የሚል ግምት ስላደረባቸውና ፤ እንዲሁም ፤ ተፀፅተው ልጆቻቸውን ለዳኛቸው ከሰጡ እንደአባት ሆነው ሊገስጡት ስለሚችሉ ፤ መተዳደሪያቸው የሆነውን የቀድሞ ውክልናቸውን ያስመልሱልናል ብለው በማሰብ ፤ ቀብሩ እንደተፈፀመ ወዲያውኑ ሽምግልና ጀመሩ ። ለጊዜው እሺ ፤ ወይም እምቢ ሳይሉ ፤ ነገሩን እንጠልጥለው ወደሱዱ ተመለሱ ። የዳኛቸው ልብ በፊትም ቢሆን ያረፈው ከታወቀችው ከኖጳዋ ውብ ኮማሪት ስለነበረ አባቱ በሞቱ

በአሰረኛው ቀን ሳይሰማ በሰማንያ አግብቷት ፤ የሁለቱም
ልብ የፈቀደውንና የተመኘውን ሶስት ጉልቻዎች መሰረቱ ።
ብቻ ለእልኩ ያህል ፊታውራሪ ተካን ከመክሰስ አልቦዘነም ።
ይሁን እንጂ የአገር ሽማግሌዎች በጉዳዩ ገብተው
ፊታውራሪ ተካ ሁለት ሺህ ብር ካሳ እንዲከፍሉት ሰላደ
ረጉ ፤ ዳኛቸው «ከፊታውራሪ ልጅ የፊታውራሪ ብር የበ
ለጠ ቁም ነገር ይሰራል» ብሎ በደስታ ተቀበለ ።

ፊታውራሪ ይህን በሰሙ ጊዜ ከንዴታቸው የተነሳ
የሚያደርጉትንና የሚጨብጡትን አጥተው ሱባኤ እን
ደገባ ሰው ሶስት ቀን ሙሉ እህል ሳይቀምሱ «የኖጺ ቤቶች
ወኔ ምላሳቸው ብቻ ነው ። የእልቋይቱ ማርያም! ምላሱ
ወደውስጥ ዘልቆ እንደሾህ ይዋጋል ። እኔ ከስድብ በጦር
ቢወጉኝ ይሻለኛል ። ስድብ ዘወትር የሚመዘምዝ መርዝ
ነው ። ጦር አንዴ ወግቶ ያሳርፋል ። ከዘሬ ይልቅ እንዴት
ብር ይመረጣል? በቁም ገደለኝ'ኮ እያሉ ሲብከነከኑ ከቆዩ
በሁዋላ አይናለምን በጥቂት ቀኖች ውስጥ ለሀዲስ ለመዳር
ቁርጥ አሳብ አደረጉ ።

ጋብቻው የተፈፀመበት ምሽት አየሩ ቀዝቀዝ ያለ ፤
የበጋው ወራት አልፎ የክረምቱ ዋዜማ የሚገባበት ምሽት
ነበር ። በጥቁሩ ሰማይ ላይ የተገመሰ ብር የምትመስለ
ዋን ጨረቃ ያጀቡት ስፍር ቁጥር የሌላቸው ከዋክብት



ለምሽቱ የበለጠ ውብትና ግርማ ሞገስ ለግሰውታል ።
ሀዲስ አዲስ በገዛው የአገር ልብስ ተውቦ ፤ ያለወትሮአ
ቸው በምላጭ ተፈግፍገው የፀዱት ጉንጮቹና የሚያበ
ሩት ትናንሽ አይኖቹ የምሽቱን ግርማ ሞገስና የድግሱን
ድምቀት እንደመስተዋት መልሰው ያንፀባርቃሉ ። ተጋ
ባዡ ህዝብ ከዳኛቸው ጋር እያወዳደረው እንደሚንሾካ
ሾክበት ሳይሰማው አልቀረም ። ትንሽ እረፍት የነሳው
ግን የሽታዬ እንባና የራሱ ጭካኔ ነበር ። ውነት እንዳለችው
ህይወቷን ታጠፋ ይሆን ? ሰውነቱን ዘገነነው መንፈሱ እረ
ፍት አጣ ።

ፊታውራሪ ተካ ልጃቸውን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሁ
ለተኛ ጊዜ ደግሰው በመዳራቸው የሱዷ ቦሮ ህዝብ ጉድ!
ጉድ ! እያለ ሲበላና ሲጠጣ ውሎ ጉድ! ጉድ! ጊዜ እያ
መጣው የለ ፤ የኖጺውን ባላባት ልጅ ከደጃቸው መልሰው ፤
ዘሩና ደረጃው ላልታወቀ ላንድ መናጢ ድሀ — መስጠ
ቱንስ ለውሻም ይስጧት — ቆማ ከምትቀር — ግን ይህን
ያህል ምን የሚያስቸኩል ነገር መጣ ? ሲሆን እድሜ ያስ
ክናል እንጂ እንዳበደች ውሻ ያቅበዘብዛል እንዴ እያለ
ነበር ወደየቤቱ የተመለሰው ።

ድግሱ ወደ መንፈቀ ሌሊት እንዳበቃ ከዚያው ከፊ
ታውራሪ ግቢ ከተዘጋጀላቸው የጫጉላ ቤት ተወሰዱ ።
ሙሽሮቹ ከዚያው እንዲቆዩ የተወሰነው አስፈላጊው ጥበቃ
እንዲደረግላቸው ታስቦ ነበር ።

ለመጀመሪያ ጊዜ በተዘጋ ቤት ውስጥ አይናለም
ብቻዋን ከእርሱ ጋር ሆና በማየቱ ፍርሀት ፤ ፍቅር ፤ ደስታ ፤
አድናቆትና ርህራሄን ባንድነት ያዘለ ፤ መንፈስ የሚያሸ
ብር ፤ የሚይዙትን ፤ የሚናገሩትንና የሚያደርጉትን ነገር

የሚያሳጣ ፤ እንደወባ በሽታ እያላበ የሚያንቀጠቅጥ ስሜት አደረበት ። ካለበት ቦታ አልተነቃነቀም ። ህይወት እንደ ሌለው ሀውልት ተገትሮ ቀረ ። በእርሷም ላይ የሚመላለሰው ስሜት ከእርሱ አልተሰወረም ። ትንቀጠቀጥ ነበር — ከአልጋው አጠገብ ከመጋረጃዎቹ መሀል ቆማ ። ፊቷ እንደ ጸ ይቀላል ። ተመልሶ ይገረጣል ። እንባ ያንቃታል — ግን አይወርድም ። ከዚያ ነበሩ — ባዶ ቤት ውስጥ — በወጥመድ ሳያስቡት በድንገት እንደተያዙ ሁለት የዱር እንስሳት — አፍጥጠው — አንዱ ከሌላው የዝምታ ወጥመድ የሚወጣበት መንገድ ጠፍቶት ። ያደረባትን ብርቱ ፍርሀት በማየት የራሱን ፍርሀት ዘንግቶ አፅናናታለሁ ብሎ በማሰብ አንድ እግሩን በጭፍን አንስቶ ከመሬት ላይ ከመትከሉ በፊት ከመደንገጧ የተነሳ ለመጮህ ከቃጣት በሁዋላ በሁለት እጆቿ አፏን በግድ አፍና ዝም አለች ። የራሱ ባልሆነ ድምፅ «አይዞሽ — አላንቅሽም አውሬ አይደለሁም ። ያለፈቃድሽ የሚሆን ነገር የለም — ባልና ሚስት ብንሆንም ። አትፍሪኝ — አውሬ አይደለሁም — በስሜት የሚሄድ» እያለ ተጠጋት ። እያንዳንዱ ቃል ውስጡ እንደቦምብ እየፈነዳ ልቡን ሲንደው ይሰማው ነበር ። ትከሻዋን ያዘ ። ትከሻዋ ከመንቀጥቀጡ የተነሳ እየነዘረ እጁን ወደላይ ይገፋው ነበር ። ልቧ እንደቃልቻ ድቤ ድው ድው ሲል ከሩቅ ይሰማል ። በእጁ ውስጥ የምትሟሟ መሰለው ። ግን ሊለቃት አልፈለገም ። ከእርሷ እንደገና ርቆ የመቆም አሳብ አስፈራው ። የባሰውኑ ተጠጋት — ጉንጭ ጉንጯዋን ነክቶ ፤ የልባቸው ትርታ እየተቀባበለ እንግዳ የሆነ ስልት እስኪይዝ ድረስ «ባልና ሚስት ነን» አላት በለሆሳስ ።



«ጋሼዬ ባክህ አታስገድደኝ» አለችው ፤ እንባዎቿ በጉንጮቿ አቋርጠው ወደአንገቷ እየኮበለሉ ።

«አውሬ አይደለሁም ዘልዬ በግድ የማነቅ ። አትፍራኝ የኔ አይናለም» አላት ባጭር ባጭሩ እየተነፈሰ ። ትላልቅ ውብ አይኖቿን እያንከባለለች ለመጀመሪያ ጊዜ ቀና ብላ አየችው ። እንደምጣድ ከሚፋጁት ከተላቀቁት ከንፈሮቿ መሀል ከንፈሮቹን አስገባ ። አፀፋውን አልመለሰችለትም ። እንደገና ከንፈሮቿን በከንፈሮቹ ፈልጎ አገኝ ። ለመጀመሪያ ጊዜ ለክብረ ንፅህናዋ የመታገል አሳብ ተረሳት ። ከዚያ ቀደም የማታውቀው ሰውነት የሚወር ስሜት መጥቶ በሰራ አከላቷ ሲሰራጭ ተሰማት ። የጋሉት ርጥብ ከንፈሮቻቸው እንደገና ለረጅም ጊዜ ተገናኙ ። መፈራራታቸው ቀረ ።

«የትምህርት ቤቱ መሰረት ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በልቤ ውስጥ ነፍስ እየዘራሽ እያደግሽ ትሄጂ ነበር ። አሁን ግን ሚስቴ መሆንሽን ለማመን ያቅተኛል ። ሁሉም ነገር ባንዳፍታ ሳላስበው ነው የሆነው — ህልም ነው የሚመስለኝ» አላት ። ውብ ፈገግታዋን ከማሳየት ሌላ የምትሰጠው መልስ አላገኘችም ። ከንፈሮቿን መልሳ ከመከደኗ በፊት ጥርሶቻቸው እስከሚጋጩበት ድረስ እየሳማት ተሸክሞ ወደአልጋው ሲወስዳት የእግሩ ህመም ጨርሶ አልተሰማውም ።

«አትጉዳኝም? አይደለም?» አለችው ። ይህን እንዳለችው እርሱ ከትምህርት ቤቱ ጣሪያ ላይ ወድቆ ፤ እርሷ ወደታች እጆቿን ስትዘረጋለት ያየው ህልም በአሳቡ መጣ ።

«አልጐዳሽም ፡፡ በልቤ ውስጥ ስገነባሽ ከርሜ እንዴት አድርጌ?» አላት ፤ ለምን እንዲህ እንዳላት ሳይገባው ፡፡ ከዚያ ነበረች — ፊት ለፊቱ — ከአልጋው ላይ በጀርባዋ ተንጋልላ — ረጅም ጥቁር ጠጉሯ ከትራሱ ላይ ተበታትኖ ተኝቶ — የፋኖሱ ብርሀን የእርሱን ጥላ ከግድግዳው ላይ ከሀይወት በላይ አሳድጐ እያሳየ ፡፡ ከንፈሮቿ አልተከደኑም ፡፡ አይኖቿ ረገብ ቢሉም ጡቶቿ ወደላይ አፍጥጠው በታል ፡፡ ፋኖሱን አጥፍቶ ፤ ጠባብ ሱሪውን በትግል ከወለቀ በሁዋላ አጠገቧ ተጋደመ ፡፡ የልባቸው ትርታ በስልት ማስተጋባት ጀመረ ፡፡ ከንፈሮቻቸው እንደገና ተገናኙ ፡፡ ከንፈሮቻቸው በሰቀቀን በሚገናኙበት ወቅት ሁሉ ከትምህርት ቤቱ ግድግዳ ውስጥ እንደመናፍስት ተፈልፍላ ወጥታ ስታቅፈው በአሳቡ ታየው ፡፡ በልቤ ውስጥ ስገነባሽ ከርሜ እንዴት አድርጌ! የሚል ድምፅ ከጆሮዎቹ ውስጥ ያለማቋረጥ ያስተጋባል ፡፡ ትምህርት ቤቱ — አይናለም — ሁለቱም በአሳቡ አንድ እየሆኑበት ሰውነቱ እየቀዘቀዘ ፤ እርሷ በማታውቀው አዲስ ስሜት ተገፋፍታ ከአንገቱ ላይ ተጠምጥማ ብትቃትትም ሊሆንለት አልቻለም ፡፡ በእፍረት ተሸማቅቆ ተዋት ፡፡ ከዚያ ሁለቱም በጀርባው ተንጋልለው ቀሩ — አንዱ የሌላውን የልብ ትርታ እያዳመጠ ፤ አንዱ ስለሌላው የሚያስበውን በግል ልቡናው እየመረመረ — ከባድ ዝምታ ዋጣቸው ፡፡ የብር አምባር ሊሰብር ያልቻለ ወንድ ፣— ልፍስፍስ ... በህብረተሰቡ ዘንድ ምን ግምት ይኖረዋል ፣ ... በቁም መሞት ... ሰውነቱ የባሰውኑ ተሸማቀቀ ፡፡

አንዳንዴ ፤ ሀዲስ ካጠገቧ ተነስቶ ለመብረር ይቃጣዋል ፡፡ ከአይናለም አይን ይሰወር እንጂ ከራሱ ሸሽቶ የትምየማያመልጥ መሆኑ ሲከሰትለት ፤ ራሱን በራሱ በመምከር የፍላጐቱን ልጓም ይገታል ፡፡ ከሽታዬ ጋር ያሳለፈውን ጊዜ ያስታውስና ፤ ከእርሷ ጋር ደህና ነበርኩ ፤ አሁን ምን ነካኝ? ወንድነቱን ምን ገደለው? በማለት ራሱን በራሱ ይጠይቃል ፡፡ መልሱ ግን አይከሰትለትም ፡፡ አይናለምም እንቅልፍ እንዳልወሰዳት ያውቃል ፡፡ እርሷም በበኩሏ እንደምታስብ ይሰማዋል ፡፡ ምን ታስብ ይሆን በልቧ ... ትንቀኝ ይሆን — የወንድ አልጫ ... ግን ሊያነጋግራት ፈራ ፡፡ ዝምታ ፤ የታፈነ ዝምታ ብቻ ነበር እንደ ብርድልብስ ሆኖ የሸፈናቸው ፡፡ እንቅልፍ የማይዞርበት ረጅሙ ሌሊት ሌላው የበለጠ ስቃይ ሆኖበት ነበር ፡፡

የፀሀይዋን ጨረር ለማየት የፈራ ይመስል ወፎች መንጫጫት ከመጀመራቸው በፊት ተነስቶ ወደትምህርት ቤቱ ሄደ ፡፡ የምስራች የለም ፡፡ ሀዘን ፡፡ ክብር የለም ፡፡ ውርደት ፡፡ ያሳበበ ጫጉላ ፡፡ ሹክሹክታ — ውርደት — ሞት ...

ከዚያ ትልቁ ድንጋይ ላይ እንደልማዱ ተቀምጦ ትምህርት ቤቱን አይኖቹ እስኪፈዙ ድረስ ይመለከት ጀመር ፡፡ የፀሀይ ጮራ አይናፋር ልጃገረድ መስላ አይኖቿን ስትገልጥ እንደተለመደው አይናለም ከትምህርት ቤቱ ግድግዳ ውስጥ እንደጀምበር ብቅ ብላ እየተንሳፈፈች መጥታ አቀፈችው ፡፡ በዚያ የህልም አለም ውስጥ ለስንት ሰአት ሲንሳፈፍ እንደቆየ ሳይታወቀው የትምህርት ሰአት ደርሶ ልጆቹ ሲንጫጩ ከእንቅልፉ ነቃ ፡፡ ትምህርት ቤቱ ፤ አይናለም ፤ ያሳለፈው ሌሊት ባንድነት መጥተው በአሳቡ ውስጥ ተጋጩ ፡፡ የተወለደበትን ቀን እየረገመ ወደፈታውራሪ ቤት ተመልሶ ከደጃፍ ሲደርስ ፤

ቶሎሳ መጥቶ ፤ ፊቱን ትኩር ብሎ በማየት ከጠናው በሁዋላ ፤ «ምንነው ጋሼ — እንቅልፍ ተኝቶ ያደረ ሰው አትመስልም» አለው ።

«ማጉላ ቤት መሆኔን ረሳህ እንዴ!» ብሎ በግድ ከንፈሮቹን አላቅቆ ሲያበቃ ወዝ የሌለው ፈገግታ አሳየው ።

ቶሎሳ ግራና ቀኝ በአይኖቹ ቃኝቶ ሰው አጠገባቸው እንደሌለ ካረጋገጠ በሁዋላ ወደጆሮው ጠጋ ብሎ «ሸታዬ የምትባለዋ ሴት አስረግዞኝ በኔ ላይ ሌላ ሴት አገባ ብላ ልትከስህ ተሰናድታለች የሚል ወሬ ከጆሮዬ ገብቷል ። የሚገናኙትም እነዚያው ጠላቶችህ መሆናቸውን ሰምቻለሁ» አለው ።

«አሁንስ አበሳዬ በዛ!» አለ ምርር ብሎ ።

«የለም'ኮ ጋሼ — ነገሩ ከልጅቷ አልመጣም ። ካገር ሊያስወጡህ ከሚፈልጉት ሰዎች የመነጨ አሳብ ነው ። እባብ ከጭንቅላቱ ላይ ከተመታ አይጎዳም — ግድ የለም — አታስብ» አለውና አፅናንቶት ቢሄድም ፤ ቶሎሳ ምን ርምጃ ለመውሰድ እንዳሰበ አልገባውም ። ለመጀመሪያ ጊዜ መንፈሱ ያጋጠሚ ሁኔታ ተገኘ በመሆኑ የባሰውኑ አዘነ ...



ጭር ያለ ቤት የሞቷን መቃረብ የሚነግራት ይመስላታል — ዝናሽ ። ገበያው የደራ ቤት ብቻ ነበር መኖሯን የሚያረጋግጥላት ።

የቡና ቤቷ ገበያ ከጊዜ ወደጊዜ እየቀዘቀዘ በሄደ ቁጥር ተስፋዋ እየመነመነ ይሄዳል ።

የቡና ምርት በድርቅ ምክንያት እንደሌላው ጊዜ ሳይሰምር በመቅረቱ ህዝቡ ገንዘብ ስለቸገረው ይሆናል እንዳትል የሌሎቹ ቡና ቤቶች ገበያ እየደራ ሲሄድ በአይኖቿ ትመለከታለች ። ሌሎች የቡና ቤት ነጋዴዎች መተት አድርገውብኝ ነው — ሌላ ምክንያት የለም በማለት ትደመድማለች ። በተለይ አንድ ቀን ጧት ከደጃፍ አንገቱ የተቀረጠ ወሰራ ዶሮ ተጥሎ ካየች ወዲህ ጥርጣሬዋ የተረጋገጠ መስሎ ስለታያት ወደአባ ጩፌ ቤት ከወትሮዋ በበለጠ መሮጥ ጀመረች ።

በአባ ጩፌ ትእዛዝ በየጊዜው ከቡና ቤቷ በር ላይ የምታርደው ቡሀ ፤ ዳለቻ ፤ ቀይ ፤ ነጭ በግ — ገብስማ ፤ ወሰራ ፤ ዛጎልማ ፤ ልበወርቅ ፤ ቀይ ፤ ነጭ ፤ ጥቁር ፤ ዶሮ — ተቀማጭ ገንዘቧን እንድታሟጥጥ ከማድረግ ሌላ ገበያዋ ተመልሶ እንዲደራ ምንም ያልረዳት መሆኑን ስትመለከት ወደቤተክርስቲያን ፊቷን ታዞራለች ። ገብርኤል — ሚካኤል — ጊዮርጊስ — መድሀኔ አለም — ማርያም — የማትሳልለት ታቦት የለም ።

የመጠጥ መደርደሪያው ባዶ እየሆነ ፤ መጠጥ ቤቱ እንደመቃብር እያዛጋ በሄደ ቁጥር በአባ ጨፌም ሆነ በታቦቶቹ ላይ ያላት እምነት እየላላ ፤ የተስፋ መቁረጥ ስሜት እያደረባት ፤ በዚህ እድሜዋ የምትገባበትና የምትጨብጠው ነገር እየጠፋት ፤ ስላለችበት ሁኔታ ከመናገር ይልቅ ፤ ስላለፈው ዝናዋ ፤ ውበቷ ፤ ሀብቷና ውሽሞቿ አዘውትራ ማውራት እየቀናት ፤ ከመሬት ተነስታ ወገቤን ሰነጠቀኝ ራሴን ፈለጠኝ ፤ ሆዴን ቀስፎ ያዘኝ ፤ ልቢ ፈሰሰ ማለት እያበዛች ትሄድ ጀመር ። ህይወቷን በገዛ እጅዋ ለማጥፋት የምታስብበትም ጊዜ አለ ። እርሱም እንደንግዲ አልሆንላት እያለ ያበሳጫታል ። መኖር አድካሚ ፤ ማሰብ አድካሚ ፤ ሞት ደግሞ የባሰ ።

«እንደሰራ አይገድል» አለች ወይዘሮ ዝናሽ ወደላይ ቀጥ ብሎ ከሚተንነው የእጣን ጢስ ጋር አሳቧ እያንሰራራ ። በጀበና የቀረበው ትኩስ ቡና ከውስጥ እየፎከረ ቀረቀንዳውን ወደላይ ይገፋል ። ሽታዬ ሀዲስን እያሰበች አንገቷን በሀዘን ደፍታ የጀበናውን ቀረቀንዳ ትመለከታለች ። አንዳንዴ ከእጣኑ ጢስ ጋር አሳቧ ይባክናል ። ጢሱን በአይኖቿ ትከተላለች ። ተስፋዋ እንደጢሱ ይሄድ ይሄድና እየመነመነ ይጠፋል ። ከንፈሯን ትነክሳለች ።

«ወተት በጨለማ ታበላሽላችሁ ፤ ቀን እንዲህ ይገፋል እኔ ላሳያችሁ የሚለውን ግጥም ሰምተሽ ታውቂያለሽ? — አዎን — የኔ ኑሮ ቀን መግፋት ብቻ ። ኑሮ አይደለም ። ሸርሙጣ ስታረጅ አቃጣሪ ትሆናለች ሲባልስ ሰምተሻል? አዎን — ይሄው ነው የቀረኝ ። ወንዱን ከወንድ ፤ መጠጡን ከመጠጥ ፤ ጌጡን ከጌጥ እንዳላማረጥኩሁሉ ። እድሌ ሆኖ ምቀኛ አላጣም ። ምቀኞቼ ባይተበትቡብኝ ኖሮ ይሄኔ ፎቅ እሰራ ነበር — ባዲስ አበባ ጉዳናዎች ሻሼን ኸርገድ አድርጌ በመኪና እሸከረከር ነበር — ይህችም ኑሮ ሆነችና ምቀኞች ተነሱብኝ!......»

«አይማረሩ እትዬ — ሰው በከንቱ ይመቀኛል እንጂ ያርባ ቀን እድልዎን......»

«እኔ ያለእድል ነው የተፈጠርኩት ። ለምቀኛ ነው ያደለኝ» አለች ፤ አባ ጨፌ ምቀኞች ይበዙብሻል ያላትን በማስታወስ ። ሽታዬ እጣ ክፍሏ አለመሆኗንና እርሷን ከላባረረች ገድ እንደማይኖራት የነገራትም ትዝ ብሏት «ካሻሻቁም ገድ ቢስ አለች ...» ብላ ስትጀምር ፤ አቶ ይርጋና የመቶ አለቃ አሸኔ ተከታትለው ገቡ ። ሽታዬ በሀዘን የባሰውኑ አቀረቀረች ።

«ምን ትለማመናላችሁ?» ብሎ የመቶ አለቃ ጠየቀ ፤ የቡና ጀበናውንና እጣኑን በቦዙት አይኖቹ እያማተረ ።

«ገበያ»

«እኛን ባለላችሁዋ!»

«ጥሩ ጥሎሽ ነው — የማታ ገበያ»

«ጀባ በሉና ከውስኪው» ብሎ ከተቀመጠ በሁዋላ ወደሽታዬ እየተመለከተ «እጮኛሽ ካገባ ወዲህ ፈገግታ ከፊትሽ ተለይቷል» አላት ። የወይዘሮ ዝናሽና የመቶ አለቃ ንግግር ስለተደማመሩባት መልስ ከመስጠት ይልቅ እንባ አነቃት ። ሳታውቀው እንባዋ ኮለል ብሎ ወረደ ።

«ፍቅር ይዞኛል ብለሽ አትበይ-ደንበር ገተር ፤ እኛም አንድ ሰሞን እንዲህ አሮጉን ነበር የተባለውን ግጥም አልሰማችሁም? በርቧ ደረሰ ። የገጠር አስተማሪን ያመነና

ጉምን የዘገነ አንድ ናቸው ። ምክሬን ብትቀበል ይህ ሀዘን ባልደረሰባት……»

«ሀዲስ ያልለከፈው ሰው የለም…… » ከማለቱ ፤ አቶ ይርጋ በብስጭት «ስሙን አትጥራብኝ ነው የምልህ! ያመኛል» ብለው የተቀዳላቸውን ውስኪ በአንድ ትንፋሽ ጨለጡት ።

ዝናሽ መጠጥ መቅዳቷን እንጂ የአቶ ይርጋን ብስ ጭት አላጤነችም — «እሱ ከመጣ ወዲህ ነው ድርቅ ባገር የገባው» አለች ።

«ተማሪውና ኩሊው አስቸግረው እኔም ፍዳ የበዛብኝ የሱ እግር ሱዲን ከረገጠ ወዲህ ነው ። እሱ ባይመጣ ኖሮ ፊታውራሪ ተካም ተከብረው የኖሩትን ያህል በሀዝቡ ዘንድ እብድ አይባሉም ነበር ። ሽታዬም ጥሩ ባል አግኝታ እንደ ምኞቷ አዲስ አበባ ትወጣ ነበር ። እርሱ ከመጣ ነው ሰው እህል — እህል — ወሀ — ወሀ — ግፍ — በደል እያለ መጮሁና አንገቱን ቀና ማድረግ የጀመረው ። የሚያስፈ ራና የሚያሳስብ ጊዜ መጥቷል ። ባላገር ካመረረ ደግ አይ ደለም ። በርሱ ያልተለከፈ ማን አለ!» አለ የመቶ አለቃ ወደ አቶ ይርጋ እየተመለከተ ።

«ምናለ ብትተወኝ! አንተ'ኮ የበቃሀኝ ከኩሊዎች ጋር ገንዘብ ያዋጣህ ለት ነው ። የምትወደውን ለመደገፍ ፤ የምትጠላውን ለመቃወም ወኔ የለህም ። እንደይሁዳ አሳልፈህ ከሰጠህኝ በሁዋላ ለምን ትነካካኛለህ?……»

ወይዘሮ ዝናሽ ጣልቃ ገብታ «ንትርኩን ተውትና ጠጡ» ብላ ሌላ ውስኪ ቀዳችላቸው ። ለራሷም ቀዳች ። ሽታዬንም ጋበዘች ። ሽታዬ በዚያን ሰአት ለውስኪ ደንታ



አልነበራትም ። ምኞቷ ከመኝታ ክፍሏ ገብታ የሚተናነ ቃትን እንባ ማፍሰስ ብቻ ነበር ። ለእንባ ጊዜ ማጣት ፡ ሀዲስን አጣች ። አዲስ አበባ የመውጣት ተስፋዋ ከሀዲስ ጋር አከተመ ። ገዶ-ቢስ መባሏም እጅግ አሳዝኖአት ውስጥ ውስጡን ይበላት ነበር ። ገዶ-ቢስ ሀዲስ ።

«ነገርን ነገር ስላመጣው ነው እንጂ አንተን ለመነ ካካት አስቤ አይደለም» አለ የመቶ አለቃ ይቅርታ እንደ መጠየቅ ብሎ ።

«የሚሰማኝን ባታውቅ ነው ። በምቀኝነት የምቃወ መው ይመስልሀል ። በምቀኝነት አይደለም ። ይሄው እን ደዚህ ይድፋኝ» አንድ መለኪያ ውስኪ አንስተው ደፉ — ወይዘሮ ዝናሽ ሌላ ቀዳች — «ምቀኝነት አይደለም ። ትምህርት ቤቱ ቢስፋፋ እወዳለሁ ። እኔ ይህን ሳድርግ ፤ አንተ በዚህ እርዳኝ ብሎ አላማከረኝም ። እኔን እንደሻገተ እንደዛገ እቃ ቆጥሮኝ ስራውን ጀመረ ። ከጀመረም በሁዋላ አንድ ቀን አላማከረኝም ። ይቅርታ አልጠየቀኝም ። እኔ ስራውን ሳይሆን ንቀቱን ነው የምቃወመው ። ከትምህርት ቤቱ ግድግዳ ጋር ንቀቱ ከፊቴ እያደገ ይሄዳል ። አላፊ ርሰው ነገር ሰው እብድ ይለኛል ። አልተወው ነገር የው ርደቱ ሀውልት መስሎ ይታየኛል ። ከዚህ ሁሉ በሁዋላ ለርሱ ተንበርክኬ ርዳታ መስጠት መጀመር የባሰ ውርደት ነው ። እንቆቅልሽ ። እንቆቅልሽ ነው ። ስሜቴ አይገባህም ። እኔንም አይገባኝም» ብለው ውስኪውን በአንድ ትንፋሽ እንደገና ጨለጡ ።

«ግትር ነው ። መጥፎ ግትር» አለች ዝናሽ ። ቀጠለ ችና ወደሽታዬ እየተመለከተች «ይህችም እንደርሱ ግትር ናት ። ሰው የሚመክራትን አትሰማም ። ልቧ በፍቅር

እንደጢፍ ነዶ ሊያልቅ ነው ። ድንቄም ፍቅር» አለች የወርቅ ጥርሷን እያሳየች ።

«አንቺ ፍቅር አይዝሽም ማለት ነው?»

«ከየትኛው ወንድ!»

«እኔ ምን ጉዶለኝና» አላት የመቶ አለቃ ፤ እየጐነተላት።

«ኡኡቴ ። ወታደር እርም ብያለሁ»

አቶ ይርጋ በአሳብ ከእነርሱ ተገንጥለው የሄዱ ቢመስሉም ፤ ሁለቱ የሚያወሩትን በግማሽ ልብ ያዳምጡ ነበረና «የፍቅርን ነገር ስታነሱ ትምህርት ቤቷ መጥታ ከፊቴ ትደቀናለች ። እንደአይኔ ብሌን ነው የማያት ። ሌላ ፍቅር አላውቅም ። ፊቷን ያዞረችብኝ መሰለኝ ። ህይወትም እንዲሁ ። እንደ፹ርሙጣ ከሌላ ጋር ስትገለፍጥ ማየት አልችልም ። ገዴ ነበር የምላት......»

«ምርር አትበል»

«እንዲያውም ይህን ሰሞን ደም ደም ይሸተኛል......»

«ኧረ ጠላትዎን» አለች ዝናሽ ሌላ ውስኪ እየቀዳች ።

ሽታዬ የሰከነውን ቡና መቅዳት ጀመረች ። የመጀመሪያውን ሲኒ ቡና ወደውጭ አፈሰሰች ። የቀረበውንም የቡና ቁርስ ዘግና ወደውጭ በተነች ።

«በኔ ይሁንብህ ። ይቅርታ እንዲጠይቅህ አደርጋለሁ»

«ከዚህ በፊትም በኔ ይሁንብህ ሰትለኝ ነበር ። ባንተ የሚሆን የለም ። ለይቅርታ ጊዜው አልፎአል ። እርሱ የተማረ — እኔ ደንቆሮ — አሳብ የሌለኝ — ምክር የማልጠየቅ......»



«በኔ ይሁንብህ ስልህ!»

«ምንነው ብትተወኝ ። በአጥፊና በጠፊ ፤ በአሳትና በጭድ መሀል ይቅርታ ቦታ የለውም ። ተማርን ተመራመርን የሚሉት ሰዎች ለእንደኔ አይነቱ ሰው ስሜትና አሳብ ደንታ የላቸውም ። በነርሱ ግምት ያገሬቷ ስረየት የውጭ ቋንቋ ማወቅ ነው ። ያገራችንን ትምርት የመቃብር ቤት ትምርት ነው እያሉ ዋጋ ያሳጡታል ። ዋጋ የለንም ። አገልግለን አገልግለን ዋጋ ማጣት አሉት ።

ጠፊና አጥፊ ፤ እሳትና ጭድ — ሽታዬ የአቶ ይርጋን ቃላት መልሳ በአሳቧ ውስጥ አስተጋባች ። የኔ ተስፋ እንደሞተ ሁሉ የእርሱም ህይወት ንፋስ እንዳጠፋው ጢፍ — አቶ ይርጋ የደረሰባትን በደል ሊበቀሉላት የመጡ ታላቅ ወንድም መስለው ታዩዋት ።

የመቶ አለቃ «ሳይደግስ ላይጣላ — ምሬት ምን ያደርጋል» አለ ዝናሽን እየጐነተለ ...

በዝምታ እንባውን አፈሰሰ ። ከፍቅር ፅላት ላይ አብረው ተሰውተው ህይወቷ ከህይወቷ ጋር ለመዋሀድ አልቻለም ። አጠገቡ እያለች በገነት አትክልት ውስጥ

እንደምትገኝ እምቡጥ ፅጌረዳ አበባ ርቃ ታየችው ። ገና ከፍፃሜ ያልደረሰው ትምህርት ቤት እንደ ህልም ሆኖ እንደሚታየው ሁሉ እርሷም ህልም ሆነችበት ። ህይወት ራሱ ህልም — ቅዠት መስሎ ታየው ። ምናል ባት ከዚህ ቅዠት አምልጠን ወደውነተኛው ህይወት ዘለአለማዊ ህይወት የምንገባውና ከፍጥረት ጋር የምን ዋሀደው በሞት ብቻ ይሆናል ፤ ሞት ብቻ ነው የፍጥረት ሁሉ የመጨረሻ ግብ — ሞት ዘለአለማዊ ነው -- የተቀ ረው ግን ህልም ነው — ቅዠት — እኛ ቂል ፍጥረቶች ግን ይህን ህልም በጊዜ ለመመጠን — በእድሜ ልንለ ካው እንሞክራለን — ሌላው ቅዠት — ለሰንት ደቂቃ ህልም እንደታየው ማን ሊናገር ይችላል? ህይወትም እን ደዚያው ነው — አንዳንዶቹ ከሌላው የበለጠ ያልማሉ — ይሄው ነው — ዘለአለማዊ ነገር ሞት ብቻ ነው — ግን'ኮ ከሽታዬ ጋር ደህና ነበርኩ — ወንድ ነበርኩ — ምናል ባት ያም ህልም ይሆናል — ለመጀመሪያ ጊዜ አቶ ይርጋን በጥላቻ አይን ተመለከታቸው ። ነፍስ ያለው ጥላቻ በልቡ ውስጥ ሲገላበጥ ተሰማው ። ትምህርት ቤቱንም ሆነ አይናለምን ለይቶ ለማየት ስላቃተው ለደረሰበት ውድ ቀት ሁሉ አቶ ይርጋ ምክንያት ሆነው ታዩት ። አእ ምሮው በአሳብ ተሞልቶ ጭንቅላቱ እንደምድጃ ጋለ ። ሌላ እንደቀንድ አውጣ የሚያዘግም ሌሊት — ሌላ እን ቅልፍ የማይዞርበት ሌሊት ። አይናለምም ፤ ምርቃ እድ ሜዋ በማያውቀው ነገር ተጠምዳ እየተገላበጠች ፤ እን ቅልፍ የማይዞርባቸው አይኖቿ የጋረዳቸውን ጨለማ እየ ዳሰሱ ከማሰብ አልቦዘነችም ። በልቧ ልታምነው ጀም ራለች ። ሴት መሆን ትርጉሙ ምን እንደሆነ ለማወቅ የነበራት ጉጉት በልቧ ውስጥ እየጠነከረ ይሄድ ነበር ።



በየጊዜው እንደጡት መጅ እየጠነከረ የሚሄደው ሴት የመሆን ምስጢራዊ ፍላጐት ልቧ ውስጥ ነፍስ ዘርቶ በተ ንቀሳቀሰ ቁጥር በስራ አካላቷ እንደደም እየተሰራጨ ያሰ ቃያት ነበር ። ሌላ ረጅም ሌሊት ። ዉት ሊነጋጋ ሲል ነበር ሀዲስ ተነስቶ ወደመቱ ለመሄድ ቁርጥ አሳብ ያደረገው ።

«ምንነው በደህና?» አሉት ፊታውራሪ ተካ ከሚ ደግሙት ዳዊት ላይ ቀና ብለው ።

«ከጠቅላይ ግዛቱ የትምህርት ቤቶች ስራ አስኪያጅ ጋር ስለስራዬ የምንነጋገረው ጉዳይ ስላለ ነው ። ዛሬ ማታ እመለሳለሁ ። ካልሆነም ከነገ አላልፍም» አላቸው ።

«ምንነው ብቻህን ታዲያ......»

«የለም ። ምንም ሰው አያስፈልገኝም» አላቸው ተጣድፎ ።

ከዚህ ላይ ነበር ትንሽ ጥርጣሬ ያደረባቸው ። በስርጉ ማግስት የምስራች አልተባሉም ። የአባትነት ወግ አልደ ረሳቸውም ። የቤት አሽከሮች ሹክሹክታ ሳይወዱ በግድ ከጆሮአቸው እየገባ የልጃቸውን ክብረ ንፅህና በአንደ ፊት እንዲጠራጠሩ ሲያደርጋቸው በሌላ በኩል ደግሞ የሚወዱትን አንዷን ልጃቸውን በመጠራጠራቸው የገዛ ህሊናቸው መልሶ እየወነጀላቸው ለሰው አያዋዩት ነገር ብቻቸውን ጥሬ እንዳጣ ፈረስ እህህ እያሉ ተጨንቀው ነበር ። ሀዲስ በድንገት ተነስቶ ወደመቱ መሄዱ ነው ሲላ ቸው የሚጠብጡት አሳብ ጠፍቶአቸው ሂድም ፤ ቅርም ሳይሉት ከዳዊታቸው ላይ እቀረቀሩ - ግን አያነብቡም ነበር ።

ሀዲስ ወደ ማጉሊ ቤቱ ተመልሶ አይናለምን በሰቀቀን አቅፎ ሳማት ። ለረጅም ጊዜ ትኩር ብሎ አይኖቿን ተመለከተ ። «እወድሻለሁ» ብሏት ወጣ ...

በበራሪ ቀዬታ የገባን ወንዝ አቋርጦ በኖጰ አልፎ ፣ በርጋታ የሚሳበውን የሶርን ወንዝ በመሻገር መቱ ከተማ ሲገባ ፣ ከጧቱ ገና አምስት ሰአት ነበር ። የገባን ግርማ ሞገስ ፣ የዲሲን ብርማ ጅረትና ለአይን የሚታክት የቡና ተክል ፣ የአፈሩን ጥቁረት ፣ የእፅዋቱን አረንጓዴነት ፣ ገና ድንግል የሆነውን የተፈጥሮ ልምላሜ እየተመለከተ ሲጓዝ ፣

«ወላጅ ኢትዮጵያ ለልጆቿ ብላ

እጅግ ሳይጥሩባት ሳይዘሯት አብቅላ» የተባለው የቀኝ ጌታ ዮፍታሄ ንጉሴ መዝሙር እየደጋገመ ከጆሮዎቹ ውስጥ ሲያስተጋባ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ፣

«ኢትዮጵያ — ድንግል አገር
ፀንሰሽ — ጥቁር አፈር

ምጥ ይዞሻል አሉ
«ማርያም ማርያም» በሉ ።
በፆምና ፀሎት አንገቷ ተደፍቶ
ክንዷ ሳይደክም እጅዋ ተዘርግቶ
ምን ነው እያየሀት



በሽልሟ ትውጣ ባክህ ተማለዳት» የሚል ድምፅ ሲሰማው በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ—

«አበባዬ አፍርቶ እሸቱ ካማረህ ፣
እንደባአድ ቆመህ ለምን ታየኛለህ?

ለብዙ ዘመናት እጆቼን ዘርግቼ በፆም በፀሎቴ እኔ
    ምማለደው ፣

በዛጉት እጆቼ ለራሱ ከሚቆርስ ሰውረኝ አምላኬ
    እያልኩ በልቅሶ ነው ።

ውዲቷ አገሬ እናት ኢትዮጵያ ብሎ ባንደበቱ ፣
የሚያሞጋግሰኝ ሞልቷል በየቤቱ ።

ምላስ አልነበረም እኔን የቸገረኝ ፣
ቤዛ የሚሆነኝ እጅ ነው ያጠረኝ ።
ባፉ ተናግሮ በእጁ ከሚክደኝ ፣
ከወጣቱ ትውልድ ከሸክም አድነኝ—

ከጋሬጣው ሳመልጥ ቆንጥር አበሳዬ
ሸማዬ አልቆብኝ ሲታይ ገበናዬ

ሰሩልኝ መርፌ ስል ልጆቼ ተምረው
ተኝተው ቀሩብኝ በቀለም ሰክረው

ቀለም ካሰከረው እጁ ከማይሰራ
አምላኬ ጠብቀኝ ሰውረኝ አደራ—

እያልኩ መማጠኔን አልተውም በርትቼ ፣

ወደፈጣሪዬ እጆቼን ዘርግቼ» እያለች በአይናለም ተመስላ ስታማውተው በመንገዱ መጥፎነት የተነሳ በሰውነቱ ላይ ይደርስ የነበረውን መጉላላት ለማጤን

ጊዜ አላገኘም ፡፡ መኪናዋ ቁልቁለቱን ስትወርድ በአፍጢሟ ለመደፋት ሲቃጣት ቀጥ ያለውን ዳገት ስትወጣ በቂጧ ለመቆም ሲከጅላት ፤ አንዳንዴ ወደጐን አዘንብላ የመንገዱን ጠርዝ በጐኗ ስትታከክ ፤ ጐማዎቿ ሲጤሱ ፤ ሞተሯ ኡኡ ሲል ፤ እንደ ሰንሰለት እጅ ለእጅ የተያያዙት ተሳፋሪዎች የተላቀቁት መቱ ሲደርሱ ነበር ፡፡

ሀዲስ ጊዜ አላጠፋም ፡፡ ሙላው ቢላቀቅም ፤ ከመኪናይቱ ወርዶ በቀጥታ ወደአንድ ቡና ቤት አመራ ፡፡ ገብቶ ገና ቁጭ ከማለቱ ፤ አንዲት ጠይም ፤ እጥር ምጥን ያለች ፤ ፊቷም አይኖቿም ፤ ጥርሶቿም የሚስቁ ኮረዳ መጥታ «ምን ይወስዳሉ?» ብላ ጠየቀችው ፡፡

በተለመደው አነጋገር «አንቺን» ብሎ መለሰላት ፡፡ የቀልድ ሳይሆን ከልቡ ነበር ፡፡ ወንድነቱ እንዳልከዳው ለማወቅ ነበር ከሱጺ በማለዳ ተነስቶ የመጣው ፡፡

«በቀን?» አለችው እየቀለደች ፡፡

«በጨለማ ብቻ እንዲሆን አስርቱ ቃላት ያዛል? ወይስ አንቺ እንደአስራ አንደኛው ቃላት አድርገሽ ያወጣሽው ደንብ አለ?»

«አስተማሪ ነዎት መሰለኝ — አንቱዬ»

«ማንባሬ ላይ ተፅፎአል?»

«ቀልዳችሁ ይመሳሰላል»

ሁለት ቢራ አዝዞ ሲጠጡና ሲጫወቱ ትንሽ ከቆዩ በሁዋላ ፤ ተያይዘው ወደጓዳ ገቡ ፡፡ ብርሀን በሌላት ፤ ግድግዳዎቿና ወለሏ በሰሌን ከተለበደ ካንዲት ትንሽ ክፍል ውስጥ እንደገቡ ፤ ቀሚሷን ከመቀፀበት ጥላ ከፊቱ ራቁቷን እየተረገረገች «ቶሎ ይበሉ አንቱዬ» አለችው ፡፡



«ጥድፊያው የት ለመድረስ ነው?» አላት ተበሳጭቶ ፡፡

«ለመተኛት ነዋ! ለዚህ አይደለም እንዴ የመጡት? ሌላ ደንበኛ ሊያመልጠኝ ይችላል ፡፡ እኔ ከዚህ ተገትሬ ፡፡ ጊዜ ወርቅ ነው ሲሉ አልሰሙም?» አለችው ፍርጥም ብላ ጉኗን እያከከች ፡፡ ድፍረቷን አልወደደም ፡፡ አይናውጣነቷ አስፈራው ፡፡ ስውነቱ ቀዘቀዘ ፡፡

«ለምን ርካሽ ትሆኛለሽ?» አላት ፤ ድምፁን ከወትሮው በላይ ከፍ አድርጐ ፡፡

«ላንድ ጊዜ አምስት ብር ጥሩ ዋጋ ነው! ሌላ አምስት ብር ከጨመሩልኝ አይከፋኝም — ደስ ይለኛል» አለችው ፡፡

ያላላውን የጫማ ክሩን አጥብቆ ተነስቶ ወጣ ፡፡ ሁኔታዋና ንግግሯ አልነበረም ያስቆጣው ፡፡ እንደፈራት ልቡ ያውቅ ነበር ፡፡ ሩቅ አልሄደም ፡፡ ግርግር የማይታይበት ጭር ያለ ቡና ቤት አይቶ ጐራ አለ ፡፡ ከመግባቱ ጠጉሩ እንደ ድል አጥቢያ አርበኞች ያጐፈረና ከለበሰው ልብስ ውስጥ ሾልኮ ሊወጣ የደረሰ ቀይ አጭር ወጣት ከሩቅ ሲመጣ ተመልክቶት ኖሮ ፤ ሮጦ ከአንገቱ ላይ ተጠመጠመበት……

«ሀዲስ ! ምን የተረገመ እግር ነው ከዚህ ከስልጣኔ ዳርቻ አምጥቶ ያገናኘን?» አለው ፤ ሀዲስን በማግኘቱ በደስታ ተውጦ ፡፡ አይኖቹና ፊቱ በመጠጥ ሀይል ቀልተዋል ፡፡ በአልኮል የተመረዘው ትንፋሹ ከሩቅ ይጋረፋል ፡፡ በቁመቱ ማጠር ላይ ከትከሻው ጐበጥ ስለሚል የተፈጥሮ ድንክ ይመስላል ፡፡ ከመንማናው ሰውነቱ በላይ ነግሶ የሚታየው ትልቅ ጭንቅላቱ ቢሆንም ፤ ያ ጐፈሬ ተጨምሮበት ጓሮ የበቀለ የጅብ ጥላ ስለሚመስል ፤ አላፊውና

አግዳሚው ሁሉ ከአንድም ሁለት ጊዜ ተገላምጦ ሳይመለከተው አያልፍም ። ሀዲስም የትምህርት ቤት ጓደኛውን በማግኘቱ ተደስቶ «አንተስ ከዚህ ምን አመጣህ?» ብሎ ጠየቀውና ሁለቱም ወንበር ይዘው ተቀመጡ ።

«ስደት ላይ ነኝ — ላንድ አመት ። የህዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር ቀጥሮኝ ነው የመጣሁት — ለጥናት ። ደግነቱ ሁለት ወር ቀርቶኛል ። ከአዲስ አበባ ውጭ ኑሮ ስደት ነው ። የምታነጋግረውና የምትከራከረው ሰው የለም — እዚህ ። አእምሮ ይበልዛል ። ሄደህ የምትደሰትበት ቦታ የለም — መለኪያ ከመጨበጥ ሌላ ከቢት እስከ ማታ ። ሰውነት ይደነዛል ። በየቀኑ መሻገት ነው — ከዚህ ከሻገተ ቦታ ጋር ። በስደት መሻገት ። ይሄው ነው ። ከመጣሁ ያገኘሁት ደስታ የለም ። ገንዘብ እንኳ አልቋጠርኩም ። ባዶ እጄን ወደዩኒቨርሲቲ መመለሴ ነው……»

ሀዲስ አቋረጠውና «በሄድክበት ሁሉ ደስታ እጅዋን ዘርግታ ትጠብቅሀለች ማን አለህ! ደስታ ራስህ የምትፈጥራት እንጂ አውላላ ሜዳ ላይ ቆማ የምትገኝ ነገር አይደለችም ። በነገራችን ላይ ያ ሁሉ መሬት ላራሹ—ሀብት ለባለወዙ ፤ ያ ሁሉ ለህዝብ ፤ በተለይ ላገር ቤቱ ህዝብ የነበረህ ተቆርቋሪነት — አሁን ከምን ጉድጓድ ውስጥ ገባ — ወይስ ከጨበጥከው መለኪያ ውስጥ ሟምቶ ቀረ?» አለው ፤ በትምህርት ቤት ጓደኛው ላይ የደረሰውን ለውጥ አይቶ በመገረም ። አንዳንድ የቀርብ ጓደኞቹ በስሙ ጠርተውት አያውቁም ። «ታርዛን» ነበር የሚሉት ። አብዛኛዎቹ ግን ማኦ እያሉ ያሞካሹታል ከላም በረት እጠገብ ታጉረው ለነበሩት ደሆች በመቆርቆር የተዋጣ ሰላማዊ ሰልፍ ከመራ ወዲህ ።



መንታ ህፃናት የታቀፈች ሴት ከቡና ቤቱ ደጃፍ ላይ ቆማ «ጡቶቼ ደረቁ — ስለገብርኤል — ገብርኤልን የመነ» ትላለች ድምፅዋን ከፍ አድርጋ ።

ሀዲስ ይቀጥላል — «ትምህርት እንደሆነ ከህዝቡ ትከሻ ላይ ወጥተን ቁጭ የምንልበት መሰላል ይመስለናል ። ከህዝቡ ደረጃ በምንወርድበት ጊዜ ስደት ግዞት እንለዋለን አሁን አንተ እንዳልከው ። ህዝቡን የምን ለውጠው ይመስለናል -- መሬት ላራሹ — ሁሉም ይማር እያሉ በመጮህ ። ይህ የአንደበት ተቆርቋሪነትም ቢሆን አንዱ ከሌላው ጥላ ስር ከሚደበቅበት ከሰላማዊ ሰልፍና ቅጥረ ግቢ ውስጥ ከሚደረግ ግርግር አያልፍም ። ራሳችንን እንወዳለን ። ለህዝቡ በልባችን ቅንጣት የምታህል ፍቅር የለንም ። ከሚጮህ ናስ አንሻልም ያለፍቅር ። ሀሊናችን ያንቀላፋል ። ወኔያችን ይሸናል ። እምነታችን ያወላውላል ። እምነቱ የሚያወላውልና ራሱን ወዳድ የሆነ ትውልድ ምን ጊዜም ቢሆን ህዝቡን ሊለውጠው አይችልም ። እኔ ምፈራው አሁን ከንፈሩን እየነከሰ በትዝብት አይን የሚመለከተን ህዝብ አንድ ቀን በኛ ላይ እንዳይነሳ ነው — የልብስ መርፌ ውለዱ ብሎ ……»

አፍንጫው በሙሉ ተጎርዶ ስርኑ የሚታይ ሌላ ለማኝ መጥቶ እየተነፋነፈ «ስለሙሉ አካላት ። አለሞቼ አበቦቹ» ይላል ። ከሁዋላው ባልና ሚስት እውራን በህፃን ልጃቸው እየተመሩ መጥተው ተራቸውን ይጠብቃሉ ።

ሀዲስ ይቀጥላል — «በአንፃሩ ፤ የህዝቡ እምነት የፀና ነው ። ሀይማኖቱ እንደጅማት የከረረ ነው ። አገሩን ይወዳል ። ለንጉስ ነገስቱ ክብር ይሞታል ። ባህሉን ያከብራል ። እንዲህ አይነቱን ህዝብ ታዲያ ልትለውጠው

የምትችለው በአፍ አይደለም ። በስራ ነው ። ሰርቶ በማሳየት ነው ። የኢትዮጵያ ስረየት የሚሰራ እጅ ነው……»

«አይ ሀዲስ — እጅ እጅ ማለትክን አሁንም አልተውክም!» አለው ታርዣን እየቀለደ ። ቀጠለና ፤ ቀልዱን ወደቁም ነገር ለውጦ «ተማሪ ሁሉ በአንድነት ተሰልፎ እንሂድ ሲል ፤ አንተ ከብዙ ሰልፍና ጩኸት ትንሽ ስራ ይበልጥ ይናገራል ብለህ ብቻህን ተነጥለህ የቀረህበት ጊዜ ትዝ ይልሀል? በዚያ አድራጎትህ ያተረፍከው ነገር ቢኖር ጆሮ ጠቢ የሚል ስም ነው! ትዝ ይልሀል?»

መላ ሰውነቱ በስጋ ደዌ የተፍተለተለ ሰው መጥቶ ቁስሉን እያሳየ ፡—

«እየው እጄ ሞቶ ፤ እየው እግሬ ሞቶ

ያስለፈልፈኛል ሆዴ ብቻ ቀርቶ» እያለ ይለምናል ።

«ትዝ ይለኛል» አለ ሀዲስ በረጅሙ ተንፍሶ — «ሺህ ሰዎች ተሳስተው አንዱ ብቻ ልክ ሊሆን ይችላል — ማለት — አዎን — መቶ አህዮች ባንድነት ቢያናፉ ፤ ከአንድ መሲንቆ የተሻለ ጣእም ሊኖራቸው አይችልም ። አሁንም ቢሆን እኔ የማምነው ከብዙ ምላስ በትንሽ ስራ ነው ። ኢትዮጵያ እጆቿን ወደሰማይ ዘርግታ ፀሎት ስታደርስ በቀለም ትምህርት 'ናላው ሰክሮ በእጁ መስራት ከማይፈልግ ትውልድ አድነኝ ሰውረኝ ብላ መለመን አለባት ። ለውጥ ብቻውን ላንድ አገር ህዝብ ደህንነት ምን የሚበጅ ይመስልሀል? ለውጥ ስለሆነ ብቻ በቀን ሶስት ሊትር ወተት የማትሰጠው ላም ሀያ አምስት ሊትር ልትታለብ አትችልም! ኢትዮጵያ የቸገራት ሰርቶ የሚያሳይ እጅ ነው … »



«በአገራችን የቀለም ትምህርት የቀሰሙ ሰዎች ከጥንት ጀምሮ በእጅ መስራት አይወዱም ። በኛ ብቻ አልተጀመረም ። በእጁ የሚሰራውን ቀጥቃጭ ፤ ባለእጅ ፤ ጠይብ ፤ ፉቂ እያሉ ይሰድቡትና ያዋርዱት ነበር ። በእጁ የሚሰራ ቄስና ደብተራ ፤ ባለስልጣንና ወታደር አልነበረም ። ነጋዴው መጫኛ ነካሽ ፤ ገበሬው አፈር ገፊ ይባላል ። የቀለም ትምህርት ያላቸው ጥቂት ሰዎች ከህዝቡ ትከሻ ወርደው አያውቁም ። በኛ ላይ ለምን ነውር መስሎ ታየህ?»

«አይኔን ግንባር ያር'ገው ብላችሁ አትማሉ

ይቸግር የለም ወይ መሬ ማባበሉ» እያለ እጆቹን ዘርግቶ ይለምናል ። አይኖቹ እንደሸማኔ መወርወሪያ ወዲህና ወዲያ የሚሉ ፉቱና አይኖቹ የቦዙ አንድ ሰው ለማኙን ገፍትሮ ይገባና በችኮላ መጠጥ ያዛል ። አይኖቹ ከሀዲስ አይለዩም ። ሀዲስ ቀና ባለ ቁጥር አይኖቻቸው ይጋጫሉ ።

ታርዣን ከፊቱ ያለውን መለኪያ አንስቶ መጠጡን ከጨለጠ በሁዋላ ይቀጥላል — «የተማረው ትውልድ አዲስ ፍጡር መስሎ ታየህ እንጂ ፤ የህብረተሰቡና የአካባቢው ውጤት ነው ። ልዩ ፍጡሮች አይደለንም ። እኛ ይድላን እናንተ የተማራችሁት መስዋእት ሁኑ በሚለው ፕሮፓጋንዳ ተመርዘሀል ። ለውጥ ከተባለ ሁሉንም የሚመለከት መሆን አለበት ። መሠረታዊ ለውጥ ። የኢትዮጵያ ስረየት መሰረታዊና ጠቅላላ ለውጥ ነው ። የኛ መለወጥ ብቻ አይደለም ጉዳዩ ። ለዚህ ደግሞ የደም ጠብታ ያስፈልጋል…»

«ባንተ መንገድ አላምንም» አለ ሀዲስ እየተበሳጨ — «ከህዝቡ አብራክ የተገኘህ መስለህ አትታየኝም —

ስመለከትህ — ሳዳምጥህ ። የህዝቡ ተረት አይጥምህም ። ባህሉ ባህልህ ፤ ኑሮው ኑሮህ ፤ አስተሳሰቡ አስተሳሰብህ አይደለም ። አንተ የምታልመውን ፤ ባእድ ህልምህን — ባእድ አሳብህን — ባእድ ለውጥህን ልትጭንበት ትፈልጋለህ ። ከህዝቡ ጋር የሚያገናኘን እትብት የተቆረጠብን አዲስ ጐሳ ነን ። ከህዝቡ ትከሻ ላይ ተቀምጦ በምቾት የሚያምን ጐሳ ። በደል ነው ። ሌላ የበደል ቀንበር...»

«አፍ ባክህ!» አለ ታርዛን ትእግስቱ አልቆ ።

«ስማኝ እንጂ!» አለና ሀዲስ ቀጥሎ — «እምን — የተማረው ወገን በምስራቅና በምእራብ የፖለቲካ ፍልስፍና ኢትዮጵያን ወዲህና ወዲያ ይጎትታል ። በስልጣን ላይ ያለው ወገን ፤ በዝግታ እናዝግም ፤ የለም ፍጥነት እንጨምር በሚል አሳብ እየተጋጨ አገሪቷን ወዲህና ወዲያ ይጎትታል ። በጉሳና በሀይማኖትም አገሪቷ ወዲህና ወዲያ እየተጎተተች ነው ። አስተሳሰር እስካሁን ያቆየን ገመድ እየመነመነ ሲሄድ ይታየኛል ። ይህን ገመድ እንደገና ለማጠንከር ፤ ከባእዳን የፖለቲካ ፍልስፍና ከጥቂት ሰዎች ጥቅምና ፍላጐት ፤ ከጉሳና ከሀይማኖት በላይ የሆነ ፤ ከኢትዮጵያውያን ባህርይ ፤ ልማድ ፤ ባህልና ኑሮ የመነጨ — ተነጥሮ የወጣ — የፖለቲካ ፍልስፍና (አይዲኦሎጂ) መመስረት አለብን......»

ታርዛን ትእግስቱን ጨርሶ ሌላ መጠጥ አዘዘና «አንተም ተወናብደህ እኔንም አወናበድከኝ» ይለዋል ።

ሀዲስ ይቀጥላል — «ባታቋርጠኝ ምናለበት! እንዲህ አይነቱን የፖለቲካ ፍልስፍና ለመመስረት አያስቸግርም ። መሰረቱ አለ ። በየትኛውም የኢትዮጵያ ግዛት ፤ እድር — ሰንበቴ — ማህበር — በምጣኔ ሀብት ረገድ



ደሞ — በጋላው አገር ደቦ — በትግሬው አገር ወፈራ በአማራው አገር ወበራ ይገኛሉ ። ስማቸው ይለያይ እንጂ አላማቸው አንድ ነው ። ይህ የሚያመለክተው ምንድን ነው? በለኝ ። የኢትዮጵያ ህዝብ ከጉሳና ከሀይማኖት በላይ የሆኑ በአላማና በግብር የሚመሳሰሉ የፖለቲካ ፤ የምጣኔ ሀብትና የማህበራዊ ኑሮ መሰረተ ፍልስፍናዎች አሉት ። በብሄራዊ ደረጃ የምንከተለው የፖለቲካ ፍልስፍና ከዚህ ተነጥሮ ቢወጣና የኑሮአችን አቋም በዚሁ ቢመሰረት — ህይወታችንን — ኑሮአችንን — አስተሳሰባችንና አለባበሳችንንም ጭምር በዚሁ ብንመራ የሚያስተሳስረንን ገመድ እናጠነክራለን ። አገራችንን ከየት ተነስተን ወዴት እንደምንመራ ለማወቅ እንችላለን ። መመሪያ ይኖረናል ። ለውጡም መሰረታዊ ይሆናል — ያለደም ጠብታ ። ለውጡ በሁሉም ዘንድ ትርጉም ይኖረዋል ። የእውራን ሩጫ አይሆንብንም — ጉዳዩ ይህ ከሆነ በመጀመሪያ ራሳችንን እንለውጥ ነው የምለው» አለና «እስቲ እጅህን አሳየኝ» ብሎ ታርዛንን ጠየቀው ።

ታርዛን ተገርሞ እጁን ይሰጠዋል ። ሀዲስ እጁን አገላብጦ ከተመለከተ በሁዋላ በተመሰጠ አነጋገር «አፈወርቅ ተክሌ የሚስላቸው ጣቶች ይመስላሉ ። ውብ አለንጋ መሳይ ። ግን ምን ያደርጋል ። የሀሊና ዝገት ምልክት መስለው ነው የሚታዩኝ» ይለዋል ።

በችኮላ የገባው ሰው ያስቀዳውን መጠጥ ሳይቀምስ እንደመጣ በፍጥነት ተመልሶ ይወጣል—ወደሁዋላ በመገላመጥ ሀዲስን በቀዥቃዣ አይኖቹ እያማተረ ።

«እጅ እጅ እንዳልክ እዚሁ ሻግተህ እንዳትቀር......»

«አልሻግትም ። አብባለሁ — ከህዝቡ ጋር ......»

«ባለቅኔ ለመሆን ምንም አልቀረህም ። ገና ከእን ቅልፉ እንደነቃ ሰው ነው የምትናገረው ። ምኑም አልተከ ሰተልህም ። ስልጣኔን ወደሁዋላ የሚጎትቱት ፤ ተስፋን ወደፊት የሚያራዝሙት እንዳንተ ያሉት ሰዎች ናቸው ። የምትሰብከው የፖለቲካ ዓላማ — አይዲኦሎጂ ምን እንደ ሚባል ታውቃለህ ? አዲስ አይደለም ። ሲሰራበት የኖረ ነው ። 'ኢዮብ — ኢዝም' ይባላል ። የራብ አለንጋ ሲገር ፍህ—ስትታረዝ ትእግስት ። ስትንገላታ ፥ መብትህ ሲገፈፍ —አፍህ ሲለጎም—ትእግስት ። ከአፍህ ስትነጠቅ ትእግ ስት ። በትእግስት ኖሮ በትእግስት መሞት ለሁሉም በለሁ ሉም ተመስገን ፈጣሪዬ እያሉ ። ሁሉም የሚሰብከው ትእ ግስት ነው—ባለስልጣኑ ፥ አገረ ገዢው— ካህናቱ—ባንድ ድምፅ ። 'ኢዮብ—ኢዝም' ይባላል ። ደሀነት ፥ ድንቁርናና በሽታን እተረፍን — በትእግስት ለትእግስት ፥ ስለት እግስት ። 'ኢዮብ — ኢዝም' እስከመቼ ድረስ ! ስሩ ! መቀነታችሁን ጠበቅ አድርጉ ። ስራም የሚ ጠብቅ አንጀትም የለም ። ይልቅ ይህን መካን ክርክር እንተውና እንጠጣ - . ስደተኝነታችንን እንድንረሳ! መጠጥ — በብዛት ናላ እስኪዞር ፤ ሲጃራ በብዛት — ሳንባ እስኪጠቁር ፤ ሴት በብዛት ወገብ እስኪበጠስ — ጤንነት ማለት ይህ ነው ። ለጤናችን......» ከማለቱ ፤ ያ በጥድ ፊያ ገብቶ ተመልሶ የወጣው ሰው ፤ ብረት የያዙ አራት ፖሊሶች አስከትሎ መጥቶ ሌባ ጣቱን ወደ ሀዲስ አመ ለከተ ። ሀዲስ ደንግጦ ሳይታወቀው ከተቀመጠበት ብድግ ሲል አራቱም ፖሊሶች የያዙትን ጠብ መንጃ አቀባብ ለው ደገኑበት ። «ታርዛን» ሀዲስን ደህና ዋል ሳይለው እንደ ልማዱ ግራ እጁን ከሱሪው ኪስ ከትቶ እንደ አንበጣ ወደጉን እየሄደ ሹልክ ብሎ ወጣ ።



ሀዲስ በፍርሀት ተውጦ ሰውነቱን እያላበው በተሰ ባበረ ድምፅ «ጥፋቴ ምንድንነው?» ብሎ ጠየቀ ።

አንዱ ፖሊስ ከሀዲስ እጆች ላይ የእጅ ብረት እያ ጠለቀ «ፖሊስ ጣቢያ ስትደርስ ትረዳዋለህ» አለው ። ጭር ብሎ የነበረው ቡና ቤት ከአፍ እስከገደፉ በሰው ተጨ ናንቆ መቆሚያ ጠፋ ።

«እጆቼ ከተቆነከሩ ኤሎሄ ኤሎሄ ከማለት ሌላ ምን ቀረኝ!» አለ ሀዲስ ነፍስ ገዝቶ ። ፖሊሱም ከመፅሀፉ ምሳሌ ጠቅሶ «ሰውም እንደ እጁ ስራ ዋጋውን ይቀበላል» አለ ውና በሰደፍ እየገፈተሩት አስቀድመውት ወጡ......

ሀዲስ ከሄደ ቀን ጀምረው የእይናለም አይኖች በቀን መንገድ መንገዱን እያዩ ማታ ማታ ደግሞ ጨለማውን እየዳሰሱ ከማልቀስ ቦዝነው አያውቁም ።

ቀኑ ጨፍግጓል ። ሰማዩ ፤ አንድ አንኮላ ኮሶ በጠጣ የጨለጠ ሰው ይመስል ፤ ግንባሩን ቋጥሯል ። ሱዳ ቦሮ በጭጋግ የድር ማግ የቱሰራ ከባድ ግራጫ ብርድ ልብስ ለብሳ ግራጫ ሆናለች ። ጥቁሩ አፈር ፤ ሳርና ቅጠሉ ድን

ጋዩ ሳይቀር ረጥቧል — በሀምሌ ካፍያ ። የአይናለም አይኖች ጉንጮቿ ሳይቀሩ ረጥበዋል — በእንባ ።

ፊቷ በእንባ ፤ ልብሷ በካፍያ እየረጠቡ ፤ ከአፍንጫዋና ከአፏ የሚወጣው ትኩስ ትንፋሽ ውስጧ እይነድ ርጥብ ማገዶ ይመስል ቡልቅ ቡልቅ እያለ የአዲሱን ትምህርት ቤት ግድግዳ ተጠግታ ብቻዋን ቆማለች ።

በሀዲስ እጅ የተገነባውን የትምህርት ቤቱን ግድግዳ በጉንጭዋ በዳሰሰች ቁጥር እርሱን ያገኘች ይመስል እንባ የሚያካፋት አይኖቿ ላንዳፍታ ተግ ይሉና ፤ መቃብሩ ላይ የቆመች በሚመስላት ጊዜ ደግሞ መልሰው እንደ ክረምት ፀሀይ ድርግም ይላሉ ። እንደሀምሌ ጉም ወሀ የቋጠሩት አይኖቿ መንገድ መንገዱን እያዩ ፤ ከሩቅ ሰውብቅ ባለ ቁጥር ልቧ እየደነገጠ ፤ መምሬ መሀረ ወይም የመቶ አለቃ አሸኔ ከፊታውራሪ ተካ ጋር ተነጋግረው በወጡ ቁጥር መንፈሷ እየተሸበረ ፤ ትንሽ ሹክሹክታና ማማታ እያስደነገጣት መሰቃየት ከጀመረች አስር ቀኖች አልፈዋል ። እህልና ወሀ ሳይሆን ተስፋ — ሀዲስን እንደገና የማየት ተስፋ — ነበር ከቀን ወደቀን የሚያራምዳት ።

ፊታውራሪ ተካም ቢሆኑ ሲያስቡት ከቤታቸው በድንገት በገባው ሀዘን ምክንያት በዝምታ ትክ ብለው ከማሰብና እህህ እያሉ በረጂሙ ደጋግመው ከመተንፈስ ሌላ የሚያደርጉት ነገር አልነበራቸውም ። ሀዲስ አቶ ይርጋ አለሙን ገድሏል ብለው ለማመንም ሆነ ላለማመን ተቸግረው መንፈሳቸው ባክኖ ነበር ። የልጃቸውን ሀዘን አይተው ሲጨንቃቸውና በአማቻቸው ላይ



መፍረድ ወይም አለመፍረድ ሲቸግራቸው ፤ ሀዲስ በተያዘ በማግስቱ ከሙቱ የፃፈላቸውን ደብዳቤ አውጥተው ያንብባሉ — ውድ አባቴ ሆይ — አቶ ይርጋ አለሙን ፣ የትምህርት ቤቱን ዲሬክተር ፤ ገድለሀል ተብዬ ሙቱ እንደደረስኩ በፖሊሶች መያዜን እስካሁን ሳይሰሙ አልቀሩም ። የሰው ልጅ ካለው ታላላቅ ፀጋዎች ውስጥ አንዱ እጅ ነው ። ስለሆነም ፤ እጄን ለስራ እንጂ ለጥፋት ዘርግቼ አላውቅም ። አልገደልኩም ። አቶ ይርጋ የበደሉኝ ነገር የለም ። በእጄ ህዝቡን ለማገልገል ያለኝ ብርቱ ስሜት ገፋፍቶኝ ስልጣናቸውን በመጋፋት የአዲሱን ትምህርት ቤት ስራ በመጀመሬ ይቅርታ ሳልጠይቃቸው በመሞታቸው ፀፀቱ ከልቤ አይጠፋም — እስቀይሜአቸዋለሁና ። አፈሩ አይክበዳቸው ። ደማቸው እንደማይፋረደኝ ግን አውቃለሁ ። እጄ ንፁህ ነውና …

ፍትህ የእጄን ዋጋ ትሰጠኝ ይሆናል ፤ ካልሰጠችኝም ሀሊናዬን የሚከብደው ነገር የለም ። የእርስዎን ታላቅ ውለታና የንፁህ ባለቤቴ የአይናለም ፍቅር ከልቤ ሙዳይ ውስጥ ተቆልፈው አብረውኝ ወደ መቃብር ይሄዳሉ ። አይለዩኝም ። ስራቸው ከልቤ ውስጥ ሆኖ ከመቃብሬ ላይ ወጥተው እንደሚያብቡ ተስፋ አለኝ …

ያመኑኝን ያሀል አሁን አይጠራጠሩኝ ። እጄ ንፁህ ነው ። ከቤትዎ የሀዘን መጋረጃ ስላመጣሁ ከእናንተ ይልቅ እኔን ሀዘኑ ይከብደኛል ። ሀዘኑ በበለጠ የሚከብደኝ ግን የጀመርኩት ትምህርት ቤት ስራ ከፍፃሜ ሳይደርስ ፤ ልጅ ያበካው ለራት አይበቃም እንዲሉ ፤ ቁሞ መቅረቱን በማ

ሰብበት ጊዜ ነው ። እሳቤ እድሜ አግኝቶ ህይወቴ ባጭሩ ቢቀር ግድ የለኝም ። ክርስቶስም የተሰቀለው በወጣትነት ዘመኑ ነው ። እሳቤን ከግቡ እንዲያደርሱልኝ አደራ እላለሁ ። ሰው የተወለደበትን እንጂ የሚሞትባትን ቦታ አያውቅም ያሉኝ ሁሉ ትዝ ይለኛል ። የእጄን ዋጋ እንደማገኝ ተስፋ አለኝ…

አቶ ይርጋ አለሙ ከግንባራቸው ላይ በጥይት ተመትተው ከትምህርት ቤቱ አጥር ስር ሞተው የተገኙት ሀዲስ አይናለምን በማለዳ ተሰናብቷት ወደመቱ በሄደበት ቀን ነበር ።

ፊታውራሪ ተካ የሀዲስን ደብዳቤ አንብበው ከጨረሱ በሁዋላ በአሳብ ተውጠው ቀርተው ኖሮ መምሬ መሀሪ መጥተው ከአጠገባቸው ሲቀመጡ ሁሉ ልብ አላደረጉም ። አይን ለአይን እንደተገናኙ «ዛሬም ያንኑ ደብዳቤ ነው የሚያነቡት?» ብለው መምሬ መሀሪ በመገረም ጠየቋቸው ።

«እንደ ዳዊት በየቀኑ እደግመዋለሁ ። ብቻ ይህን ደብዳቤ ባነበብኩ ቁጥር እያመንኩት ነው የምሄደው……»

«አሁንም ይጠራጠራሉ? ሰውዬውን ሲገድል ያየች የአይን ምስክር ተገኝታለች አሉ ። ቃሏን እንድትሰጥ ዛሬ የመቶ አለቃ አሸኔ ወደመቱ ይዟት ሲሄድ አኔም አይቻለሁ……»

«አይደረግም!» አሉ ፊታውራሪ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በእጃቸው የያዙትን ደብዳቤ ትኩር ብለው እየተመለከቱ ።



«ስሟም ሽታዬ ይባላል ። ሴትኛ አዳሪ ነች አሉ»

ፊታውራሪ በእጃቸው የያዙትን ደብዳቤ በማጭቀው ጥለው ሲያበቁ የሰው ልብ እንደመፅሀፍ ተገልጦ ሳይነበብ! ብለው ዝም አሉ ። አይኖቻቸው ደም ጉርሰው እሳት የሚተፉ መሰሉ ።

«እስካሁን አልነገርኩትም እንጂ ሌላም ጉድ አለ ። እርስዎ እንደሚያስቡት አይናለም ጧት በማለዳ እየተነሳች የምትሄደው ወደ ቤተክርስቲያን አይደለም……»

«ታዲያ ወዴት ነው?» አሉ መምሩ ሳይ አፍጥጠው ።

«በጧት እየተነሳች የምትሄደው ወደ አዲሱ ትምህርት ቤት ነው»

«ምን ልትሰራ?»

«እረ የሚገርም ነው ። ግድግዳውን በጉንጮችዋ እየዳሰሰች ፣ በጥፍሮቿ እየፏጠጠች ፣ ትሳለመዋለች እንደ ቤተክርስቲያን ። እጆቿን ወደሰማይ እየዘረጋች ትማለደዋለች — እንደፈጣሪ።»

«ትምህርት ቤቱን?»

«እንደ ቤተክርስቲያን! ተለክፋለች ። ሰው ባዶ ድንጋይ ሄዶ ከተሳለመ የጤንነት አይደለም ። ወደ ጠበል መውሰድ ያስፈልጋል — ጋኔኑ ጨርሶ ክንፉን ሳይዘረጋባት» አሉ መምሩ ፣ ባንድ ትንፋሽ በሆዳቸው የያዙትን ቶሎ ለማውጣት የፈለጉ ይመስል ።

ፊታውራሪ ተካ አንገታቸውን በሀዘን ወደመሬት ደፍተው ተበጣጭቆ ከፊታቸው የተበተነውን ደብዳቤ በአይናቸው እየቆጠሩ «ልጄን የለከፍኳት እኔ ነኝ — ጋኔን አይደለም ። በእፎይታ ወደመቃብሬ እንዳልሄድ — የማታ ማታ ሀዘን አጥንት የሚሰብር — መቃብር የገባ ምንኛ አረፈ? ሰላም — ፀጥታ — የልጅ ልቅሶ የማይሰማበት......»

መምሬ መሀሪ ከተቀመጡበት ተነስተው በመስቀላቸው እራቱን ማእዘናት እያማተቡ «በአልቄይቱ ማርያም እንዲህ አይዘኑ ። እርሷ ምንም የለባትም ። ትንሽ ጠበል ነው የሚያድናት ።»

ፊታውራሪ የመምሬ መሀሪን ምክር የሰሙ አይመስሉም ። አቀርቅረው «መቃብር — የልጅ ልቅሶ የማይሰማበት አለም — ያመኑት የማይከዳበት አለም — የጊዜ እግረ — ሙቅ......ሰንሰለት...... ቀጠሮ የሌለበት ከጊዜ ውጪ የሚኮንበት አለም — ዘለአለማዊ ። ይናፍቃል አንዳንዴ የመቃብር አለም — የአፈር ትራስ — ጥቁር አፈር......»

«ኧረ እንዲህ አይበሉ ። ፊትዎን በፆም በፀሎት ወደ ፈጣሪዎ ይመልሱ ። እድሜን ከሽበት ጋር የሰጠዎት ፈጣሪ ምስጋናው ይህ አይደለም......»

«እህህ ብቻ ሆኖ ቀረ የማታ እድሌ ። እፎይ በምልበት ሰአት ሀዘን — ታፍሬ በምከበርበት ሰአት ውርደት — ድንጋይም ይሸብታል ሲሸግት — ምንኛ ይናፍቃል የመቃብር አለም — የአፈር ቡሉኮ — የድንጋይ ትራስ......»



«ምንነው ፊታውራሪ — የእርስዎ የመንፈስ ብርታት የሚታወቀው በመከራ ጊዜ ነበር......ስንቱን መከራ በትእግስት በቆራጥነት አሳልፈው አሁን ለትንሹ ነገር ለምን እንዲህ ተስፋ ይቆርጣሉ? ልጅቷ እንደሆነች በጠበል ትድናለች ። እድሜዋም ገና ነው ። እርሱም ቢሆን የእጁን ዋጋ ያገኛል ። እርሱ በበደለ እርስዎ ምናለብዎት?» — የመምሩ መስቀል እንደተደገነ ነው ። በግራ እጃቸው ነጭ ጭራ ይዘዋል — ዝንብ ቢኖርም ባይኖርም ሁልጊዜ ስራ የማትፈታ ።

ፊታውራሪ ከተቀመጡበት ተነስተው እየተንጐራደዱ ፤ «ሊፈትነኝ ነው ይሆን ጉድ ባንዴ አምጥቶ የከመረብኝ ። እንደኢዮብ ሰውነቴ አይቁሰል እንጂ በልጄ ሀዘን ልቤ ቆስሏል ። እንደቶማስ ያመንኩትን ሰው መንፈሴ አልጠና ብሎ ይከዳል ። ግን ሆዴ እሺ አይልም ። ልጄም በሊጋ እድሜዋ እንደራሄል — እንደጲላጦስ ከደሙ ንፁህ ነኝ አልል ነገር! እጄ ንፁህ ነው ይለኛል ። ልቤ ዮሀንስ መጥምቁ እንደመኘበት ምድረበዳ — ያሳደግሁት ልጄ ቶሎሳም ሀዲስ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ ጤና የለውም ። ከመሬት ተነስቶ ይባንናል ። እንቅልፍ የለውም ። እዚህ ላይ ያመኛል ብሎ አይናገርም — መተከዝ ፤ አይኑ እያየ መባነን ብቻ......» »

«ልክፍት እንደሆነ — ወደ ጠበል መውሰድ ነው ። እኔ ዘንድ ና ብለው ሸሸኝ ። መስቀል ሲያይ ይበረግጋል ። ይህ ራሱ ለመለከፉ አንድ ምልክት ነው ። በቤቱ የመጣውን ቁጣ እንዲመልስልን እግዚኦ ማለት ነው ። ማማረር አይገባም......»

ከፊታውራሪ አያና መቃብር ላይ ገረዷ የፈረከሰችው ድስት ከፊታቸው መጥቶ ተደቀነ ።

ከንቱ ድካም ።

ገል ።

የገል ስባሪ ። ህይወት ።

በእለተ አርብ — እንደ ክርስቶስ ። እኩለ ቀን ሆኗል ። ከጠራው ሰማይ እምብርት ላይ የተንጠለጠለች የምትመስል ፀሀይ በጨረሮቿ ወስፌ በቀጥታ እናት ትወጋለች ። ጥላው በየሰዉ እግር ስር ጥቁር ኩሬዎች አብጅቷል ።

ወበቅ ። አቧራ ። ላብ ። አቧራና ላብ ። ወበቅ ። ሁልቁ መሳፍርት የሌለው ህዝብ — ጃንጥላዎች — ቀይ ሻሽ — ነጭ ሻሽ — ጐፈሬ — ሹሩባ ፤ ሳዱላ — ጋሜ — በያይነቱ ። ትልቅ የዶሮ ገበያ መስሏል ። ግን ህዝቡ የሚገበያየው ነገር የለም ። ከሩቅ እንደሚሰማ የንብ መንጋ እያመመ ወደላይ አንጋጦ ለሰው መስቀያ ማለዳ በጠዋት የተበጀውን ቋሞ ከመመልከት በቀር ። ሁሉም ያችን ደቂቃ ይጠብቃል ። ነጋሪት ተጐሽሞ ክተት የታወጀ



ይመስል በእግር ፤ በፈረስ ፤ በበቅሎ ገና የሚመጡ ሰዎች ይታያሉ—ወደገበያው ቦታ ። በብዙ ምንጮችና ድንገተኛ ጐርፎች መመገብ እንደጀመረ እንደክረምት ሀይቅ የስንበተ ጉዳ ገበያ በህዝብ ብዛት እየሰፋ — እየሰፋ ይሄዳል — በየደቂቃው — ዘግይተው የደረሱት ሰዎች የመስቀያው እንጨት ካለበት ቦታ እየራቁ — እየራቁ — ተንጠራርተው ከሩቅ ለማየት እንኳ እያቃታቸው ። ወበቅ ። አቧራ ። ላብ ። አቧራና ላብ ። ወበቅ ። ግፊያ ። የሰው ነጭ — ትርምስ — ሰው በሰው ላይ ተደራርቦ — ሰጋ እንዳየ ጉንዳን ።

አንድ ወንጀለኛ በአደባባይ እንዲሰቀል የሚደረገው ለሌላው መቀጣጫ እንዲሆን ታስቦ ቢሆንም ፤ በሰንበተ ጉዳ ገበያ በተሰበሰበው ህዝብ ፊት ላይ የሚነበብ ነገር ቢኖር ፤ ድንቅ ትርኢት ተመልክቶ ለመደሰት የመጣ ህዝብ ስሜት አይነት ነው ።

በአደባባይ በገመድ ማፍ ተንጠልጥሎ ላንድ ሴኮንድም ብትሆን ለመኖር በከንቱ የሚፈራገጥ ሰው ከማየት የበለጠ ብርቅ የህይወት ድራማ ምናለ? ደስታ የሚገኘው አስቂኝ ትርኢት በማየት ብቻ ሳይሆን ፤ የሚያሳዝነውንና ሀሊና የሚሰቀጥጠውንም ጭምር በማየት ስለሆነ ፤ ወንጀለኛ በአደባባይ ተሰቅሎ እንዲሞት በተደረገ ቁጥር ተመልካቹ ህዝብ ድራማው እንዲያስተላልፍ ከታሰበው መልእክት ይልቅ ከትርኢቱ ውበት ላይ ያተኩራል ። ይህም በመሆኑ ፤ በአደባባይ እንዲሰቀሉ የሚደረጉት ወንጀለኞች ሲፈሩ ሀዘንን ፤ የቆራጥነት ስሜት ሲያሳዩ የሞራል ድጋፍን ከህዝቡ ያገኛሉ — ሜድረክ ላይ እንደሚታዩ መሪ ተዋንያን ። ከዚያ ከዚያች ደቂቃ ወይም ሴኮንድ በሁዋላ ተመል

ካቹ ህዝብ አዬ ምን የሞተ ነው! ሽንቱን ለቀቀው’ኮ — አስታወከው — ከፍርሀቱ ብዛት...... እያሉ በመታዘብ ፤ ወይም ወንድ ነው — ጀግና — ልበሙሉ — ገመዱን ራሱ ካንገቱ አጥልቋት ተወረወረ’ኮ ...... እያሉ በማድነቅ ፤ ወይም ሲመጣ በፉከራው ብቻ አንድ ሰራዊት ይፈታ ነበር — ግን ምን ይሆናል — በመጨረሻ እንዲያ ተልፈ ሰፍሶ — ሬሳው’ኮ ነው የተሰቀለው...... እያሉ በማዘን ፤ የወንጀለኛውን ባህርይ ፤ ማንነቱንና የፈፀመውን ወንጀል በመመርመር በተመለከቱት ተደስተው ከመመለስ ሌላ ፤ ነግ በኔ የሚል ትምህርት ቀስመው የተመለሱበት ጊዜ ይኖር ይሆን? — ከክርስቶስ ስቅለት ጀምሮ? ተጀምሮ ከፍፃሜ ሳይደርስ ከቆመው ትምህርት ቤት ፊት ለፊት በሰንበቱ ጉዳ ገበያ የተሰበሰበውም ህዝብ ፤ የሀዲስ ሳህሌ ባህርይ ከየትኛው ወገን ይሆን? በፍርሀት ይልፈሰፈስ ይሆን? ይፎክር ይሆን? የርግማን ናዳ ያወርድ ይሆን? ቁራጥ ይሆን — ገመዱን ካንገቱ በገዛ እጁ የሚያጠልቅ? ወይስ ፀሎተኛ — የአለምን አራቱን ማእዘናት እየዞረ የሚሳለም? እያለ ነበር የዛቺን ደቂቃ ድራማ በናፍቆት የሚጠባበቀው — ትእግስቱ አልቆ ፡፡

ሀዲስ የፊጥኝ እንደታሰረ በፖሊሶች ታጅቦ መጥቶ ከመስቀያው ስር ከቆመው በርሜል ላይ በፖሊሶቹ አማካይነት እንደወጣ ወደአንዱ ፖሊስ ዞሮ እጄ እንደታሰረ አትስቀሉኝ ፤ የመጨረሻ ልመናዬ ይሄው ነው ይለዋል ፡፡ ፖሊሶቹ አርስ በርሳቸው ክርክር እንደጀመሩ አይኖቹን ወደ ህዝቡ አዞረ — ለድራማ የተዘጋጀ ህዝብ — እልልታው ካንድ በኩል ይቀልጣል ፡፡ ከመስቀያው ቦታ ትንሽ ራቅ ብላ አይናለም በነጭ ረጅም ቀሚስ አጊጣ ፤ ረጅም ጠጉሮቿን ለቃ ፤ እጆቿን ወደሰማይ ዘርግታ ፤ እንባ የሚያንገረገሩትን አይኖቿን ከሰማዩ ላይ ተክላ ቆማለች — እንደሀውልት ቁሞ የቀረውን ትምህርት ቤት ወደሁዋላ ዙሮ ላንዳፍታ ትክ ብሎ ተመለከተው ፡፡ አይናለምና ትምህርት ቤቱ ሲዋሀዱ በአሳቡ ታየው ፡፡ እርሷ ወዳለችበት ተመልሶ ሲዞር ከቦታው አጣት ፡፡



እጁ ተፈታ ፡፡

ህዝቡ በአንድ ድምፅ እንደገባ ወንዝ ፍፍቱ ኢያሰተጋባ ፤ እንደእጅህ ስራ ዋጋህን ትቀበላለህ! እንደእጅህ ስራ ዋጋህን ትቀበላለህ...... እያለ ሲጮህበት አሳቡ ሺህ ዘመናት ወደሁዋላ ተጉዞ ክርስቶስ ከተሰቀለበት እለት — እለተ አርብ — ላይ አረፈ ፡፡

ስቀለው! ስቀለው!......

ጲላጦስም እጁን ታጠበ ፡፡

ሀዲስም እጆቹን እንደባእድ ቆጠራቸው ፡፡ ህይወቱን ለማዳን እንዳይከላከልባቸው ቃል ገብቷልና! እጆቹም እንደጲላጦስ ከደሙ ንፁህ ነን በማለት ሲደነዝዙ ተሰማው ፡፡ እጁን ወደፈታለት ፖሊስ ዞሮ ከዚያ ጥቁር አፈር — ጥቁር ድንግል አፈር ቆንጥረህ አቅምሰኝ ብሎ ለመነ ፡፡

መሬት ነህና ወደመሬትም ትመለሳለህ እንዲሉ?

አይደለም

ታዲያ ጥቁር አፈር ለምን?

የኔ ስጋ ወደሙ ጥቁር አፈር ነው ፡፡ ባክህ ቆንጥረህ አቅምሰኝ ፡፡ ስጋ ወደሙ ፡፡

ጥቁሩን አፈር ቆንጥሮ ያቀምሰዋል ፖሊሱ ። ሀዲስም ጥቁሩን አፈር አጣጥሞ ይውጣል ። አይናለምን በአይናቹ ይፈልጋታል ። የለችም ። አዲሱን ትምህርት ቤት ለመጨረሻ ጊዜ ሳንዳፍታ ይመለከትና ወደገመዱ ቀና ይላል——

ከጥቁር አፈር ወደጥቁር አፈር ። የህይወት ኡደት— ይህ ሞት አይባልም ። ለኔ ። እንደገና ሳብብ ይታየኛል ። ይህ ጥቁር አፈር — ይህ ስጋ ወደሙ — ይህ ቤዛ ። አንድ ነበርን ። አንድ እንሆናለን — እንደገና ። እትብቱ ወደተቀበረበት ጥቁር አፈር ትንሽ ጉዞ — ያለስንቅ ። እትብቴን ፍለጋ ።

ስቀለው! ስቀለው!......

እንደ እጅህ ስራ ዋጋህን ትቀበላለህ! እንደ እጅህ ስራ ዋጋህን ትቀበላለህ...... ትቀበላለህ......

ገመዱ ካንገቱ እንድትጠልቅ ተደርጋ የቆመበት በርሚል ከእግሩ ስር ተገፍቶ እንደወደቀ ፤ ደንዝዘው የነበሩት እጆቹ አላስችል ብሏቸው ከገመዱ ጋር መታገል ሲጀምሩ...... ሀዲስ ባንኖ ከእንቅልፉ ይነቃል ። እጆቹ ከጉሮሮው ላይ ተጠምጥመው ነበር ።

በእንቅልፍ ልቡ እየተፈራገጠ ሲያጓራ የሰሙት ካጠገቡ የተኙት አንዳንድ እስረኞች ይነቃሉ ። «ምንነው፣ ደህና?» ይለዋል አንዱ በጐረና ድምፅ ።

«መጥፎ ህልም አይቼ ነው ፤ ደህና ነኝ» ብሎ ይመልስለታል ፤ ሰውነቱ እየተንቀጠቀጠና እጆቹን በጭለማው ለማየት እየሞከረ ።

«የመጥፎ ህልም ትርጉሙ ጥሩ ነው ይላሉ» ብሎት ከአጟራው ውስጥ እንደ እቃ ጥቅልል ብሎ ይተኛል የተራበው አንጀቱ እያተረመረመ ። ሀዲስ ለመተኛት ይሞክራል ። ግን አይሆንለትም ። ህልሙ ይዘገንነዋል ።

መሬትን ከሰማይ የሚደባልቅ ዝናብ ይወርዳል — አልፎ አልፎ መብረቅ እየቀላቀለ — ሰማዩ በቁጣ እያጉረመረመ ። የታሰሩባት ደሳሳዋ ጐጆ ዝናብ ታንጠባጥባለች ። የአፈሩ ሽታ ከእስረኞቹ ጠረን ጋር እየተቀላቀለ ክፍሏን ማወድ ይጀምራል......እና ያስታውሳል ። መቆምአቅቷት ከጐንና ከጐኗ በምሰሶ ተደግፋ ቀናን እንዲያራዝምላት በማጐንበስ ፀሎት የምታደርግ — የሳር ጐጆ — የሚተኙበትን አልጋ ፤ ያገኙትን የሚያበስሉበትን ምድጃ ፤ ያላቸውን ንብረት በሙሉ የሚያጉሩባትን ጓዳ ሁሉንም በአንድነት እንደለማኝ ስልቻ አምቃ የያዘች ፤ ከእናቱ ጋር ገብቶ ሲተኛባት የምትሞቀው የህፃንነት ዘመን ትንሽ አለም ። ዝናብ በሚያንጠባጥብበት ትይዩ እናቱ የሚደቅኑት ሳፋ ከነጠብጣቦቹ ጋራ እየተነጋገረ የሚሰጠው ድምፅ ከጆሮዎቹ መጥቶ ያስተጋባል ። እና ፤ ሀዘን በተመላበት ልብ የእናቱ ሻካራ እጆች እየደባበሱት ይሰጡት የነበሩትን የህይወት ዋስትና ያስታውሰዋል ።

ሀዲስ አባቱን በዝና እንጂ ፤ በመክል አያውቃቸውም ። አባቱ የሞቱት ገና ጡት በሚጠባበት ወቅት ነበር ። አባቱ ሲሞቱ የተውለት ቅርስ ከጐጆዋ ግድግዳ ላይ እንደጌጥ ተንጠልጥሎ የሚኖር ፤ ከጊዜ ብዛት ማህደሩ በጥቀርሻ የጠቆረ አንድ ትልቅ ዳዊት ብቻ ነበር ። ሀዲስ ግን መንደር እየሄደ አማርኛ በሚማርበት ዘመን ሁሉ ተጠቅሞበት አያውቅም ። መምሬ ሳህሌ በህይወት በነበሩበት ዘመን ዳዊታቸውን ከጉያቸው ፤ መስቀላቸውን

ከእጃቸው አይለዩም ነበር ይባላል ። በኑዛዜአቸው መሰረት መስቀሉን ከደረታቸው ላይ እንደያዙ ከልደታ ማርያም ጋር ተቀበሩ ። አባቱ ከሞቱ ወዲህ እናቱ ሌላ ተስፋ ስላልነበራቸው ፣ ሀዲስ ትምህርት ቤት ውሎ በተመለሰ ቁጥር «ልጄ — እጅህ እንዳይዝግ ብትሰራበትስ — የድሀ እንጀራ እጁና ትከሻው ናቸው» ይሉታል ። ጭራሮና ቅጠል ለቀማ ወደጓሮ ይዞራል ። እንጀራ ይሁን ጥሬ ፣ ያገኘውን ከእናቱ ጋራ ተካፍሎ ሲያበቃ ፣ እናቱ ፣ ልትወድም የደረሰችውን እሳት እየቆሰቆሱ ፣ «ሰርቶ የሚያበላህ ፣ ቆርሶ የሚያጐርስህ ፣ ከጠላት ተከላክሎ የሚያስጥልህ እጅ ለሰጠህ አምላክ ምስጋና አድርሰህ ተኛ» ይሉታል እሳቷ እስክትወድም ድረስ ሲነጋ ምኑን ከምን አድርገው ቀኑን እንደሚያሳልፉት እያሰቡ ። ከቀን ወደቀን መራመድ — ይሄው ነበር ትልቁ አሳባቸው — አንዳንዴ መሸቶ መንጋቱን እየጠሉ — ግን ለአንዱ ልጃቸው የነበራቸው ፍቅር ብርታት እየሰጣቸው ሲኖሩ ሀዲስ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርቱን በማአረግ አልፎ ፣ አንድ ወር ስራ ፍለጋ ሲንከራተት ከቆየ በሁዋላ ፣ መጠነኛ ስራ ማግኘቱን ሲነግራቸው ልቡ እየፈነደቀ ፣ በወር መጨረሻ ላይ ደመወዙን ሲያገኝ ለእናቱ የሚያደርገውን እያሰበ ከቤት ሲደርስ ከመጠን በላይ ደክመው ያገኛቸዋል ። የተነጋገሩትን አንድባንድ ያስታውሳል ፣—

«ምን ነው እማዬ?»

«ደከምኩ ልጄ!»

«ስራ አገኘሁ'ኮ»

«እጅ እጅህን ስጠብቅ ኖርኩ ። እጆችህ ጡቶቼን ይዘው መጥባት ከጀመርክ ጊዜ አንስቶ የምሽት ቀን አለኝታዎቼ እላቸው ነበር ። ደከምኩ ልጄ ። በቃኝ መሰለኝ......»



«እማዬ — ደርሼልሻለሁ'ኮ ......»

«እኔ ግን አልደረስኩብህም ......»

«እማዬ!»

«የነካሽው ነገር ሁሉ ይለምልም ። እጅህ ርጥብ ይሁን ። የእግዜር ትንሽ እጅ ይሁን ። በጅህ ክፉ አትስራ ። ለራስህ ብቻ አትቁረስበት ። ለሌላም በረከት አድርገው ።» የመጨረሻ ቃላቸው ነበር ።

ሀዲስ በከባድ ሀዘን ተውጦ ፣ ራሱንና ፈጣሪውን እያማረረ ፣ እናቱ ሲጠባበቋቸው የኖሩትን እጆቹን እየረገመ ፣ ሁለት ወር ያህል ከአዲሱ ስራው ላይ ከቆየ በሁዋላ ፣ ባጠራቀመው ገንዘብ የእናቱን ቤት በማሳደስ በአስራ አምስት ብር አከራይቶ ፣ በተረፈው ገንዘብ አዲስ ልብሶችና ጫማ ገዝቶ ትምህርቱን ለመቀጠል ከቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ ዩኒቨርሲቲ ገባ ። እናቱን ያልረዱትን እጆቹን ለአገሩ — ለኢትዮጵያ እናቱ — ለማዋል የቆረጠው ያኔ ነበር ። የሚሰራ እጅ ለኢትዮጵያ ስረየት መሆኑን አዘወትሮ ስለሚናገር የትምህርት ቤት ጓደኞቹ የእጅ ፈላስፋ እያሉ እንደቀልድ አድርገው ይሳለቁበት ነበር ።

እግዜር ሁለት እጆች የሰጠን እንድንሰራባቸው ነው ። አእምሮ ያሰበውን ፣ ያንን ስራ ላይ እጅ ማዋል አለበት ። በእጅ አማካይነት በስራ ያልተገለጠ አሳብ የማይታይ ፣ የጋን መብራት ሆኖ ይቀራል ። ርግጥ አለም በአሳብ ባህር የሚዋኙ መለኮት የሚታያቸው ሰዎች ያስፈልጓታል ። አለ እነርሱ ወደፊት ልትራመድ አትችልም ። ይሁን እንጂ ፣ የአክሱም ሀውልቶችና የላሊበላ አብያተ

ክርስቲያናት የታነፁት በሀልም ብቻ አይደለም ። በእጅ ነው ። የፖለቲካ ፍልስፍናን በመለፈፍ ብቻ ኢትዮጵያን እናሻሽላለን ማለት ዘበት ነው ። የመንፈስ ደካማነት ምልክት ሊሆን ይችላል ። ምላስን ከማወናጨፍ ይልቅ እጅን ለትንሽ ስራ መዘርጋት የበለጠ ወኔን ፣ ቆራጥነትንና መስዋእትነትን ይጠይቃል…… እያለ ከጓደኞቹ ጋር ከመከራከር ቦዝኖ አያውቅም ።

እጅ እጅ እልክ ይሉታል ተናግሮ በጨረሰ ቁጥር ።

አዲስ ሀይማኖት ነውክ……የኢትዮጵያ ስረየት ይለው የለም እንዴ! እጅ ቤዛ ሲሆን በክርስቶስ ምትክ ። አዲስ ሀይማኖት ነው — ጋሪውን ከፈረሱ የሚያስቀድም ሀይማኖት — እጅን የሚያንቀሳቅሰው አእምሮ እንዳልሆነ ሁሉ…… ይሉታል ፣ እየተሳሳቁበት ።

የለምኮ! አእምሮን የሚመራው እጅ ነው ማለቴ አይደለም ። እጅ ለስራ እንዲቃጣ የማያደርግ አእምሮ ህሊና — ቢስ ነው ለማለት ነው…… ብሎ ክርክር ሲጀምር ጥለውት ይሄዳሉ ። አያዳምጡትም ። እርሱም ቢሆን ከመናገር ሌላ እጁን በስራ ፈትኖ አለማወቁን እየተገነዘበው በመሄዱ ከጊዜ በሁዋላ የህሊና ግጭት አድሮበት ያስጨንቀው ነበር ።

ሀዲስ — በእጅ ማምለክህን ተውከው እንዴ? — ብዙዎቹ የሚያቀርቡለት ጥያቄ ነበር ።

በስራ የማይገልጡትን መናገር ምላስን ማባለግ ነው ። የባለገች ምላስ ህሊና ላይ ታምፃለች ። እምነትና ድርጊት ከተለያዩ ምሰሶው በምስጥ እንደተበላ ቤት መዛግ ከዚያም መፍረስ ይመጣል — ወና ቤት መሆን ። ግን…… እምን……ሰውን ሰው የሚያሰኘው በአሳብ ፀንቶ እምነ



ትን ከድርጊት ጋር ማስተባበር መሆኑን ስንቶቻችን እናውቃለን፣ እምነቱ ከድርጊቱ የተለየ ሰው ወኔ የለውም — ውሸት — ስብቀት ሀሜት — ተደልሎ — መደለል የግል ምልክቱ ናቸው ። አድር ባይ ፣ ጨዋ መሳይ በሸንጐ ይሆናል ። ሆዳም ነው ። ምቾትን ያመልካል ። ምቾቱን ለመጠበቅ ሲል መሳሪያ ይሆናል ። ከኢትዮጵያ ጥቅሙን ያስቀድማል ። ግን በእሱ ፣ ህሊናው ላይ ባመፀች ምላሱ ፣ በደል ፣ ጥቃት ፣ ፍትህ እያለ መጮሁ አይቀርም ። እንዲህ አይነቶቹ ሰዎች እየበዙ በሄዱ ቁጥር ፍትህ ትላላለች ። መተማመን ጠፍቶ ጥርጣሬ ያይላል ፤ ህብረት ጠፍቶ በየአግጣጫው ማፈንገጥ ይነግሳል ። እምነት ትጠፋለች ። እንዲህ አይነቶቹ ሰዎች ለማንኛውም ጥቃት ምንኛ ምቹ ይሆኑ ! እንዲህ አይነቶቹ ሰዎች እኛው ነን — እኔ — አንተ ። ስለዚህ ፣ የሌባ ጣታችንን ወደ ሌላ ከመጠቆም ፣ ወደኛው መልሰን ፤ ራሳችንን በአይነ ህሊናችን እንመልከት ። መሻሻል ያስፈልገናል ግን መሻሻል ሲባል የሚጀመረው በያንዳንዱ አእምሮ ውስጥ መሆን አለበት — አለዚያ መሻሻል በተለይ በባእድ አሳብ ላይ የተመሰረተ መሻሻል ትርጉም አይኖረውም ። ድሪቶ ይሆናል ። እውነተኛ መሻሻል ከያንዳንዱ አእምሮ ውስጥ መመንጨት አለበት —

————ዝምታ ።

የጓደኞቹ ዝምታ ራሱን መልሶ እንዲጠራጠር ያደርገው ነበር ። ራሱን በተጠራጠረ ቁጥር የእናቱ ድምፅ ከጆሮው ውስጥ መጥቶ ያስተጋባል ።

ወደሱዳ ቦሮ መጥቶ የአዲሱን ትምህርት ቤት ስራ ከጀመረ ወዲህ እጆቹ ከስራ ላይ ውለው ፣ አሳቡና ድርጊቱ

ተገናኝተው በማየቱ እምነቱ እየጠነከረ ህይወቱ አዲስ ትርጉም እያገኘች ፣ ከትምህርቱ ቤት ሀንጃ ጋር እያደጉ ፣ ቁመትና ወርድ እየጨመሩ ይሄዱ ነበር ። ከትምህርት ቤቱ የተለየ ህይወት እንዳልነበረው አድርጐ ነበር ሀል ውናውን የሚመለከተው ። በአሳቡ አይናለምም ብትሆን ከትምህርት ቤቱ የተለየ ግላዊ ሀልውና የላትም ። አሁን ግን……እምን……እጃቹ ታስረዋል ። የትምህርት ቤቱ ስራ ቆሟል ። የአይናለም ፍቅር በጅምር ቀርቷል ። ህይወቱም አብራ የቆመች መስላ ነበር የምትታየው ። የውፎቹ ዝማሬ ንጋትን ቢያበስርም ፣ የቀኑን መጥቶ መሄድ ከማየት ሌላ የሚጠብቀው ነገር ስላልነበረ ከያንዳንዱ ቀን ጋር አብሮ የሚወለደው የሀልውና ተስፋ መጥቶ መንፈሱ እንዲነቃቃ አላደረገውም ። ካለፉት አስር ቀኖች የተለየ ቀን መስሎ አልታየውም ። እንዳለፉት አስር ቀኖች ሁሉ ምንም ተስፋ ያልተመረኮዘ ፣ ያለትርጉም እንደ መጣኛ ተዘርግቶ የሚጐተት ረጅም ቀን መስሎት ነበር ። እንቅልፍ ሳይኳልባቸው ያደሩትን አይኖቹን ጨፍኖ ፣ የሳር ፍራሹ ላይ በመገላበጥ ፣ ሌሊት ከእንቅልፉ አባንኖ የቀሰቀሰው ቅዠት ወደእውነት ተለውጦ ምንነው ከዚህ ገድሎ ከማይገድል ፣ ሸሮ ከማይሽር የቁም ፣ የቀስታ ሞት በገላገለኝ እያለ በልቡ በመመኘት ፣ በየቀዳዳው እያሰረገች ለምትገባው የጧት ጨረር ጀርባውን ሰጠ ። ወደሱኳ በሮ የመጣበትን ቀን ለመርገም ጊዜ አላገኘም ። ወዲያውኑ ተረኛ ፖሊስ መጥቶ ለእዳሪ እንዲወጡ አዘዛ ቸው ። ሌላ እድል እንደማያገኙ ያውቃሉና ሁሉም ተነሱ ። ሀዲስም ያለውዴታው ተነሳ ። እዳሪ ወጥተው ሲመለሱ ሀዲስ ወደቢሮ ተጠራ ። እንደሌላው ጊዜ ሁሉ ለተለመ ደው መስቀለኛ ጥያቄ መስሎት ተበሳጨ ።



ከቢሮ ሲገባ ሺታዬን በማየቱ ልቡ ደነገጠ ። ቶሎ ብላ ፊቷን አዞረችበት ። እርሱን ለማነጋገር ፈቃደኛ አለመ ሆኗን በሁኔታዋ ስለገለጠችለት ሊያነጋግራት አልሞከ ረም ። አንገቱን ደፍቶ ዝም ብሎ ቆመ — ምን እግር እን ደጣላት በልቡ እያሰላሰለ ። የግቢያው አዛዥ «ይህን ሰው ታውቂዋለሽ?» ብሎ በጠየቃት ጊዜ ነበር አንገቷን ቀና ያደረገውና አይኖቻቸው የተጋጩት ።

«አዎን — አውቀዋለሁ — ሀዲስ ሳህሌ ይባላል» — ባገር ልብስ አሸብርቃለች ። ጆሮዎቿ ላይ የሚታዩት የወርቅ ጉትቻዎች ፣ የእጆቿ አምባሮች ፣ ከአንጦንጡ ጡቶቿ መሀል የተጋደመው ትልቅ የወርቅ መስቀል በመ ስኮት የገባችውን ጨረር እየተቀበሉ መልሰው በማን ፀባረቅ ይንቦገቦጋሉ ። ውበት የጨመረች መስላ ታየችው ። በአይኖቿ ውስጥ የተመለከተውን ጥላቻ ግን አልወደ ደም ።

«ምንሽ ነው?»

«ምኔም አይደለም።»

«አቶ ይርጋ አለሙ የተባሉትን ሰው የገደለው ማን ነው?»

«እርሱ ነው ። ከመጠጥ ቤት አምሽተው ሲመጡ ከትምህርት ቤቱ አጥር ስር ጠብቋቸው በሽጉጥ ተኩሶ ሲገድላቸው በአይኔ አይቻለሁ ። እርሱ ግን አላየኝም……»

«አንቺ በዚያን ሰአት ምን ታደርጊ ነበር?»

«ከአባ ጨፌ ዘንድ ወዳጄ ላይ ቆይቼ ወደቤቴ ስሄድ ነበር……»

ሀዲስ በድንገት በሳቅ ፈነዳ ። ሳቁን ለማቆም አል ቻለም ። ከሳቁ ብዛት የተነሳ እንባ ይወርደው ነበር ።

«ያለበትን የነገሩት ሰው የኮረኮሩትን ያህል ይስቃል» ይላሉ አበው ሲተርቱ ። እንዳጋጣሚ ሆኖ በያመቱ በክረምት ወራት ከአዲስ አበባ መጥተው እዚህ የሚያስችሉት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች ሰሞኑን ስራቸውን ጀምረዋል ። እነርሱ የበለጠ ያስቁህ ይሆናል!» አለው የጣቢያው አዛዥ ድምፁን ከሀዲስ ሳቅ በላይ ከፍ አድርጐ ።

ሀዲስ ሳቁን አጽርጦ ፤ «የኔ ሞት ደስታ የሚሰጣት ከሆነ ምንኛ ደግ ነው!» አለ በታፈነ ድምፅ ። አልጠላትም ። ይሁዳ መስላ አልታየችውም ። ይልቅ ፤ በእርሱ ላይ ያደረባት ቂም ምን ያህል እንደሆነ በመረዳቱ አዘነ ። ባልሰሩት ሀጢአት መሞት … ስቀለው … የእጅህን ዋጋ ታገኛለህ … ህልሙን አስታወሰ ። ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተቸንክሮ ታየው ……

የፊታውራሪ አሽከሮች ትንሹም ትልቁም ባልቴቶች እንኳ ሳይቀሩ በጅምር የቀረውን ትምህርት ቤት ከፍፃሜ ለማድረስ ከአይናለም ጋር በመሰለፍ በስራ ተጠምደዋል ። ንፍሮው ከዚያው ይቀቀላል ፤ ጠላው ከየመንደሩ በገንቦ ፤ በማንቆርቆሪያ ይመጣል ። በገዛ ፈቃዱ የስራው ተሳታፊ የሚሆነው ህዝብ ከቀን ወደቀን እየጨመረ ይሄድ ነበር ። አይናለም ጠባብ ሱሪ አጥልቃ ፤ ከፊትለፊት የቀሚሷን ጫፍ ወደላይ በመቀለስ ከመቀነቷ ጋር አያይዛ እንደወንድ መስላል ወጥታ በመውረድ ስትሰራ የተመለከታት ሁሉ ሴቷ እንደወንድ ስትሰራ ቆሜ ማየት ለኔ ሞት አይደለም እንዴ? እያለ ነጠላውን ጥሎ ከስራ መሀል ዘሎ የሚገባው ሰው ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ ይሄዳል ። ከቅርብም ሆነ ከሩቅ የሚመጡት ሰዎች በመጀመሪያ አይናለም ስትሰራ ለማየት ነበር ። ዝናዋ በመላ ሱዴ በሮ ተናኘ ።



ባሏ ቢታሰር እርሱ የጀመረውን ከፍፃሜ ለማድረስ ሴቷ ልጅ እንደወንድ ታጥቃ ተነሳች እያሉ የሚያደንቋት ቢኖሩም ፤ ሴሎቹ ደግሞ ፤ ሁለት ባሎች አግብታ በመግፋቷ እንደአብደት አድርጓት ነው በማለት ያወሩ ነበር ። ከዚያም አልፈው አባ ጨፌ በፊታውራሪ ተካ ቤት ላይ ያለው ጥላቻና እርግማን ነው የባላባቱን ልጅ ለድንጋይ ሸክም የዳረጋት በማለት ፊታውራሪ ተካ ከአባ ጨፌ ቤት ወዳጃ እያደሩ ምህረት ይወርድላቸው ዘንድ እንዲማለዱ የሚመኙም ነበሩ ። ነገር ግን ፤ እርሷ ስትሰራ ለማየት ቢመጣም የስራው ተካፋይ በመሆን እጁን የማይዘረጋ ሰው የለም ።

አይናለም በጅምር የቀረውን ትምህርት ቤት ከፍፃሜ ለማድረስ ታጥቃ ከተነሳች ቀን ጀምሮ ፤ የአልጋ ቁራኛ ሆኖ የሰነበተው ቶሎሳም እረፍት ላይ እንደከረመ ሰው በአዲስ ጉልበት ተነስቶ ሲሰራ ላየው ሰው ያስገርም ነበር ። ደከመኝን አያውቅም ። ለአህል እንኳ ጊዜ የለውም ። ከሀዲስና ከአይናለም ጉጉት ይልቅ የእርሱ የበረታ መስሎ ነበር የሚታየው ። የአልጋ ቁራኛ ሆኖ የከረመ ሰው በድንገት ተነስቶ ያለማቋረጥ ሲሰራ እየተመለከቱ ይገረሙ ነበር ። ከስራ የበለጠ መድሀኒት የለም እስከ ማለት ደርሰው ነበር ። ሆኖም በሚሰራበት ወቅት

አንዳንድ ጊዜ ፍዝዝ ብሎ ይቆይና እንደመባነን ሲያደርገው የተመለከቱት ጓደኞቹ ጨርሶ እንዳልተፈወሰ ያውቁ ነበር ። አባ ጨፌ ቤት ወስደውት እንዲለማመን ለማድረግ ከጓደኞቹ መካከል የተዘጋጁም ነበሩ ። ቶሎሳ ከልጅነቱ ዘመን ጀምሮ የህብረተሰቡን ሀሳብ ሲዳፈር የቆየ እንደ መሆኑ ፤ ከነገ ዛሬ ይቀጣል በማለት የሚጠባበቁት ሰዎች ቁጥር ብዙ ነበር ።

የአባ ጨፌ ቤቶች ባሉበት አግጣጫዎች ከመንገድ ዳር የሚቆለሉት ድንጋዮች ላይ አላፊ አግዳሚው የሚጥለውን «ገልቻ» ቶሎሳ እየጠበቀ ያላንዳች ፍርሀት ይወስድ ነበር ። እንዲህ አይነቱን ሀሳብ መንካቱን የሰሙ ወላጆች ልጆቻቸው ከእርሱ ጋር እንዳይውሉ በጥብቅ ይከላከሉ ስለነበረ ቶሎሳ በልጅነቱ ብዙ ጓደኞች አልነበሩትም ። ሆኖም ዝናውን የሰሙ ልጆች ሁሉ ወላጆቻቸውን በመፍራት ባይጠጉትም ፤ ድፍረቱን በመገንዘብ በልባቸው ያደንቁት ነበር ። እረኞች በየሜዳው ያወድሱታል ፤ ልጃገረዶች እንጨት ሰበራ ሲሄዱ ስሙን እየጠሩ ይዘፍናሉ ። ልጃገረዶች ወሀ ለመቅዳት ወይም እንጨት ሰበራ ሄደው ጉረምሳ ሊደፍራቸው የመጣ እንደሆን «ቶሎሳን እንጠራብሀለን» ቢሉት ዝንጀሮ የማት ወጣውን አቀበት ጥሶ ይጠፋ ነበር ይባላል ። ፈታውራሪ ተካና አባ ጨፌ ሆድና ጀርባ ሆነው የቀሩት በቶሎሳ ምክንያት ነው እየተባለ ቢወራም ፤ በሁለቱ መካከል የነበረው ጥላቻ የቆየ ነበር ። ፈታውራሪ ቃልቻ አይወዱም ፤ ቢቃልቻ አያምኑም ። የእልቂ ማርያምን ቤተክርስቲያን ለማሳነፅ የተነሳሱበትም ዋናው ምክንያት ህዝቡ በቃልቻ ላይ ያለውን እምነት ለማስወገድ ነበር ። ግን እንዳሰቡት ሳይሆንላቸው ቀረ ።



አይናለም በጅምር የቀረውን ትምህርት ቤት ከፍፃሜ ለማድረስ ቆርጣ የተነሳችው ፤ እንደልማዷ በማለዳ ተነስታ ወደትምህርት ቤቱ በመሄድ ግድግዳውን ይዛ ስታለቅስ ቆይታ ወደ ቤት ለመመለስ በምትጣደፍበት ወቅት «እኔ ከፍፃሜ ለምን አላደርሰውም?» የሚል አሳብ በድንገት ካደረባት በሁዋላ ነበር ። ወደ ቤት ማምራቷን ትታ ወደትምህርት ቤቱ ተመለሰች ። ለጊዜው የምታደርገው ነገር ቢጠፋትም ለብዙ ጊዜ ስታስብ ቆየችና የተበታተነውን እቃ ሰብስባ ማከማቸት ጀመረች ። የአእምሮዋን ጤንነት የተጠራጠሩት አንዳንድ ሰዎች ወደ ፈታውራሪ ቤት ሲሮጡ ፤ ሌሎቹ ደግሞ በማዘን ዝናቡን እየተዳፈሩ ይረዷት ጀምረው ነበር ። ዝናቡ እንዳባራ ፈታውራሪ ሲገሰግሱ ደርሰው ፤ በዝናብ የራሰውን ሰውነቷን እየተመለከቱ «ምን ታደርጊያለሽ!» ብለው መላቅጡን ባጣ ድምፅ ይጠይቋታል ።

ፊቷን ኮስተር አድርጋ «ይህን በጅምር የቀረውን ትምህርት ቤት ከፍፃሜ ማድረስ አለብኝ ። ባሌ ከዚህ የበለጠ ደስ የሚያሰኘው ነገር ያለ አይመስለኝም......» ትላቸዋለች ፤ ከቅንድቦቿ ላይ ዝናቡን እየጠረገች ።

ፈታውራሪ በልባቸው የተሰረፀውን ሀዘን ይሁን ደስታ ለጊዜው ለይተው ባያውቁም አይኖቻቸው እንባ ያቀርራሉ—

«ታዲያስ ጉበዝ ጊዜ በከንቱ ለምን እናጠፋለን» ብለው ከበቅሎአቸው እንደወረዱ ሁሉም የምንቶ እፍረቱን ነጠላውን እየጣለ ከስራው ጋር መያያዝ ይጀምራል ። ቶሎሳም ይህን እንደሰማ ነበር ከተኛበት ተነስቶ የመጣው ።

ፊታውራሪ ተካ የጊዜን ትርጉም ረስተው አይኖቻቸውን ከአድማስ ላይ በማሳረፍ ፣ ያሳለፉትን ዘመን ፣ የትናንቱን ዘመን ክብራቸውንና የባላባትነት ስልጣናቸውን እያሰቡ ፣ ምንም የተስፋ ጭላንጭል የማይታይበትን የነገውን ቀን እየጠሉ ፣ በእርሳቸውና በልጃቸው ላይ የደረሰውን ውርደት እያሰላሰሉ በትካዜ ተውጠው ፣ ህይወት ከውስጣቸው ተጨምቃ የደረቀች ይመስል ፣ ቁጭ ብለው ያልተከዙትን ያህል ፣ ከህዝቡ መሀል እየተንጎራደዱ ፤ የደከመውን ሲያበረታቱና አይዞህ ሲሉ ላያቸው ሰው እንደገና የወጣትነት ጉልበትና መንፈስ የተዘራባቸው ነበር የሚመስሉት ።

«ጎበዝ ጊዜን አታባክኑ — አንድ ጀምበር ላንድ ስራ መሆን አለባት —» ስለሚሉ ስራ ፈትቶ የሚታይ ሰው አልነበረም ። ለሁለት ወር ክረምት ወደየቤታቸው የሄዱትም ተማሪዎች ተመልሰው ፤ በመላላክ ፤ እቃ በማቀበል ፤ በእድሜ ላቅ ያሉትም የታዘዙትን በመስራት ሲያገለግሉ ይውሉ ነበር ። ስራው በመጣደፉ ትምህርት ቤቱ ከፍፃሜ የመድረስ መልክ እየያዘ በሄደ ቁጥር ፣ ከሁሉም ፊት ላይ እንደጧት ጮራ የሚሞቅ ፈገግታ ሲፈነጥቅ ይታይ ነበር ። ወደቀኑ መጨረሻ ላይ ፣ ፀሀይዋ የጋለ እሉሎ መስላ ለጥቂት ጊዜ ከአድማሱ ላይ ተንሳፍፋ ስትጠልቅ ሁሉም ከትምህርት ቤቱ ፊት ለፊት ካለው ድንጋይ ዙሪያ ተቀምጠው ትኩስ ቡና እየጠጡ ቀን ያከናወኑትን ስራ በፍቅር አይን በሚመለከቱበት ወቅት ፣ ፊታውራሪ ተካም ጨለማ እየጋረደው የሚሄደውን የትምህርት ቤቱን ህንፃ ትኩር ብለው እየተመለከቱ ፤ የትምህርት ማስፋፋትን ስራ ቀደም ባለው ዘመን ጀምሬ ብሆን ኖሮ ፤ ስንቱን ሰው ለቃልቻ ከመስገድ ለማዳን በቻልኩ ነበር እያሉ በልባቸው ያስላስላሉ ። የእልቄ ማርያምን ቤተክርስቲያን ቀደም ብለው በማሳነፃቸው የቆማቸው እንዳይመስልባቸው ራሳቸውን በራሳቸው መልሰው በመገሰፅ የሰይጣን ጆሮ አይስማው — በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ብለው ያማትቡና ወደአይናለም መለስ ብለው «ልጄ ከእንግዲህ ወደ ቤታችን እንሄድም ? ከፀሀይዋ ጋር ውለናል ። የእለት ተግባራችንን ፈፅመናል» ይሏታል ። ትምህርት ቤቱን ትኩር ብላ በመመልከት በህሊናዋ ትሰናበተውና ሁሉም ተነስተው ይሄዳሉ ። እስኪነጋ ድረስ ስራው ይናፍቃታል ። በአሳቧ የምትገነባው አዲሱን ትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን ሀዲስንም ጭምር ነበር ። ነጋ አልነጋ እያለች ስታስብ ስለምታድር ገና ወፎች ሳይንጫጩ ትነሳለች ። ቶሎሳ ግን ቀድሟት ስለሚነሳ ተያይዘው ይሄዳሉ ። ክፍያም ሆነ ዝናብ እያግዳቸውም ። ሌሎችም ሰዎች እንኳን ዝናብ አህያ የማይችለው ዶፍ ቢወርድም ከስራ አይቀሩም ። ፊታውራሪ «በገንዘብ ከሚሰሩት ስራ በበጎ ፈቃድ ተነሳስተው የሚፈፅሙት ተግባር የበለጠ ግዴታን ያስከትላል — የህሊና ጉዳይ ነውና!» ማለት የጀመሩትም ህዝቡ በእዋጅ የታዘዘ ይመስል በሰአት ለስራ ተሰልፎ መገኘቱን ከተመለከቱ በሁዋላ ነበር ።

ፊታውራሪ አንድ ቀን ወደመምሬ ፊታቸውን መልሰው «እነዚህ ሰዎች ከጧት እስከ ማታ ክፍያ ፣ ዝናብ ፣ ቁርና ሀሩር ሳይሉ ለድካማቸው ዋጋ ሳይጠይቁ የሚሰ

ሩት ለምን ይመስልዎታል!» ብለው ድንገተኛ ጥያቄ ወረወሩባቸው ።

«እርስዎንና ልጅዎን በመመልከት ነዋ!» በማለት ኮስተር ብለው ባጭሩ መልሱን ሰጡ ። የሰጡት መልስ ፊታውራሪን ያስደሰተ ስለመሰላቸው ፈገግ አሉ ።

«የኔና የልጄ እዚህ መገኘት መነሾ ምክንያት ሊሆን ይችላል ? ነገር ግን ፣ በደፈናው የህዝቡ ምክንያት ይህ ብቻ ነው ለማለት አይቻልም ። የጥረቱና የቆራጥነቱ ምክንያት በዚህ ብቻ ተተርጉሞ የሚቀር አይደለም ። ጠለቅ ያለ ምስጢር ያለው ይመስለኛል ። እንደኔስ ከሆነ ሌላ ፍች አለው ። እንደበቱ ባይናገር በያንዳንዱ ሰው ፊት ላይ ልብ አድርጎ ለተመለከተ በጉልህ ተፅፎ ይነበባል ። በገዛ እጃቸው የወደፊት እድላቸውን ለመገንባት የተነሳቡ መስለው ነው የሚታዩኝ ። የወደፊት እድላቸው ከሰማይ እንደመና የማይወርድ መሆኑን የተገነዘቡት መስለው ነው የሚታዩኝ ። በፈጣሪያቸውና በመሪዎቻቸው ላይ ብቻ ተስፋቸውን ጥለው መቀመጥ የማያዋጣ መሆኑ የተከሰተላቸው መስለው ነው የሚታዩኝ ። እግዜር ካልረዱት አይረዳም ። መሪዎችም እንዲሁ ናቸው ። ከመገዛት ራሳቸውን ወደመግዛት ማዘንበል የጀመሩ መስለው ነው የሚታዩኝ ። ራሱን በራሱ መግዛት የጀመረ ህዝብ ትልቅ ህዝብ ነው ። ከፊታቸው ላይ ተፅፎ ይታየኛል ። የወደፊት እድሉን ለመጨበጥ ቆርጦ አንድ ርምጃ የወሰደ ሰው መቆሚያ የለውም ። እንዲህ አይነቱ መንፈስ ከታፈነ ይፈነዳል ። የሚፈነዳ ነገር አግጣጫው አይታወቅም ። መንፈሱን ወደበጎ ዓላማ ካልመሩት — መንገድ ካልቀየሱለት — እያደረ ነቀርሳ — አውሬ — ይሆናል ።



ዳሩ ግን ማንኛውንም ነገር በቀና መንፈስ የማየት ልማድ የለንም ። ቀናው ነገር እንዲጣመም ፣ መልካም መንፈስ ወደጥፋት እንዲያመራ ፣ እውነት ተደብቆ ፣ ተንኮል ፣ ሸርና ሸፍጥ እንዲስፋፋ እናደርጋለን ። በዚህ አካሄድ የትም ልንደርስ አንችልም ። የዚህ ትንሽ ትምህርት ቤት ስራ ፍፃሜ ሌላ ተአምር እንደሚያስከትል ይሰማኛል ። አንዱ ተአምር ወደሌላ ተአምር ማምራት አለበት ። እግዚአብሄር ተአምሩን በመረጣቸው ሰዎች አማካይነት ይገልጣል ። ሰው የእግዜር መሳሪያ ነው እንጂ ምክንያት ሊሆን አይችልም ። በፊት ባለቤቷ ፣ አሁን ደግሞ ልጄ — ልጆቼ — ለዚህ ተአምር መመረጣቸው ነው መንፈሴን ያነቃቃው ። ተስፋዬ እንደገና እንሰራርቷል» ካሉ በሁዋላ ትምህርት ቤቱን ትክ ብለው መመልከት እንደጀመሩ ፣ ወደመቱ ስንቅና ቅያሪ ልብስ አስይዘው የላኩት ሰው የሸምማ እየጋለበ መጥቶ ከፈረሱ በሚያስደንቅ ቅልጥፍና ተወርውሮ እንደወረደ ባንድ ትንፋሽ «ተፈረደበት'ኮ!» አላቸውና አንድ ደብዳቤ ከደረት ኪሱ አውጥቶ ለአይናለም ሰጠ ። አይናለም እጆቿ እየተንቀጠቀጡ ተጣጥፎ የመጣውን ደብዳቤ ዘርግታ ማንበብ ጀመረች — «ውድ አይናለም — ከተለያየን ዘመኑ ሩቅ መሰለኝ ። በስቀቀን የሚያስታውሱት ነገር ጊዜው የመናፈቁን ያህል ይርቃል ። ትምህርት ቤቱን ከፍፃሜ ለማድረስ ታጥቀሽ መነሳትሽን በፃፍሽልኝ ደብዳቤ ገልፀሽልኛል ። ከዚህ የበለጠ ውለታ የለም — ለኔ — ለወገኖችሽ — ለሀገርሽ ። በአሳብ ካንቺ ጋር ሆኜ ስሰራ እውላለሁ ፣ ካንቺ ጋር ስለመጪው ቀን ስራ ሳስብ አድራለሁ ። በመንፈስ ሁልጊዜ ካንቺ ጋር መሆኔ ይሰማኛል......

አሁን ግን ሲያገናኘን የነበረው የመንፈስ ድልድይ እንኳ ሊቋረጥ ነው ። የህይወቴ ዕዋ ሞላች መሰለኝ ። የምሞትበትን ቀን ቁጭ ብዬ ከመጠበቅ ሌላ ምንም ለማድረግ አልችልም ። ይግባኝ እንኳ አላልኩም — እን ደክርስቶስ ። ለምን? ትይኝ ይሆናል ። መኖርን ጠልቼ አይደለም ። መኖር እፈልጋለሁ ። ካንቺ ጋር ለመሆን እመኛለሁ ። አብረን በእጃችን ትምህርት ቤቱን ከፍፃሜ እንድናደርሰው እመኛለሁ ። ከቀጭን ገመድ ጫፍ የተን ጠለጠለ ሰው እንኳ ሳንዷት ሴኮንድም ብትሆን ለመኖር ይፍጨረጨራል ። ህይወት አትጠገብም ። እንዲያውም ወደመጨረሻው ላይ እየጣፈጠች ትሄድ እንደሆነ እላው ቅም ፣ የማየው ነገር ሁሉ ልዩ ደስታ ይሰጠኛል ። የፀሀይ ሙቀት ሰውነቴን ሲዳስሰው ፣ ነፍሴ ከዚህ ቀደም በማታ ውቀው ሀሴት ተውጣ ትፈነድቃለች ፣ ትወራጫለች ። ግን ኑሮ በዚህ ሁኔታ ኑሮ መስላ አትታየኝም ። ስለዚህ ይግ ባኝ አላልኩም ። ለየትኛው ፍትህ! ግን የማማርረው ሰው የለኝም ......»

«ምን ፈረዱበት?»

«ሞት ። ወንጀሉን በፈፀመበት ቦታ በሞት እንዲ ቀጣ ተፈረደበት ። ይግባኝ ጠይቅ ቢባል ሞቼ እገኛለሁ አለ!»

.. የፊታውራሪ ፊት ባንድ ጊዜ ገረጣ ። ሁሉም ስራውን ትቶ አቀረቀረ ። አይናለም እንባዋን እያፈሰሰች ደብዳ ቤውን ማንበብ ትቀጥላለች — «ከመሰልቸትና ከመንገ ፍገፍ ይግባኝ ያላልኩበት ሌላ ምክንያት አለኝ ። ለኔ ህይወት ማለት እንቅስቃሴ ነው ። እንቅስቃሴ ድርጊትን ያስከትላል ። ካለእንቅስቃሴ ህይወት የለኝም ። ድርጊት አይኖርም ። አለም ትዞራለች ፣ ጨረቃ ትወጣለች— ትገባለች ፣ ከዋክብት ይወጣሉ ይጠፋሉ ። እህል ይዘራል ፣ ይታጨዳል ፣ ይወቃል ፣ ይገባል — እንደገና ይዘራል ። ሰውም ካንቀልባ እስከ ቃሬዛ ባለው ህይወቱ እንደተ ጓዘ ነው ። አገርም ብትሆን በየጊዜው ለውጥ ያስፈልጋ ታል ። ለውጥ የኑሮ ህግ ነው ። ይህን ህግ ካልተከተልን ፍትህ ትቃወሳለች ። እንደፈሳሽ ወሀ መታየት ያለበት የለውጥ ህግ ከተገደበ ወደኩሬነት ተለውጦ ይጠራቀምና ሁዋላ ጤናማ አይሆንም ። ከዚያ በሁዋላ ከኩሬው ለመ ጠጣት አይቻልም ። በሽታ ይሆናል ። አዎን — ህይወት የእንቅስቃሴ ኡደት ነች — ለኔ ። ማንኛውም ፍፃሜ ሌላ መጀመሪያ እንዲኖረው ያስፈልጋል ። እጅና እግሬ ታስሮ የእንቅስቃሴዬ ኡደት ከተቋረጠ በህይወት አለሁ ለማለት አልችልም ። ሞቴን እመርጣለሁ — ምናልባት ሌላ ጉዞ ለመጀመር! ምንም ሳልሰራ ፣ እጅና አእምሮዬ ዝጎ ፣ መንፈሴ ታምቆ ለመኖር አልከጅልም ። ይግባኝ ማለት የአእምሮዬን ጭንቀትና የመንፈሴን መታወክ ማራዘም ይሆናል — ህይወት የማትጠገብ ብትሆንም ቅሉ ......»

ፊታውራሪ እንባ አነቃቸው — በታፈነ ድምፅ «ሰንቴ ደቂቃ በማትሞላ ጊዜ ውስጥ ፈጣሪን አመስግኜ እን ደገና ላማርረው? ሰው ሆኖ መፈጠር ከንቱ» አሉ አንገታ ቸውን ደፍተው ።

«ገዳዩ እሱ መቼ ሆነና!» አለ ቶሎሳ ፣ ባንድ ፊት ላብ እንደወሀ እየወሰደው ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ብርድ እንደያዘው ሰው እየተንቀጠቀጠ ። ፊታውራሪ አንገታ

ቻውን ቀና አድርገው ፊት ለፊት ተመለከቱት ። አይን ለአይን ተጋጩ ። ከዚያ በፊት ያላሰቡት ነገር መጥቶ ተከሰተላቸው ።

አይናለም እንባዋን በእጇዋ ጠርጋ ማንበቧን ትቀጥላለች — «የፀሀይ ሙቀት ፤ የጨረቃ ድምቀት ፤ የከዋክብት ውበት — አዎን — ያንቺ ትንፋሽ — ልትሰጥኝ ስትይ ያልወሰድኩት ፅጌረዳ አበባ — ወግ ሳይደርሰኝ ወግ ሳላሳይሽ — ሁሉም ያንጉኛል ። አንቺ ከቤት እያለሽ ፤ አንቺን ፍለጋ ፤ ራሴን ፍለጋ ከቤት ወጥቼ ፅጌረዳ አበባ ይዘሽ ስትጠብቂኝ ሳልመለስ ቀረሁ ። አይኖችሽ የኔን መመለስ ሲጠብቁ እንደተንከራተቱ ይገባኛል ። በፃፍሺልኝ ደብዳቤ ምን ያህል የአእምሮ ጭንቀት እንደደረሰብሽ ገልፀሽልኛል ። ክብርናዋን ቢያጣ ነው ጥኋት የጠፋው — በማለዳ ተነስቶ አይኗን ሳያይ ፤ የፊታውራሪ ጋለሞታ ድሮውንም ገፊ ናት ፤ እናቷን የገፉች ፤ ሁለት ባሎች የገፉች ፤ እያሉ እንዳወሩብሽ ሁሉ ገልፀሽልኛል ። አባቴም ሳይቀሩ ስለንፅህናዬ ተጠራጠሩኝ ስላልሺኝ አዘንኩ ። እንደምታውቂው የሴት ልጅ ክብርና በህብረተሰባችን ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠው ነገር ነው ። የምስራች ኪልተባለ ጥርጣሬ ማስከተሉ አይቀርም ። አባትሽም የተጠራጠሩሽ ለዚሁ ነው ። ክብርሽ ክብራቸው ነውና ። ግን ያንን ሁሉ ሹክሹክታ ችለሽና ምስጢራችንን ደብቀሽ መቆየትሽ የመንፈስሽን ብርታት ያሳያል ። ሌሎች ልጃገረዶች ቢሆኑ ስማቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ከቤት ይኮበልሉ ፤ ወይም ለወላጆቻቸው እኔ ንፁህ ነኝ ፤ እርሱ ነው ያቃተው ብለው ይናገሩ ነበር አንቺ እንዳልሺው ። ግን ይህን አላደረግሽም ስለምትወጂኝ ። ከትምህርት



ቤቱ ጋር ስገነባሽ ነው የከረምኩት ። ስገነባሽ የኖርኩትን ያህል በድንገት ባላሰበው ባገኘሁሽ ጊዜ ሰውነቴ ደነገጠ ። ሰውነትሽን እንደታቦት ፈራሁት ። ብርክ ያዘኝ ። የማረክስሽ መሰለኝ ። ከትምህርት ቤቱ ጋር በአሳቤ ውስጥ ተወሳሰበሽ ስለኖርሽ ገላሽን መንካት ትምህርት ቤቱን እንደመናድ መሰሎ ታየኝ ። ስሜቱ አሁን ነው የተከሰተልኝ ። የተማታ ስሜት ነው ። እወድሻለሁ ። ደብዳቤሽ አብሮኝ ከመቃብር ይወርዳል ። አይለየኝም ። ስለዚህ በዚህ ጨለማ ስአት የሚያፅናናኝ ነገር አለ ። እንባሽ አይደለም ። ፅናትሽ ነው ። በአሳብሽ ውስጥ ህያው ሆኜ እንደምኖር አውቃለሁ ። ትምህርት ቤቱ አብረን ላሳለፍናቸው ጥቂት ቀናት — ባናረካቸው ለቀረነው የፍቅር ሌሊቶች — መታሰቢያ ሀውልት ይሁን ። ደህና ሁኚ» — የአይናለም እንባ እንደበጋ ዝናብ በወፍራሙ እየወረደ ከደብዳቤው ላይ ተንጠባጠበ ።

«ከንዴ — አይደረግም» አሉ ፊታውራሪ ከእንቅልፋ እንደነቃ ሰው ባንነው ።

«ለክፋት አልነበረም ። አይናለም ከፊትዎ እንዳት ለይ እ……አዎን……ሀዲስ እዚሁ እንዲቀር ነበር ። ለሱዳ ልጆች ያለው ምኞትም አንጉቶኝ ነው……ጉጉቱ አይኔን ጋረደው ። ከፊቱ እንቅፋት ያነሳሁለት መሰለኝ — ለራሱ እንቅፋት እንደምሆን ሳይገባኝ ። ግን……» ብሎ ነገሩን ሳይደመድም ከመቱ ከመጣው ሰው እጅ የፈረሱን ልጓም መንጭቆ በማይታመን ፍጥነት ዘሎ ከኮርቻው ላይ ወጣ ። ከአይኖቹ ጥንድ ጥንድ የእንባ ዘለላዎች ይወርዱ ነበር ። ቶሎሳ ለማድረግ ያሰበው ነገር ስላልተከሰተላቸው ሁሉም ፈዝዘው ይመለከቱት ነበር ።

በእንባዎቹ ውስጥ ፊታውራሪን ፤ ከእርሳቸው ቀጥሎ አይናለምን ፤ በመጨረሻ ትምህርት ቤቱን አንድ ባንድ ትኩር ብሎ ተመለከተና ፤ የፈረሱን ግንባር ወደ ገባ ወንዝ አዙሮ ሜዳውን እያቋረጠ ሲጋልብ ፤ እር ሱና ፈረሱ ለአይን እያነሱ እያነሱ — ወደጥቁር ጥላ — ወደትንሽ ነጥብ እየተለወጡ — ዝናብ አዝሎ ከመሬቱ ጋር እየታከከ — እየቀረበ እየጐላ — የቀኑን ብርሀን እየ ደመሰሰ ከሩቅ ከሚመጣው ጉም ውስጥ ገብተው ለአይን ተሰወሩ......

ጠብመንጃ የያዙ ሁለት ፖሊሶች መጥተው ሲጠ ሩት የሀዲስ ልብ እንደመቆም አለች ። ለጥቂት ጊዜ መተ ንፈስ እንኳ ተሳነው ። ፖሊሶች በመጡ ቁጥር ነፍሱ ከስጋው እስክትለይ ድረስ መደንገጥ ከጀመረ ሰንብቷል ። ከተፈረደበት ቀን ጀምሮ አጠገቡ የሚተኙት እስረኞች ከመኝታቸው ላይ ሲነሳበሙ እንኳ ባንኖ ይነሳል ። በስ ጋት ብቻ ብዙ ጊዜ ሞቷል ። ግን ድንጋጤው ሲያልፍ ፤ የሙጢኝ ብላ ከውስጡ በፍርሀት የምትወራጨው ነፍሱ መረጋጋት ስትጀምር ምንነው ቀኔ ደርሶ በተገላገልኩ እያለ ፤ በህይወት መኖርን ሳይጠላ ሞቱን ይመኛል ። ድንጋጤው ጥቂት ጊዜ ቆየና አለፈ ። ሰውነቱ ግን እን



ደደነዘዘ ቀረ ። የመጨረሻ ሰአቱ ደረሰች የሚል እም ነት ስላደረበት በድኑን ተነስቶ የእስር ቤት ጓደኞቹን አን. ባንድ እየዞረ የእጅ ሰላምታ ሲሰጣቸው አንዳ ንዶቹ እየተነሱ ጉንጮቹን አገላብጠው በመሳም ይሰ ናበቱት ጀመር ።

—«ሞትና ከሰን ባንድ ትንፋሽ ነው — አይዞህ!»

—«የልቡን ለሰራ ጀግና ሞት ሰርጉ ነው»

—«እንገናኛለን — ፅዋው የሁሉም ነው ፤ ሞት የሁ ሉም ርስት ናት»

—«አይዞህ ወዳጄ — ሳይሀ በደል የሚሰራ ሰው አት መሰለኝም ። ግን ክርስቶስም ያለበደሉ ተሰቅሏል ። እርሱ ካንተ ጋር ይሁን»

ይተኛበት የነበረውን ፍራሽ ፤ ቡሉኮውን ፤ ብርድል ብሱን ፤ ነጠላውንና ፤ ቅያሬ ልብሱን ለያንዳንዳቸው ሰጠና ከወሀ ውስጥ ዘልሎ ለመጥለቅ እንደሚዘጋጅ ሰው አየር በብዛት ወደውስጥ ስቦ ወጣ ። በሩን እንደወጣ የእ ስር ቤት ጓደኞቹ፡—

«ጓዴ — ጓዴ የክፉ ቀን ጓዴ......»»

«መከረዬ ፤ ባላውቅህ ምን ነበር! ኧረ ምን ነበር ። ጓዴ — አይኩሰኩሴ......»

«የፍርፋሪዬ ጌታ — የጨርቄ ጌታ ፤ ራቁቴን እስቀ ረሀኝ — ደጉ ወዳጄ ። ምንነው እጅህን ባላየሁት» እያሉ ሲያለቅሱለት እየሰማ በፖሊሶቹ ታጅቦ በድኑን ሲራ መድ ዋይታው ለጆሮው እየራቀ እያነሰ በሚሄድበት ወቅት — የእንቅስቃሴ ኡደት መቆም የህይወት ፍፃሜ —

አይናለም — ፅጌረዳ አበባ ገና ያልረገፈ — ከፍኛሜ ያል ደረሰ ትምህርት ቤት ስራ — የእጅ ስረየት — ያልተ ያያዙ ፣ እንደተፈታ ልቃቂት ውላቸው የጠፋ አሳቦች በአእምሮው ይመላለሱ ነበር ። አይኖቹ የሚያዩት ከአእ ምሮው የሚመነጩትን ውስጣዊ አሳቦች እንጂ አፍአዊ ነገሮችን አልነበረም ። የጧት ፀሀይ ሙቀት እንኳ አይሰ ማውም ነበር ። በሀልም አለም ውስጥ እንደመንሳፈፍ ያሀል ነበር ጉዞው ......ጉዞ ፍታት ።

ከከፍተኛው ፍርድ ቤት ደርሶ ፣ ከፊቱ ቀድሞት የሚሄደውን ፖሊስ ዱካ እየተከተለ ጥቁር ካባ ለብሰው ከተቀመጡት ሶስት ዳኞች ፊት ሲቀርብ ሁሉ የት እንደ ነበረ ለማስታወስ አልቻለም ።

«ስምህ?!...... አንተን ነው!»

የራሱ ስም የተዘነጋው ይመስል ትንሽ አመንታና «ሀዲስ ሳህሉ» ብሎ የራሱ ባልሆነ እንግዳ ድምፅ መለሰ ። የራሱን ስም ከመጥራቱ እንደመባነን ብሎ ነቃ ። የት እን ዳለ ታወሰው ። ሰውነቱ በላብ ሰምጦ ይንቀጠቀጥ ጀመር ። በፍርሀት ታስሬ ከሚገድሉኝ ምናለ ቢያሳርፉኝ? ብሎ ራሱን በራሱ ጠየቀ ።

«አድራሻህ?»

«የእልቁ ማርያም ትምህርት ቤት አስተማሪ ነኝ — ነበርኩ» የአዲሱ ትምህርት ቤት ምስል መጥቶ በአሳቡ ተቀረፀ ። እጆቹን ሳንዳፍታ ትኩር ብሎ ተመለከታቸው ። በእጅ ብረት ተጣብቀዋል ። እጆችህን ከፉ አይንካቸው — በእጅህ የነካኸው ሁሉ ይለምልም — በእጅህ ክፉ አት ስራ......እጆችህን ስጠባበቅ ኖርኩ...... የእናቱ ድምፅ ከጆሮዎቹ ውስጥ ያስተጋባል ።

«እድሜህ?

«ሀያ ሰባት» አለና ፣ ያለምንም ትርጉም ያለፈ ሀያ ሰባት ዘመኖች ብሎ ተጨማሪ ማብራሪያ ለመስጠት አስቦ ነበር ።

«የተከሰስክበት ወንጀል?»

«አቶ ይርጋ አለሙ የተባሉትን ሰው ገድለሀል በመ ባል......»

የመሀል ዳኛው የሀዲስን ማንነት አረጋግጠው ሲያበቁ ፣ አንድ ወረቀት ከዶሴ ውስጥ አውጥተው ሀተታውን ማን በብ ጀመሩ — «ሀዲስ ሳህሉ ፣ እድሜው ሀያ ሰባት አመት ፣ አድራሻው እልቁ ማርያም ትምህርት ቤት የሆነ ፣ አቶ ይርጋ አለሙ የተባሉትን ሰላማዊ ሰው በቂም በቀል ተነ ሳስቶ ፣ ቀንና ሰአት ወስኖ በማድባት ሁለት ጥይት ተኩሶ በግፍ ገድሏቸዋል በመባል በወንጀለኛ መቅጫ ህግ መሰ ረት በአቃቤ ህግ ተከሰሰ ። ሙቱ ከተማ ያስቻለው የከፍተኛው ፍርድ ቤት በቀረበለት መረጃ መሰረት ጉዳ ዩን መመርመር ጀመረ ። ተከሳሹ ወንጀል አልፈፀምኩም ሲል ቃሉን ቢሰጥም ፣ አቃቤ ህጉ የአይን ምስክር አቅ ርቦ ፣ በምስክርነት የቀረበችው ሻታዬ...... ተከሳሽ ፣ ሀዲስ ሳህሉ አቶ ይርጋ እለሙ የተባሉትን ሰላማዊ ሰው ሁለት ጥይት ተኩሶ ሲገድላቸው በአይኔ አይቻለሁ ብላ

በመሀላ የምስክርነት ቃሏን ስጥታ ፤ መስቀለኛ ጥያቄ በቀረበላትም ጊዜ የሰጠችው መልስ አጠራጣሪ ሆኖ ስላልተገኘ……»

የዳኛው ድምፅ ለሀዲስ ከሩቅ የሚመጣ ያህል ነበር ደብዝዞ የሚሰማው ። አተኩሮ የሚያዳምጠው የልቡን ትርታ ነበር ። ሀልውናው የልቡን ትርታ ስልት እየተከተለች ለመኖር ያላትን ፍላጐት በፍርሀት ሞፈራ ትገልፃለች ።

«……እንዲሁም ፤ በተከሳሹና በሟቹ መካከል የከረረ የአሳብ ግጭትና አለመግባባት ስለመኖሩ የመቶ አለቃ አሸኔ የሰጠው የምስክርነት ቃልና ሟቹም በበኩላቸው ለጠቅላይ ግዛቱ የትምህርት ቤቶች ስራ አስኪያጅ ፤ ተከሳሹ ተማሪዎችን በማሳደምና በማነሳሳት ከሚፈፅመው ህገ — ወጥ ተግባር ሌላ ፤ ስልጣናቸውን በመጋፋት ለሌሎች አስተማሪዎች መጥፎ አርአያ ስለሆነ ፤ ወደሌላ ቦታ እንዲዛወር ያመለከቱበት ሁለት ደብዳቤዎች በኤግዚቢት ቀርበው ፤ በሁለቱ መካከል የከረረ አለመግባባት መኖሩን በተጨማሪ ስላረጋገጡ ፤ በተለይ ፤ አቶ ይርጋ ሞተው በተገኙበት እለት ተከሳሹ ያለፈቃድ ከስራ ገበታው ላይ ጠፍቶ መቱ ከመጠጥ ቤት ተይዞ ፤ ለምን እንደመጣ ቢጠየቅ «ለግል ጉዳይ ነው» ከማለት ሌላ ምክንያት ለማቅረብ ባለመቻሉ ፍርድ ቤቱ የአካባቢውን ሁኔታ በማመዛዘን ፤ ተከሳሹ ወንጀሉን በፈፀመበት ቦታ በስቅላት እንዲቀጣ በይኖበት ነበር……»

«ነበር» የተባለችው ማሰሪያ ግስ ከጆሮዎቹ ስትገባ ፤ ሀዲስ የልቡን ትርታ ማዳመጥ አቁሞ ከዳኛው ድምፅ



ላይ ያተኩር ጀመር ። ዳኛው በድንገት ግዙፍ መስለው ታዩት ። ግዙፍነታቸው በአእምሮው ውስጥ እየጐላ ሄደ ።

«ፍትህ የእግዚአብሄር እንጂ የሰው አይደለችምና ፤ በቀረበልን ማስረጃ መሰረት ህጉን ተርጉመን ውሳኔ ብን ሰጥም ፤ የንፁህ ሰው ሀይወት በከንቱ አልጠፋም …

«ቆሎሳ የተባለው ሰው አቶ ይርጋ አለሙን የገደልኳቸው እኔ ነኝ በማለት እጁን ሰጥቶ ፤ ወንጀሉን የፈፀመበትን ቦታ ስለመራና የገደለበትንም መሳሪያ ስላስፈከበ ፤ አንተ ሀዲስ ሳሁሌ ከዛሬ ጀምሮ በነፃ ፍርድ ቤቱ አሰናብቶሀል ። በነፃ ለመለቀቅህ አስፈላጊውን ማዘዣ አስተላልፈናል …

«ቃለ መሀላዋን አፍርሳ በሀሰት የመሰከረችብህ ሽታዬ ……የተባለችው ሴት ላይ የወንጀል ክስ እንዲመሰረትባት ትእዛዝ ሰጥተናል። »

ሀዲስ ከደስታው ብዛት የተነሳ ለጊዜው ልቡ እንደ መቆም ፤ የታፈነ ይመስል መተንፈስ አቃተው ። ጥቂት ጊዜ ቆይቶ ነበር ደስታው ተበርዞ ወደሀዘን እየተለወጠ የሄደው ። ቆሎሳ በእርሱ ገመድ መግባቱን እየሰማ በመደሰቱ ራሱን መልሶ ታዘበ ።

«ህግን የሚተረጉመው ሰው እንደመሆኑ መጠን ፍትህ አትጓደልም ማለት አይቻልም ። በህግ ስም በደል ሊፈፀም ይችላል ። ይሁን እንጂ በስልጣን የተለያዩ ፍርድ ቤቶች እንዲቋቋሙ የተደረጉት በህግ ስም በደል እንዳይፈፀም ለመከላከል ነው — አንዱ ከሌላው አይሻልም ካላልን በቀር ። ይግባኝ አልጠይቅም በማለትህ ያሰወ

ቅሰሀል ። ፍትህ በትእግስት እንጂ በትእቢት አትገኝም የዘመኑን ልጆች እግዜር ከትእቢት ሰውሮ ትእግስት ይስጣችሁ ።» ሀግ አስከባሪው ፖሊስ መጥቶ የእጅ ብረቱን ሲያወልቅለት ፣ እንባ ባቀረሩ ትናንሽ አይኖቹ ነፃ የወጡትን እጆቹን ለጥቂት ጊዜ ትኩር ብሎ ተመለከተና ፣ እንደልማዱ ግንባሩን ከመሬት ትይዩ አድርጐ እያዘገመ ወጣ ። ብዙም ርቆ አልሄደ ፣ ቶሎሳ በፖሊሶች ታጅቦ ሲመጣ ከሩቅ አይቶት ሮጦ ሄደና አቀፈው ።

«ጋሼ — ጠቁረሀል — ከስተህ ከሰውነት ወጥተሀል ። ቅስምህ ተሰብሯል ። አትጠራጠረኝ ። ሞት እንደሆነ አያስፈራኝም ። አትዘንልኝ ። ድፍረት ከልጅነቴ ጀምሮ አብሮኝ ያደገ ነገር ነው ።»

«ምን አሳሰበህ?»

«አንድ ቀን……ተመልሰን ወደቤት ስንሄድ የአቶ ይርጋን ቦታ ብትይዝ ምን ታደርጋለህ ብዬ ስጠይቅህ የሰጠህኝ መልስ ትዝ ይልሀል?»

«አዎን» ።

«ያ አሳብህ ለምን እንደሆነ እንጃ መንፈሴን ቀሰቀሰው ። ዋናው ምክንያት ግን አንተ ያቶ ይርጋን ቦታ ይዘህ ሱጴ ከአይናለም ጋር እንድትቀር ባደርግ ፈታውራሪ ይደሰታሉ ብዬ በማሰብ ነው ። የታየኝ ያንተ ፣ የአይናለምና የፊታውራሪ ደስታ ነው ። አልተማርኩም ። ምን ላድርግ……»

«ጥፋቱ የኔ ነው ። አጉል ተስፋ ባላሳድርብህ ኖሮ ለዚህ አትደርስም ነበር……»



«የለም ጋሼ እንዲህ አትበል ። ያሳደርከብኝ አጉል ተስፋ አይደለም ። ያስብከውን በእጅህ ስራ ላይ ካላዋልከው የኔ ሞት በከንቱ ይሆናል ። ምን ባልማር ምኞት አለኝ ። ባላገርነቴን ብቻ አትመልከት ። ሌላ መታሰቢያ የለኝም ። ጋሼ ቃል ግባልኝ ።»

ቶሎሳን ያጀቡት ፖሊሶች ትእግስታቸውን ጨርሰው ነበርና ሀዲስ ሌላ ቃል ሳይተነፍስ አንገት ሳንገት ተያይዘው ጉንጭ ለጉንጭ ተሳሳሙና በእንባ ተለያዩ ። ሀዲስ ወደ ሁዋላ እንኳ መለስ ብሎ ለማየት አልደፈረም ። የመኖር ሸክም የተጫነው ይመስል አንገቱን እንዳቀረቀረ መንገዱን ቀጠለ…… ምን ባልማር ምኞት አለኝ ። ባላገር መሆኔን ብቻ አትመልከት …… አትመልከት ……አትመልከት ……የቶሎሳ የመጨረሻ ቃላት ከአረማመዱ ጋር በስልት ከጆሮዎቹ ውስጥ ያስተጋቡ ነበር……

በአስራ ሁለት ብር በቅሎ ከመቱ ተከራይቶ የሶርን ፣ የዲሲንና የገባን ወንዞች በመሻገር ዝናብና ፀሀይ ፣ ብርድና ሙቀት እየተፈራረቁበት እህል ወሀ ሳይል ገስግሶ ፀሀይ ከመጥለቋ ጥቂት ደቂቃዎች ቀደም ብሎ ከትምህርት ቤቱ ከመድረሱ በፊት ፣ ሲጓዝ ሁሉ የተፈጥሮ ውበትን ማድነቁ ቀርቶ የነበረበትን ቦታ አያውቅም ነበር ። ተፈጥሮ እንደመድረክ ላይ መጋረጃ በአእምሮው ውስጥ የሚመላለሱትን አሳቦች ከማጉላት ሌላ የራሷ የሆነ ሀልውና አልነበራትም ። የእናቱና የቶሎሳ ቃላት ከገባ ወንዝ ፏፏቴ በላይ ነግሰው ከሰጋር በቅሎዋቱ ፍጥነት ጋር በስልት ከጆሮዎቹ ውስጥ ሲያስተጋቡ ይቆዩና ፣ እየደበዘዙ ፣ እየደከሙ ሄደው ሳዲሱ ትምህርት ቤትና

ለአይናለም ቦታ ይለቃሉ ። አይናለም ፣ ትምህርት ቤቱ ፣ ትምህርት ቤቱ ፣ አይናለም ፣ ባንድነት አንድ አካል ሆነው በአሳቡ ጉዳና ሽርሽር ይላሉ ። ያሳቡ ሑደት ይቀጥላል ። በዚያ የአሳብ ሑደት ውስጥ እየተማነው ለውነቱን እያደ ከመውና አይኑን እያፈዘዘው ለሚሄደው ስቃይ ከመን ፈሱ ብርታት የተነሳ ቦታ አልሰጠውም ። ከትምህርት ቤቱ ደርሶ ላብ ከምትደፍቀው በቅሎ እንደወረደ እልልታው እንደጉድ ሲቀልጥለት አፀፋውን በመመለስ የእጅ ሰላምታ እንኳ ለመስጠት ጊዜ አላገኘም ። ወደ አዲሱ ትምህርት ቤት ሮጦ ገባ ። ገና እግር እንዳወጣ ህፃን ወለሉን ፣ ግድግዳውን ፣ ጣሪያውን ፣ መስኮቱን ፣ መዝጊያውን በአድናቆት እየተመለከተና ሊደርስበት የሚችለውን ሁሉ በእጅ እየነካና እየዳሰሰ ካንዱ ክፍል ወደ ሌላው በመሮጥ ስድስቱንም ክፍሎች አዳረሰና ፣ ከቤቱ ምሰሶዎች ውስጥ አንዱን አቅፎ ቆመ — በእጆቹና በጉንጮቹ እየዳሰሰው እንባዎቹ አፍንጫውን ተከትለው እየ ወረዱ ከደገው ጢሙ ውስጥ እየገቡ ፣ መነሻ እንጂ መድረሻ እንደሌለው ነገር ሲጠፉ ይታያሉ ።

አይናለም ወደላይ የቀለበችውን ቀሚሲን ለቅቃ ከደ ስታዋ ብዛት እንባዋን እያንዠረዠረች መጥታ ከእግሩ ላይ ልትወድቅ ስትል እጅዋን ይዞ ወደምሰሶው አስጠ ጋችና ሁለቱም ከምሰሶው ጋር በቁም የታሰሩ መስለው ቀቅራኞቹው ቀሩ ። የመንፈስ ጥንካሬው እየደከመ ፣ እየከዳው ፣ በመላ ሰውነቱ የተሰራጨው ስቃይ እየየለ ፣ እየበረታ ፣ ናፍቆቱንና ስቀቀኑን እየደመሰሰው ሄደ ። እያላበው ፣ ባንድ በኩል ደግሞ ሰውነቱ ውርጭ እንደ መታው ሲንቀጠቀጥ ይታያል ። ምሰሶውንና አይና



ለምን እንደያዘ ጉልበቱ ከድቶት ተንበረከከ ። ከዚያ ማንኛውም ነገር ባንድ ጊዜ ጨለመበት ። ፈታውራሪ ከምሰሶው እጁን አላቀው በወሳንሳ ወደቤት ቢያስወስ ዱትም ፣ በጠና በመታመሙ ከደረባቸው ሀዘን ይልቅ በነፃ የመለቀቁ ደስታ ስላመዘነባቸው ቤታቸው ሲበላና ሲጠጣ ቢታደርም በአይናለም አይን እንቅልፍ የሚሉት ነገር ፈፅሞ አልተኳለም ። ሀዲስን ከመጠን በላይ ሲያ ተኩሰውና ተቅማጥና ትውከት ሲፈራረቁበት ነበር ያደ ረው ። የአይኑ ሞራ ወደላይ ተገልብጦ የሞተ ይመስልና ባንድ በኩል ደግሞ እየተወራጨ ድምፁን ከፍ አድርጐ ይቃዣል — ያልረገፈ ፅጌ ረዳ አበባ……ስረየት ነው…… እናቱ እጁን ስትጠብቅ ብትሞት እናት ኢትዮጵያ እጆቿን ዘርግታ እጁን ታያለች — ትጓጓለች ። እጅ'ኮ ነው መድ ሀኒ ። እጁን እያየች ስትጓጓ ምን ብዬ ባዶ እጄን ይገኜ ልያት — አይናን! የትምህርት ቤቱ ስራ ለፍፃሜ የተቃ ረበው ባንድ ቋንቋ — በእጅ — መናገር ስለቻልን ነው ። የባቢሎን ግምብ ለምን ፈረሰ? በቋንቋ አለመግባባት ምክ ንያት ነው……የባቢሎን ግምብ…… አይናለም ከግ ንባሩ ላይ ላቡን በነጠላዋ እየጠረገች ትርጉም የማይሰ ጠትን ቅዠቱን በፍርሀት ታዳምጣለች ። ትንሽ ሸለብ ያደርገውና ደግሞ ይቀጥላል — ነፃ እጅ…… አለም አቀፍ ቋንቋ……እምን…… ሀልውና ያለእንቅስቃሴ ሑደት ሞት ነች — ከአለም ፣ ከከዋክብት ፣ ከጨረቃ ፣ ከተፈ ጥሮ ጋር መንቀሳቀስ — የእንቅስቃሴ ሑደት የመኖር ትርጉም…… ሀይወት…… እህ…… ሀይወት ምንኛ ጣፋጭ ናት ። ነገን የሚያበስር ደወል ጣእም……የትናንቱ ቀን ሀይወት ሙዚቃ ትዝታው! የዛሬው ቀን ሀይወት ፍንደቃ ፣ የትናንቱን ከዛሬ ፣ የዛሬውን ከነገ ጋር የሚያገናኘው የእ

ንቅስቃሴ ኡደት……ስራ …… እጅ ……ስረየት…… እያልፍ የለምና ሲነጋጋ አቅራቢያ አይናለምን ያሳደጓት አሮጊት ወፍ ያልዘረበት ወሀ ይዘው መጥተው የሀዲስን ግላ አጠቡና «አይዞሽ ልጄ ፣ አትስጊ ። ምንም አይን ካውም ። ሲታጠብ እንዳየሽው ከገላው እንፋሎት ከተነሳ ይድናል» አሏት ።

«በሽታው ምን እንደሆነ ታውቆ መድሀኒት ቢገኝ ለት ጥሩ ነበር ። ዛሬውኑ ወደመቱ ካልወሰድነው እዚሁ መሞቱ ነው……»

«ተስቦ ነው የያዘው ፣ ሌላ አይደለም ። የውስጥ አይኑ ነጥቶ አይታይሽም ። የፈረንጅ መድሀኒት ተስቦ ሲያድን አላየሁም ። እዚሁ ብዙ መድሀኒት አለ ። የሚያ ቃዠው ነገር እንዲተወው ደግሞ ፣ ንፍሮ ተቀቅሎ ቡና ተፈልቶ ፣ ትንሽ ደም አፍስሶ መለማመን ነው ። ልብሱ በእምቧይ ከታጠበና ቤቱ ሁሉ ቄዬው ሳይቀር በባህር ዛፍና በግራዋ ታጥኖ ከተጠረገ ምንም አይደርስበትም ። ተቅማጡንና ትውከቱን የሚያስተወው መድሀኒት አው ቃለሁ ። አታስቢ» ብለዋት ወጡ ። አይናለም አልተፅ ናናችም ። አባቷ እስኪነሱ ነበር የምትጠብቀው ። ግን ፊታውራሪ ቀደም ብለው ወደ «ሀኪም» የሺጥላ ሰው ልከው ኖሮ ፣ የጧት ፀሀይ ሙሉ ድምቀቷን ተጐናፅፋ መውጣት ስትጀምር መልእክተኛው እየገሰገሰ ተመልሶ መጥቶ «ሀኪም የሺጥላ ባገሩም የሉም!» አላቸው ።

«የት ሄደ‚ል?»

«ምኑ ቅጡ! ትናንት ማምሻውን ፖሊሶች ይዘውት ወደ መቱ ወሰዱት አሉኝ»



«ለምን?»

«ምኑ ቅጡ! አንድ ሴት ታመምኩ ብላ ወደቤቱ ሄዳ መርፌ ወጋትና ፣ ሰአት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ሰው ነቷ ተንርቶ ብትሞትበት ፣ ጓሮ ከበቆሎ ውስጥ ቀበራት አሉ ። ባለቤቷ መጥቶ ቢጠይቅ ፣ እንዲህ አይነት ሴት ጨርሶ ቤቴ አልመጣችም ብሎ ስላባረረው ፣ ሰውዬው ሄዶ ለፖሊስ አመለከተ ። ሴቲቱ ወደሀኪም የሺጥላ ቤት ስትገባ የተመለከቱ የአይን ምስክሮች ቀረቡ ። ምኑ ቅጡ ሀኪም በገንዘብም በምንም እያለ ነገሩን ለማረሳሳት ሞክሮ ነበር ። ሴቲቱ ባለብዙ ወገን ነበረችና ምርመራው ቀጥሎ ሬሳዋ ከተቀበረበት ከበቆሎ ማሳ ውስጥ ተገኘ ። ምኑ ቅጡ! »

የፊታውራሪ ተካ አሳብ አስራ አምስት አመት ወደ ሁዋላ ተመለሰ ። የአይናለም እናት ሀኪም የሺጥላን ከቤት ድረስ አስጠርተውት መርፌ ከተወጉ በሁዋላ ሰውነታቸው አባብጦ «ተቃጠልኩ ፣ ነደድኩ» እንዳሉ በሶስት ቀን ውስጥ ለአፈር መብቃታቸው ትዝ አላቸውና «ለካስ ልክ ፍት ሌላ ኖሮአል!» አሉ ፊታውራሪ ።

«ምኑ ቅጡ! ልክፍት መቸ ሆነና ። መርፌው መርዝ ሆኖባት ነው የሞተችው አሉ!»

«ነገሩ ወዲህ ነው ። ሰው የእጁን ዋጋ አያጣ!»

«የእጁን ዋጋ አገኘ እንጅ!»

«እርሱ ብቻ ነበር አለኝታችን ። ቅጠላ ቅጠልና ስራ ስር አትብሉ አደገኛ ነው እያሉ ይመክሩናል — በራ ዲዮና በጋዜጣ ። የፈረንጅ መድሀኒት ደግሞ የለንም ። በምኑም በምናምኑም እንደቅጠል መርገፍ……የእግዜር

ፍርጃ ነው እያልን ፡፡ የጤና ታክስ መክፈላችን ሳይቀር ፡፡ አሁን ታዲያ ይህን ልጅ የት ልውሰደው? አሁንስ ግራ ገባኝ ፡፡ ሀዘኑም ደስታውም እንደቀንና ሌሊት ተፈራረቁብኝ……» በማለት ጊዜውንና እድላቸውን እያማረሩ ሲተክዙ ቆዩና ፤ ሀዲስን ወደመቱ ወስደው ሀኪም ቤት ለማስገባት ስለወሰኑ በቅሎአቸው እንድትማን አዘዙ ፡፡ የጉዞው ዝግጅት በጥድፊያ ቀጥሎ አንድ ሰአት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ሀዲስ በአራት ሰዎች በወሳንሳ ተይዞ ፤ ሌሎች ስድስት ሰዎች ደግሞ በረዳትነት እየተከተሉ ፤ ፊታውራሪ በበቅሎአቸው ከፊት ቀድመው ፊታቸውን ወደገባ አዞሩ ፡፡ ከደጃፍ ሲደርሱ ሀዲስ የገረጣ ፊቱን ወደእይናለም መልሶ በደከመ ድምፅ «አንቺ እዚሁ ቅሪ ስላልኩ አዝናለሁ ፡፡ አብረን ብንሄድ ደስ ባለኝ ነበር ፡፡ ነገር ግን የትምህርት ቤቱ ስራ በኔ ምክንያት መቆም የለበትም ፡፡ ከፍፃሜ መድረስ አለበት ፡፡ እኛ እናልፋለን ፤ ትምህርት ቤቱ ግን ይኖራል — ጊዜና ዘመንን አቋርጦ ፡፡ እኔንም ፊታውራሪ አስገድደውኝ ነው እንጂ ትምህርት ቤቱ ሲሰራ እያየሁ ብሞት ደስ ባለኝ ነበር» ብሏት ፤ እርሷም እስከትምህርት ቤቱ ድረስ ተከትላው ሄደች ፡፡

ሀዲስ ላንዳፍታ ከተኛበት ቀና ብሎ ትምህርት ቤቱን ተመለከተ ፡፡ አይኖቹ እንባ አቀረሩ ፡፡ አይናለምንና ትምህርት ቤቱን ወደ ሁዋላ በመተው ጉዞው ወደፊት ቀጥሎ የገባን ወንዝ ቁልቁለት እንዳጋመሱ የፍፋቴው ድምፅ እየጐላ ፤ እየቀረበና በፍርሀት የሚያሸብር ስሜት እየፈጠረ ይሰማ ጀመር ፡፡ ቁልቁለቱን ሳይጨርሱ ፤ የገባን ወንዝ አቋርጠው አቀበቱን በበቅሎ የተያያዙ ሁለት ጠያይም ወጣቶችና የብረት ሳጥኖቻቸውን የተሸከሙ ሶስት ተከታዮች በመንገድ ተገናኙ ፡፡ አንደኛው ወጣት ከበቅሎው ወርዶ አፍንጫውን በንፁህ ነጭ መሀረብ ሸፈነና ወደሀዲስ ተጠግቶ ፤ የአይኖቹን ክፈን ከፍቶ ተመለከተውና «እንዴት ነው የሚያደርግሀ?» ብሎ ጠየቀው ፡፡



«ያስታውከኛል ፤ ደም ያስቀምጠኛል……»

«ያተኩስሀል?»

«በጣም»

«መቼ ነው የጀመረህ?»

«ትናንት ነው»

«ቀላል ነው ፡፡ ተስቦ የያዘህ ይመስለኛል» ብሎ ከበቅሎ ላይ ተቀምጦ ወደሚጠብቀው ጓደኛው ሄደ ፡፡ ለአምስት ደቂቃዎች ያህል በሹክሹክታ ሲወያዩ ቆዩና ከበቅሎዋ ላይ ያለው ወጣት ድምፁን ከፍ አድርጐ «አንተ ደግሞ የእግዜር ባህርይ ያለህ ይመስል በሄድክበት በሽተኛ እያየሁ አላልፍም ትላለህ! ትናንት በዚሁ ምክንያት ኖጳ ከቁንጫና ከቴሀን ጋር ስታገል አደርኩ ፡፡ አሁን ደግሞ ይህን ሰው እዚሁ ቆይተን እንርዳው ማለትህ ያስገርማል ፡፡ አንተን ለመሆኑ የአለም ተቆርቋሪ ሀሊና ያደረገህ ማን ነው !» አለው በንዴት ፡፡

«አንተ ብትፈልግ ሂድ ፡፡ እኔ ግን ይህን ሰው መርዳት አለብኝ ፡፡ የያዘው ተስቦ ነው ፡፡ የተከተሉትም ሰዎች ሊለከፉ ይችላሉ……»

«አገሩን በሙሉ ልትከትብ ነዋ!»

«የተቻለውን ያህል……»

«ማን ፈቀደልህና!»

«ፈቃድ መጠየቅ አያስፈልገኝም……»

«እየሀ.....እነዚህ ሰዎች ክሊኒክ አቋቁመው ፤ ትምህርት ቤት ከፍቱ ፤ መንገድ ሰሩ ሲባሉ እሺ አይሉም ። ካልተገደዱ አይሆንላቸውም ። ተአምር ነው የሚጠብቁት — ከሰር ከሰሩ መቅሰፍት ሲጨርሳቸው እያዩ ። እግዜርም የሚረዳው ራሱን ለመርዳት የሚጣጣረውን ነው ። አንተ የምን ቤት ነህና ነው እንዳቄስ በቅሎ በየበታው እንቄም የምትለው! አሁን ብትረዳው ነገ ተመልሶ ያው ነው ። መፈወሱን እንጂ ምክርህን አይቀበልም ። እኔ አውቃለሁ ። ካንተ የበለጠ በጤና መኰንንነት ሰርቻለሁ ። ልትለውጥ የምትችለው ነገር የለም ። ማንኛውም እንደሰንበለት የተያያዘ የማይበገር ጋራ ነው ። በዚህ ሁኔታ ከቀጠልክ ከዚህ አልጋ ለመድረስ አመት ሳይፈጅብህ አይቀርም.....» ።

«ይህ ሁሉ ሀተታ አያስፈልግም ። ካሰቡበት ጋራው ሜዳ እንዲሆን ለማድረግ ይቻላል ። አንተ ሂድ» አለውና ሀዲስን ይዘውት እንዲመለሱ አዘዘ ።

የፊታውራሪ ስሜት በሙሉ የሀዲስን ህይወት ወደማትረፍ ተመርቶ ነበርና ፤ ጓደኛው በተናገረው ቃል ለመናደድም ሆነ ለማዘን ጊዜ ስላልነበራቸው ፤ እርሱን ወደጐን አድርገው «ሱዴ ይዘነው ብንመለስ ምን ይገኛል ብለህ ነው? ሆስፒታል የለም ። መድሀኒት የለም ። ያለው የመንደር መርፌ ወጊ ብቻ ነው.....» ብለው ሳይጨርሱ አቋረጣቸውና —

«ተስቦ ነው የያዘው ። ለተስቦ የሚሆን መድሀኒት ይጠፋል ። እኔና ጓደኛዬ የጤና መኰንኖች ነን ። መቱ ቢወስዱትም እኛ ከምንሰጠው ርዳታ የበለጠ አያገኝም ።



መቱ እስኪደርስ ድረስ በሽታው ይጠናበትና ሊሞት ይችላል» አላቸውና ቀጥሎ «ልጅዎ ነው?» ብሎ ጠየቃቸው ።

«አማቼ ነው» አሉት ።

ፊታውራሪ የተሻለ ምርጫ ስላልነበራቸውና ፤ በሽተኛ ይዞ ረጅም መንገድ መጓዝ አደገኛ መሆኑ ስለተከሰተላቸው ከጤና መኰንኖቹ ጋር ሀዲስን ይዘው ወደ ሱዴ በመመለስ አሳብ ተስማሙ......

የገባን አቀበት ወጥተው ፤ የእልቄን ወንዝ ተሻግረው ፤ ሜዳውን አቋርጠው ሰንበተ ጉዳን አልፈው ከአዲሱ ትምህርት ቤት አጠገብ ሲደርሱ ፤ ሀዲስ እንደምንም ከተኛበት አንገቱን ቀና አደረገ ። በወሳንሳ ተሸክመውት የሚሄዱት ሰዎች ፍላጐቱንና ስሜቱን ያውቁ ነበርና ቆሙ ። ወደሱዴ እንዲመለሱ ያዘዘው ወጣት ተደናግጦ ፤ «ምንድን ነው? ምን ሆናችሁ?» ብሎ በጥድፊያ ሲጠይቅ ፤ ሀዲስ ትምህርት ቤቱን በፈዘዙት ትናንሽ ጥቁር አይኖቹ ፍዝዝ ብሎ ለጥቂት ደቂቃዎች ተመለከተና ከወሳንሳው ላይ ተመልሶ ተጋደመ ። ሰዎቹም መንገዳቸውን ቀጠሉ ። ፊታውራሪ ለወጣቱ የጤና መኰንን ስለትምህርት ቤቱ ስራና ስለሀዲስ አንስተው ያጫወቱት ነበር ። በተመሰጠ መንፈስ ሲያዳምጣቸው ቆይቶ ከቤት ሊደርሱ ሲሉ «ትምህርት ቤቱን እንደዚያ ትኩር ብሎ ሲመለከት ባየሁት ጊዜ የሚያመልከው መስሎኝ ነበር ። ውነትም ደግሞ በእጅ እየሰሩ ለዚህ ህዝብ መስዋእትነት ምን እንደሆነ ማሳየት አዲሱ አምልኮት መሆን አለበት» አላቸው ።

«የሱ ጠባይና ዝንባሌ ትንሽ ትንሽ ይታይብሀል» አሉት ከበቅሎ ከመውረዳቸው በፊት ።

ከቤት እንደደረሱ አሞር ፣ ጠይም የጤና መኰንኑ ጊዜ ሳያጠፋ ለሀዲስ ርዳታ አደረገና ለቤተሰቡ ሁሉ የመከላከያ ክትባትና አስፈላጊውን ምክር ሰጠ ። ይህ ሁሉ ሲሆን ጓደኛው የቀረበለትን ጠጅ ከታዛ ስር ቁጭ ብሎ እየተከዘ ይኰመኵም ነበር ። ጓደኛው ስራውን ጨርሶ ብቅ እንዳለ «እህስ — አቶ ሀሊና!» አለው ፣ ወዝ የሌለው ፈገግታ እያሳየው ።

«ጥሩ ስም ሰጠህኝ ጃል» አለውና ከፊቱ ላይ ላቡን እየጠረገ አጠገቡ ቁጭ አለ ።

«አዎን — ግን አሁን በትንሹም በትልቁም የሚወራጨው ሀሊናህ ብዙ ነገር ማየት ሲጀምር ቀስ በቀስ ማንቀላፋት ይጀምራል……»

«ያኔማ ሞትኩ ማለት ነው……»

«የለም — እንደሁኔታው መኖር ትጀምራለህ ። ምን አለ በለኝ ። የድርሻህን አትስራ ማለቴ አይደለም ። ህሊናህ የአለም መድህን ሊሆን አይችልምና በሁሉም ነገር ማልቀሱን ቢተው ይሻላል ። በነገራችን ላይ ፣ ከታመመው ሰውዬ አጠገብ የማትጠፋው ልጅ ማን ናት?»

«የሀዲስ ሚስት ፣ የፈታውራሪ ልጅ ናት……»

«ውብ ናት ። የውብ ውብ ። አይናቿን ገለጥ ስታደርጋቸው እንደጦር ተወርውረው ልብ ይወጋሉ ። የአይናቿን ጦር እንዳትሸሸው የደም ግባቷ ይስባል ። ፊቷ ላይ እንደጕህ የሚቀደው ፈገግታዋ እንደጠዋት ጮራ እየሞቀ በመላ ሰውነት ውስጥ ይሰራጫል……»



«ባለቅኔ ነህና!»

«አንተኮ ጮርቃው ሀሊናህ ብቻ ነው እንጂ የሚወራጨው አይኖችህ ውበት አይከስትላቸውም ። እህ — በየባላገሩ የመንከራተት ትርፉ እንደቧ አይነቶቹን ትኩስ — ለጋ አበባዎች መቅሰም ነው ። ቀለሟ'ኮ ይሆን ጠጅ ነው የሚመስለው» አለና ጠጁን አንስቶ ተጐነጨ ።

«ዝንባሌህ አስፈራኝ ። ብንሄድ ይሻላል ። ትናንት ያቺን ሴት ከመንገድ ላይ ይዘህ ማካ ውስጥ የሰራኸው ስራ……»

«አህ — የአደቧ መአዛ እስካሁን ካፍንጫዬ ውስጥ አልጠፋም ። በመጨረሻ ያሳየችኝ ፈገግታ ይታየኛል ። ግን ይህችኛዋ……»

«ብንሄድ ይሻላል ነው የምልህ!»

«ብሽተኛህስ! የሀሊናውን ነገር ወዴት ትተህ?»

«መድሀኒት ሰጥቼዋለሁ ። ርግጠኛ ነኝ ደህና ይሆናል……»

«ምቀኛ ነህ ልበል — ምቀኛ ። የማትታለፍ እሸት ነች ። የባላገርነት ጠባይ አይታይባትም ። የባላገር ኑሮና ባላገሮችን እንደማልወድ አጫውቼሀለሁ ። የባላገር ሰው ልብሱ አዳፋ ፣ እንደበቱ ጕልዳፋ ፣ ቢነግሩት የማያዳምጥ ፣ ቢመክሩት የማይሰማ እምቢ ሳይል ግትር ነው ። ያለም ክንያት ይጠራጠራል ፣ ያለሰበብ ይተናኰላል ። ምክንያቱና ሰበብ አለው ስትል ደግሞ ልቡ እንደቅቤ ቀልጦ ይገኛል ። ጠባዩን ለመተንበይ አትችልም — እንደተፈጥሮ ። ያለበትን የኑሮ ደረጃ አያውቅም — የተሻለ

አላየምና ። አለማወቅ ከፋ! ራዲዮ ማዳመጥና ጋዜጣ ማንበብ የሚችሉት አንዳንዶቹማ የምን መሻሻል ፤ የምን ስልጣኔ እንደአገራችን የሰለጠነና የተሻሻለ የለም ይሉሀል ። ሰው ቢያገኝም ቢያጣም በእግዚአብሄር ቸርነት ነው ይሉሀል ። መንግስት በህይወታቸውና በኑሮአቸው ውስጥ ያለውን ቦታ አያውቁም ። የመንግስት ተግባር ግብር መሰብሰብና ፀጥታ ማስከበር ብቻ ይመስላቸዋል ። በተረፈ ግን መንግስት እንደኮከብ ከሩቅ የሚታይ — እንደጣኦት የሚመለክ — እንደፈጣሪ የሚፈራና የሚከበር — ከሰማይ የተሰጠ ታቦት መስሎ ነው የሚታያቸው ። ስለዚህ አፈር መስለው ከአፈር ጋር ቀርተዋል ። አፈሩንና ሰውን ልለይ አልችልም ። አንድ ናቸው ለኔ ። አንድ ባላገር እግሮቹን ከመሬት ተክሎ ቆሞ ስመለከተው አፈሩ የት ተጀምሮ ሰውዬው የት እንደሚያበቃ አይታየኝም — አንዱ የሌላው ቅጥያ ይሆንብኛል ። የከተማ ኑሮ ነው ደስ የሚለኝ ። በከተማ ተፈጥሮንና ሰውን ለይተህ ለማየት ትችላለህ ። የከተማ ሽታ ነው የሚናፍቀኝ ። ግን አልታደልኩም — ከተማ ለመኖር — የደሀ ልጅ በመሆኔ ። ወገን በማጣቴ እኔም እንደባላገሩ ከአፈሩ ፤ ከተፈጥሮ ተለይቼ የማልታይበት ደረጃ ላይ ልደርስ ነው ። እንደዚህች ከአፈሩ በላይ የመጠቀች ውብ ሳገኝ ግን ብስጭቴ ይረሳኛል……ግን የምልህ ሁሉ የሚገባህ አይመስለኝም……»

ጓደኛው ከተቀመጠበት ተነስቶ «ገብቶኛል ። ብንሄድ ይሻላል» አለው ትእዛዝ በተመላበት ድምፅ ። ፈታውራሪ ተካ መጥተው ነበርና ፤ ወደእርሳቸው መለስ ብሎ በጥሞና «መሄዳችን ነው ። አልጋ መድረስ አለብን ። ልጁ መድሀኒቱን በነገርኩት መሰረት ከወሰደ በሶስትና በአራት ቀኖች ውስጥ እንደሚሻለው ተስፋ አለኝ» አላቸው ።



ፈታውራሪ ተገርመው ፤ «እንዴ! እንዴት ተደርጐ! ባሁን ሰአት መንገድ ጥሩ አይደለም ። ባይሆን በማለዳ ተነስታችሁ ትሄዳላችሁ ። ዝግጅቱን በሰፊው ይዘን ነበር» አሏቸው ።

«የለም በእውነቱ መሄድ አለብን……»

«ቅድም እዚሁ ቆይተን ካልረዳናቸው ብለህ የተከራከርከው አንተው ነበርክ ። አሁን ደግሞ ካልሄድን ብለህ የምትከራከረው አንተው ነህ ። ምን የሚያስቸኩልህ ነገር መጣ ? ምንም እንኳ ዘመን ያለፈብኝ ፈታውራሪ ብሆንም እናንተን እዚህ ማሳደር አያቅተኝም ። ወይስ ቁንጫውንና ቱሀኑን ፈርታችሁ ነው!» አሉ ፤ በነገር ለመጐንተል ያህል ።

ረዘም ያለው ወጣት በነገር መጐንተሉን ወደጐን አድርጐ ፤ «እርስዎ እንዳሉት እንቅር ! እንሂድ የሚለው እሱ ነው ። እንቺው ታመጭው እንቺው ታሮጭው እንዲሉ» አላቸው ተዝናንቶ ከተቀመጠበት ለመነሳት አለመፈለጉን እያሳየ ።

«ፍፁም ! አሁን መሄድ አለብን……»

«እረ በእልቁይቱ ማርያም ምን ነካብኝ? ምን የሚያሮጥ ነገር መጣ? ወይስ ያስቀየምናችሁ ነገር አለ? የተቀየማችሁበት ነገር ካለ ባላገሮች ነንና ይቅርታ አድርጉልን……»

«መሄድ ስላለብን ነው ። ሌላ ምክንያት የለንም»

«መምሬ መሀሪ ቢኖሩ ደግ ነበር ። እኔ እንግዲህ መለመን አላውቅበት» አሉ ፤ ፊታውራሪ ተስፋ ወደመ ቁረጥ ላይ ደርሰው ። አንደኛው ለመሄድ ቁርጠኛ ሆኖ የተ ነሳ መሆኑን ፊታውራሪ ስለተገነዘቡ ፤ አገልግልና ጠጅ አስይዘው ፤ ሁለት ሰዎች ጠብመንጃ ይዘው አልጌ ድረስ እንዲከተሏቸው አዝዘው ሸኙዋቸው ። ከግቢ እንደወጡ በመሄዳቸው ያዘነው ወጣት «ምቀኛን አርቅልኝ ብሎ መለመን ትልቅ ፀሎት ነው» አለውና መንገዳቸውን ቀጠሉ ። እነርሱ ከሄዱ አስር ደቂቃዎች በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ለቶሎሳ ስንቅ ይዞ ወደ መቱ ተልኮ የሄደው መልእክተኛ መጥቶ ፤ ቶሎሳ ከእስር ቤት ለማምለጥ ሲሞክር በጥይት መገደሉን እንባ እያነቀው ለፊታውራሪ ነገራቸው ።

«ሞተ! ክንዴ ሞተ! ቀኝ እጄ ። ምርኩዜ ። አሁንማ ሀዘኑም አበሳውም እየቀለለኝ ሄደ ። ሀዘን ሲበዛ ተራ ነገር ይሆናል ። ለካ አይኖቹ ጉድ እንዲመለከቱ ነው የጐለተኝ ። እንግዲህ ምን ቀረኝ የገባ ወንዝ ሲደርቅ ከማየት በቀር ። አይ ይህች ህይወት!» አሉ ፤ እንባ — አልባ የሆኑትን አይኖቻቸውን ከአድማስ ላይ ተክለው ። የመልእክ ተኛው እዬዬ ነበር ቤተሰቡን በሙሉ የቀሰቀሰው ። ልቅሰውን በመሀል አቋርጦ ሀዲስ ከተኛበት ክፍል ሄዶ ከመቱ ይዞለት የመጣውን አድራሻ የሌለው ደብዳቤ ለአይናለም ሰጠለት ። ሴቶቹ ደረታቸውን እየደለቁና ዋይታቸውን እያቀለጡ ሀዲስ ወደተኛበት ክፍል በማ ምራት ላይ ነበሩ — «ልጄን ገድለው ሄዱ ? እኔ አይሆንም



ብዬ ነበር — የፈረንጅ መድሀኒት......» እያሉ የአይ ናለም ምግዚት ቀደሙ ። ብዙ እንባ ሳይፈስ ነበር የሞት ፅዋው የሀዲስ ሳይሆን የቶሎሳ መሆኑ የታወ ቀውና ልቅሰው ከመጠን በላይ የደራው ። ወዲያውኑ ሬሳውን እንዲያመጡ ብዙ ሰዎች ወደመቱ ተላኩ ። በሁ ለተኛው ቀን ከብቶች ወደ ቤት በሚገቡበት ሰአት አቅራ ቢያ አስከሬኑ በጃኖ ተሸፍኖ ከቤት ሲደርስ ፊታውራሪ አስከሬኑን እየዞሩት ምርር ያለ ልቅሶ በመጀመራቸው ሲለቀስ ታድሮ ጧት የሉጺ ህዝብ በተገኘበት በእልፍ ማር ያም ቤተ ክርስቲያን የቶሎሳ ግባተ መሬት ተፈፀመ ። ቶሎሳ ያሰብከውን በእጅህ ስራ ላይ ካላዋልከው የኔ ሞት በከንቱ ይሆናል......ምን ባልማር ምኞት አለኝ......ቃል ግባልኝ ብሎት ትቶለት የሄደው ነዛዜ ትዝ እያለው ሀዲስ በዝምታ እንባውን በሚያፈስበት ጊዜ ነዛዜውን ለመፈጸም ለራሱ ቃል እየገባ በትምህርት ቤቱ ስራ ፍፃሜ አማካይነት እንደፈጣሪ ትኖራለህ......ትኖራለህ ......ለዘለአለም ይል ነበር በልቡ ። ሆኖም ፤ በሀዘኑ ምክንያት የትምህርት ቤቱ ስራ ፈፅሞ በመቆሙ የቶ ሎሳ ምኞት፡ኮ ይህ አልነበረም በማለት መንፈሱ እየተ ሸበረ ስለሄደ አይናለም ቶሎሳ በተቀበረ በአራተኛው ቀን ጧት በሌሊት ተነስታ ወደትምህርት ቤቱ ስራ ፊቷን አዞረች ። በሶስት ቀኖች ውስጥ ስራው ፍጥነት እየጨ መረ መሄድ ጀመረ ። ሀዲስም በመድሀኒቱ ሀይል ብቻ ሳይሆን በመንፈሱ ብርታት ከእለት ወደእለት እየተሻ ለው ሄደ ። ግን ከሀዲስና ከአይናለም ይልቅ ፊታ ውራሪ ተካ ስለትምህርት ቤቱ ስራ ከፍተኛ ስጋት አድሮ ባቸው ለእረፍት ቀርቶ ለእህል እንኳ ጊዜ ማጣት ስለ ጀመሩ ፤ አንድ ምሽት ሊጠይቁት መጥተው ገና ቁጭ

ከማለታቸው «ለምን እንደዚህ ይሯሯጣሉ? ለጤናዎም ቢሆን ጥሩ አይደለም ። እኔም ተሸሎኛል ። አይናለም እንደምትነግረኝ ስራው ወደማለቅ ላይ ነው......» ብሎ ሳይጨርስ ከአፉ ቀበል አደረጉና «ስራ ማንንም አልገደለም ። እንዲያውም ህይወቴ እየታደሰ ነው የሄደው ። ቢሆንም የምሯሯጠው የቀጠሮ ሰአት ስለደረሰ ነው» አሉት ።

የህይወታቸውን መታደስ ከፊታቸው ላይ ለማንበብ ይቻል ነበር ። «የምን ቀጠሮ?» አላቸው እንደመደንገጥ ብሎ ።

«ሙሽራው መጣ በርበሬ ቀንጥሱ እንዳይሆን ብዬ ነው ። የሙሽሮቹ መምጫ ሰአት ተቃርቧል ። አዎን — ሙሽሮች ናቸው — ተማሪዎች ። ትምህርት ቤት ሊከፈት ከእንግዲህ ምን ቀረው? ሀያ ቀን ብትሆን ነው ። ቀጠሮውን አክብረን ተዘጋጅተን ሙሽሮቹን መቀበል የለብንም?» አሉት ፈገግ ብለው ።

ሀዲስ ባለፉት ጥቂት ሳምንቶች ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በፊካ ፈገግታ ፤ ልቡ ደግሞ በአዲስ ተስፋ ተሞሉ ። ይሁን እንጂ ፤ የትምህርት ቤቱ ስራ ከተፈፀመ ህይወቱ ምን አግጣጫ እንደምትይዝ ባለማወቁ ያደረበትን ደስታ የሀዘን ሽውታ ሙልሶ ጋረደው ። ለአንድ አጭር አመት የመጣ ቢሆንም የትምህርት ቤቱን ስራ ከፍፃሜ እስከደረሰ ድረስ ከሉዱ የትም እንደማይሄድ ልቦናው ቢያውቅም ስራው ወደፍፃሜ በመቃረቡ መንፈሱ በድንገት መሸበር ጀመረ ።



ከሞቱ ተልኮለት በሀመሙ ምክንያት ተረስቶ የቆየውን ደብዳቤ አይናለም ወደስራ ከመሄዱ በፊት ሰጥታው ነበርና አድራሻ ያልተፃፈበትን ፖስታ ከፍቶ ለማንበብ ልቡ ፈራ ። እጆቹ ተንቀጠቀጡ ። ቶሎሳ ከመሞቱ በፊት የፃፈው ደብዳቤ ነበር የመሰለው ። ጠከኖ ፖስታውን ሲከፍተው ደብዳቤው ከሽታዬ የተፃፈ ሆኖ አገኘው — «ስለእጅ ፅሁፌ ይቅርታ ። የፃፍኩልህ ይቅርታ ለመጠየቅ ነው ። ጥፋተኛ ነኝ ። ለኔ ካልሆንክ ለሌላ ቤት እባልፌ አልሰጥህም ብዬ ነበር ። ከነበርኩበት ኑሮ ለማገላገል አንተን የመጨረሻ ተስፋ አድርጌ ነበር ። ስጠብቀው የኖርኩት እድል መስለህ ነበር የታየህኝ......

«አባትና እናቴ ተከታትለው የሞቱት የአስራ አራት አመት ልጅ ሆኜ ነው ። ዳዊት አስደግመውኛል ። ባለኝ ትንሽ እውቀት ስራ እጣሁ ...

«ጉሬ ምን ስራ ይገኛል ? ሰው ቤት በግርድና መቀጠር የግድ ሆነብኝ ። ውዬ ሳላድር ከማድርበት ምድጃ ዳር መጥቶ የቤት አሽከር ተማወተብኝ ። ከብሬ ከአመዱ ጋር ተቀላቀለ ። ለአበሳ የተፈጠርኩ መሆኔን ያወቅሁት ያኔ ነው ። ታመምኩ ። እመቤቴ ለመተኛት ጊዜ አልለጡኝም ። መጥተው ተነሽ ፤ መኝታ እንደሆን የምትፈ

ልጊው ከቤቴ ጨርቅሽን ጠቅልለሽ ውጭልኝ አሉኝ ። እንጀቴን በመቀነት ሸብ አድርጌ ለስራ ተነሳሁ ። ከጧት አስራ ሁለት ሰአት ጀምሬ እስከሌሊቱ ስድስት ሰአት ነበር በየቀኑ የምሰራው……ሳጥብ ፤ ሳቦካ ፤ ሳጋግር ፤ ሰወቅጥ ፤ ስፈጭ ፤ ስላላክ ያለትንፋሽ ። በዚያ ላይ ስድቡ ፤ ርግማኑ ጥፊው አይጣል ። በዚህ ሁኔታ ለሁለት አመት ሰራሁ ። ዘመናዊ ባርያ ሆኜ ። እንደድመት ከአመድ ውስጥ ጥቅልል ብዬ መተኛቱ አንገፈገፈኝ ። የሰራሁበትን ደመወዝ ሳልጠይቅ ኮበለልኩ ወደሱዱ ። እንደእድል ሆኖ ወይዘሮ ዝናሽ አገኙኝ ። አለማመዱኝ ። ከታህሳስ እስከ የካቲት ባለው ጊዜ ውስጥ እንኳን በእውኔ በህልሜ አይቼው የማላውቀውን ገቢ አገኝ ጀመርኩ ። ግንያው የገሀነም ኑሮ ነበር የምኖረው ። አንዳንዱ ሰክሮ ሲያስታውከብኝ ፤ ሌላው በጥፊ ሲያጮለኝ ፤ በውድቅት ጨለማ ከተኛሁበት አውጥቶ ሲያባርረኝ ኑሮ አይበለው ። ስንቱ ተወርቶ ። ያንዳንዱ ሰው ጠረን ሲገርፈኝ — ሲያጥወለውለኝ የአመድ ውስጥ መኝታዬ ትናፍቀኝ ነበር……

«ይህንንም ኑሮ ትቼ ለመኮብለል አስብ ነበር ። የባሰ የእድል ወጥመድ እንዳይገጥመኝ እየፈራሁ ሳመነታ አንተ መጣህ ። ደግነትህ ፤ ጨዋነትህ ፤ ቁም ነገረኛነትህ ማረኩኝ ። አዲስ ተስፋ አደረብኝ ። እንደክርስቶስ እኔን ከገሀነም ኑሮ ለማውጣት ተልከህ የመጣህ መሰለኝ ። እድሌ ነውና ሳይሆን ቀረ ። አንተንም ጭምር ማስቃየቴ ነው የሚፀፀተኝ ። ወይዘሮ ዝናሽ ለኔ ተቆጭተው ተይ ተይ ስልሽ ይሄው እርር ድብን ለማለት በቃሽ ። እርሱም እርር ድብን ይበል ብለው ስለገፋፉኝ ነው ። በነገራችን ላይ ወይዘሮ ዝናሽ የመቶ አለቃ አሸኔን አግብተው ወደ አጋሮ መሄዳቸውን ሰምተሀል? ወታደር ሁለ



ተኛ እያሉ ሲምሉ ቆይተው? እርሳቸው ብዙ የለመዱ ፤ እርሱ ቀናተኛ — ሳር ቅጠሉ ሁሉ የሚመኛቸው ነው የሚመስለው ። አይናቸውን ገለጥ ያደረጉ እንደሆን እንኳን ሰው ጠቅሰሻል ብሎ አይኑ ደም ይለብሳል ። ሽርሚሞቷን ስትሽ ስታበዛ ሩጫ ፤ ሄዳ ታሸታለች የፍቅር አፍንጫ የሚሉኝ ትዝ ይለኛል……

«ባንድ በኩል ስለጥፋቴ ይቅርታ እየለመንኩህ በሌላ በኩል ደግሞ አዲስ የህይወት በር ስለከፈትክልኝ አመሰግንሀለሁ ። እዚህ እስር ቤት ሁኜ አዲስ ህይወት ይታየኛል ። ከነበርኩበት ኑሮ የተሻለ ነው ። ከዚህ ስወጣ ደግሞ የተሻለ የመንፈስ እርጋታና ፀጥታ ወዳለበት ሄጄ ልቤን ወደ ፈጣሪዬ በመመለስ ፤ በጌጥና በገንዘብ ሳይሆን በፆምና በፀሎት ለመኖር እመኛለሁ ። የክርስቶስ ሳምራ ህይወት ይታየኛል ገድሏን ሳነብ እደንቃት ነበር ። ተስፋ ከመቁረጥ የተነሳ አይደለም ይህን የተመኘሁት ። ለእግዜር ማደር ተስፋ ያጡ ሰዎች ምኞት መሆን የለበትም ። እግዜር የተስፋ መጀመሪያ እንጂ መጨረሻ አይደለምና ። በአሳቤ አዲሱ ኑሮዬ ይናፍቀኛል — የቤተክርስቲያን ደወል ሲሰማኝ ከዚህ ቀደም የማላውቀው ደስታ መጥቶ በልቤ ይሰረፃል ። ይህን ደስታ በምንም አልለውጠውም ። የጀመርከው ስራ ይባረክልህ ። ደህና ሁን ።»

ዳብዳቤውን አንብቦ እንደጨረሰ አይኖቹ እንባ ቢያቀሩም ተሸብሮ የነበረው መንፈሱ ተረጋጋ። ደህና ሁኚ አላት በልቡ……

ለአዲሱ አመት ሀዲስ ከተኛበት እንገቱን ቀና አድርጐ ከአልጋ ወርዶ ከቤተሰቡ ጋር ለመቀላቀል በመቻሉ እጥፍ ደስታ ሆነ ። ከጠጅ ሳርና ከሀሬቲ ጋር ባንድነት የተርከፈከፈው ቄጠማ ፤ በሰጋ ቅቤ ተፈልቶ የሚቀርበው ቡና ፤ አበባዬ ሆይ እያሉ በየቤቱ እየዞሩ የሚዘፍኑት ሳዱላቸው እንደጨረቃ የሚያበራ ልጃገረዶች ፤ ከጥራቱ የተነሳ ቅርብ መስሎ የሚታየው ሰማይ ፤ የአደይ አበባዎች ለጌጥ ያህል አልፈው አልፈው ፈንጠቅ ማለት የጀመሩበት ጥቁር አረንጓዴ ብርድልብስ ለብሶ የተንጣለለው ሜዳ — ሁሉም ባንድ ድምፅ አዲሱን አመት ቢያስተጋቡም ፤ ከሀዲስ ልብ ውስጥ እየጐላ የሚሰማው የፍርሀትና የመሸበር ደወል ነበር ። ፊታውራሪ በሀዲስ ፊት ላይ የሚመላለሰውን ስሜት በማስተዋላቸው «ለምን ትተክዛለህ? በዛሬው ቀን» አሉት ። ጧት በማለዳ ወንዝ ወርደው ገላቸውን ታጥበው ስለነበረ በርዶአቸው ቡሉኮአቸውን እንደተከናነቡ ነበሩ ።

መተከዙን ስላወቁበት ደንግጦ «ኢ……አዲስ አመት በመጣ ቁጥር መንፈሴ ይሸበራል ። ያለፈው አመት ትዝ የሚለኝን ያህል አዲሱ ደስ ቢለኝም ያስፈራኛል» አላቸው ።

«እግዜር ያሰበው ነገር ሳይቀር ሰው በከንቱ ይጨነቃል ። ነገ የሚሆነውን ለማወቅ መጨነቅ'ኮ የእግዜርን



ስልጣንና ጥበብ መሻማት ነው ። እርሱ በፈለገው ቀንና ሰአት ምስጢሩን ይገልጥልናል ። የኛ ፈንታ ለቀጠሮው እንዳንዘገይ ተዘጋጅተን በትእግስት ተአምሩን መጠበቅ ነው ። መጨነቅ አያስፈልግም ። ዛሬ እንጂ ነገ በኛ እጅ አይደለችምና» አሉት ።

«ቢሆንም ሰው ሆኖ ስለነገ ማሰቡ ይቀራል? ነገ በእጁ ባትሆንም! የእግዜርን ስልጣን ለመካፈል ሰው እንደጣረ ነው — ነገ የሚሆነውን ዘልቆ ዛሬ ለማወቅ — ለመተን በይ — እንደፈጣሪ ። ብቻ ስሜት ነው……አንድ ነገር ሲጨልምብኝ መንፈሴን ያሸብረዋል ። በርግጥ ለማወቅ ባንችልም እንኳ እንዲህ ሲሆን ይችላል ብሎ ማመኑ ትልቅ እረፍት ነው ። ነገ የእምነት ጉዳይ ነው ። ለእምነት ደግሞ መሰረት ያስፈልገዋል» አላቸው ወደሚከነክነው ስሜት እየተቃረበ ። መምሬ መሀሪ ጠበል ለመርጨት መጥተው ነበርና ውይይቱ ቢቋረጥም ፤ ሀዲስ በአሳብ ተውጦ ቀረ ። ከአሳቡ ለመገላገል በጧት ተነስቶ ወደትምህርት ቤቱ ለመሄድ ተዘጋጅቶ ነበር ። ለምችና ለግርፋት ትጋለጣለህ ተብሎ በስንት ልመናና ተማፅኖ ለጥቂት ቀኖች ቤት እንዲውል ተደረገ ። ነገር ግን ከዚያን ቀን ጀምሮ ልቡ አላረፈም ።

አንድ ምሽት አይናለም ከቤት እንደገባች ትንፋሽ እያጠራት ፊቷ በፈገግታ ፈክቶ ከፋኖሱ ብርሀን ጋር እየተወዳደረ «አለቀ……ተፈፀመ……የትምህርት ቤቱ ስራ» አለችውና ፈገግታው ከፊቷ ላይ እንዳለ እንባዋን ዘረገፈችው ።

«አለቀ! ተፈፀመ!» አለ የአይናለምን ቃላቶች እንደገና እያስተጋባ ።

«አለቀ» አለችው ።

እጆቹን ትኩር ብሎ ለጥቂት ጊዜ ተመለከተና በሳቅ ፈነዳ ። እንደሚያመልካት ሰው ከፊቷ ተንበረከከ ። እጆቿን አገላብጦ ሳማቸው ። እንደገና በሳቅ ፈነዳ ።

«በቃ አለቀ?» አላት እንደገና ።

«የትምህርት ቤቱ ስራ በሙሉ አልቋል ። የደወል ቤቱም ስራው አልቋል ። የቀረው ደወሉን አውጥቶ መስቀል ብቻ ነው — ነገ......»

«ደወሉ ቀርቷል? ደወል......ደወል......አዎን — ደወሉን ከቦታው ማንጠልጠል ያለብኝ እኔ ነኝ ። ትምህርት ቤት በሌለበት ፣ ቤተክርስቲያን ባልተተከለበት ደወል አስቀድሞ አይቆምም ። ደወል ማንጠልጠል የመጨረሻ ስራ እንደመሆኑ እንደቡራኬ ይቆጠራል...... ደወል...... አዎን......ደወል ጥሪ ነው......የጥሪ ድምፅ ።»

ከፊቷ እንደተንበረከከ እጆቿን እንደገና አገላብጦ ሳመ ። ሳይታወቀው አንድ የተዳፈነ ስሜት በልቡ ውስጥ ነፍስ ዘርቶ በመላ ሰውነቱ እየተሰራጨ ሲያግለውና ወንድነቱን ሲቀሰቅሰው ተሰማው ። ያደረበት ምትሀት አልፎ ስሜቱ እንዳይበርድ እጆቿን እንደያዘ ከተንበረከከበት ተነስቶ መጀመሪያ ከጡቶቿ መሀል ፣ ቀጥሎ ጉንጮቿን... አይኖቿን ......ከዚያ ከንፈሮቿን...... የጋሉትን ከንፈሮቿን በጋለ ስሜት...... በስቀቀን እየሳመ «ከ......ከ...... የለም......ሳንገናኝ በፊት ነበር መሰለኝ የምወድሽ......» እያላት ፣ የሁለቱም ልብ ትርታ እየተምታታ ከአልጋ ላይ ወደቁ......ተነፍጉት የቆየው ፅጌረዳ አበባ......እምቡጥ ፅጌረዳ አበባ......ፈነዳ......ረገፈ ። አይናለም እንግቷን ከአንገቱ ውስጥ ሸጉጣ በዝምታ እንባዋን ታነባዋለች ። በፍቅር ጢፍ የነደደ ሳይጠገብ የነጋ አጭር ሌሊት ። ጧት የመስከረም ጮራ ስሜታቸውን ተቀብላ አስተጋባች ።



ሀዲስ ከእንቅልፉ ሲነቃ በመጀመሪያ በአእምሮው መጥቶ የተቀረፀው ከትምህርት ቤቱ ሄዶ ደወሉን ከቦታው የማንጠልጠል አሳብ ነበር — ደወል — ከገባ ፍጹቱ በላይ ነግሶ የሚያስተጋባ ደወል — የደወል ጥሪ......

ሜዳው ሸንተረሩ ፣ ተራራውና ሸለቆው በአደይ አበባ አሸብርቆ ፣ ተፈጥሮ መልካም ሸማኔ የሰራው ጥበብ መስላ በቡና ፣ በአረንጓዴና በብጫ ቀለማት ተሽኮርኮራለች ። ኩል መስሎ የተንጣለለው ሰማይ በጣም ቅርብ መስሎ ነበር የሚታየው ። የመስከረም ጮራ ሜዳውን ፣ ሸንተረሩን ፣ ተራራውንና ሸለቆውን ያለበሰውን ወርቅማ አደይ አበባ እየዳሰሰች ውበቱን በበለጠ ታጐላለች ።

ፊታውራሪ ቢከለክሉትም ሀዲስ አሻፈረኝ በማለት ደወሉን እንደምንም ባንድ እጁ አንጠልጥሎ በአክሱም ሀውልት ቅርፅ በቀጭኑ ከተሰራው ደወል ቤት ላይ በረጅም መሰላል ወጣ ። ከነሀስ የተሰራው ደወል ከባድ ስለሆነ ከመሰላሉ ጫፍ ሲደርስ በረጅሙ ተነፈሰና ወደ

ታች ተመለከተ ። ብዙ ህዝብ ወደላይ አንጋጦ ይመለከተዋል ። ነጭ ሻሽ — ቀይ ሻሽ — ጃኖ — ጥንግ ድርብ — የሀገር ልብስ — ቁምጣ ሱሪ — ቦላሌ ሱሪ — ቀይ ፣ ቅጠልያ ፣ ደማቅ ሰማያዊ ካኪ ፣ መርዱፋ ፣ አቡጀዲድ ልብሶች — እንደምድሪቱ የተዥጎረጎረ ቀለም የለበሱ — ልጆች — ወጣት ሴትና ወንዶች — አሮጊቶች — ሽማግሌዎች ይታዩታል ። ገና በመምጣት ላይ የሚገኙም አሉ — ከሩቅ — ከቅርብ ። ሁሉም ወደ አዲሱ ትምህርት ቤት ፊቱን አዙሮአል ። የአባጨጓሬ ድቤ ፀጥ ብሎ ከሚነፍሰው አየር በላይ እየተንሳፈፈ ይሰማል ። ለመደመጥ ፉክክር የገጠመ ይመስል እየናረ — እየናረ ይሄዳል ። የሰጋር በቅሎዎቻቸው ግስጋሴ የድቤውን ምት ስልት የሚጠብቅ ፣ ሁለት ወጣቶች ከወደ አልጌ መንገድ ወደትምህርት ቤቱ ያመራሉ ። ሁለቱም ከበቅሎዎቻቸው እንደወረዱ «ያቺ የዕጌረዳ እምቡጥ» አለ ፣ በቁመናው ዘለግ ያለው ጠይም ወጣት ወደአይናለም አይኖቹን እየወረወረ ።

«ጀመርክ እንግዲህ! አይንህ ሌላ ነገር አያይም — ከሴት ሌላ! ይልቅ ያ የደወል ቤቱ ላይ ቆሞ ራእይ የሚታየው ይመስል ሩቅ የሚመለከተው ሰው ያኔ ወደአልጌ እግረ መንገዳችንን በዚህ በናልፍ ያከምኩት ልጅ አይደለም እንዴ? ፊቱ ትዝ ይለኛል» አለው ፣ ከጓደኛው በቁመት ትንሽ መለስ የሚለው ሌላው ጠይም ወጣት ።

«አዎን እሱ ነው ። አልጌ ውስጥ ተጋንኖ የሚወራው ስለእርሱ ኖሮአል ለካ! ሀዲስ ይሉሀል እርሱ ነው — ንጉሱ እብድ ነው ይለዋል ። ውነትም ደግሞ ሲመለከቱት ጤነኛ ሰው አይመስልም ። በቅዠት … በሀልም አለም ውስጥ የሚንሳፈፍ ይመስላል — ከዚያ ደወል ቤት ላይ ቁሞ……»

«ከዚያ ላይ ቁሞ ለእርሱ የሚታየው ሀልም — ለምን እንደሆነ እንጃ — ለኔም የሚታየኝ ያህል ሆኖ ይሰማኛል ። ካንተ ሙሉ ጤንነት የእሱ እብደት ነው ለዚህ ለምታየው ህዝብ የሚበጀው……»

«ስለርሱ እንደሰማሁትና አንተንም እንደማውቅህ ባህሪያችሁ ይቀራረባል ። በውጭ ጠንካራ መስለው የሚታዩት ሸካራ መልካችሁ በውስጣቸው በየሜዳው የምታለቅስ ነፍስ የደበቁ ናቸው ። በየሜዳው የሚጮህ ሀሊና አልወድም ። ባጉል ብሄራዊ ስሜት በጭፍን የሚመሩ ሰዎች አልወድም ። ወገኔ አገሬ ስንል የአለም ህብረተሰብ አባል መሆናችንን እንዘነጋለን……»

«ለወንዜ ፣ ለወገኔ ፣ ለአገሬ ብሎ የማያስብ ሰው ለሰው ልጅ አስባለሁ ቢለኝ አይገባኝም ። የቅርቡን ትቶ የሩቁን እናስብ ማለት ሀሊናን ማሳወር ነው ። ይልቅ ከዚያ ወርዶ ባነጋገርኩት……»

«እንደሱ እጅ እጅ እያልኩ እዚሁ እቀራለሁ እንዳትለኝና እንዳታስቀኝ……»

«ማን ያውቃል? ማን ያውቃል — የሰው ህይወት ምን አግጣጫ እንደሚይዝ! የህይወት ጥሪ……በዚች ሰአት ደስታው ምን ያህል እንደሆነ ይሰማኛል ። ህልሙ ይታየኛል……» እያለ ወደሀዲስ ሲመለከት ፣ ጓደኛው በመገረም አተኩሮ አይኖቹን ይመረምር ነበር ። ስሜቱ እስ ደነገጠው ። ለመጀመሪያ ጊዜ በህይወቱ የራሱም ስሜት አስፈራው «ወይ'ኔ ያራዳዬቱ ልጅ!» አለ በልቡ……

ሀዲስ በልቡ ከሚሰማው ደስታ የተነሳ መላ ሰውነቱ
ይንቀጠቀጥ ነበር ። ደወሉን በሁለት እጆቹ ወደላይ እን
ሰቶ በሰፊው መስኮት ወደውስጥ አሳለፈውና ከደወል
ቤቱ ጣሪያ ስር ከተሰራለት የብረት መንጠቆ ላይ እንጠ
ልጥሎ ሲያበቃ ገመዱን በውስጥ በኩል ወደታች ለቀ
ቀው ። ደወሉ ትንሽ ድምፅ በማሰማቱ ከደወል ቤቱ ላይ
አርፈው የነበሩት አራት ርግቦች ተነስተው ደስታውን ለማ
ብሰር የተላኩ ይመስል አንዳንዴ ደረታቸውን እንደገና
ደግሞ ጀርባቸውን ለመስከረም ፀሀይ እየሰጡና ቀዝቃዛ
ውን አየር በክንፎቻቸው እየቀዘፉ በረሩ — ለአይን እስኪ
ሰወሩ ድረስ እንባ ባዘሉት አይኖቹ ተከተላቸው ። ለመ
ከራ ያህል ገመዱን ይዞ የደወሉን ድምፁ ለመጀመሪያ
ጊዜ ከፍ አድርጎ አሰማ ። የአይናለም ፊት ከሁሉም ይበ
ልጥ ጉልህ ሆኖ ታየው ። እንደአጋጣሚ የአባጨፌ ድቤ
በድንገት ፀጥ አለ ። ልቡን በፍፁም ሊመስጠው የቻለ
እንደዚያ ያለ የሙዚቃ ቃና ከዚያ ቀደም ሰምቶ እንደማ
ያውቅ አመነ ። አይኖቹ ረጠቡ ። የእግዜር ትንሽ እጅ!
የእናቱ ቃላት ከጆሮዎቹ ውስጥ ያስተጋባሉ ።

«በሀይል ደውለው እንጂ!» አሉት ፊታውራሪ ተካ
ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ። የአይናለም አይኖችም ረጥ
በው ነበር ። መምሬ መሀሪ ከፊታውራሪ አጠገብ ትል
ቁን ወርቅማ መስቀላቸውን በቀኝ እጃቸው ከፊት ለፊት
ደግነው ፤ ነጭ ጭራቸውን በግራ እጃቸው ወዲህና ወዲያ
እየነሰነሱ ቆመው ነበር ። ክብሳታቸው ከመጠን በላይ
ተቆልሎአል ። ስለትምህርት ቤቱ ስራ ፍፃሜ ቡራኬ
ለመስጠት የተዘጋጁ ይመስላሉ ። ቡራኬዬን ምን ብዬ
ልጀምር ይሆን? ……ክርስቶስ በዚህች ከፉና አላፊ በሆ



ነችው አለም ስጋ ለብሶ በኖረበት ዘመን ተቀዳሚ ስራ
አድርጎ የያዘው የማስተማርን ተግባር ነበር ። በትምህ
ርቱና በሞቱም የመንግስተ ሰማያት በር ለሰው ልጅ ተከ
ፈተ……ይህም ትምህርት ቤት እንደስብከት ተራራ አይ
ናችንን የምንከፍትበት የተቀደሰ ስፍራ……ይሁን ። አይ —
እንዲህ ማለት አይገባኝም ። ምንነው በነካ እጁ ቤተክር
ስቲያን ቢሰራ አሉ ፤ ሀዲስ አንድ ጊዜ ስለትምህርት
ቤቱ ሲገናር አዲሱ ቤተ እግዚአብሄር ነው ያለው ነገር
ትዝ ብሎአቸው…… የማስተማር ተግባር ከቤተክርስ
ቲያን ወደአለማዊው ትምህርት ቤት እየተላለፈ የመሄዱ
ጉዳይ እየከነከናቸው……ቢሆንም ፤ ቢያምኑበት ባያም
ምኑበትም ቡራኬ የመስጠቱ ግዴታቸው እየተጫናቸው
ምን ብዬ ልጀምር? እያሉ ወደማሰብ ተመለሱ………

«ልጁ ያንን መናጢ አግብታ ብትሄድ ኖሮ የዛሬውን
ደስታ ሳላይ እሞት ነበር» አሉ ፊታውራሪ በትካዜ ።

«አዎን — የፊታውራሪ አያና ልጅ ርስቱን ሁሉ
ሸጦ ጨርሶአል አሉ ። ያገባትም ኮማሪት አባረረችው
ይባላል ። የስንቱን ጨዋ ልጅ ርስት ያስሸጠች ናት…»

«የፊታውራሪ አያና ነፍስ ትማር ። ጥለውኝ ሄዱ ።
እኔ የጎዳኝ ጠላትነታቸው አይደለም ሞታቸው ነው ።
ቶሎሳ ቢኖር የዛሬው ደስታዬ እጥፍ በሆነ ነበር ። ምቀ
ኝነት ፤ ተንኮልና ሸር ከዚህ ትምህርት ቤት ስራ ፊት
ባይደቀኑ ኖሮ ዛሬ በህይወት ከኛ ጋር ይገኝ ነበር ። በሀቅ
ልስራ ብሎ የሚነሳውን ከመወንጀልና ጭንቅላቱን ቀጥቅ
ጠን አንገቱን ዝቅ እንዲያደርግ ከምናደርግ ብንደግፈው ፤
ብናበረታታው ጥቅሙ የጋራ ይሆናል ። ግን ልማድ የለ
ንም ። ልማዳችን ፤ ተንኮል ፤ ሸርና ምቀኝነት ነው ። ይሆን

ልማድ ይዘን የትም ልንደርስ አንችልም ። ባዶ ኩራት ብቻ ይዘን እንቀራለን ። ባዶ ኩራት ። ጊዜ ይፈርድብናል ። ህልውናን መቆመት ያለብን በስራ እንጂ በእድሜ ፤ በአሳብ እንጂ በትንፋሽ በስሜት እንጂ በከንቱ በሚባክኑ ደቂቃዎች አይደለም ። ጊዜን የምናሰላው በልብ ትርታ መሆን አለበት ።»

«እውነት ነው» አሉ መምሩ ስለቡራኬአቸው እያሰቡ……

ፊታውራሪ ትእግስታቸው አልቆ «ስማኝ እንጂ ! በሀይል ደውለው……ያስተጋባ……በሱዴ……» ሲሉት ፤ አይናለም ከአጠገባቸው ሹልክ ብላ ሄዳ በደወል ቤቱ በር ገባችና ገመዱን ይዛ በሀይል መደወል ጀመረች……

ፊታውራሪ በደስታ ተውጠው አይናቸውን እንዴ ወደ ሀዲስ ፤ መልሰው ደግሞ ወደአይናለም እየወረወሩ የሰላም እረፍት ላገኝ ነው መሰለኝ አሉ በልባቸው ። የደወሉ ድምፅ እየገነነ እየነገሰ ሲሄድ የፊታውራሪ ልብ ትርታ እየቀነሰ እየደከመ ፊታቸው እየገረጣ ሆኖም ከፊታቸው ላይ ያለው ፈገግታ እየፈካ እየጐላ ሲሄድ—

ገል ።

የገል ስባሪ……ህይወት……

ቃለ እዋዲውን እንደ የገደል ማሚቶ እየተቀበለች ወደሌላዋ ስታስተላልፈው ፤ እያስተጋባ ፤ የሀዲስን ደስታ እያበሰረ — የወደፊት ህይወቱን……ህይወታቸውን…… የትምህርት ቤቱን የወደፊት እድል……እየከሰተለት ይሄድ ነበር……

## ካድማስ ባሻገርን
### ያበረከተላችሁ ደራሲ

## የህሊና ደወል

## የተባለውን አዲስ
## ልብ ወለድ ድርሰት
## ይዞላችሁ ቀርቧል



ሐዲስ ሣህሌ የዩኒቨርስቲ ትምህርቱን አቋርጦ ለአንድ ዓመት በማስተማር ራሱን ለመርዳት የተሠማራ ቢሆንም በገጠሩ ችግር ምክንያት ራሱን ለሕዝቡ - እንዲሰዋ የተገፋፋ ወጣት ነው:: ያለፈውን ትውልድ ሥራና ክንውን በማውጠንጠንና ከሚገባው በላይ ታላቅነቱን በማጋነን በትዝታ ተውጦ አይባክንም:: በትዝታ የሚባክን ትውልድ፣ በራሱ የማይተማመን፣የሚኖርበትን ዘመን ችግሮች መቋቋም ያልቻለና መኖር ያቃተው መሆኑን የተገነዘበ ይመስላል ::ሐዲስ ለኢትዮጵያ አዲስ ፍጡር ነው:: በወሬ አይፈታም ፣ ዓላማው በሙሉ ሠርቶ ለማሳየት ነው:: መሰናክሎች ይገጥሙታል፣ ፈተና ይደርስበታል ፣ ለሕይወቱ ያሰጋበትም ጊዜ ነበር:: እንዴት ሊወጣው ቻለ?

ጥንታዊውን ሳያሞካሽ ወይም ሳያንኳስስ፣ ዘመናዊውምን ሳያጋንንና ሳያካኪስ በተደላደለ መንፈስ የቀረበ ውብ የሆነ ልብ ወለድ ጽሑፍ ነው:: ከ'አድማስ ባሻገር' ይታይ የነበረው ወጣት፣ በኅሊና ደወል ከአድማስ ወዲህ ተከሠተ::

ዳኛቸው ወርቁ

ማንኩሳ አሳታሚ

ዋጋው ብር 50.60